## ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ

በ
በላይነህ ደሴ

IES LIBRARY

ነሀሴ 1999 ዓ/ም
አዲስ አበባ

# የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ኤም ኤ ዲግሪ

በከፊል ለማሙዋላት የቀረበ ጥናት

በ

በላይነህ ደሴ

የጥናቱ አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

ነሀሴ 1999 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ
# በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ

በ

በላይነህ ደሴ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ትምህርት
ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዮናስ፡አድማሱ ------------------------ ------------------
አማካሪ ፊርማ

[illegible] ------------------------ ------------------
የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

[illegible] ------------------------ ------------------
የውጭ ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

ላለፉት ሀያ ሶስት አመታት የልጅነት ጊዜዎን ሳትቆጥብና ድካም ሳይሰማት ጫካ፣ ገደልና ዳገቱን አብራኝ ለተንዋዘችው አጋሬ ስፍራሽብዙ ከሃሊውና በጉዙዎችን ለተገኙት ልጆቻችን ሀሊና፣ አብርሃምና ክብር በላይ ለዘወትር ትእግስታቸው ምስጋናዬ ወደር የለውም።

ትልመ ጥናቱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የጥናት ረቂቁን በማረምና በማስተካከል ተገቢ አስተያየታቸው ላልተለኝ ለጥቱ አማካሪ ዶ/ር ዮናስ አድማሱም ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው።


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ማውጫ

ርእስ ገጽ

ምስጋና

ማስታዎሻ.........vi

ምእራፍ አንድ

1.1 የጥናቱ መነሻ.........1

1.2 የጥናቱ አላማ.........2

1.3 በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች.........3

1.4 የጥናቱ ወሰን.........4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ.........4

1.6 የጥናቱ ዘዴ.........5

1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የነበሩ እድሎች

1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች.........6

1.7.2 የነበሩ እድሎች.........7

ምእራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

2.1 የርእስ ነገሩ መነሻዎች.........8

2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.........10

2.2.1 የታተሙ(መጻህፍት) .........10

2.2.2 ያልታተመ .........13

2.3 ጸዋትወ ቅኔ.........15

2.3.1 የግእዝ ቅኔ ምንነትና ጠቀሜታ.........15

ሀ. ምንነት .........16

ለ. ጠቀሜታ.........21

2.3.2 የግእዝ ቅኔ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ.........22

ምእራፍ ሶስት

የቅኔ ጉባኤዎች፣ መንገዶችና አይነቶች

3.1 የቅኔ ጉባኤዎችና መንገዶች........................................34

3.2 የቅኔ አይነቶች........................................39

ምእራፍ አራት

የግእዝ ቅኔ እና ጎጃም

4.1 የቅኔ ቤት ህይወት በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ........................................64

4.1.1 የእንግዳ ተማሪ አቀባበልና መስተንግዶ........................................66

4.1.2 የምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስርአት........................................70

4.1.3 አለባበስና የቁሳቁስ አጠቃቀም........................................74

4.1.4 የሆሳእና አዘገጃጀትና አወሳሰድ........................................77

4.1.5 በደመና መንሳፈፍና በነፋስ ሰረገላ መክነፍ........................................80

4.1.6 የግእዝ ቅኔ መነሻ ታሪክና የአተራረክ ስልት........................................85

4.1.7 የግእዝ ቅኔ መምህራን ህይወት........................................87

4.2 የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ........................................93

4.2.1 የግስ ግሰሳና እርባታ ስርአት........................................94

4.2.2 ዘረፋ፣ ቅበላና ቅጸላ........................................111

4.2.3 ቆጠራና ነገራ........................................116

4.2.4 ነጠቃና ግልበጣ........................................121

4.3 የቅኔ አቀራረብ ስርአት በማህሌትና በክብረ በአላት........................................124

4.3.1 የቅኔ አቀራረብ ጅማሬ በቤተ ክርስቲያን........................................124

4.3.2 የቅኔ አቀራረብ ህግና ስርአት ........................................125

4.3.3 የሚቀርብበት ጊዜና ወቅት........................................125

ማጠቃለያ........................................128

አስረጂዎች........................................i

አባሪዎች

- ማህደረ ቃላት---------------------------------------- --iv
- መጠይቆች---------------------------------------- xv
- ተጠያቂዎች---------------------------------------- xvii

## ማስታወሻ

የጥናት ርእሱ ተመርጦ የምርምር ስራው እስከ ተጀመረበት ጊዜ ድረስ የግእዝ ቋንቋዋ ፊደላት በአማርኛ ቋንቋዋ ጽሁፍ ውስጥ ሲገቡ ያላቸው ቦታና አጠቃቀም ይህን ያህል አስቸጋሪ መሆኑ በውል የታወቀ አልነበረም፡፡ የጥናት ስራው ተጀምሮ ረቂቁ መጻፍ በተጀመረ ጊዜ አንድን ድምጽ ወክለው የሚገኙ ሁለትና ከዚያ በላይ ፊደላትን ያለግድፈት እንደየሙያቸው በተለያዩ የአማርኛ ቃላት ውስጥ መጠቀም መቻል ራሱን የቻለ ሌላ ረጅም ጥናት የሚያስፈልገው በመሆኑ የተጀመረውን የጥናት ስራ ከተገቢው በላይ አስቸጋሪ የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቱዋል፡፡

የጉዳዩን አስቸጋሪነት የበለጠ አሳሳቢ ያደረገው ደግሞ የግእዝን ቅኔ ርእሰ ጉዳያቸው አድርገው የተለያዩ መጻህፍትን የጻፉ የሙያው ሊቃውንት ሳይቀሩ በጽሁፎቻቸው ውስጥ ችግሩ ጎልቶ የታየባቸው መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል "አጼ" የተሰኘውን የአማርኛ ቃል የተለያዩ ሊቃውንት በተለያዩ መጽሀፎቻቸው እንደሚከተለው ጽፈውታል፡፡

| የጸሀፊው ስም | የመጽሀፉ ርእስ | የታተመበት ጊዜ | ቃሉ የተገኘ በት ገጽ | ቃሉ የተገለጸበት ፊደል |
|---|---|---|---|---|
| ሀብተ ማርያም ወርቅነህ | ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት | 1963 | 173 | አጼ |
| አለማዬሁ ሞገስ | ሰዋስወ ግእዝ ተሰነአወ | 1950 | በመጽሀፉ ሽፋን | ዐፄ |
| ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም | ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ .ተ. ቤ .ክ | 1992 | 29 | አፄ |

የጉዳዩ አሳሳቢነት ህሊናየን እረፍት ቢነሳው በሀዲስ አለማዬሁ የልብ ወለድ ድርሰት መቅድም ውስጥ ደጋግሜ ያነበብኩት የመፍትሄ ሀሳብ ታወሰኝ፡፡ ችግሩን አስቀድመው የተረዱት ሀዲስ አለማዬሁ በታዋቂው ልብ ወለድ መጽሀፋቸው በፍቅር እስከ መቃብር መቅድም ውስጥ ስለዚህ ችግር አንስተው መፍትሄ ይሆናል ያሉትን እንደሚከተለው አስፍረውት አልፈዋል፡፡

> ዛሬ ለማንኛውም ነገር አቋዋራጭ መንገድና ቅልጥፋና በሚፈለግበት ጊዜ የፊደሎቻችን ያለ መጠን መብዛት ትምህርታችንንም ሆነ ስራችንን ሳያስፈልግ አስቸጋሪ አድርጉብናል፡፡ ይህም ታውቆ የፊደል አሻሻይ ኮሚቴዎች በየጊዜው እየተሾሙ አሳብ መለዋወጣቸውንና ፊደሎቻችን የሚሻሻሉብትን መንገድ ማጥናታቸውን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን የነዚህ ኮማሚቴዎች ጥናት ውጤት ገና አልታወቀም፡፡ . . . እኔ በዚህ መጽሀፍ የጻፍኩበት ዘዴ ከእኔ በሁዋላ ለሚጽፉ ደራሲያን

> የሚስማማ መስሎ ቢታያቸውና ቢነተሉት፣ የፊደሎቻችን ብዛት ያስከተለውን ችግር በመጠኑ ያቃልለዋል ብዬ በማመን አሳቤን ከዚህ ቀጥየ አቀርባለሁ:: አንደኛ ሶስት "ሀ" ዎች፣ ሁለት "ሰ" ዎች ፣ ሁለት "አ" ዎች እና ሁለት "ጸ" ዎች ስላሉን ከነሱ አንዳንድ ብቻ ይገቼ የቀሩትን ጥያቸዋለሁ:: ስለዚህ የተጠቀሱት አምስት የግእዝ ፊደላት ከነአርባታቸው ሰላሳ አምስት መሆናቸው ነው:: ሁለተኛ ከፊደሎቻችን መጨረሻ "ኰ" ፣ "ጕ" ፣ "ቈ" ፣ "ኊ" የሚባሉትን ከነ አርባታቸው ጥያቸዋለሁ:: ድምራቸው ሃያ ነው:: ሶስተኛ "ኸ" እና "ኧ" ን ግእዛቸውን ብቻ ይገቼ አርባታቸውን ጥያለሁ:: ከነሱ የወደቁት ፊደሎች አስራ ሁለት ናቸው:: እንግዲህ በጠቅላላው የተጣሉት ፊደሎች ስድሳ ሰባት ሲሆኑ፣ እነሱ በመጣላቸው ይህን ያህል የንባብ ችግር ወይም የምስጢር መሰወር ይገጥማል የሚያሰኝ እንደሆነ ፍርዱን ይህችን መጽሀፍ ለሚያነቡ ሁሉ እተወዋለሁ (ሀዲስ አለማዬሁ፣ 1958)

ሀዲስ አለማዬሁ ያስቀመጡት መርህ ለግራ መጋባቴ መፍትሄ ሆኖ አገኘሁትና እኔም በዚህ የጥናት ስራዬ ውስጥ መርሁን ተከተልኩት:: ከሌሎች የጽሁፍ ስራዎች በአስረጅነት የተጠቀሱት ጽሁፎች ግን በተገለጹበት ሁኔታ እንዳሉ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል::

የዚህ ጥናት ስራ ትኩረት በግእዝ ቋንቋዋ ውስጥ ስለ ተመሰረተው የግእዝ ቅኔ በመሆኑ በውስጡ ለዘመኑ ትውልድ እንግዳ የሆኑ አያሌ ቃላት ተካተውበታል:: ለግእዙ ቋንቋዋና ለስርአተ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ የሆኑ የዚህ ጥናት አንባቢዎችን ችግር ለመጋራት ማህደር ቃላት (Vocabularies) ማዘጋጀቱ አስፈላጊ በመሆኑ ማህደረ ቃላቱ ከጥናቱ መጨረሻ እንዲቀርቡ ተደርገዋል::

# ምእራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ መነሻ

ዘመናዊ የትምህርት ተቋማት ተመስርተው፣ ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተው፣ የዘመኑ ትምህርት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ሀገራችን ብዙ መቶ አመታትን ያስቆጠሩ የራስዋ የሆኑ የትምህርት ተቋማት ነበሩዋት። ብዙዎቹ የወቅቱን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚወክሉ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ዘመነኞቹን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚስተካከሉ ነበሩ። ዘመነ ስልጣኔ በጣለባቸው በረዶ ከርስሰው እንደወትሮው ሁሉ አሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ እንደቀዘቀዙ ይገኛሉ።

ጉባኤዎቹ፣ አቡጊዳ፣ፊደለ ሀዋርያና የጽህፈት ትምህርት የሚወጠኑበት፣ ንባብና የቃል ትምህርት (የቀን፣ የሌሊት) እየተባሉ የሚጠኑበት፣ የቅዱስ ያሬድ ስራዎች ከነዜማቸው (እዝል፣ ግእዝ፣ አራራይ) እየተባሉ በምልክት የሚጮሁበት፣ ዝማሬ፣ መዋሲት፣ አቋቋቁዋምና ቅዳሴ የሚዜሙበት፣ ቅኔ ከነጉዋዙ የሚፈለሰፍበት፣ መጻህፍት በአንድምታ፣ በምስጢርና በነጠላ የሚተረጐሙበት፣ የዘመን አቆጣጠር፣ ባህረ ሀሳብና አቡሻክር የሚቀመሩበት፣ የስነጽሁፍ፣ የፍልስፍና እና የድጉስ ስራዎች የሚረቀቁበት፣ ህብረ ቀለማት ከእጽዋት፣ ከአዝርእትና ከአፈር የሚቀመሙበት፣ የሆሳእና ቅመማ፣ የጥንቆላ ጥበብና የብህትውና ህይወት የሚዛነቁበት፣ ጥንታዊ፣ ባህላዊ፣ ኪናዊና ህይማኖታዊ የሆኑ የጥበባት ትምህርት ቤቶች ነበሩ።

አሁን ድረስ የበረዶውን ቅዝቃዜ ቀዝቅዘው ትምህርቱን እየሰጡ ከሚገኙት የቤተ ክርስቲያኑዋ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱና አንጋፋው የግእዝ ቁዋንቁዋ መሰረት የሆነው ግስ የሚገሰስበት፣ የቅኔ መሰረት የሆኑ ጥንታዊ ታሪኮች የሚተረኩበት፣ ቅኔ የሚቆጠርበት፣ የሚነገርበትና የሚዘረፍበት፣ ነጠቃና ግልበጣ የሚካሄድበት የግእዝ ቅኔ ጉባኤ ነው። ይኸው የቤተ ክርስቲያኑዋ ትልቅ የትምህርት ተቋም ዛሬም ወትሮ ይጠቀምበት በነበረው የማስተማር ዘዴና የመማሪያ ጐጆ ውስጥ እንዳለ ነው።

የዚህ ጥናት አቅራቢም ከተዘረዘሩት አያሌ የቤተ ክርስቲያኒቱ ስርአተ ትምህርቶች መካከል ስለሙያው ያለውን ውስን እውቀት መሰረት በማድረግ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙዋያ ጥናቱን «ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ» በሚል ርእስ በግእዝ ቅኔ ስርአተ ትምህርት ላይ ለማካሄድ ወስኑዋል። ምንም እንኩዋን ጥንታዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ጉባኤዎች የማስተማር ስልትና የትምህርቱ ይዘት ጥልቅ ምርምርን የሚጠይቅ፣ ትምህርቱ የሚቀርብበት ቁዋንቁዋም እንኩዋን ለሌላው በሙያው ውስጥ ባለፉ

ምእመናን ዘንድ በአግባቡ የማይታወቅ፣ ተመራማሪዎችም ገና በወጉ ያልተመለከቱት በመሆኑ የጥናት ስራውን አስቸጋሪ የሚያደርገው ቢሆንም ባለው ላይ የተወሰነ ነገር ለመጨመር በርእስ ጉዳዩ ላይ ጥናት ማካሄዱ ተመራጭ ሆኑዋል፡፡

የጥናቱን ስራ በአግባቡ አደራጅቶ ለማቅረብ ያመች ዘንድ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀረቡዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል በጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን በውስጡም የጥናቱ መነሻና አላማው እንዲካተት ተደርጉዋል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የሚሸፍነው አካባቢ፣ ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦና በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የነበሩ እድሎች ተካተውበታል፡፡

ሁለተኛው ክፍል ለዚህ ጥናት ስራ አጋዥ የሆኑ የጽሁፍ ውጤቶች የተዳሰሱበት፣ ተዛማጅ ስራዎች የተቃኙበትና መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች የተገለጹበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የርእሰ ነገሩ መነሻዎች ምን እንደሆኑ፣ የግእዝ ቅኔ ምንነትና ጠቀሜታ፣ እንዲሁም የግእዝ ቅኔ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ የተገለጸበት ሲሆን በክፍል ሶስት ስር ደግሞ የቅኔ ጉባኤዎች፣ መንገዶችና አይነቶች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

ዋናውን የጥናት አካል የያዘው ክፍል አራት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ስር የቅኔ ተማሪዎች ህይወት በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ምን መልክ እንዳለው፣ ማለትም እንግዳ ተማሪ አቀባበልና የመስተንግዶ ስርአቱ፣ የምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስልቱ፣ አለባበስና የቁሳቁስ አጠቃቀሙ፣ የሆሳእና አዘገጃጀትና አወሳሰዱ፣ በደመና ስለመንሳፈፍና በንፋስ ሰረገላ ስለመክነፍ፣ የቅኔ መሰረት የሆነው ታሪክና የአተራረክ ስልቱ፣ እንዲሁም የግእዝ ቅኔ መምህራን ህይወት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ቀርቡዋል፡፡ የግስ ግሰሳና የእርባታ ስርአት፣ የግእዝ ቅኔ ዘረፋ፣ ቅበላ፣ ቅጸላ ፣ቆጠራ፣ ነገራ፣ ነጠቃና ግልበጣ የተሰኙ ርእስ ጉዳዮችና የቅኔ አቀራረብ ስልቶች በማህሌትና በክብረ በአላት ምን መልክ እንዳላቸው የሚያመለክቱ ርእስ ጉዳዮችም በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፡፡

## 1.2 አላማ

ጎጃም በግእዝ ቅኔ ትምህርት ከሚታወቁ የሀገራችን አካባቢዎች የቀዳሚነቱን ስፍራ የያዘ ነው ተብሎ ይታመናል (አለማየሁ 1950፡117)፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በተመረጡ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎችና የአከዋወን ስርአታቸው ላይ ያተኩራል፡፡ የጥናት ስራው ሲወጠን ታሳቢ የተደረጉ የጥናቱ አቢይና ዝርዝር አላማዎች ተቀምጠዋል፡፡

የጥናቱ አቢይ አላማ፣ በግእዝ ቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በትምህርትነት የሚቀርቡና በተለምዶ የሚከናወኑ ተግባራትን በጽሁፍና በምስል ቀርጾ ለዘመናዊውና ተተኪው ትውልድ በማስተማርና በማስተላለፍ ጥበባዊ ቅርሱ አሁን ካለበት በተሻለ ተደራጅቶና ተከብሮ እንዲኖር ለማስቻል ሀብቱ ላላቸው ተቆርቋሪ ወገኖች መጠቆም፣

በብቸኛ ቅርስነቱም ከሚገኝ ጥቅም ሀገርና ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና በያንዳንዱ ቅንጣት የሙያው ዘርፎች ጥልቅ ምርምርና ጥናት ማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ መሰረት የመሆን አላማ አለው። ዝርዝር አላማዎቹም ከዚህ የሚነሱ ናቸው።

1- በጉባኤዎች ውስጥ በትምህርትነትና በተለምዶ የሚከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራትን በጽሁፍና በምስል በመቅረጽ ለዘመኑ ወጣቶችና ለተተኪዎቹ ህጻናት ከተቻለ ለማስተማር ካልሆነ ቀርሶ /ቅርስ አድርጐ/ ለማቆየትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመጠቆም፤

2- በሙያው ውስጥ ከተነሱ አያሌ ርእሰ ጉዳዮች መካከል መርጦ ዝርዝር ጥናት ማድረግ ለሚፈልግ ደፋር ተመራማሪ መነሻ የመሆን፤

3- የመማር ማስተማሩ ወግና ባህል ሳይከለስ፣ ፈቃደኛ ወጣቶች ሊማሩበት በሚያስችል ሁኔታ የተደራጀ፣ ለቅርስነት በሚያመች መልኩ የተጠበቀ፣ የግእዝ ቅኔ ሙያ መማሪያ ሞዴል ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩ የመጠቆም፤

4- በወትሮው የጎጃም የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎችና አሁን ባሉት መካከል በየወቅቱ እየተከሰቱ ያሉትን ልዩነቶች የማወዳደር፤

5- በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በአፈ ታሪክነት የሚዘከሩ ጉዳዮችን በማንሳት መነጋገሪያና መወያያ እንዲሆኑ ከማድረግ በተጨማሪ የጥናትና የምርምር ርእስ እንዲሆኑ መነሻ ሀሳብ የማቅረብ አላማ አለው።

## 1.3 በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች

1- የግእዝ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋ፣ ነጠቃና ግልበጣ በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ እንዴት ይከናወናሉ?

2- በጉባኤዎቹ ውስጥ የሚከናወነው የግእዝ ቅኔ ትምህርት አሰጣጥ ስርአትና የተማሪዎቹ የአኑዋኑዋር ሁኔታን በተመለከተ በቀድሞዎቹና በአሁኖቹ በጎጃም ጉባኤዎች መካከል የሚታየው ልዩነት ምንድን ነው? ለምን?

3- በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ተዘውትረው በአፈ ታሪክነት የሚነገሩ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

4- የቅኔ ጉባኤ መምህራንና ተማሪዎች የአኑዋኑዋር ስርአትና የመማር ማስተማር ፍላጐት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

5- ጥንታዊዎቹ የቅኔ ጉባኤዎች ከነባህላዊና ሀይማኖታዊ ቅርሳቸው ተጠብቀው እንዲኖሩ ምን ቢደረግ ይሻላል?

## 1.4 ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት አድርጐ የሚመለከተው የተመረጡ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎችን (ፍኖተ ሰላም ደብረ ጊዮርጊስ፣ ድንግራ ማርያም፣ ሸለል ገብርኤልና ገዳመ አስቄጥስ) የተባሉ ቦታዎችን መነሻ በማድረግ በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚከናወኑትን የመማር ማስተማር ስርአትንና በውስጡ የሚታዩ ሌሎች ተግባሮችን ማለትም ስለ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋ፣ ነጠቃና ግልበጣ እንዲሁም፣ የቅኔ አቀራረብ ስርአት በማህሌትና በክብረ በአላት ላይ ምን መልክ እንዳለው ይዳስሳል፡፡ የእንግዳ ተማሪ አቀባበልና መስተንግዶ፣ ምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስርአት፣ አለባበስና የቁሳቁስ አጠቃቀም፣ የሆሳእና አዘገጃጀትና የአወሳሰድ ስርአቱ፣ በደመና ስለመንሳፈፍና በነፋስ ሰረገላ ስለመክነፍ፣ የቅኔ መምህራን ህይወትና የቅኔ መነሻ ታሪኮች ምንነት የሚሉት ርእሰ ጉዳዮችም በዚህ ጥናት ወሰን ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

## 1.5 ጠቃሜታ

ይህ ጥናት ከርእስ ነገሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ላላቸው አካላትም ሆኑ አባላት ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል ተስፋ የጣልኩባቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የግእዝ ቅኔን ርእስ ጉዳያቸው አድርገው በዝርዝር ማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች መነሻም ደጋፊም ሊሆን ይችላል፡፡
2. በፎክሎር ጥናትና ምርምር በተለይ በ «ሀይማኖታዊ ፎክሎር» ጥናት ዘርፍ ለተሰማሩና መ ሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች በጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ስርአት ውስጥ ተገዘውት የማያልቅ የጥናትና ምርምር መስመር መኖሩን ሊጠቁም ይችላል፡፡
3. የግእዝን ቅኔ ከነጉዋዙ ስርአተ ትምህርት ቀርጾ፣ የትምህርት ሚኒስቴርን መስፈርት አሙዋልቶና ዘመናዊ የትምህርት ተቋዋም ገንብቶ ሙያውን ማስተማር ለሚፈልግ ተቆርቋዋሪ ባለሀብት መነሻ እውቀት ይሰጣል፡፡
4. ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነት ስርአትና ስለ ግእዝ ቅኔ ስርአት አመጣጥ ታሪክ ማጥናት ለሚፈልጉ የታሪክ ተመራማሪዎች አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
5. በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሀሳቦች የግእዝን ቅኔ በግል ጥረት ለመማርና ለማወቅ የሚፈልጉ ሁሉ ስለሙያው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡



ILS LIBRARY

6. የዘመኑ ወጣቶችም ሆኑ መጭዎቹ ህጻናት ፍላጎቱ ኖሩዋቸው ስለሀገራቸው ጥንታዊ የግእዝ ቅኔ ባህል ለማወቅ ከፈለጉ እንብበው እንዲረዱ መንገድ ይከፍታል።

7 ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስርአተ ትምህርትና ጥንታዊ ባህሎች መረጃ ማሰባሰብ ለሚፈልጉ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

### 1.6 የጥናቱ ዘዴ

የምርምር ስራን ለማከናወን የሚያግዙ የተለያዩ የጥናት ዘዴዎች እንዳሉ ይታወቃል። አንድ ተመራማሪም የምርምር ስራውን ለማከናወን በቅድሚያ የትኞቹን የጥናት ዘዴዎች መከተል እንደሚገባው ሊያጠና ከወሰነው የጥናት ስራው ባህርይ አኳዋያ መወሰን አለበት። የዚህ ጥናት አቅራቢም የተከተላቸው የጥናት ዘዴች፣ ምልከታ/observation/ ፣መጠይቅ /interview/ እና ተሳትፎ /participation/ የተሰኙት ናቸው።

የጥናት ስራው የተጀመረው ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን መጻህፍትና የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን በማሰባሰብና በማንበብ ነው። ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች እንዲሰበሰቡና እንዲነበቡ የተደረገበት ዋናው ምክንያት፣ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተነሱትን ነጥቦች በመለየት የዚህን ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ለመወሰን፣ እንዲጠና ስለተመረጠው ርእሰ ጉዳይ በቂ የሆነ ጽንሰ ሀሳብና መነሻ መሰረት ለማግኘ ት፣ የተሻለ ያጠናን ስልት ለመምረጥና በተዛማጅ ስራዎች ላይም ተገቢ ቅኝት ለማድረግ ሲባል ነው። በቤተ መጻህፍትና ከቤተ መጻህፍት ውጭ የሚከናወነው ስራ እንደተገባደደ ለመስክ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን /ካሜራ፣መቅረጸ ድምጽ፣ ማስታወሻዎች . . ./ እና በቂ ገንዘብ በመያዝ ለጥናት ስራው ወደ ተመረጡትና ጉጃም ውስጥ ወደሚገኙ የቅኔ ጉባኤዎች/ ፍኖተ ሰላም ደብረ ጊዮርጊስ፣ ድንግሪ ማርያም፣ ሸለል ገብርኤልና ገዳመ አስቄጥስ/ ጉዞ ተደርጉዋል።

ለሁለት ጊዜ ያህል ወደጥናት ቦታዎች በመመላለስ በምሳሌነት የታዩትን የቅኔ ጉባኤዎች መነሻ በማድረግ በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚከናወነው የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ፣ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደትና የተማሪዎቹና የመምህራኑ ህይወት ምን እንደሚመስል ለማየት ጥናት ተሞክሩዋል።

በተጨማሪም፣ ጥናት አቅራቢው አስቀድሞ ከ20 እና 30 አመታት በፊት በውስጡ ሆኖ ከሚያውቀው አንጻር በቅኔ ቤት ህይወት ውስጥ አሁን ምን የተለየ ክስተት እንዳለ ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ ተግባሩ በሚፈጸምበት ቦታ በአካል በመገኘ ትና ተሳታፊ በመሆን የምርምር ስራውን አከናውኑዋል።

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የነበሩ እድሎች

### 1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናትና ምርምር ሲካሄድ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ የሚታወቅ ነው፡፡ በተለይ ሰፊ የምርምር ስራ ባልተሰራበትና ሀሳቡ በዘመናዊ ዳታ /ኢንተርኔት/ በበቂ ሁኔታ በማይገኝበት መስክ ጥናትና ምርምር ማድረግ አስቸጋሪነቱን የበለጠ ያጉላዋል፡፡ ይህ የጥናት ስራ በሚካሄድበት ጊዜ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የዚህ ጥናት አቅራቢ ስራውን ለመስራት ወደ ተመረጡ የቅኔ ጉባኤዎች በሄደ ጊዜ በአካባቢው የሚኖሩ ታዋቂ የቅኔ መምህራን በተደረገላቸው የተለየ ጥሪ አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደ ሀይማኖታዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የተመለሱበት ወቅት በመሆኑ፤ በዚህም ምክንያት መምህራኑ በአካባቢው አንዳንድ አባቶችና በብዙ ታዋቂ ሰዎች ዘንድ በመናፍቅነት ተወቃሽ እንዲሆኑ የተደረገበት ወቅት ስለነበረ፤ የቅኔ መምህራኑን በአካል በተገኙበት ጊዜ ለጥናት ስራው ለመተባበር ፈቃደኛ ለመሆን አለመፈለጋቸውና አጥኚውንም መጠርጠራቸው፤
2. ርእስ ጉዳዩን አስመልክቶ ተዘጋጅተው የታተሙት አንዳንድ መጻህፍት ለሚጠቅሱት ሀሳብ በቂ ማስረጃ የማያመላክቱና በአፈ ታሪክነት የሚነገሩ ጉዳዮችን ከእውነታው ጋር ቀላቅለው የሚያቀርቡበት ሁኔታ መኖሩ፤
3. ስለሙያው የተጻፉት አብዛኛዎቹ ጽሁፎች የሚያቀርቡት ርእስ ነገር በአብዛኛው ቀድሞ ከተጻፉት ስራዎች ያልተለየና የነበረን ሀሳብ እንዳለ ከማስተላለፍ ያለፈ የጎላ የተለየ ነገር የማይገኝባቸው መሆኑ፤
4. የጥናት መስኩ ስለጥናትና ምርምር በቂ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ገና በአግባቡ ያልተጠና በመሆኑ በጥናቱ ወቅት ትክክለኛ ማስረጃ ለማግኘት ችግር መኖሩ፤
5. በጥናት ስራው ወቅት በአቀባይነት የተመረጡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ሆሳእና (መድኃኒት) አዘገጃጀትና ምንነት በዝርዝር እንዲገልጹ ሲጠየቁ «ሚስጢሩ ከወጣ ይረክሳል፡፡» በሚል ምክንያት ጉዳዩን ለመግለጽ አለመፈለጋቸው፤

6. በጥናት ስራው ውስጥ የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ ቃላት የግእዝ ቃላት በመሆናቸው ምክንያት የጽህፈቱ ስራ በሚሰራበት ጊዜ በተደጋጋሚ ቃላትንና ፊደላትን በትክክል መገልበጥ ማዳገቱ፤

7. የጥናት ስራው አካል የሆነው የመስክ ስራ የተካሄደው በዘመነ ጽጌና ክብረ በአላት በሚነግሱበት ወቅት በመሆኑ፤ ወቅቱም የቅኔ ተማሪዎች የአመት ቀለባቸውን የሚያሰባስቡበትና ቀለብ በልመና እንደልብ የሚገኝበት ወቅት ስለነበር ተማሪችዎን በጉባኤ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ማግኘት አለመቻሉ ናቸው።

1.7.2 የነበሩ እድሎች

1. የዚህ ጥናት አቅራቢ በተመረጠው ርእሰ ጉዳይ ላይ መጠነኛ ግንዛቤና እውቀት የነበረውና በስርአተ ትምህርቱም ውስጥ ያለፈ በመሆኑ በወቅቱ መረጃ ላለመስጠት ተፈጥሮ የነበረውን አንዳንድ ችግር ከቅኔ ተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን ጋር በቀላሉ በመግባባት የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት ችሉዋል፤

2. የጥናት ስራው በተካሄደበት አካባቢ የጥናት አቅራቢው ቤተዘመዶች የሚኖሩበት በመሆኑ ሊያጋጥም ይችል የነበረውን የገንዘብ እጥረት ለመቀነስ አስችሉዋል፤

3. አጥኚው የግእዝ ቁዋንቁዋ ውስን እውቀት ያለው በመሆኑ የጥናት ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በቁዋንቁዋው የተጻፉትን ጽሁፎችም ሆነ የሚነገሩ ሀሳቦችን በመረዳትና በመመርመር ለጥናት ስራው በሚያመች መልኩ በማደራጀት ረገድ ትልቅ እገዛ ነበረው።

# ምእራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የርእሰ ነገሩ መነሻዎች

> እስካሁንም ድረስ አስተሳሰባችንንና ተግባራችንን የሚመሩ ሶስት ዓይነት ሚቶች አሉ፡፡ እነርሱም፤ ነገረ ፍጥረት፣ ነገረ አማልክት (ነገረ መላእክት) እና ተረክ (ነገረ) ተጋዳሊ ናቸው (ዮናስ፣ ለማስተማሪያ የተዘጋጀ ጽሁፍ፡ 1998፡ ገጽ2)፡፡

ነገረ ፍጥረት፤ ከየት መጣሁ? ፍጥረት እንዴት ተጀመረ?.... የተሰኙ ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ ነገረ አማልክት ደግሞ፣ ማን ፈጠረኝ? እንዴትስ ተፈጠርኩ?.... እያለ የሰውን ልጅ አመጣጥና ሀይማኖታዊ ስርአቱን ይመረምራል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችና ጥያቄዎቹ የሚፈጥሩት የይሆናል መልስ ጥርቅም የፎክሎር (ትውፊት) ጥናትና ምርምር መስክ አንዱ ክፍል ሆኑዋል፡፡ ከዚህ አኩዋያ ሲመረመር ስርአተ አምልኮ ከነአከዋወን ስርአቱ የፎክሎር ጥናትና ምርምር መስክ አካል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የምርምር መስኩም ከሰው ልጅ መገኘት ጊዜ ጀምሮ የነበረና አብሮ ያደገ ስለመሆኑ መገመት አይከብድም፡፡

ፎክሎር፣ የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጸው በ1846 በዊሊያም ጆን ቶምስ ነው፡፡ በውስጡ ያካትታቸዋል ተብለው የተዘረዘሩትም ብዙ ናቸው፡፡ ዳንደስ ባዘጋጀው መጽሀፍ ውስጥ ከ60 ያላነሱትን ዘርዝሩዋል (ዳንደስ፡1963፣3) ማሪያ ሊች ባዘጋጀችው መጽሀፍ፤ ቅጽ አንድ ላይም ቃሉ በ21 የአሜሪካ ፎክለረኞች የተለያዩ ትርጉዋሜ የተሰጠው መሆኑ ተገልጽዋል (ማሪያ ሊች፣1949፣398-403)፡፡

ሀይማኖታዊ ስርአቶችና ባህላዊ ክዋኔዎች በፎክሎር ጥናትና ምርምር መስክ ስር ሆነው ሊጠኑ የሚገባቸው ስለመሆናቸው የተለያዩ ጸሀፊዎች የፍክሎርን የጥናትና ምርምር መስክ በዘረዘሩባቸው የጥናት ስራዎቻቸው ውስጥ በግልጽ አስፍረዋል፡፡ ከነዚህ ጸሀፊዎች መካከል ዶርሰን አንዱና ዋናው ተጠቃሽ ነው፡፡ ዶርሰን የፎክሎርን የጥናት ዘርፎች በአራት መድቡዋቸዋል፡፡ ፈቃደም ለአማርኛ ቁዋንቁዋ አተረጉዋጎም በሚያመች መልኩ ወደ አማርኛ መልሱዋቸዋል፡፡ እነሱም፣ ስነቃል (oral folklore)፣ ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበባት (Performance Folk art)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Customs) እና ቁሳዊ ባህል (Material Culture) የተሰኙት ናቸው (ድርሰን፣1972፣2፤ ፈቃደ፣ 1991፣15)፡፡

ፈቃደ ከዶርሰን ሀሳብ በመነሳት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performance folk art) በተሰኘው የፎክሎር ጥናት ዘርፍ ስር ልዩ ልዩ ሀይማኖታዊ ስርአቶችን ማለትም፣ የመስቀል፣ የልደት፣ የጥምቀት.... በአላት አከባበር፤ የቅዳሴ ስርአት፣ የታቦት ንግስ፣ የስግደት ስርአት፣..... ሊጠኑ እንደሚችሉ አስፍሩዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ሀይማኖትና ባህላዊ

የእምልኮት ስርአቶች ደግም ሀገረሰባዊ ልማድ (Social folk custom) በተሰኘው የጥናት ዘርፍ ስር ሊጠኑ እንደሚገባ አሳይቱዋል:: /ፈቃደ 1991፣12-13/

ሌላዋ አሜሪካዊት ፎክሎረኛ ዛይናብ ሀሩና (Zainab Haruna) ፎክሎር በሶስት የጥናት ዘርፎች ተመድቦ ሊጠና የሚገባ መሆኑን ስታመለክት፣ የብሪቲሽ ፎክሎር ሶሳይቲ አባል የሆነው ማይክ ባላንታይን (Mike Ballantyne) በበኩሉ የጥናት ዘርሶበን በአራት ይከፍለዋል::

> Folk literature is one of the three main genres of folklore namely: folk literature, folk custom (what people do to communicate their culture etc.) and material culture (what people make or material objects people use to communicate their culture, etc (Zainab www.ultimate counter.com.2003).

> For a proper understanding and definition of folklore and folktale it is essential to look at its separate parts. Among these parts are; social customs, occupational folklore, oral literature and material culture (Mike:mike@folklore.bc.ca.2001)

ሁለቱም የፎክሎር ተመራማሪዎች ስለ ፎክሎር የጥናት ዘርፎች ባሰፈሩት ጽሁፍ የሃይማኖት ስርአት በፎክሎር የምርምር መስክ ስር ሊጠና የሚገባ መሆኑን ገልጸዋል:: ዘይናብ፣ ሀይማኖታዊ ስርአቶች የቃላዊ ጽሁፍ /Folk literature/ ጭብጦች እንደሆኑ የገለጸች ሲሆን፤ ማይክ በበኩሉ ሃይማኖታዊ ፌስቲባሎች በሀገረሰባዊ ልማድ (Social Customs) ስር ሊጠኑ የሚገባቸው መሆኑን አስፍሩዋል:: ሃይማኖታዊ ስርአቶች በፎክሎር የምርምር ዘርፍ ስር የሚጠኑ ስለመሆናቸው ሌሎች የሙያው ሊቃውንትም በተለያዩ ስራዎቻቸው አመልከተዋል:: አሜሪካዊው ፎክሎረኛ አለን ዳንደስ (Alan Dundes) የፎክሎር ምርምር ዘርፍ ምንን ማካተት እንዳለበት በገለጸበት ጽሁፍ ውስጥ የአምልኮ (እምነት) ስርአትን አካትዋል::

> *Folklore includes myths, legends, folktales, jokes. . . It also includes folk custom, folk dance, folk drama (and mime), folk art, folk belief (or superstition), folk medicine,…(Dundes1965:3)*

ፎክሎር መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ እንጂ ቁሳዊ ነገሮች ላይ የሚያተኩር እንዳልሆነ፤ ትኩረቱም በቃላት አማካይነት በሚፈጠሩት ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት ፈቃደ ቭላድሚር ፕሮፕ (Vladmir Propp) ያሰፈረውን ሀሳብ እንደሚከተለው ገልጾታል::



LIBRARY

... ፐሮፐ ደግሞ ባንድ በኩል «By folklore we mean only spiritual production and only verbal, Poetical products » /1993:4/ ሲል ሙያው መንፈሳዊውን እንጂ ቁሳዊውን እንደማይጨምር፣ ትኩረቱም በቃላዊ አማካኝነት በሚፈጠሩት ላይ ብቻ መሆኑን ይናገራል *(ፈቃደ 1991፣15)::*

በሌላም በኩል ሩት ፊኒጋን (Ruth Finnegan) Oral literature in Africa በሚል ርእስ በ1970 ባሳተመችው መጽሀፍ Religious Poetry በሚለው ርእስ ስር ስለ ሀይማኖታዊ ግጥሞች ምንነት በዝርዝር ካነሳች በሁዋላ «የኢትዮጵያውያን ደብተራ ግጥሞች» በሚል የግእዝ ቅኔን በምሳሌነት አንስታለች (Finnegan:1970:167):: ዳንኤልሰን (Danielson) የተባለው ፎክሎረኛም ሀይማኖታዊ ፎክሎር (Religious Folklore) በሚል ርእስ ባዘጋጀው ጽሁፍ ሀይማኖታዊ ክዋኔዎችና የአፈጻጸም ስርአቶቹ በፎክሎር ጥናትና ምርምር ስር ሊጠኑ የሚገባቸው ስለመሆኑ በጥናት ስራው ውስጥ በሰፊው አመላክቱዋል::

የዚህ ጥናት አቅራቢም የፎክሎር ምርምርና ጥናት ዘርፍ አንዱ መሰረት ሃይማኖታዊና አምልኮታዊ ስርአት መሆኑን በመገንዘብ ነው ጥናቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነት ስርአት አንዱ በሆነው የግእዝ ቅኔ አከዋወን ስርአት ላይ አትኩሮ ለመስራት የወሰነው::

## 2.2 ተዛማጅ ስራዎች

የግእዝ ቅኔን መሰረት አድርገው የተሰሩትን ዋና ዋና ስራዎች በሁለት ዘርፎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል:: አንደኛው የግእዝን ቅኔ ርእስ ጉዳይ አድርገው የተጻፉና የታተሙትን መጻህፍት የሚያጠቃልል ነው:: ሁለተኛው ደግሞ የተጠቀሰውን ርእስ ጉዳይ መነሻ በማድረግ ተጽፈው ያልታተሙትንና ለዲግሪ ማሙዋያ የተጻፉትን የጥናት ወረቀቶች የሚያካትት ነው::

### 2.2.1 የታተሙ

የግእዝን ቅኔ መነሻ አድርገው የተጻፉትና የታተሙት አብዛኛዎቹ መጻህፍት በሙያው የላቀ ደረጃ በበቁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተዘጋጁ ናቸው:: ከነዚህ አባቶች መካከል የተወሰኑት በቲዎሎጂ ዲግሪ ያላቸው ይገኙበታል:: ሌሎች ደግሞ የቅኔው ሙያ እውቀት ያላቸው ሆነው በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ሆነው ያለፉ ናቸው::

ብዙዎቹ ለህትመት የበቁ መጻህፍት ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የላቸውም:: ሆኖም የግእዝን ቅኔ ርእስ ጉዳያቸው አድርገው የተጻፉ በመሆናቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት ስራ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: የበለጠ ቀረቤታ ኖሩዋቸው በዚህ ርእስ ስር ቅኝት የተደረገባቸው ብዙ መጻህፍት ይገኛሉ:: ከነዚህም መካከል፣



UNIVERSITY LIBRARY

አለማዬሁ ሞገስ፣ በ1950 «ሰዋስወ ግእዝ» በሚል ርእስ፤ ሀብተ ማርያም ወርቅነህና አድማሱ ጀንበሬ ደግሞ በ1963 «ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት» እና «መጽሀፈ ቅኔ» በሚሉ ርእሶች ስለግእዝ ቅኔ ተቀራራቢ ይዘት ያላቸው ሀሳቦችን አስፍረዋል፡፡ አለማየሁ «ቅኔ» በሚል ርእስ ስር ባዘጋጁት ጽሁፍ ስለ ቅኔ ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ፣ እንዲሁም ስለ አይነቱና የአቀራረብ ስልቱ ሰፋ ያለ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ሀብተማርያም ወርቅነህም በመጽሀፋ ምእራፍ አራት እንዲሁ «ቅኔ» በሚል ርእስ ባዘጋጁት ጽሁፍ ውስጥ ስለ ቅኔ ትርጉም፤ ስለ ጀማሪ ደራሲው ማንነት፣ አይነቶቹንና መንገዶችን በዝርዝር አስፍረዋል፡፡ የአድማሱ ጀንበሬ ስራም 1619 የቅኔ ስብስቦችን ከመያዙ በስተቀር ከሁለቱ ስራዎች የጎላ ልዩነት የለውም፡፡ በ1960 በይኄይስ ወርቁ የተጻፈው «ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት» የተሰኘው መጽሀፍም ከላይ ከተጠቀሰው የተለየ ሀሳብ የያዘ አይደለም፡፡

በ1950ዎቹ መጀመሪያና መጨረሻ የተጻፉት እነዚህ መጻህፍት ቅኔን እንደ አንድ ርእስ ጉዳይ ያነሱ በመሆናቸው ስለ ግእዝ ቅኔ ትርጉም፣ ታሪካዊ አመጣጥና ስለ አይነቶቹ ምርምር በተደረገበት ወቅት የነበራቸው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነበር፡፡ በተለይ አለማየሁ ሞገስ ያዘጋጁት መጽሀፍ የጎጃምን ቅኔ ታሪካዊ አመጣጥና የጀማሪ መጻህፍት ደራሲውን ማንነት በመጠቆም ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይህን ጥናት ከተጠቀሱት መጻህፍት የሚለየው ትኩረቱ በተመረጠ ውስን የጎጃም አካባቢ የቅኔ ጉባኤዎች መነሻነት በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ስለሚከናወነው የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ነው፡፡

በዜና ማርቆስ እንዳለው «ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር አንድ፤ የግእዝ ቋዋንቋዋ ለአራተኛ ክፍል፤ እና ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር ሁለት» በሚሉ ርእሶች የተጻፉት ሶስት መጻህፍትም ቅኔን ርእስ ጉዳያቸው አድርገው የተጻፉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው መጽሀፍ፣ ስለ ቅኔ አስተዋጽኦ፣ ስለጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ተማሪ ህይወት፣ ስለ ግእዝ ቋዋንቋዋ ስርአተ ንባብ፣ ስለ ቅኔ ጠባይና ሌሎችንም ርእስ ጉዳዮች ያነሳል፡፡ የሁለተኛው መጽሀፍ ትኩረት የቅኔን ቋዋንቋዋ ቀለል ባለ መንገድ በማስተማር ዘዴ ላይ ነው የሚያተኩረው፡፡ በተለይ የግስ አረባብ ስርአቱንና አረፍተ ነገር አመሰራረቱን ከአማርኛ ቋዋንቋዋ ጋር እያመሳከረ ያስተምራል፡፡ ሶስተኛው መጽሀፍ ደግሞ ስለ ቅኔ አይነቶችና መልኮች፣ በግእዝ ቅኔ እና በአማርኛ ግጥሞች መካከል ስላለው ልዩነትና ተመሳሳይነት ያሳያል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱም መጻህፍት ስለ ግእዝ ቅኔና የግስ ግሰሳ ስርአት ሰፊ ሀሳብ ያሰፈሩ ቢሆንም በተለይ የጎጃምን የግእዝ ቅኔ በአርእስትነት ለይተው አያሳዩም፡፡ ስለ ቅኔ ቆጠራ ነገራም ሆነ ዘረፋ የተለየ ርእስ ሰጥተው አይመለከቱም፡፡ የጎጃምን የቅኔ ቤት ህይወትም አይዳስሱም፡፡ ስለዚህ ሶስቱም መጻህፍት የግእዝን ቅኔ ርእስ ጉዳይ አድርገው ከማንሳታቸው በስተቀር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ብዙ ነገር የለም፡፡



IES LIBRARY

ቅኔን መሰረት አድርገው የተጻፉ ሌሎች ስራዎች ደግሞ «የግእዝ ቅኔያት የኪነ ጥበባት ቅርስ» በሚል ርእስ በ1980 እና በ1984 በተከታታይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎች አካዳሚ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር የታተሙ መጻህፍት፣ «ትርጉዋሜ ቅኔ ፈለገ ህይወት» በሚል ርእስ በ1992 በነአለቃ ኤሊያስ ነቢየ ልኡል የታተመው መጽሀፍና (The Meaning of Quine) በሚል ርእስ በ2006 በቀሲስ ክፍያለው የተጻፈው መጽሀፍ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን መጻህፍት ከላይኞቹ የሚለያቸው፣ የቅኔን ትርጉም፣ ታሪካዊ አመጣጥና አይነታቸውን ከመግለጻቸው በተጨማሪ የተለያዩ የቅኔ ስብስቦችን በማካተት የእያንዳንዱን ቅኔ ንባብ፣ ትርጉዋሜና ሀተታ (ሚስጢር) ጭምር የሚያመላክቱ መሆናቸው ነው፡፡

«የግእዝ ቅኔያት» በሚል ርእስ፣ የታተሙት ሁለት መጻህፍትም በድምሩ 737 የቅኔ ስብስቦችን ከነትርጉዋሜያቸውና ሀተታቸው አሰባስበው የያዙ ከመሆናቸው በተጨማሪ ስለግእዝ ቅኔ አጀማመርና አረማመድ፣ ስለ ቅኔ ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ፣ እንዲሁም ስለ ቅኔዎቹ ባለቤት ማንነት በዝርዝር ተመልክቶባቸዋል፡፡ በነአለቃ ኤሊያስ ነቢየ ልኡል ተጽፎ «ትርጉዋሜ ቅኔ ፈለገ ህይወት» በሚል ርእስ የታተመው መጽሀፍም በግእዝ ቅኔያት ውስጥ ከተጠቀሱት ሀሳቦች በተጨማሪ በጥንታዊዎቹ የቅኔ ጉባኤዎች የሚነገሩ አፈ ታሪክ መሰል ሀሳቦችንም ይዙዋል፡፡ በውስጡ የተሰበሰቡት ቅኔዎችም እንደ ቅኔ አይነቶቹ ተለይተው በቅደም ተከተል የሰፈሩ ናቸው፡፡ በቀሲስ ክፍያለው «The Meaning of Quine» በሚል ርእስ የተዘጋጀው መጽሀፍም የቅኔን ጽንሰ ሀሳብ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ለማስተዋወቅ ሲባል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመጻፍ የተሞከረ ከመሆኑ በስተቀር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኝ የተለየ ነገር የለውም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱም መጻህፍት ለስራቸው መነሻ መሰረት ያደረጉት በ1950ዎቹና 1960ዎቹ ቅኔን ርእስ ጉዳያቸው አድርገው የተጻፉትን መጻህፍት በመሆኑ የተወሰኑ የአቀራረብና የትርጉም ለውጥ ከማድረጋቸው በስተቀር በይዘት ደረጃ የጐላ ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚያገናኛቸው የጐላ ነገር የለም፡፡

«ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ» በሚል ርእስ በ1992 በገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም ተጽፎ የታተመው መጽሀፍ ስለቅኔ ከተጻፉት መጻህፍት መካከል አንዱ ነው፡፡ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ቅኔና ሂደቱ፣ የቅኔ ትምህርት አጀማመር፣ ቅኔ የተለያየ ስሜት መግለጫ ስለመሆኑና ቅኔ በኢትዮጵያውያን አድባራትና ገዳማት በሚሉ ርእሶች ውስጥ ጠቃሚ ሀሳቦች ሰፍረዋል፡፡ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ቀደምት አባቶች ስለቅኔ የጻፏቸውን ጽሁፎች በመመርመር ጥንካሬና ድክመቶችን ለማመላከት ተሞክሯል፡፡ የተጠቀሱት ርእሰ ጉዳዮችም የጥናትን መንገድ ተከትለው የቀረቡ በመሆናቸው ለዚህ ጥናት ሥራ ጠቀሜታቸው የጐላ ነው፡፡



ES LIBRARY

መጽሀፋ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የቅኔን መሰረታዊ እውቀቶች ማንሳቱ ብቻ ነው። በተጨማሪም ስለጎጃም ቅኔ አመሰራረት የሚያነሳ በመሆኑ ግንኙነት ይኖረዋል። ይሁን እንጂ መጽሀፋ በጉጃም ውስጥ ስለሚካሄዱ የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ የሚዳስስ ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰልም።

በመጨረሻ የሚነሱት «ሰዋሰወ ግእዝ» በሚ ል ርእስ በ1992 የታተመው መጽሀፍና «መጸሀፈ ታሪክ ወግስ» በሚል በ1997 በመምህር አፈወርቅ ተክሌ ተዘጋጅቶ የታተመው መጽሀፍ ነው። የሁለቱም መጻህፍት ይዘት ዋናው ትኩረት የቅኔ ትምህርት አንዱ አካል በሆነው የግስ ግሰሳ ስርአት ላይ ነው። መጽሀፈ ታሪክ ወግስ የተሰኘው መጽሀፍ በውስጡ እንደሌሎቹ መጻህፍት ሁሉ ስለ ቅኔ ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጡ፣ ስለቅኔ ዜማ ልክና መንገዶችም ተመልክቱዋል። የመጽሀፋ ዋና ይዘት ሆኖ የቀረበው ግን የግእዝ ቁዋንቁዋ ግስ አወራረድና ለቅኔ ነገራ መነሻ ሆነው የሚተረኩት እለታዊ፣ ወርሃዊ፣ ወቅታዊና አመታዊ በአላት በዝርዝር ተገልጸውበታል። ሰዋስወ ግእዝ የተሰኘው መጽሀፍም እንዲሁ ትኩረት የሚሰጠው በስርአተ ግስ ላይ ነው። መጽሀፋ በውስጡ የግእዝ ቁዋንቁዋ መማሪያ መሰረት የሆነው እርባ ቀመር፣ እርባ ግስ፣ ነጠላ ግስና አገባብ በዝርዝር ተገልጸውበታል። የግእዝን ቁዋንቁዋ ግሶችም በየቤታቸው ከፋፍሎ ይዝዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት መጻህፍት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው የቅኔ ትምህርት መሰረት የሆነውን የግእዝ ቁዋንቁዋ ማስተማሪያ ግስ ከነቀመሩ በውስጣቸው መያዛቸው ነው። ቅኔን ተምሮ ለማወቅ በተጠቀሱት ሁለት መጻህፍት ውስጥ የተጠቀሰውን የግስ አረባብ ስርአት ከነቀመሩ ማወቅን ስለሚጠይቅ ነው። ከዚህ ባሻገር የመጽሀፎቹ ይዘቶች ከዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ ጋር ግንኙነት የላቸውም።

ከላይ ከተጠቀሱት መጻህፍት በተጨማሪ ከግእዝ ቅኔ ጋር በተገናኘ የተጻፉ ሌሎች መጻህፍትም አሉ። ለምሳሌ ያህል «ፍኖተ ግእዝ» በሚል ርእስ በ1986 በያሬድ ፋንታ የተጻፈውን፣ «የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ» በሚል ርእስ በ1986 በከፍያለው መራሂ ተጽፎ የታተመውን፣ «ሀገረ መጻህፍት ሰዋስወ ግእዝ ወአማረኛ» በሚል ርእስ በ1988 በአለቃ አፈወርቅ ዘውዴ የተጻፈውን እንዲሁም «የግእዝ ቁዋንቁዋ መማሪያ» በሚል ርእስ በ1994 በገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም የተጻፈውን መጽሀፍ መጥቀስ ይቻላል። ይሁን እንጂ ሁለም ቢሆኑ ቅኔን ለመማር ከሚያስፈልጉት ጉዳዮች የተወሰኑትን ከመጥቀሳቸው ያለፈ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኛቸው ጉልህ ነገር የለም።

### 2.2.2 ያልታተሙ

ያልታተሙ የጽሁፍ ውጤቶች የሚባሉት፣ በተለያዩ ሴሚናሮችና አውደ ጥናቶች ላይ ቀርበው በመጽሄቶች ላይ የታተሙና ያልታተሙ ጥናቶች፣ ከኢንተርኔት የተገኙ ጽሁፎችና፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ስርአተ

ትምህርትና የአምልኮ ስርአት ከሚጻፍባቸው ዌብ ሳይቶች የሚገኙና ለዲግሪ ማሙያ የቀረቡ ጥናቶችን የሚያጠቃልል ነው። የግእዝ ቅኔን መነሻ በማድረግ፤ የምርምር ውጤቶችን በአውደ ጥናቶች ላይ በማቅረብ የሚታወቁት አለማየሁ ሞገስ ናቸው። በአለማየሁ ሞገስ ተጠንተው ከቀረቡት መካከል በተለይ፣ 'Language teaching and curricula in traditional education of Ethiopian Orthodox Church' በሚል በ1972 የቀረበውና 'Geez and Amharic study without quine is incomplete' በሚል በ1966 የቀረቡት የጥናት ጽሁፎች ተጠቃሾች ናቸው። አለማየሁ በነዚህ የጥናት ስራዎች ያስፈሩዋቸው ሀሳቦች አብዛኛዎቹ በ1950 «ሰዋስወ ግእዝ» በሚል ርእስ ካሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ የተቆነጠሩ ናቸው። ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ግንኙነትም ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የተለየ አይደለም።

http //www. Ethiopia. Com በተሰኘ ዌብሳይት 'The Ethiopian othodox church school system' በሚል ርእስ የቀረበሙ የጥናት ውጤት፣ http.ll members. Lycos .co. uk በተሰኘ ዌብሳይት 'A brief introduction to qene' በሚል ርእስ የወጣ ጽሁፍም ሆነ በኤፍሬም ይስሀቅ 'Religion of Ethiopia' በሚል ርእስ በቀረበው የጥናት ውጤት የግእዝ ቅኔን እንደ አንድ ርእሰ ጉዳይ አንስተዋል። በተለይ 'The Ethiopian orthodox church school system' በሚል ርእስ በተዘጋጀው ጥናት ውስጥ ስለ ግእዝ ቅኔ የትምህርት ስርአትና ስለ ትምህርት ይዘቱ ሰፋ ያለ ሀሳብ ሰፍሩዋል። ሁሉም ስለ ግእዝ ቅኔ የተለያየ ሀሳብ ያንሱ እንጂ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ አይደሉም። ይህ ጥናት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ትኩረቱ በጐጃም የቅኔ ጉባኤዎች ላይ ሆኖ በይዘቱም ስለጐጃም የግእዝ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋና ሌሎች የግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ስነ ስርአቶችን ይመለከታል። ይህም በመሆኑ ከተጠቀሱት ጥናቶች ይለያል።

ከዚህ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪም ቢሆን ግንኙነት ያላቸው ብዙ የዲግሪ ማሙዋያ ጥናቶች ቀርበዋል። የበለጠ ቀረቤታ ያላቸው ግን ሶስት ጥናቶች ናቸው። እነሱም በጽጌ አባተ «ቅኔያዊ ውርስ» በሚል ርእስ በ1972፣ በምስጢረ ሰዋስው «ጥንታዊ የግእዝ ቅኔ ትምህርት አሰጣጥ» በሚል በ1974 የቀረበውና «የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሸራ ውስጠ ዘ የግእዝ ቅኔ ከሌሎች ቅኔዎች የሚለይባቸው ባህርያት» በሚል ርእስ በ1993 በአበበ ከበደ የቀረበው የዲግሪ ማሙዋያ ጽሁፍ ተጠቃሾች ናቸው። በጽጌ አባተ እና በምስጢረ ሰዋስው የቀረቡት ጽሁፎች ስለ ግእዝ ቅኔ ምንነት፣ አጀማመርና ስለቅኔ አይነቶች ለማሳየት ከመሞከራቸው በተጨማሪ በተለይ ምስጢረ ሰዋስው ስለግእዝ ቅኔ ትምህርት አሰጣጥ፣ ስለጥንታዊ የቅኔ ተማሪ ህይወት፣ እንዲሁም ስለ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ ስርአት መጠነኛ ሀሳብ አስፍሩዋል። አበበ ከበደ ደግሞ፣ ስለ ውስጠ ዘ ቅኔ ልዩ ባህርይ፣ ውስጠ ዘ ቅኔ ከሌሎች የግእዝ ቅኔ አይነቶች በምን እንደሚለይና

የውስጠ ዘ ቅኔ መነሻ መሰረትም ጎጃም እንደሆነ በመዘርዘር ሰፊ ምልከታ አድርጉዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኛቸው የተወሰነ ነገር አለ፡፡ በምስጢረ ሰዋሰው ስለ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ መነሳቱ፣ አበበ ከበደም የጎጃም የቅኔ ሊቃውንት መለያ ስለሆነው ውስጠ ዘ ቅኔና የጎጃም የቅኔ መሰረት እንደሆነ ስለሚነገርለት የዋሸራ ጉባኤ ዘገባ ማቅረቡ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚያገናኛቸው ይሆናል፡፡

ይህ ጥናት ከነዚህ የመመረቂያ ወረቀቶች የሚለየው የተመረጡ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎችን መነሻ በማድረግ በጉባኤዎቹ ውስጥ የሚከናወኑ የመማር ማስተማር ስርአቱንና በውስጡ የሚታዩ ሌሎች ተግባሮችን፤ ማለትም ስለ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋ፣ ነጠቃና ግልበጣ እንዲሁም፣ የቅኔ አቀራረብ ስርአት በማህሌትና በክብረ በአላት ላይ ምን መልክ እንዳላቸው፤ የእንግዳ ተማሪ አቀባበልና መስተንግዶ፣ ምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስርአት፣ አለባበስና የቁሳቁስ አጠቃቀም፣ በቀደምት የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በአፈ ታሪክነት ስለሚነገሩ ስለመሰወር፣ በደመና ስለመጫንና በንፋስ ሰረገላ ስለመክነፍ እንዲሁም ስለሆሳእና አዘገጃጀትና የአወሳሰድ ስርአቱ በዝርዝር የተመለከተ በመሆኑ ከተጠቀሱት ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡

## 2.3 ጸዋትወ ቅኔ

የግእዝ ቅኔ ትምህርት በሀገራችን ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የኖረ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ የስነ ግጥም ጥበብ የሚጠናበት፣ የግእዝ ቋንቋዋ መማሪያ መሰረት የሆነው ግስ ከነቀመሩ የሚገሰስበት፣ የእምነትና የህይወት ታሪኮች ከነትርጉዋሜያቸው የሚተረኩበት፣.... ትልቅ የትምህርትና የምርምር ዘርፍ ሆኖ የቆየ የሀገራችን ሀብት ነው፡፡ የሙያው ሊቃውንትም መንፈሳዊውንም ሆነ አለማዊ ሀሳባቸውን ሲገልጹበት የኖሩ፣ የተከበረ ሙያቸው፣ መተዳደሪያቸውና መታወቂያቸው ሆኖ ቆይቱዋል፡፡

### 2.3.1 የግእዝ የቅኔ ምንነትና ጠቀሜታ

የግእዝ ቅኔ ትምህርት ደቀ መዝሙር ስለነባራዊ እና ኢነባራዊ (ምናባዊ) አለም እንዲያስብ፣ እንዲመራመር፣ እንዲራቀቅና ለፈጠራ ስራ እንዲገፋፋ የማነሳሳት ሀይል ያለው የሀገራችን የምርምርና የትምህርት ዘርፍ ሆኖ የኖረ ሙያ ነው፡፡ ቅኔ በአጋጣሚ፣ በተሰጥኦና በልማድ የሚደርሱት ድርሰት እንዳልሆነ ዜና ማርቆስ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> ቅኔ በአጋጣሚ፣ በተሰጥኦና በልማድ የሚደርሱት ድርሰት አይደለም፡፡ የቅኔ ትምህርት ቤት ተከፍቶለት፣ መምህር ተሠይሞለት፣ ጉባኤ ተዘርግቶለት፣ ሥርአተ ትምህርት ተዘጋጅቶለት፣

> ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሮ፣ ከመምህር መምህር ተመርጦ፣ ደበሎ ለብሶ፣ ከውሽ ተከላክሎ፣ ቁራሽ ለምኖ፣ ቆሎ ቆርጥሞ፣ የመምህሩን ቅኔ አጥንቶና አስመስሎ ቆጥሮ፣ ለመምህሩ አሳርሞ የሚማሩት ድርሰት ነው (ዜና ማርቆስ፡ 1994፡2)።

እንደተገለጸው፣ ቅኔን ተምሮ ለመቀኘትና የቅኔ ባለሙያ ለመሆን የሚፈልግ አንድ የቅኔ ተማሪ የቀደሙ የቅኔ ምሁራንን ቅኔ እየሰበሰበ አገባቡን፣ ፍችውን፣ ምስጢሩን፣ ምርምሩን፣ ፈጠራውንና ስንት ቃላት፣ ስንት ሀረጋትና ስንት ቤቶች ሊኖሩት እንደሚገባ፣ ስለቅኔው የዜማ ምጣኔ፣ ስለ ሰዋስዋዊ ሙያውና ስለ ሰምና ወርቅ አተካከሉ በዝርዝር መርምሮ ትክክል ስለመሆኑ ማወቅና ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ይህንም ተግባር በሚፈጽምበት ጊዜ ተማሪው በአስተሳሰብ፣ በምርምርና በኪነጥበብ ፈጠራ አእምሮው እየጎለበተ ስለሚሄድ ከአሰበው ለመድረስ የሚገታው አይኖርም።

## ሀ. የግእዝ ቅኔ ምንነት

ስለ ግእዝ ቅኔ ትርጉዋሜ ወይም ምንነት አያሌ የሙያው ሊቃውንት የተለያየ ብያኔ ሰጥተዋል። ብዙዎቹ ከየግላቸው እምነት ከሚመነጭ ስሜት የተስነዘሩ ሀሳቦች ናቸው። አብዛኛዎቹ ብያኔዎች የተቀራረበ ሀሳብ የያዙ ሲሆን የተወሰኑት ግን ከብዙዎቹ የተለዩ ሆነው ተገኝተዋል።

ቅኔ ለተሰኘው ቃል ሰፋ ያለ ትርጉዋሜ ከሰጡት ምሁራን መካከል ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም አንዱ ናቸው። ቅኔ እና ቃና የተሰኙት ቃላት «ቀነየ» ከተሰኘው የግእዝ ግስ የወጡ ዘሮች መሆናቸውን ገልጸዋል። ቃሉ በሀገራችን የሚሰጠውን ትርጉዋሜ በተመለከተም የዜማ ድምጽ ወይም የዝማሬ ስልት የሚለውን እንደሚያመለክት ይገልጹና በሌላ በኩል ደግሞ ገዝቶ የራስ ማድረግ ወይም አንዱ በሌላው ላይ የበላይ ገዥ (ባለስልጣን) መሆንን እንደሚያመለክትም ገብረ ዮሀንስ ይገልጻሉ። ገብረ ዮሀንስ (1993፡19) ቅኔ የተሰኘው ቃል ከእብራይስጥ ቁዋንቁዋ ጋር ግንኙነትና ትስስር ያለው መሆኑንም አስፍረዋል።

> የግዕዝ ቋንቋ ሴማዊ ስለሆነ በብዙ ቃላት ከዕብራይስጥ፣ ከሱርስትና ከአረብኛ ቋንቋዎች ጋር ይገናኛል። በተለይ በግስ አወራረድ መንገድ ከዕብራይስጥ ቋንቋ ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አለው። ስለዚህ በግዕዝ፣ በትግርኛና በአማርኛ ቅኔ እየተባለ የሚጠራው ቃል በዕብራይስጥ «ቆኔን» እንደሚባል፣ የዕብራይስጥ ቋንቋ ምሑራን ሲያስረዱ በዚሁ ለብዙ ትርጉም እንደሚውል ያረጋግጣሉ። ሙሾ ማልቀስ፣ መቆዘም፣ መዝፈን፣ መግጠም፣ ማጉረምረምና ማቀንቀን ለማለት የዕብራይስጥ ቋንቋ ተናጋሪዎች «ቆኔን» የሚለውን ቃል ብቻ እንደሚጠቀሙ ከምሁራኑ ዘገባ እንረዳለን።

ቅኔ ከነትርጉዋሜው ሊውል የሚገባው ለስርአተ አምልኮ ብቻ ነው የሚል እምነት ያላቸው ገብረ ዮሀንስ «ቅኔ» ለሚለው ቃል አለማዊ ትርጉዋሜ መስጠቱን በጥብቅ ይቃወሙታል። በግእዝ ቅኔ ሰዎችን ማሞገስም ሆነ ማጥላላት አግባብ



ILS LIBRARY

አለመሆኑን በአጽንኦት ይገልጻሉ። በአጠቃላይ በእርሳቸው እምነት ቅኔ ከነገዋዘ ሊውል የሚገባው ለአምልኮታዊ ተግባር ብቻ መሆን እንዳለበት ይገልጹና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለማይገባው ተግባር እየዋለ መሆኑን በጸጸት ገልጸውታል።

> … የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሆኑ ይታመንበት የነበረው ቅኔ ለማይጠቅምና በስጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ምንም አገልግሎት ለማይሰጥ አጉል ፍልስፍና እንዲውል ተደረገ። ከዚህ አልፎ ደግሞ የማንነት መታወቂያ ሆነ። ነገሥታት፣ መሳፍንትና መኳንንት በቅኔ እየተወደሱ፣ እየተመሰገኑና ሐረግ ትውልዳቸው ሳይቀር እየተቆጠረ የከንቱ ውዳሴ ተገዥዎች ብቻ ሆነው ቀሩ። ከደብር ዕልቅና ጀምሮ ያሉት የቤተ ክርስቲያን የሥራ ምድቦች አብዛኛውን ጊዜ ይሰጡ የነበረው የመንግስትን ባለስልጣናት በቅኔ ለሚያሞግሱ ግለሰቦች ነበር። ይህ አድራጎት ቤተ ክርስቲያንን በብዙ መንገድ ጎድቶአታል። የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ካህናት ዓላማ ቅኔ ተምሮ ቅኔን ለባለስልጣኖች በማበርከት ለስልጣን መብቃት ሆኖ ቀረ። ይህም ሆኖ የቅኔን ለአልባሌ ተግባር የማዋልን አላስፈላጊነት የተረዱ አባቶች እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አልጠፉም ነበር። የሚቀኙት ቅኔ እጅግ ተጠበውና ተጨንቀው፣ ሱባኤም ገብተው የመንፈስ ቅዱስን ረዳትነትንም ጠይቀው የሚያቀርቡት እንደነበረ ግልጽ ነው (ገብረ ዮሀንስ 1993:33)።

ገብረ ዮሀንስ ስለ ግዝ ቅኔ ከሰጡት ሀሳብ ጋር ተቀራራቢ ሀሳብ የሰጡት እነ አለቃ ኤልያስ ናቸው። አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልኡልና ቀሲስ ከፍያለው መራሂ በጋራ ባሳተሙት መጽሀፍ (1992:16) ቅኔ ለኢትዮጵያ መምህራንና ሊቃውንት ከአምላክ የተሰጣቸው መንፈሳዊ ሀብት እንደሆነ በማመላከት ነው የቅኔን ትርጉዋሜ የሚገልጹት።

> ቅኔ ማለት "ቀነየ ገዛ" "ተቀነየ ተገዛ" ከሚለው አንቀጽ የወጣ፣ በገጸ ንባብ ብዙ ኃይለ ቃልን የሚያሰባስብ ዘር ሲሆን ትርጓሜው የገዥና ተገዥን ምልክት የሚያሳይ ሰዋሰው፣ መሰላል፣ መመላለሻ ማለት ነው። ገዥው ፍጥረታትን ያስገኘ እግዚአብሔር፣ ተገዥው በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ነው። …ቅኔ ማለት ለእግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚቀርብ አዲስ ምስጋና ማለት ነው። ልበ አምላክ ዳዊትም «ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ» እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት፤ ለስሙም ተገዙ። እያለ በየመዝሙሩ የገለጸው ይህን ለማመልከት ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ስለቅኔ ትርጉም የሰጡትን ሀሳብ የሚያመሳስለው፣ ቅኔ ሊውል የሚገባው ለስርአተ አምልኮ እንጂ ለአለማዊ ህይወት መሆን የሌለበት መሆኑን መግለጻቸው ነው። ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር ተቀራራቢ ሀሳብ ያላቸው ደግሞ ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህና አለማየሁ ሞገስ ናቸው። ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል።

> የቅኔን ትርጉም ሊቃውንት ሁሉ እንደመሰላቸው የቃሉን መሰልነት እየተከተሉ አንድም እየፈለጉ የሆነውንም ያልሆነውንም ትርጉም ሰጥተውት ይገኛሉ። እንደመሰላቸው ይተረጉማሉ ለተባለው አስረጂ የሚከተለውን እንመልከት፤ ቅኔ ማለት «ቆንቆን» ነቀዘ፤ ቁንቁን ማለት ነው ብለው ቁንቁን እንጨትን እንደሚበላው ቅኔም የሰውን ልጅ አእምሮ ይባላል በማለት ፈጽሞ ንባቡ ከትርጉሙ ያልተስተካከለ አስተያየት ይሰጣሉ። ሌሎች ደግሞ የተሻለ ትርጉም ሰጠን



… LIBRARY

መስኂቸው «ተቀንየ» ተገፃ ከአለው ከግዕዙ የወጣ አገባዝ ማለት እንደሆነ የሚተረጉሙ አሉ። ... እውነተኛ ትርጉም ግን ቅኔ ማለት ግጥም፣ አንድም የምስጋና ግጥም ማለት ነው። የጥንት ሕዝቦች በተለይም ዕብራውያን ግጥም እየገጠሙ ማለት ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን አመስግነዋል፤ ከነዚህም ውስጥ በተለይ ነቢዩ ዳዊት የራሱን ግጥም ገጥሞ ፈጣሪውን ከማመስገኑ በላይ ሌላው ሰው ቅኔን እንዲቀኝ ምስጋናም እንዲያቀርብ ሲያዝ «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት» ሲል ዘምሮዋል፤ ሌላውንም አዟል፤ በኋላም የኢትዮጵያ ሊቅ የዜማና የቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ የተባለው «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት» ሲል ዘምሯል ሌላውም እንዲቀኝ አዟል፤ ስለዚህ ቅኔ ማለት ምስጋና አንድም የግጥም ምስጋና ማለት ነው (1963፡172)።

ሊቀ ስልጣናት ከሰጡት ብያኔ አኩዋያ ሲታይ ቅኔ ለፈጣሪ ምስጋና በግጥም የሚቀርብበት ሀይማኖታዊ የጥበብ ዘርፍ መሆኑን እንረዳለን። ይህም አስተሳሰብ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሀሳቦች ጋር ያመሳስለዋል። ቅኔ በዘመነ ኦሪት በዳዊት ዘመን የታየ ጥበብ መሆኑን መግለጻቸው ሊቀ ስልጣናት ከሌሎች የሚለዩበት ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ያሬድ በደረሳቸው በተለያዩ ሀይማኖታዊ መጻህፍት (ድጓ፣ ጾመ ድጓ) ውስጥ የተጠቀሱት ግጥሞችም ቅኔዎች መሆናቸውን መግለጻቸው ደግሞ የቅኔን ጥንታዊነት ከሚያቀነቅኑት የሙያው ሰዎች ጎራ ያሰልፋቸዋል።

አለማየሁ ሞገስ በበኩላቸው ለቅኔ የሰጡት ትርጉም ከላይኞቹ መምህራን ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ቢሆንም ቅኔን የሚመለከቱት ራሱን የቻለ የፍልስፍና ጥበብ ሆኖ የቆየ እንደሆነና በመጨረሻም ራሱን ችሎ ለመኖር ባለመቻሉ ለስርአተ አምልኮ ማቅረቢያነት (መሳሪያነት) የዋለ መሆኑን ነው።

ቀነየ ተቀነየ ተቀኘ፤ ዘመረ፤ በምስጢርና በስልት ተናገረ፤ የሚለው ግሥ ጥሬ ዘር ስለሆነ ምሥጢር የተጎናጸፈ መዝሙር ማለት ነው። ደራሲው የጕንጅ (ጕጃም) ተወላጅ በ14ኛው መቶ ዘመን የነበር ተዋነይ የሚባል ሊቅ ነው። ... በዘመኑ ፍልስፍና ነጻ ስላልነበረችና ቅኔ ራሱን ችሎ ለመኖር ስለማይችል ያምላክ ማመስገኛ የጻድቃንና የሰማዕታት ማወደሻ፣ የቤተክርስቲያን ማገልገያ ነው ብሎ ወደ ቤተክርስቲያን ስላስጠጋው እስከ ዛሬ ድረስ በዚያው ሲወርድ ሲዋረድ መጣ (ዓለማየሁ 1950፡117)።

የቅኔን ትርጉም ከስርአተ አምልኮ ጋር አቆራኝተው የሚያቀርቡት ሌላው የሙያው ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ናቸው።

ቅኔ ማለት ባጭሩ ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ሊያቀርብ ባሰበ ጊዜ ምሳሌ መስሎ፣ ምስጢር አሻሽሎ ግጥም በመግጠም የልቡናውን እውቀት፣ የአእምሮውን ርቀት የሚገልጽበት የዕውቀቱን ደረጃ የሚያስተዋውቅበት፣ የሰሚንም ልቡና የሚያነቃቃበትና የሚያራቅቅበት ድርሰት ነው (አድማሱ፣1963፡9)።

ከላይ ከተገለጹት አስተሳሰቦች በተለየ ሁኔታ ከሀይማኖታዊ አስተሳሰብ በተጨማሪ አለማዊ ይዘት ያለው ትርጉዋሜ ያከሉበት ደግሞ ዜና ማርቆስ እንዳለው፣

መምህር ይኄይስ ወርቁና በ1972 ዓ.ም «የቅኔ ውርስ» በሚል ርእስ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረበው ጽጌ አባተ ናቸው።

ዜና ማርቆስ እንዳለው የቅኔን ብያኔ ሲገልጹ መሰረቱን ሀይማኖታዊ፤ መነሻውን ከክርስቶስ ልደት በፊት ማድረጋቸው ከሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ብያኔ ጋር የሚያመሳስላቸው ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ የቅኔ ግጥም ለአለማዊ ተግባር፤ ማለትም ለሙገሳም ሆነ ለወቀሳም ሊቀርብ የሚችል መሆኑን መግለጻቸው ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች የሚለያቸው ሆኑዋል።

> .... በቀልድ በጨዋታ የተለመደ ቅኔያዊ ዘለፋ በስፋት ይቀጥላል። የቅኔ ተማሪዎች የቅኔ መምህራን በሚሆኑበት ጊዜ እርስ በእርሳቸው ቅኔ ይዘራረፋሉ። በቅኔ ይተቻቻሉ። ይወቃቀሳሉ .... ቅኔ መሳፍንቱ የሴት ወይዘሮው ነገሥታቱና ጳጳሳቱ ሕዝቡን በበጎ አስተዳደር ሲመሩ የሚሞገሱበትና የሚወደሱበት ሕዝቡን በአስተዳደር ሲበድሉ ደግሞ የሚወቀሱበት የሚዘለፉበትና የሚመከሩበት ድርሰት ነበር (ዜና ማርቆስ 1994፡8)።

በሌላ በኩል የቅኔ አቀራረብን አስመልክቶ ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያምንና ዜና ማርቆስ እንዳለውን የሚያለያያቸው ሌላ ነጥብ አለ። ገብረ ዮሀንስ፤ ቅኔን በስሜት ውስጥ ሆኖ እየተወራጩ መቀኘትን ከስርአተ ቅኔ ውጭ የሆነ፣ ከቅኔ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የውንብድና ተግባር መሆኑን «ምንም ሳናስብ፣ ሳንቆጥርና ሳናቀናብር ከመቅጽበት ቅኔውን እናወርደዋለን ይላሉ። አነባባቸው እጅግ ይዘገንናል። ምናልባትም ቅኔን ለማያውቅ ሰው ሁኔታው እውነት ሊመስለው ይችላል። ... ዘራፊ የሚለው ቃል ባልባሌነት የሁዋላ ሁዋላ የመነጨ ይመስላል። ይህ ቃል የውንብድናን ተግባር ከሚያከናውኑ ግለሰቦች የሚውል ስለሆነ ከቅኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም» (ገብረ ዮሀንስ 1993፡34) በማለት በቅኔ ዘረፋ ስም የሚደረግን አላስፈላጊ እንቅስቃሴና መወራጨት የሚኰንኑ ሲሆኑ ዜና ማርቆስ እንዳለው ግን «ቅኔ ስሜት ቀስቃሽ ድርሰት ነው ማለት ይቻላል። አንድ ባለ ቅኔ በሊቃውንቱ መካከል ገና ለመቀኘት ሲጀምር ሰውነት ይለወጣል፣ ይሞቃል፣ ላብ ይጀምራል፣ ሰውነትንም መቆጣጠር ያዳግታል። ባለ ቅኔው በሰዎች መካከል መሆኑንም የሚረሳበት ጊዜ አለ። ቅኔ እንኩዋንስ ንቁውን ሰው ይቅርና ሞኛሞኙንም ቢሆን ቅኔ መቀኘትና ዘረፋ ሲጀምር «ዘራፍ ሲሸበር ገዳይ» ነው የሚያሰኘው ... ይህ የምርምሩ፤ የርቀቱና የፈጠራው ምስጢር ውጤት ነው (ዜና ማርቆስ 1994፡3) በማለት ሃይለ ቃል በተሞላበት ስለሚደረግ የቅኔ ዘረፋ ተግባርና እንቅስቃሴው ያላቸውን በጎ አመለካከት አስፍረዋል።

ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ሀሳብ የምንረዳው ገብረ ዮሀንስ ቅኔን በአርምሞ (በጸጥታ) በማሰብና በመመራመር አዘጋጅቶ ለሀይማኖታዊ ተልዕኮ ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ አጽንኦት ሲሰጡ፣ ዜና ማርቆስ ግን የቅኔ መንፈስ በራሱ በሚፈጥረው ስሜት ተሳፍሮ ቅኔን በመዘረፍ ለአለማዊውም ሆነ መንፈሳዊ ተግባር ማዋሉ ተገቢ መሆኑን ይገልጻሉ። ከዜና ማርቆስ እንዳለው መደምደሚያ ጋር ተቀራራቢ ሀሳብ ያላቸው ሌላው ጸሀፊ መምህር ይኄይስ ወርቁ ናቸው። መምህር ይኄይስ የቅኔን

ትርጉዋሜ አስመልክቶ የምስጋና፣ የስራና የታሪክ መግለጫ መሆኑን ከገለጹ በሁዋላ ቅኔ ከሀይማኖታዊ ተግባሩ በተጨማሪ አለማዊ ባህርይም እንዳለው ይገልጻሉ።

> ቅኔ የተባለውም ድርሰት የታሪክና የስሜት መግለጫ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም ሰው የጓደኛውን የህይወት ታሪክ ለምስጋናም ሆነ ለነቀፌታ በአሽሙር ጠቅሶ በተናገረ ጊዜ እገሌ በእገሌ ተቀኘበት ይባላል። የአነጋገሩም ስልት ታሪክ ቀመስ፣ ጽድቅ ለበስ፣ ውስጠ ወይራ .... እየተባለ ይጠራል (ይሔይስ፡ 1994፡ 8)።

በመጨረሻ የሚጠቀሰው ጽጌ አባተ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ስለቅኔ የሰጠው ሀሳብ ነው። እንደ ጽጌ አባተ አገላለጽ ቅኔ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ እጥር ምጥን ያለ እንደሆነ፣ ምቱና ምጣኔውም የሰውን ስሜት የሚስብ እንደሆነና ገሀዱን አለም ቀርጾ ምናባዊ አለም በመሳል አእምሮን የሚገራ የስነጽሁፍ ዘርፍ እንደሆነ ገልጽዋል (ጽጌ አባተ፡ 1974፡ 11)።

ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው ስለግእዝ ቅኔ የተሰጡ ብያኔዎች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ በሁለት የተለያዩ ጽንስ ሀሳቦች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። በቀዳሚነት የተጠቀሱት የሙያው ሰዎች የአተረጉዋጎም ትኩረት፣ በአመዛኙ ሀይማኖታዊና መለኮታዊ ትርጉዋሜ ይዞ እንዲወጣ አድርገው የተረጎሙት መሆኑ ተመልክቱዋል። በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሱት ሊቃውንት በበኩላቸው ቅኔ ለሀይማኖታዊ ተግባር የሚውል መሆኑን እምነው፣ በተጨማሪም ለአለማዊ ተግባር እንደሚውል በማመልከት የበኩላቸውን ብያኔ አስፍረዋል። ከነዚህ አስተሳሰቦች በተለየ ቅኔ ሲፈጠር የፍልስፍና ጥበብ የነበረ መሆኑንም አለማየሁ ሞገስ ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ቅኔ ራሱን የቻለ የፍልስፍና ጥበብ እንደነበረ የሚጠቅሱትን የአለማየሁ ሞገስን ጽንሰ ሀሳብ መነሻ ስናደርግ፣ ዜና ማርቆስ እንዳለው፣ አድማሱ ጀንበሬና መምህር ይሄይስ ወርቁ ስለቅኔ ትርጉምና ምንነት ያቀረቡትን ትንተና ስንመረምር፣ የግእዝ ቅኔ ለመንፈሳዊ ተግባር ብቻ ሳይሆን በገሀዱ አለም የሚከሰቱ አለማዊ ተግባሮችን በተዋበ ቋዋንቋዋ አሳክቶና አራቅቆ መግለጽ የሚችል ሚስጢራዊ የሆነ አስተሳሰብን የሚያበለጽግ፣ ህሲናን የሚገዛ፣ የሚያነቃቃና በተመስጦ የሚያማልል ጥንታዊ የጥበብ ዘርፍ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ከላይ የተጠቀሱትን አስተሳሰቦችና እምነቶች ለመቁዋጨት፣ ቀጥለው የሚቀርቡትንም አስተሳሰቦች በአግባቡ ለመረዳትና የግእዝ ቅኔ ጅማሪን ማንነት ለመወሰን እንዲረዳ ጠቅለል ያለ ብያኔ ማስቀመጡ ተገቢ ነው። ከዚህ አኩዋያ ሲታይ የግእዝ ቅኔ የሚከተለውን ትርጉም እንዲይዝ ቢደረግ የተገባ ነው።

የግእዝ ቅኔ ማለት አቀራረቡ በግጥም የሆነ፣ የተለያየ ቅርጽ እና መጠን ባላቸው ቃላትና ሀረጋት በተገነቡ ቤቶች የተከፋፈለ፣ በሰምና በወርቅ የተመሰጠረ፣ የራሱ የሆነ የዜማ ስርአትና ልክ ያለው፣ ወቅት ወይም እለትን መሰረት ባደረገ ታሪክ የሚቀናበር፣ ቃላትንና ሀረጋትን የሚያስተሳስር ምሳሌና ሙያ ያለው፣ መንፈሳዊንም



IES LIBRARY

ሆን አለማዊ ህይወትን መነሻ እያደረገ ለስርአተ አምልኮ፣ ለምስጋና፣ ለውደሳና ለነቀፌታ ተግባር የሚውል፣ ራሱን የቻለ የአደረጃጀት፣ የአዘገጃጀትና ያቀራረብ ደንብ፣ ስርአትና ህግ ያለው ጥንታዊ የሀገራችን የፍልስፍናና የስነ ጽሁፍ ትምህርት ዘርፍ ነው በሚል ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ለ. የግእዝ ቅኔ ጠቀሜታ

ቅኔ ለንግግር፣ ለስነ ጽሁፍ ስራና ለምርምር ተግባር፣ ለሰው ልጅ አእምሮ ብልጽግናና ለስጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊ ጥበብ የእውቀት መሰረት በመሆኑ ሙያውን ተምረው ያለፉ ሁሉ በየትኛውም የሙያ መስክ ቢሰማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ዜና ማርቆስ እንዳለው የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> ..ቅኔ የሚያውቅ ካህን ኪዳን ቢያደርስ፣ ሰዓታትና ማሕሌት ቢቆም፣ ቅዳሴ ቢቀድስ የሚሳነው ሙያ አይኖርም፡፡ በህዝብም መካከል ቆሞ ከቅዱሳት መጣሕፍት እየጠቀሰ ቢሰብክ፣ ቢያስተምር፣ ቁም ነገር ቢናገር ያምርበታል፡፡ ሰሚ፣ አድማጭና ተቀባይም ያገኛል፡፡ .... በቅኔ የሰለጠነ ወጣት በትያትር ሙያ ቢሰለፍ፣ ግጥም ቢገጥም፣ መወድስ ቅኔ ቢቀኝ፣ ይሆንለታል፣ ይሳካለታል፡፡ በኪነትም በኩል ቢሰለፍ፣ የሽለላ (ቀረርቶ) ግጥም ይችላል፡፡ ዘራፍ የሚያስኝ የፉከራ ግጥም እየገጠመ የጀግና ወኔ መቀስቀስ አይሳነውም፡፡ አሽሼ ገዳሜ ማለትም ቢሆን ማቀንቀንም ቢሆን አያቅተውም፡፡ ምክንያቱም ቅኔ በሚማርበት ጊዜ መዝሙር እየዘመረ፣ ዜማ እየጮኸ፣ ግጥም እየገጠመ፣ ቅኔን እየተቀኘ፣ ማህሌት በመቆም፣ በማስረገጥ፣ በመወረብ፣ በማሽብሸብና በማህሌተ ገንቦ ሁሉ ልምድ አለውና ነው (ዜና ማርቆስ 1994:5-6)፡፡

ዜና ማርቆስ ሀሳባቸውን በመቀጠል ቅኔን የተማረ ሰው አለማዊ በሆኑ ስራዎች ውስጥ ቢሰለፍ እንኳዋ የተሳካለት እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡ እድል አጋጥሞት ለጥብቅና ቢቆም፣ ለሽምግልና ቢቀመጥ፣ ለዳኝነት ቢሰየም የተዋጣለት ተግባር ለማከናወን እንደማይቸገር በጽሁፋቸው አስፍረዋል፡፡

ቅኔ ለማይገባው አገልግሎት እየዋለ መሆኑን በምሬት የሚገልጹት ደግሞ ገብረ ዮሀንስ ገብረማርያም ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው አስተሳሰብ ቅኔ ሊውል የሚገባው ለስርአተ አምልኮ ተግባርና ግልጋሎት ብቻ ሊሆን ይገባል የሚል አቅዋም አላቸው፡፡ ከ15ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በአመዛኙ ቅኔ ለምስጋና፣ ለጸሎት፣ ለመዝሙርና ለሌሎችም የስርአተ አምልኮ ክፍሎች መገለጫ ሆኖ የቆየ መሆኑንና፣ ያም ወቅት ቅኔ ለትክክለኛ ተግባሩ የዋለበት ጊዜ መሆኑን የሚገልጹት ገብረ ዮሀንስ፣ በሀገራችን የሃይማኖት ስርአት ጣልቃ የገቡት ካቶሊኮች በፈጠሩት መጥፎ ጠባሳ የቅኔ አገልግሎት ላልተፈለገ ተግባር መዋል የጀመረ መሆኑን በቁጭት እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> .... የካቶሊኮች ጣልቃ ገብነት በፖለቲካና በሃይማኖት በቀላሉ የማይሽር ጠባሳ በኢትዮጵያዊያን ጥሎ አልፏል፡፡ ጸጋ፣ ቅብዐትና ካራ የሚሉ የክፍፍል ስሞች የመነጩትም በዚህ ጊዜ ነው፡፡

> ይህ የሃይማኖት ክፍፍል ለሁለት ምዕት ዓመታት የሃይማኖት ጦርነት እያስነሳ ቆይቶአል፡፡ መከፋፈሉን ያስፋፉት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን አንዱ በሌላው ላይ ይሠነዝሩት በነበረው ነቀፋ ነው፡፡ ነቀፋውም የሚገለፀው በቅኔ ነበር፡፡ ከእያንዳንዱ ክፍል ብዙ ቅኔዎች ለትችትና ለነቀፋ ውለዋል፡፡ ከነሱም ብዙዎቹ ተመዝግበውና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፈው ያሁኑ ትውልድ እንዲመለከታቸው ሆነዋል፡፡ ... ቅኔ የሚለው ስያሜ ትርጉም ያጣውም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው (ገብረ ዮሀንስ 1993፡33)፡፡

የቅኔን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ለመረዳት ምሁራን በየራሳቸው መንገድ በጥልቀት ገልጸውታል፡፡ በተለይ ዜና ማርቆስ እንዳለውና አለማየሁ ሞገስ አስፈላጊነቱን ለመግለጽ የተጉዋዙበት መንገድና የተከተሉት የአቀራረብ ስልት የግእዝ ቅኔ በዘመኑ የነበረው ተፈላጊነትና ተወዳጅነት የበለጠ ጎልቶ እንዲታይ አድርገዋል፡፡

እንደተገለጸው የግእዝ ቅኔን መማርና ማወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ትምህርቱ በውስጡ አያሌ የጥበባት ዘርፎች በጋራ ተዋህደው የሚቀርቡበት ነው፡፡ ሰምና ወርቁን ለማዋሀድና ለመለየት መፈላሰፍን፣ ቤት እንዲመታ ገጣሚነትን፣ ዜማ እንዳይሰብር ዘማሪነትን፣ ሙያው እንዳይፋለስ መመራመርን፣ በአግባቡ ለመተርጎም የግእዝ ቋዋንቋዋ ማወቅን የሚጠይቅ በመሆኑ በትምህርት ሂደቱ የሚዘልቁ ሁሉ የተሙዋላ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል፡፡ ስርአተ ትምህርቱና የመማር ማስተማሩ ፍልስፍና ትእግስትን ሳትገደድ እንድትቀበላት ስለሚያስገድድ እንዲሁም ትህትና እና ታዛዥነት የትምህርት ስርአቱ አቢይ ባህል በመሆናቸው በትምህርት ጉባኤው ያለፉት ብዙዎቹ በአለማዊ ኑሩዋቸው ሳይቀር የተሳካላቸው እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ ትምህርቱና ቋዋንቋዋም የሀገራችን ብቸኛ ሀብትና ቅርስ ከመሆኑ አኩዋያ ሲታይ ደግሞ የግእዝ ቅኔ ትምህርት ሊበረታታ! ሊደገፍና በዘመናዊ መልክ ሊደራጅ የሚገባው እንጂ ባለበት «እንደፈቀደው» ተብሎ የሚተው አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

## 2.3.2 የግእዝ ቅኔ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ

የግእዝ ቅኔ መቸ? የት? እንዴትና በማን ተጀመረ? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ እርግጠኛ መልስ ማግኘትና መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ መልስ ማግኘቱን አስቸጋሪ የሚያደርገው የተለያዩ የሙያው ሰዎች የተለያየ መልስ አስፍረው ማለፋቸው ነው፡፡ አንዳንዶቹ ከልደተ ክርስቶስ በፊት እብራውያን ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን ያመሰግኑ እንደነበር፣ ነቢዩ ዳዊት «ተቀነዩ ለእግዚአብሄር በፍርሀት» በማለት ሁሉም ሰው ለአምላኩ ታዛዥና ተገዥ በመሆን ፈጣሪውን እንዲያመሰግን የተናገረውን ቃል ቅኔ መሆኑን እየመሰከሩ ቅኔ ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ የነበረ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ አንዳንዶቹሞ ከቅዱስ ያሬድ በፊት በዘመነ ኦሪት ማብቂያ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የታዬ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በስድስተኛው ምእት አመት በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት የተነሳው ቅዱስ ያሬድ የግእዝ ቅኔ ጀማሪ መሆኑን በራሱ የድርሰት ስራዎች



IES LIBRARY

ውስጥ ያስፈራቸውን ግጥሞችና ረቂቅ ስንኞች በማስረጃነት እየጠቀሱ ቅዱስ ያሬድ የግእዝ ቅኔ ጀማሪ መሆኑን ይመሰክራሉ። አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት የሚያሙዋላ ቅኔ የተጀመረው ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ፣ በወቅቱ የተነሱትን የሙያውን ሊቃውንት በስም እየጠቀሱና ምሳሌ እየሰጡ ቅኔ የተጀመረው ከያሬድ ቀጥሎ በተነሱ ሊቃውንት ስለመሆኑ የሚከራከሩትም ብዙዎች ናቸው።

ቅኔ ከጥንታዊው የኦሪት ዘመን ጀምሮ የነበረ፣ በተለይ ለፈጣሪ የምስጋና ጸሎትና ዝማሬ ይቀርብ የነበረው በቅኔ እንደነበረ የሚገልጹት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ናቸው። ሀብተ ማርያም በኦሪት ዘመን ቅኔ የነበረ ስለመሆኑ በምሳሌነት የሚጠቅሱት የዳዊትን መዝሙር ነው።

> የጥንት ህዝቦች በተለይም እብራውያን ግጥም እየገጠሙ፣ ማለትም ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን አመስግነዋል። ከነዚህም ውስጥ በተለይ ነቢዩ ዳዊት የራሱን ግጥም ገጥሞ ፈጣሪውን ከማመስገኑ በላይ ሌላው ሰው ቅኔ እንዲቀኝ ምስጋናም እንዲያቀርብ ሲያዝዝ «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሀት» ሲል ዘምሮዋል (ሀብተ ማርያም 1963፡172)።

በሌላም በኩል ከቅዱስ ያሬድ በፊት በዘመነ ኦሪት መገባደጃና በክርስቶስ ልደት መጀመሪያ አካባቢ ቅኔ መሰል ግጥሞች በኢትዮጵያ ታይተው የነበረ መሆኑን ዮሀንስ አድማሱ እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> ቅኔ የተጀመረው አገው ነው። ጀማሪውም «ዘሱቱኤል» የሚባል የአገው ሰው ነው። ዘሱቱኤል የተባለው ስለሊቅነቱ ነው እንጂ መጠሪያ ስሙ «አንድሪም» ነው ይላሉ። ዘሱቱኤል ኦሪታዊ ነበር። ከኦሪት ያመጣል፣ ይጠቅሳል። የነበረው በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና ከመግባቱ በፊት ይሁን ወይንም በኋላ በእርግጡ አልታወቀም። ምናልባትም ኦሪታዊ ስለነበር በኢትዮጵያ ክርስትና ከመግባቱ በፊት ይኖር ነበር የሚል ግምት ያስከትል ይሆናል። ይህ ደግሞ ኦሪታዊ ቢሆን ከክርስትናው ዘመን ደርሶ እንደሆነስ የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። በኢትዮጵያ ውስጥ ቅኔን የጀመረው በእርግጥ ዘሱቱኤል ከሆነ በቁርጥ ልናውቅ የምንችለው እርሱ ከቅዱስ ያሬድ በፊት መኖሩን ብቻ ነው (ዮሀንስ 1959፡5)።

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ቅኔ የታየው በዘመነ ኦሪት በእብራውያን ዘመን እንደሆነ ቢገልጹም ዋናው የግእዝ ቅኔ ጀማሪ ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ መሆኑን ቀደም ሲል ጠቅሰዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የግእዝ ቅኔ አሁን ያለውን መልክ፣ ቅርጽና ስርአት እንዲይዝ የተደረገው በአጼ እስክንድር ዘመነ መንግስት ወቅት መሆኑን በመጥቀስ ትክክለኛውን ቅርጽና መልክ የያዘው ቅኔ ጀማሪዎች በ14ኛውና በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተነሱ የሙያው ሊቃውንት መሆናቸውን የሚመስክሩ መኖራቸውንም ገልጸዋል። በሌላ በኩል በዮሀንስ አድማሱ ጥናት ወረቀት ውስጥ የተጠቀሰው የቅኔ ጀማሪ ማንነት ምንም እንኳዋ በሌሎች መጻህፍት ተጠቅሶ ያልተገኘ ሀሳብ ቢሆንም

የኢትዮጵያ ቅኔ ደራሲ «ዘሱቱኤል» ነው የሚለው ሀሳብ ዝም ተብሎ ሊተው የሚገባ አይሆንም። ራሱን ችሎ ምርምር ሊደረግበት ይገባል።

የግእዝ ቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ በየመጽሀፎቻቸው ካሰፈሩት መካከል፣ መምህር አፈወርቅ ተክሌ፣ አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልኡልና ቀሲስ ክፍያለው መራሄ ተጠቃሽ ናቸው።የግእዝ ቅኔያት በሚል ርእስ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎች አካዳሚ ከባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ በአለቃ አፈወርቅ ዘውዱ የተዘጋጀው መቅድም ቅዱስ ያሬድ የግእዝ ቅኔ ጀማሪ መሆኑን የሚጠቁም ነው። በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት እንደተነሳ የሚነገረው ቅዱስ ያሬድ በግእዝ መጻህፍት ምስጢር የተራቀቀ በመሆኑ ከመጻህፍት እያጣቀሰና ከእርሱም እየጨመረ እያሌ መዝሙራትን ከነዜማቸው የደረሰ ለመሆኑ በተለያዩ የቤተክርስቲያን የታሪክ መጻህፍት ሰፍሮ ይገኛል። አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት የሚከተለውን አስፍረዋል።

> የያሬድ የመዝሙር ድርሰቶች በግጥም ረገድ አብዛኛውን ቤት አልባ ቢሆኑም፣ አልፎ አልፎ ቤት እየመታ፣ ከስድ ንባብነት ወደ ጉትነት ያመራ፣ በሰምና በወርቅ የተመሰጠረ፣ በሁለትም፣ በሦስትም፣ በአምስትም ቤት የተወሳ በመሆኑ ሂደቱ የቅኔን መንገድ የተከተለ ነው። ቤት አልባ ቅኔዎችና ቤተኛ ቅኔዎች ሁለቱም በያሬድ ድርሰት ውስጥ ይገኛሉ (አለቃ አፈወርቅ 1950፡15)።

አለቃ አፈወርቅ የቅዱስ ያሬድን የግእዝ ቅኔ ደራሲነት ለማረጋገጥ ያህል በድጉዋው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቤት አልባና ቤተኛ ስንኞችን በምሳሌነት በጽሁፋቸው ውስጥ አስፍረዋል። (የግእዝ ቀኔያት፣ 1980፡15-17 ተመልከት)። «መጽሀፈ ታሪክ ወግስ» በሚለው የመምህር አፈወርቅ መጽሀፍ ደግሞ የቅዱስ ያሬድን የቅኔ ደራሲነት በተመለከተ የሚከተለው ሀሳብ ሰፍረዋል።

> ቅኔን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው። የያሬድ የድርሰቱ መነሻና መድረሻ ቅኔ ሲሆን በድርሰቱ ግን ቤት እየመታና ሳይመታ የተቃኛቸው ክብር ይእቲና እጣነ ሞገር በድጓው ተጽፈው ይገኛሉ። ቅኔንም እንደደረሰ «ሞቅናይ» በሚለው ድርሰቱ ይታወቃል። የእርሱ ደቀ መዛሙርትም እስጢፋና እስክንድር፣ ሀዊራና መንክራ እንዲሁም ብሁር ይባላሉ። ከነዚህ የተማሩ ሊቃውንትም ቤት እየመቱ ተቀኝተዋል (መምህር አፈወርቅ 1997፡22)።

እነ አለቃ ኤልያስ «ትርጉዋሜ ቅኔ ፈለገ ህይወት» በሚል ርእስ አዘጋጅተው ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥም የግእዝ ቅኔ ጀማሪ ቅዱስ ያሬድ መሆኑን ነው የሚመሰክሩት። ከቅዱስ ያሬድ ቀጥለው የተነሱትን የሙያውን ሰዎች በተመለከተም ከሀብተ ማርያም ወርቅነህ ጋር ይመሳሰላሉ። ሁለቱም ሰዎች ቅኔን የጀመረው ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ፤ መልክ አበጅተው፣ በስርአት ደንግገው፣ ቤት ሰጥተው፣ በቁጥር ወስነው፣ የአሁኑን የቅኔ ውበት የሰጡት ከቅዱስ ያሬድ ቀጥለው የተነሱት ሀዊራ፣ መንክራ፣ እስክንድራ፣ ፓኦድራ፣ አቢኖራ .... እንደሚሰኙ ይጠቅሳሉ። በሌላም በኩል

ዋድሎች ቅኔን የደረሰው ዮሀንስ ገብላዊ ነው ሲሉ፣ ጎንጅዎች በበኩላቸው ተዋነይ ነው እንደሚሉ ሁለቱም የሙያው ሊቃውንት ተመሳሳይ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

ሁለቱ የሙያው ሊቃውንት በጻፉዋቸው መጻህፍት ውስጥ የሚስተዋለው ሌላው ተመሳሳይነት በግእዝ ቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ ላይ ያሰፈሩት ሀሳብ ነው፡፡ ዮሀንስ ገብላዊ፣ ወሎ ክፍለ ሀገር፣ አማራ ሳይንት፣ ታቦር ተራራ ላይ ይኖር እንደነበር ሁለቱም ይስማማሉ፡፡ ዮሀንስ አስተምሮት በቦታው የተካው አባ ወልደ ገብርኤል የተባለ መነኩሴ እንደሆነ፣ አባ ወልደ ገብርኤልም ሰምረ አብ የተባለን ሊቅ አስተምሮ በቦታው እንደተካ፣ ሰምረ አብም ለአጼ በእደ ማርያም ቅኔን እንዳስተማራቸው፣ በሚል የተገለጹትን ሀሳቦች ሁለቱም ይስማሙባቸዋል፡፡

የተወሰነ ልዩነት የሚስተዋለው የሰምረ አብ ተከታዮች ማንነት ላይ ነው፡፡ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ ሰምረ አብ ለልሂብና ለኤልያስ ማስተማሩን፣ ኤልያብ በበኩሉ ለተዋነይና ለድድቅ ወልደማርያም ማስተማሩን ይገልጹና ተዋነይ የጎንጅ /ጎጃም/ ቅኔ መንገድ አባት እንደሆነ ድድቅ ወልደ ማርያም ደግሞ ለዋድላ የቅኔ መንገድ አብነት እንደሆነ ይገልጻሉ፣ የቅኔ መንገድ ልዩነትም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተከሰተ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

እነ አለቃ ኤልያስ በበኩላቸው፣ ሰምረ አብ ለልሂብና ለኤልያብ፣ ልሂብ ለዘትረ ወንጌል፣ ዘትረ ወንጌል ለዝክሪ፣ ዝክሪ ለብኩሩ፣ ብኩሩ ለዮናታን፣ ዮናታን ለዘነብያትና ለቃለ አዋዲ፣ ቃለ አዋዲ አማራ ሳይንት ለነበሩት ለአለቃ ማሩ፣ አለቃ ማሩ ደግሞ ሊቁን አቃቤ ሰአት ከብቱን እንዳስተማሩ ይገልጻሉ፡፡ አቃቤ ሰአት ከብቱም ለሰባት አመታት ቅኔንና መጻህፍትን ተምረው ከአጼ በካፋ ዘመነ መንግስት እስከ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት መጨረሻ ድረስ የጎንደር ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናትና አቃቤ ሰአት ተብለው የአለቅነቱን ሹመት ጨምረው ፍትህ ነገስት ተርጉዋሚ እንደነበሩ በዝርዝር ይገልጹታል፡፡

የግእዝ ቅኔ መቸና በማን ተጀመረ? ለሚለው ጥያቄ ከላይ ከተጠቀሱትና የቅዱስ ያሬድን ጀማሪነት ከሚያቀነቅኑት የተለየ አስተያየት ያላቸው አያሌ የሙያው ሰዎች ቢኖሩም ለምሳሌ ያህል አለማየሁ ሞገስ፣ ዮሀንስ አድማሱና ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያምን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አድማሱ ጀንበሬም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ያሉና ስለ ግእዝ ቅኔ አመጣጥ ታሪክ የተሻለ ብያኔ የሰጡ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው፣ ከቅዱስ ያሬድ በፊት በዘመነ ኦሪት መገባደጃ ወቅት ቅኔ በኢትዮጵያ የነበረ መሆኑን ዮሀንስ አድማሱ፣ ነቢየ ልኡል ከተሰኙ የሙያው ሰው ያገኙትን የቅኔ አጀማመር ታሪክ በዝርዝር አስፍረዋል፡፡ በዮሀንስ አድማሱ ጥናት እንደተመለከተው፣ ቅኔ በኢትዮጵያ የተደረሰው አገው ውስጥ «ዘሉቱኤል» በተባለ ሊቅ አማካኝነት በዘመነ ኦሪት መገባደጃና በዘመነ ሀዲስ መግቢያ ወቅት ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ ሰፍሯል፡፡ የቅኔ ደራሲው እንደ ተባለው በእርግጥ

ዘሱቱኤል ከሆነ ቅኔ ከያሬድ በፊት በኢትዮጵያ ተጀመረ ማለት እንደሚቻልም በዝርዝር ተጠቅሷል፡፡ ቅዱስ ያሬድ ቅኔን ያልጀመረው ስለመሆኑ በዮሀንስ አድማሱ ጥናት የሚከተለው ሀሳብ ተገልጽዋል፡፡

> .... ቅዱስ ያሬድ ቅኔን አልጀመረውም የሚሉት ብዙ ናቸው፡፡ እንዲህ ባዮችም ቅኔ ከቅዱስ ያሬድ በፊት ለመኖሩ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ውስጥ ከቅኔ ጥበብ የወረሳቸው የሀረጋትና የዜማ ስልቶች እነሱንም የመሳሰሉ ብዙ ነገሮች አሉ ይላሉ፡፡ ዋናው ክርክራቸው በጠቅላላው ቅዱስ ያሬድ ከቅኔ ወርሶ ከድጓው ውስጥ ያስገባቸው ነገሮች ቅኔ ከሱ መነሳት በፊት የነበረ ጥበብ ለመሆኑ አስረጅ ናቸው የሚል ነው (ዮሀንስ 1959፡4)፡፡

በዮሀንስ አድማሱ ጥናት ውስጥ እንደ ተተረከው፣ ዘሱቱኤል የደረሳቸው አያሌ ቅኔዎች እንደነበሩና በጊዜ ብዛት የተዘነጉ ስለመሆናቸው፣ ቅኔዎቹም ሀይልና ውበት የነበራቸው ስለመሆኑ ከተገለጸ በሁዋላ በታሪክ የዘሱቱኤል ቅኔ ተብሎ የሚጠቀሰው «መኑ ጠቢብ ወመለብው፣ ከመ እግዚአብሄር አገው» የሚለው እንደሆነና ምስጢሩም፤ እንድ አገው ዘጠኝ ልብ (አገው ልቡ ዘጠኝ) ካለው፣ በዘጠኝ ልቡ ቢሰራ ከእግዚአብሄር አያንስም፣ እግዚአብሄርን ያህል ሳይሆን አይቀርም ማለት እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ተካትዋል፡፡

በመቀጠልም «ዘሱቱኤል» የተባለው የቅኔ ሊቅ ብዙ ደቀ መዛሙርት እንደነበሩት፣ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ስሙ እጅግ የገነነው ከመምህሩም ብልጫ ያለው ሆኖ የተገኘው እዝራ (እዝራ ዘሱቱኤል) የተባለው ሊቅ እንደነበር ተገልጽዋል፡፡ ከዚህም በመቀጠል የመምህሩና የደቀ መዝሙሩ ስም እየተፈራረቀ እስከ ሰባት ትውልድ የደረሰ መሆኑን ይገልጹና ሰባተኛው ትውልድ ላይ ጌዲዎን ቀዳማዊ የሚባል ባለቅኔ መነሳቱን፣ ከዚያም በየጊዜው እየተተካ ከጌዲዮን ቀዳማዊ ዜና አዳም፣ ከዜና አዳም የማነ አብ፣ ከየማነ አብ ስርግው ጥበብ፣ ከስርግው ጥበብ ህላዌ አብ፣ ... እያለ በ35ኛ ደረጃ ግጨው ገብሬ ይጠቀሳል፡፡ ከግጨው ገብሬ ወልደ ዮሀንስ፣ ከወልደ ዮሀንስ ነቢየ ልኡል፣ በማለት ሲዘረዝር 37 ተከታታይ መምህራን እንደነበሩና እነዚህም የዋሸራ ጉባኤ ተከታታይ ምሁራንን የሚያመላክቱ መሆኑ በዮሀንስ አድማሱ ጥናት በዝርዝር ተገልጽዋል፡፡

አለማየሁ ሞገስ በበኩላቸው፣ ስለቅኔ አጀማመርና ደራሲ ማንነት የራሳቸው የሆነ አስተሳሰብ አላቸው፡፡ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የጎንጅ (ጎጃም) ተወላጅ የሆነው ተዋነይ የደረሰው መሆኑን ነው የሚገልጹት፡፡

> ... ደራሲው የጎንጅ (ጎጃም) ተወላጅ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ተዋነይ የሚባል ነው፡፡ እርሱም ከልጅነቱ የድርሰትና የፍልስፍና ተውህቦ የተሰጠው ስለነበር በየአድባራቱና ሊቃውንቱ ተምሮ አገባብን ካጠናቀቀ በኋላ ደቀ እስጢፋኖስ (ጣና ደሴት) ገብቶ፣ ብዙ መጻሕፍትን አንብቦ፣ የቅኔን መንገድና አይነት አስማምቶ አውጥቶ ለተማሪ ቶሎ እንዲገባው እንደዋድላ



ILS LIBRARY ADDIS ... UNIVERSITY

ሳያስረዝም፣ አገባቡን ወስኖ፣ አዋጁን አሳጥሮ፣ ለሁሉም መርህ የሚሆን አብነቱን ጽፎ ወጥቶ በጎንጅ ሲያስተምር ኖሮ ሞቷል። ስለ ተዋነይና ስለቅዱስ ያሬድ ብዙ የባልቴት ተረቶች ይተረታሉ። ከእርሱ በፊት የነበረው መልክእና ግጥም እንጅ ቅኔ አይደለም። የዜማ ቤት ሰዎች ቅዱስ ያሬድ ነው የደረሰው ይላሉ። ግን የእርሱው ተራ ግጥም እንጅ ቅኔ ስላልሆነ ጉንጭ አልፋ ክርክር ከመሆን አይዘልም። ዋድሉችም ዮሀንስ ገብላዊ ተናግሮታል ይላሉ። እርሱም ሰዋስው እንጅ የቅኔን ህግ ስላልጻፈ ቀዳሚውና ደንበኛው ደራሲ ተዋነይ መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ከእርሱ በኋላም የተነሱ ሊቃውንት የእርሱን መሰረት ተከትለው እያስፋፉት እንደሄዱ አይካድም (አለማየሁ፡ 1950፡117)።

የግእዝ ቅኔ ጅማሬን በተመለከተ አድማሱ ጀንበሬና ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም የተቀራረበ ሀሳብ አላቸው። የግእዝ ቅኔ ጀማሪ ቅዱስ ያሬድ ያለመሆኑን ሁለቱም ይስማማሉ። በኢትዮጵያ ምሁራን ዘንድ ስለ ግእዝ ቅኔ ጅማሬ ሲወሳ ሁለት አይነት አስተሳሰብ መኖሩንም ይገልጻሉ። አንደኛው አስተሳሰብ ዮሀንስ ገብላዊ ቅኔን ጀምሮታል የሚለው አስተሳሰብ ነው። አድማሱና ገብረ ዮሀንስ የሚለያዩት በሁለተኛው አስተሳሰብ ላይ ነው። እንደ ገብረ ዮሀንስ እምነት ቅኔን ደቀ እስጢፋ የደረሰው መሆኑን የሚገልጹ ሲሆን አድማሱ ጀንበሬ ግን ደቀ እስጢፋንና ተዋነይን አንድ በማድረግ «ተዋነይ ደረሰው» የሚባል ስለመሆኑ ይገልጻሉ።

.. እንግዲያ ማን ጀምሮታል ቢሉ «ዮሀንስ ዘገብሉን» የተባለ የዋድላ ተወላጅ ነው የሚሉ አሉ። ተዋነይ ወይም ደቀ እስጢፋ የተባለ የጎጃም ተወላጅ ነው የሚሉም አሉ። የኒህ የሁለቱ መረጃዎች በየበኩላቸው የጎጃም አገባብ፣ የዋድላ አገባብ፣ የጎጃም ቅኔ ፣ የዋድላ ቅኔ እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየ ዛሬም ያለ ስለሆነ የሁሉንም አምን ብሎ ከመቀበል በቀር የሚያዋጣ ነገር የለበትም ብለን ከሁለቱም ወገን ያገኘነውን አጭር አጭር ታሪክ እንጽፋለን (አድማሱ 1963.10)።

እዚህ ነጥብ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ስለ ግእዝ ቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ አያሌ ሊቃውንት የየራሳቸውን ሀሳብ የሰጡ መሆኑ ነው። ብዙዎቹ ተቀራራቢ ሀሳብ አስፍረዋል። ጥናት አቅራቢው ከተመለከታቸው መረጃዎች ውስጥ ደቀ እስጢፋ ማለት ተዋነይ ስለመሆኑ ሀሳብ የሰጡት ግን አድማሱ ጀምበሬ ብቻ ናቸው። ሀሳባቸውም ሲመረመር ተዋነይ በግራኝ ጦርነት ምክንያት ደቀ እስጢፋ የሄደ መሆኑ ተደጋግሞ የተገለጸ ስለሆነ፣ ደቀ እስጢፋ የተባለ ስያሜ የተሰጠውም ከኖረበት ደሴት ስያሜ በመነሳት ሊሆን ስለሚችል ተዋነይና ደቀ እስጢፋ አንድ ሰው መሆናቸውን አድማሱ ጀንበሬ መግለጻቸው ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ይመስላል።

ዮሀንስ ገብላዊ የግእዝን ቅኔ ጀምሩዋል (ደርሱዋል) የሚለው ክፍል ቅኔ ከጉት ወደ ሙሉ ቤት ግጥምነት በመሸጋገር እስፈላጊው የተሙዋላለት፣ ትምህርት ቤት የተቋቋቋመለት፣ ጉባኤ የሰፋለት፣ በዮሀንስ ገብላዊ መሪነት መሆኑን ይናገራሉ። ዮሀንስ ገብላዊ በዋድላ (ላስታ) ገብሉን ወይም ገብላት በተባለ ቦታ የተወለደ ታላቅ ሊቅ በመሆኑ በትውልድ ቦታው ስም ዮሀንስ ገብላዊ፣ በፈላስፋነቱ ደግሞ «ዮሀንስ ፊልሱፍ»

እየተባለ ይጠራ የነበረ መሆኑና ይኖር የነበረውም በአጼ ዘርአያእቆብ ዘመነ መንግስት እንደ ነበር ተገልጽዋል።

በዚያን ዘመን በአጼ ይኩኖ አምላክ ከተማ፣ ታቦርና ኤርሞንኤም በተባሉ ተራሮች መካከል ተቀምጦ የቅኔን ምስጢር አረቀቀ፣ አፍታታ፣ እውቀቱንም አደላደለ። ብዙ ደቀ መዛሙርትንም አፈራ። ከደቀ መዛሙርቱም መካከል አብነት አድርጎ ያወጣው አባ ወልደ ገብርኤል የተባለውን መነኩሴ ነበር። አባ ወልደ ገብርኤል ሰምረ አብን፣ ሰምረ አብ ደግሞ በዘመኑ ንጉስ የነበሩትን አጼ በእደ ማርያምን ጨምሮ ልሄብንና አልያብን እንዳስተማረ ተገልጽዋል (ገብረ ዮሀንስ፡ 1993. 19)።

በአጼ በእደ ማርያም ዘመነ መንግስት ሰምረ አብ ቅኔን ስያስተምር በቅኔ ጥበብ የተነሳ ከበእደ ማርያም ጋር አለመግባባት ተፈጥሮ የነበረ ስለመሆኑ፣ የቅኔው መንገድና አቀራረቡ ለንጉሱ እንግዳ ስለሆነበት የቅኔውን አነጋገር እንደ ድንፋታና መቀባጠር ቆጥሮ ቅኔውን እንዳቃለለበትና በመጨረሻም ንጉሱና ሰምረ አብ ሱባኤ ገብተው የቅኔ ደገኛ ትምህርትነት ለንጉሱ የተገለጸለት ስለመሆኑ፣ በዚህም ጊዜ «ድህረ ተሰብረ አጽንኦ ለሰብእናነ ልህኩት፣ ለብህዊ ክርስቶስ በማየ ህዲስ ጥምቀት» በማለት ቅኔን የዘረፈ ስለመሆኑ፣ ስለቅኔ አመጣጥ ታሪክ የጻፉት አብዛኛዎቹ ይስማሙበታል።

የተወሰነ ልዩነት የሚስተዋለው ከሰምረ አብ ቀጥሎ በተነሱት ተከታዮች ማንነት ላይ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ ፣ የግእዝ ቅኔያት ፣ ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ እና መጽሀፈ ታሪክ ወግስ በሚል ርእስ በቀረቡት መጻህፍት ውስጥ ያለው ሀሳብ ተቀራራቢ ነው። በዩኒቨርሲቲውና በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በጋራ በተዘጋጀው መጽሀፍ ውስጥ የሚከተለው ሰፍሩዋል።

> ... ሰምረ አብ ለልሄብ ፣ ልሄብ ለኤልያብ ፣ ኤልያብ ለተዋነይ እና ድድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ። ከዚህ በሁዋላ መንግስት ታወከና ግራኝ ተነሳ። ድድቅ ወልደ ማርያም በዳውንት (ጎንደር) የጨረቃ ከሚባል ቀበሌ ገባ። ተዋነይ በጣና ባህር ውስጥ ደቀ እስጢፋ ከሚባል ደሴት ገብቶ ተቀመጠ። ... ከድድቅ ወልደ ማርያም ቀጥሎ የጨረቃ በሚባለው ቦታ ድድቅ ድድቅ ተብለው የተሰየሙ ስድስት መምህራንን አስተምረዋል። (ድድቅ ማለትም የእውቀት የምስጢር ጀግና ማለት ነው።) በስድስተኛው ድድቅ ጊዜ የቅኔ ጉባኤ ሰፋ። ስድስተኛው ድድቅ ሶልያና ወልደ ማርያምን አስተማረ። ሶልያና ወልደ ማርያም ለሚጫው (ጎጃም) ማእበል ወልደ ህይወት አስተማረ። ማእበል ወልደ ህይወት ለደብረ መዊእ (ጎጃም) ሊቀ ህሩያን ዘገየና ለሚካኤል ደብር (ጎንደር) ጌቴ ገምረው (አለቃ ጌታነህ) አስተማረ። «ማእበል ገሞራው» የሙያ ሙገሳ ስም ነው (ቅኔውን የሚያጎርፍ ማለት ነው) (አፈወርቅ ዘውዴ ፣1950.19)።

ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ፣ በሚል ርእስ በገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም በተጻፈው መጽሀፍ ውስጥ ዳግሞ፣

> ድድቅ ወልደ ማርያምና ተዋነይ የሰምረ ክርስቶስ (ሰምረ አብ) አራተኛ ትውልድ መሆናቸውን የጻፉ ባለታሪኮች አሉ። እንደነሱ አመዘጋገብ ሁለቱ ማለትም ድድቅ ወልደ ማርያም እና ተዋነይ ከአንድ ት/ቤት የወጡ ናቸው። ከይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት ጀመሮ እስከ 16ኛው



ILS LIBRARY

ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ነገስታት መዲና አማራ ሳይንት ነበር። ከዮሀንስ ገብላዊ ጀምሮ እስከ ተዋንይና ድድቅ ወልደ ማርያም ድረስ የነበሩ የቅኔ መምህራን ከአማራ ሳይንት አክባቢ አልራቁም ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ግራኝ መሀመድ ሲነሳ ድድቅ ወልደ ማርያም ወደ ጎንደር ሔዶ ዳውንት ውስጥ ጨረቃ ማኬል በተባለ ደብር ቅኔን እያስተማረ ተቀመጠ። ተዋንይ በበኩሉ ወደ ጎጃም በመሔድ እዚያው ቅኔን አስፋፋ (ገብረ ዮሀንስ 1993 28-29)

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በመምህር አፈርቅ ተክሌ «መጽሀፈ ታሪክ ወግስ» በሚል ርእስ ተጽፎ በታተመው መጽሀፍ ውስጥም፣ ከላይ ከሰፈረው ጽሁፍ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ሰፍሩዋል።

ሁለተኛው አስተሳሰብ የግእዝ ቅኔ ደራሲ ደቀ እስጢፋ ነው የሚለው ነው። ደቀ እስጢፋ ማለት ተዋንይ ማለት እንደሆነ የሚገልጹም እንዳሉ ቀደም ሲል የተገለጸ መሆኑ አይዘነጋም። የደቀ እስጢፋ የቅኔ ደራሲነትን የሚመሰክሩ ሊቃውንት ስለመኖራቸው በተለያዩ መጻህፍት ውስጥ ተገልጾ ይገኛል። ከነዚህም መካከል ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፣ ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም፣ መምህር አፈወርቅ ተክሌ ፣ አለቃ ኤልያስና አድማሱ ጀንበሬ ይገኙበታል። ስለ ደቀ እስጢፋ የቅኔ ደራሲነት ሰፋ ያለ ሀሳብ ያሰፈሩት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ናቸው።

.. በሌላ በኩል ደግሞ ቅኔን ደቀ እስጢፋ የተባለ ሊቅ እንደደረሰው ይናገራሉ፣ እርሱም ጽርዕ ድረስ ሔዶ ብዙ ጥበባትን ከቀሰመ በኋላ ሰባት አይነት የሚያስደንቁ ነገሮችን ይዞ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ይናገራሉ። ይሁን እንጅ ስድስቱ ጥበባት የጥንቆላ ሥራዎች ስለሆኑ በሀገሩ ላይ ተጠልተዋል፣ ተቀባይነትም አላገኙም፣ ግን እስካሁንም ይሠራል። በሥውር ከእንዱ ወደ አንዱ መተላለፉ አልቀረም። ቅኔ ግን በግጥሙ፣ በምስጢሩ በቃል አስካኩ ተወዳጅነትን ስላገኘ ሁሉም በግልጽ ይማረውና ያስተምረው ጀመረ። ደቀ እስጢፋም ቅኔውን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ለአጼ እስክንድር አስተምሯል። የቅኔ ሥርአት በዚያን ጊዜ የታወቀ የተወደደም ይሁን እንጅ ቤቱ፣ ሀረገ፣ እንደዛሬው የተመጠነና የተለካ አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ግን ቤት ሲኖረው፣ አንዳንድ ጊዜም እንዲሁ ያለ ቤት በጉት መልክ ሲቀኙት ኖረዋል። ... ደቀ እስጢፋም ከንጉሱ ጋር ወዳጅነት፣ ከፍ ያለም ባለሟልነት ነበረው። ነገር ግን በራሱ መጥፎ ስራ የነበረውን ወዳጅነት አጣ። ጥፋቱም የንጉሱን ሚስት ያወስልት ስለነበር ነው። በዚህም ሳይመለስ ጽርዕ ከተማረው በአንደኛው ጥበቡ እንደ መሠወር አድርጎ ይዞ ጠፋ። ሁሉም በነገሩ ሲጨነቁ ሲያዝኑም ሳለ ከሊቃውንቱ አንዱ ነገሩ ተገልጦለት የንጉሡ ሚስት እጅዋን ተሰብራ ከማሕሉ ደቅ አለች አሉ ብሎ ተቀኘ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ እስክንድር ቅኔ ዐዋቂ ስለነበር ነገሩ ገባውና ደቅ ውስጥ መገኘቷን አረጋገጠ። ወዲያውም ጉዞውን ጀመረና ሲገሠግሥ ደቅ ደረሰ። ደቀ እስጢፋም ከንግሥቲቱ ጋር በሰላም ተቀምጦ ሳለ ንጉሡ በድንገት ስለደረሰበት ደነገጠና እየተርበተበተ ይህንን ተቀኘ።

ይቤ አጋግ ከመ ዝኑ ሞት መሪር፣
በጊዜ ረዝዞ ሳሙኤል መምህር፣

ወሰራቱ ንግሥት እነ ደቀ እስጢፋ ኀሱር፣
እንበሳ እስክንድር፣ ዕጓለ እንበሳ እንዘ ትጥህር፣
እም እርእየከ ተኀጠኒ ምድር፡፡ እለ፡፡

ንጉሱ እስክንድርም ለቅኔው አጻፋውን እንዲህ ሲል መለሰ

ምንት አገበረከ ቀንጽለ ገዳም አንተ ቤተ አንበሳ በዊእ፣
ኢትሰምዕኑ ጥኀረቶ በአፍእ፣
እስመ እምኔየሰ ተጋንዮትከ ጠፍእ፣
እንበሳ በኃይሉ እምድኀረ ሞዓ
ኀድግስ ዘለከ ብጽእ
ጽንሖ ለእሳት ከዊንከ ብርእ፡፡

ብሎ በተቀመጠበት ቤት እሳት ለቀቀበት፡፡ ይህ አይነት ግጥም የቅኔ ግጥም ሲባል ወይንም ሲሆን መንገዱ የጉት አይነት እንጂ የአሁኑን መንገድ አልተከተለም፡፡ .. ይሁን እንጂ ደቀ እስጢፋም በዕፀ መሠውር ከጢሱ ጋር ንግሥቲቱን ይዞ ሳይቃጠል ጠፋ ይባላል፡፡ እስከ አሁንም አለ አልሞተም ተሰውሯል እየተባለ እርሱም የአገሩ ሰወችም ሳይቀሩ በተሰወረው ደሴት ውስጥ ይኖራል እየተባለ በተረት መልክ ይተረካል፡፡ ይሁን እንጂ ከደቀ እስጢፋ ከተማሩት ብዙዎቹ ሊቃውንት አንደኛው ተዋነይ ስለሆነ እርሱም የቅኔ ደራሲ ተብሎ በመገመት ይነገርለታል (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ 1963.173-174)፡፡

ስለ ደቀ እስጢፋ ከሀብተ ማርያም ወርቅነህ አስተሳሰብ ጋር ተቀራራቢ ሀሳብ ያቀረቡት ሌላው ጸሀፊ ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም ናቸው፡፡ ገብረ ዮሀንስ የደቀ እስጢፋን ወደ ግሪክ (ጽርእ) ሄዶ መማር ይጠቅሱና ሀሳቡን አምኖ ለመቀበል አስቸጋሪ መሆኑን በምክንያት አስፍረዋል፡፡

ደቀ እስጢፋ ግሪክ ሄዶ ፍልስፍናን ተማረ፡፡ የተማረውም የፍልስፍና መንገድ ከቅኔ መንገድ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ስለዚህ በፍልስፍናው ባገኘው ዘዴ ተጠቅሞ የቅኔውን መንገድ ፈለሰፈ የሚሉ አሉ፡፡ ደቀ እስጢፋ ከ1470-1486 ባለው ጊዜ ውስጥ እንደነበር ይታመናል፡፡ ደቀ እስጢፋ ቅኔን ማስተማር ሲጀምር አጼ በዕደ ማርያም በሕይወት ነበሩ፡፡ አጼ እስክንድር ከሱ ቅኔን ተምረዋል፡፡
አንድ ኢትዮጵያዊ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ግሪክ ሄደ ተማረ ማለት ያስቸግራል፡፡ ቱርኮች ከዚያ በፊት ጀምሮ ለብዙ ዘመናት ግሪክን በመቆጣጠር ላይ ነበሩ፡፡ ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን ለመውረር የቻለው ከነሱ የመሳሪያ ድጋፍ ስላገኘ ነው፡፡ ብዙ የሚደትራንያን አከባቢ አገሮችን በቁጥጥር ከማዋል አልፈው የኢትዮጵያ ጠረፎች የነበሩት የቀይ ባህር አከባቢዎች በነእርሱ እጅ ወድቀው ነበር፡፡ የግሪክ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶችም በዚህ ወቅት ከተዘጉ ዘመናትን አሳልፈው ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች እያሉ ከኢትዮጵያ ተነስቶ አንድ ኢትዮጵያዊ ግርክ ድረስ ሔዶ ሊማር አይችልም፡፡ ደቀ እስጢፋ ወደ ጎጃም የሔደበት ምክንያትም በንጉሱ ሚስት ስለታማና ንጉስም ስለጠረጠሩት በሽሽት መሆኑ ይነገራል፡፡ ሆኖም በጎጃም ቅኔን አስፋፍቷል (ገብረ ዮሀንስ፣ 1993.29)፡፡

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ ደቀ እስጢፋ የተዋነይ መምህር የነበረ ስለመሆኑ የገለጹትን ሀሳብ በመቃወም ስለ ደቀ እስጢፋ ሀሳባቸውን ያሰፈሩት ደግሞ እነ አለቃ ኤልያስ ናቸው፡፡

> … ደቀ እስጢፋ የተዋነይ መምህር ነው የተባለው እውነት ያይደለ፣ በታሪክና በዘመን የማይገናኙ፣ የተራራቁ ፈላስፎች ናቸው፡፡ በፍልስፍና ግን ይመሳሰላሉ፡፡ ደቀ እስጢፋ የነበረው በዐጼ ምዕደ ማርያም ዘመነ መንግስት ነው፡፡ ይሔውም ሊታወቅ ለዐጼ ምዕደ ማርያም ልጆች ለእስክንድርና ለናዖድ ቅኔን ከፍልስፍና ጋር ያስተማረ ደቀ እስጢፋ ነው፡፡ ኋላ በዐፄ እስክንድር ባለቤት በእቴጌ ማርታ ምክንያት ባገኘው ድቀት ማርታን በፍልስፍና ይዞ እስከተሰወረበት ቀን ድረስ የነበረው በወሎ ክፍለ ሀገር በጥንቷ አምሀራ ላኮ መልዛ በሚባለው በደብረ ኮላንቶ ነበረ፡፡ .. ከዚያ እስከ ተዋነይ ድረስ ዘጠኝ መምህራን ነበሩ፡፡ ተዋነይን ግን ያስማረው በደሴተ ጣና ውስጥ በምትገኘው በደቀ እስጢፋ ገዳም ውስጥ የነበረው ሥውሩ «ዘእብኖዲ» ይባል የነበረው መምህር ነው (እነ አለቃ ኤልያስ 1992.18-19)፡፡

ስለ ደቀ እስጢፋ የቅኔ ደራሲነት የሚገልጸው ሌላው መጽሀፍ «የግእዝ ቅኔያት» የተሰኘው መጽሀፍ ነው በአለቃ አፈወርቅ ዘውዴ በተዘጋጀው በዚህ መጽሀፍ መቅድም ውስጥ የሚከተለው ስፍሮ ይገኛል፣ በተጨማሪም ሀብተ ማርያም ወርቅነህ መጽሀፍ ውስጥ የተገለጸው ሀሳብ ሳይለውጥ ሰፍሩዋል፡፡

> ደቀ እስጢፋ የተባለ ሊቅና ፈላስፋ በአፄ በእደ ማርያም ዘመን ወደ ፅርእ (ግሪክ) አገር ወርዶ ሰባት አይነት እውቀት ተምሮ መጣ፡፡ ከዚህ ውስጥ ሰባተኛው ቅኔ ስለሆነ በሊቃውንት ዘንድ ተወዶ ትምህርት ሆኗል፡፡ ደቀ እስጢፋ የቅኔን ጥበብ ለአፄ እስክንድር (1470-1486) እንዲሁም ለሀዊራ፣ ለመንክራ፣ለብሁርና ለሌላው እስክንድር አስተማራቸው፡፡ ደቀ እስጢፋ በንጉሱ ግቢ ቤተኛ በመሆኑ ከንግስቲቱ ታማ፡፡ ታማኝ አሽከርም በዘዴ ለንጉሱ ነገረበት፡፡ አፄ እስክንድር አሽከሩ እንደመከረው አንድ ቀን ድንገት ሳይታሰብ ሄዶ ከነበረበት ቢመለስ ቤት ተዘግቶ ደቀ እስጢፋ ከእቴጌይቱ ጋር የፍልስፍናን ነገር ሲጫዋወት ንጉስ ሰማ፡፡ ቤቱ ስለተዘጋበት ንጉሱ እውጭ ሆኖ እየፎከረ ደቀ እስጢፋም እውስጥ ሆኖ ፈርቶና ደንግጦ ሁለቱ የሚከተሉትን ቅኔዎች ተዛርፈዋል ይባላል (አለቃ አፈወርቅ 1980-19-20)፡፡

የግእዝን ቅኔ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጡን አስመልክቶ የተለያዩ የሙያው ሊቃውንት በጥናታቸው ውስጥ ያካተቱትን የተለያየ አስተያየት በዝርዝር ለመመልከት ተሞክሩዋል፡፡ የቅኔን ጅማሬና የጀማሪውን ማንነት በተመለከተ የቀረቡት ሀሳቦች ሲመረመሩ በአራት አይነት አስተሳሰቦች የተከፋፈሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አንደኛው አስተሳሰብ የቅኔ መነሻ የኦሪት ዘመን ሰዎች ፈጣሪያቸውን ለማመስገን ይገጥሙዋቸው የነበሩ የመዝሙር ግጥሞችን ከዳዊት የምስጋና መዝሙሮች ጋር እያጣቀሱ የቅኔ መነሻ (መጀመሪያ) የዳዊት መዝሙር ሊሆን ይችላል በሚል የሚቀርበው አስተሳሰብ ነው፡፡



ILS LIBRARY ADDIS ... UNIVERSITY

ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ የግእዝ ቅኔ የተጀመረው በዘመነ አሪት ማብቂያና በአዲስ ኪዳን መግቢያ አገው በተባለ የኢትዮጵያ አካባቢ «ዘሉቱኤል» በተባለ ሰው መጀመሩን የሚገልጸው አስተሳሰብ ነው። በድጓው ውስጥ የሰፈሩትን ቃላትና የግጥም ስንኞች እየጠቀሱ የግእዝ ቅኔ ጀማሪ ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ የሚነሳው አስተሳሰብ ደግሞ ሶስተኛው አመለካከት ነው።

የመጨረሻው አስተሳሰብ ከያሬድ በሁዋላ በተነሱ ምሁራን የግእዝ ቅኔ ተጀምሩዋል፤ የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱት ናቸው። የአሁኑን መልክ፣ ቅርጽና ይዘት ያለው ቅኔ የተጀመረው ከያሬድ በሁዋላ በተነሱ የቅኔ ሊቃውንት መሆኑን ማስረጃ እያጣቀሱ የሚከራከሩትም በበኩላቸው በሁለት የተከፈለ አስተሳሰብ አላቸው። የመጀመሪያዎቹ፣ ማለትም የዋድላ ጉባኤ ተከታዮች፣ በዮሀንስ ገብላዊ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በድድቅ ወልደ ማርያም ተጀመረ የሚል አመለካከት የሚያራምዱ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት ጎንጅዎች በበኩላቸው በተዋነይ ወይም በደቀ እስጢፋ ስለመጀመሩ በእርሱ የተደረሱትን ቅኔዎች እየጠቀሱ ይከራከራሉ።

እንደ ጥናት አቅራቢው እምነት የግእዝን ቅኔ ጀማሪ ማንነትና ጊዜውን ወስኖ ለመግለጽ በቅድሚያ የግእዝ ቅኔ «ቅኔ» ሊሰኝ የሚገባው በምን ደረጃ ላይ ሲገኝና የትኞቹን ነጥቦች ሲያሙዋላ እንደሆነ በቅድሚያ መወሰን ያስፈልጋል። ብዙዎቹ ምሁራን በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ብያኔ ለመስጠት የተቸገሩት ወጥ የሆነ ብያኔ ሊሰጡ ባለመቻላቸው ነው። አንዳንዶቹ በውስጡ ህብር ቃል የገነነበትን ስንኝ ሁሉ «ቅኔ ነው» ብለው ይናገራሉ። ሌሎቹ ደግሞ በተለያዩ የእምነት መጻህፍት ላይ የተገለጹና በህብር የተመሰጠሩ ጉቶችና ግጥሞች ቅኔዎች ስለመሆናቸው አጥብቀው ይከራከራሉ። ሌሎች ደግሞ አሁን ባለበት መልክ ቅርጽና ይዘት ተዘጋጅቶ ያልቀረበ ሁሉ «መልክና ውዳሴ» እንጅ ቅኔ ሊባል አይገባም ይላሉ።

ስለዚህ፣ የግእዝን ቅኔ ደራሲና የተጀመረበትን ጊዜ ለመወሰን አስቀድሞ የግእዝን ቅኔ ትክክለኛ ትርጉም መወሰን ተገቢ ነው። ጥናት አቅራቢው በዚህ ጥናት ውስጥ የገለጸውን የግእዝ ቅኔ ትርጉም መነሻ ማድረግ ከተቻለ የግእዝ ቅኔን ጀማሪ ማንነትና የአሁኑን መልክ ይዞ ብቅ ያለበትን ጊዜ ወስኖ መናገር የሚያስቸግር አይሆንም። ከዚህ አኩዋያ ሲታይ ቅኔ የአሁኑን መልክ፣ ቅርጽና ይዘት አሙዋልቶ መቅረብ የጀመረው ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን (ገብረ ዮሀንስ 1993፤29) ባለው ጊዜ እንደሆነ በወቅቱ የተደረሱትን ቅኔዎች በማስረጃነት እያቀረቡ መናገር ይቻላል።

በአጠቃላይ ሲታይ፤ ስለ ግእዝ ቅኔ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ አስመልክቶ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱትን መነሻዎች ብቻ መሰረት በማድረግ



ILS LIBRARY

እውነታን መሰረት ያደረገ የተሙዋላ መደምደሚያ መስጠት ተአማኝነቱን ያጎድለዋል። ስለታሪኩ ትክክለኛነት ማጠቃለያ ሀሳብ ለመስጠት በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ስለ ተዋነይና ደቀ እስጢፋ ግንኙነትና አንድነት፣ ስለ ድድቅ ወልደ ማርያምና ዮሀንስ ገብላዊ ግንኙነት፣ ስለጥንታዊዎቹ (የመጀመሪያዎቹ) ጉባኤዎች (ዋድላና ጎንጅ) አመሰራረት፣ ልዩነትና አንድነት፣ ደቀ እስጢፋ (ተዋነይ) ጽርእ (ግሪክ) የሄደ ስለመሆን አለመሆኑ፣ ሄዶ ከሆነ ይዝዋቸው መጥቶዋል የተባሉት ሰባቱ ጥበባት ምን ምን እንደሆኑ፣ አንደኛው ጥበብ (ቅኔ) ብቻ ለምን ወደ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስርአት እንደገባና ሌሎችስ ለምን እንደተከለከሉ፣ «አውደ ነገስት» በተሰኘው የጥበባት መጽሀፍ መግቢያ ላይ፣ ንጽሀፍ እንከ ዘንተ መጽሀፈ ዓውደ ነገስት ዘተረከበ በደሴተ ጣና እምደብረ ደቀ እስጢፋ... (ገብረ ስላሴ ብርሀኑ፣ ሀተታ መናፍስት ወአውደ ነገስት ከነጠልሰሙ፣ 1997፣ ገጽ-151) እደተባለው፣ አውደ ነገስት የተሰኘው የጥበባትና የፍልስፍና መጽሀፍ መነሻው ደቀ እስጢፋ የተባለው ቦታ ስለመሆኑና ከቅኔው ባላባት ከተዋነይ(ደቀ እስጢፋ) የጥበባት ስራዎች ጋር ሊኖረው ስለሚችለው ትስስር፣ ደቀ እስጢፋ ከአጼ እስክንድርና ከባለቤቱ ጋር ስለነበረው ግንኙነት፣ ወዘተ እውነታን መሰረት ካደረጉ የታሪክ ምንጮችና ማስረጃዎች አኩዋያ በባለሙያ ተጨማሪ ትኩረት አግኝተው በተናጠልና በጥልቀት ሊጠኑና ሊመረመሩ ይገባል።

## ምእራፍ ሶስት

### የቅኔ ጉባኤዎች፣ መንገዶችና አይነቶች

### 3.1 የቅኔ ጉባኤዎችና መንገዶች

ስለ ግእዝ ቅኔ ጉባኤዎችና መንገዶች ታሪካዊ አመጣጥ በተለያዩ መጻህፍት የተለያዩ ሀሳቦች ሰፍረው ይገኛሉ። በቅኔ አመጣጥና አጀማመር ታሪክ ውስጥ መቁዋጫ ያላገኙ የተለያዩ አስተሳሰቦች ያሉ መሆኑን ከዚህ ርእስ ጉዳይ አስቀድሞ በቀረቡ ርእሶች ውስጥ በዝርዝር ተገልጽዋል። ይሁን እንጅ፣ ቀዳሚዎቹ የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎች ዋድላና ጎንጅ መሆናቸውን፣ የዋድላ የቅኔ ጉባኤ መስራች ድድቅ ወልደ ማርያም (አንዳንዶቹ ዮሀንስ ገብላዊ) መሆኑንና የጎንጅ ጉባኤ መስራች ደግሞ ተዋነይ ወይም ደቀ እስጢፋ (ሁለቱ አንድ ከሆኑ) መሆኑን፣ እንዲሁም ከዚያን ወቅት ጀምሮ የቅኔ መንገድ ልዩነት መከሰቱን ስለሙያው ታሪካዊ አመጣጥ የጻፉት ምሁራን አብዛኛዎቹ ይጋሩታል።

በወቅቱ ለቅኔው መንገድ መለያየትና ለተለያዩ ጉባኤዎች መመስረት ምክንያት የሆነው፣ ግራኝ መሀመድ በጦርነት አሸንፎ አብዛኛውን የኢትዮጵያ አከባቢ በመቆጣጠር የክርስትናን እምነት በማጥቃቱ ምክንያት፣ በአንድ ጉባኤ የተማሩት ድድቅ ወልደ ማርያምና ተዋነይ (አፈወርቅ ዘውዴ፡1980፣19፣ አፈወርቅ ተክሌ፡ 1997፣24) ወደተለያየ ቦታ በመሰደዳቸውና በስደትም በቆዩባቸው ጊዜያት የየራሳቸውን የቅኔ መንገድ ይዘው በመገኘታቸው እንደሆነ ብዙዎቹ ሊቃውንት ስለሙያው በጻፉዋቸው መጻህፍት አስፍረውታል።

> ... ኤልያስም ለተዋነይና ለድድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ። ተዋነይ የጎንጅ መንገድ አባት ሆነ፤ ድድቅ ወልደ ማርያም ደግሞ የዋድላ መንገድ አብነት ሆነ። የቅኔ ቤት ወይም መንገድ ልዩነት በዚህን ጊዜ ተጀመረ (ሀብተማርያም፣ 1963.175)።

ከላይ በተጠቀሱት የመጀመሪያዎቹ የቅኔ ጉባኤዎች ተምረው የወጡ ሊቃውንት ስለ ግእዝ ቅኔ ጀማሪ ማንነት የሚሰጡት አስተያየት የተለያየ ነው። የልዩነታቸው መሰረቱ ሁሉም የተማሩበትን ጉባኤ መሰረት እያደረጉ የየጉባኤዎችን መስራቾች የግእዝ ቅኔ ጀማሪ አድርገው የሚናገሩ መሆናቸው ነው። በዋድላ የቅኔ ጉባኤ ተምረው ሙያውን ወደ ጎንደር ያስፋፉት ሊቃውንት ቅኔ ጥንታዊ ፍልስፍና መሆኑን ያምኑና የግእዝ ቅኔ ጀማሪነትን፣ አንዳንዶቹ ለዮሀንስ ገብላዊ ሲሰጡት፣ የተወሰኑት ደግሞ ለድድቅ ወልደ ማርያም ያደላሉ። በጎንጅ ጉባኤ የተማሩት ሊቃውንት ደግሞ የትክክለኛው ግእዝ ቅኔ ጀማሪ ተዋነይ መሆኑን ከቅኔዎቹ

ማስረጃ እየጠቀሱ ይከራከራሉ። በዚህ ነጥብ ላይ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት አንዱ፣ ስለ ቅኔ ሙያ ሰፊ ምርምር ያደረጉት አለማየሁ ሞገስ ናቸው።

ከአለማየሁ ሞገስም ሆነ ሌሎች ካሰፈሩት ሀሳብ የምንረዳው የጎጃም የቅኔ ጉባኤና መንገድ መስራች ተዋነይ መሆኑን ነው። ተዋነይ ከጣና ደሴት (ደቀ እስጢፋ) ወጥቶ ቅኔውን ማስተማር የጀመረው ጎንጅ በተባለ ቦታ ጎጃም ውስጥ መሆኑን ስለጉዳዩ ያጠኑ ሁሉም ይስማሙበታል። ስለ ቅኔ መንገዶችና ጉባኤዎች ገብረ ዮሀንስ በዝርዝር አስፍረዋል።

> የቅኔ ቦታዎች ከ15ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ለሁለት ምእት አመታት የዋድላና የጎንጅ በመባል በሁለት ተከፍለው ቆዩ። ቆይቶ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች የጎንጅና የዋሸራ በመባል ለሁለት ተከፈሉ። በ17ኛው ክፍለ ዘመን የጎንደር ከተማ ስትቆረቆር አራተኛው የቅኔ ቦታ በዚችው ከተማ ተስፋፋ። ከዚያ ወዲህ የቅኔ ቦታዎች አራት ሆኑ። የአራቱ ክፍሎች የቅኔ መንገድም ይለያያል የዋድላ የጎንጅና የዋሸራ መምህራን ለግእዝ ሰዋስው መመሪያ ሊሆን የሚችል ዝግጅት በየራሳቸው አዘጋጅተው ትተዋል። ይህም መመሪያ በነሱ አባባል አጠቃላይ ስሙ አገባብ ይባላል። በዝርዝር ሲነገር ደግሞ እርባ ቀመር፣ ዐቢይ አገባብ፣ ንዑስ አገባብና ደቂቅ አገባብ ይባላል። ዋድሎችና ዋሸሮች ሆን ብለው አገባቡን ትምህርት ይሠጡበት ነበር። ወደ ቅኔው ይህን ያህል ትኩረት ሳይሰጡ በይበልጥ አገባብን በማስተማር የታወቁ ምሑራን ነበሩ። .. የጎንጅ የቅኔ መምህራን ይህን ያህል የጽሁፍ አገባብ አላስተላለፉም። የእነርሱ የአገባብ ትምሕርት አብሮ ከቅኔው ጋር ነው የሚሰጠው። ከጎንጅ የቅኔ መምህራን የተማሩ ሁሉ የጽሑፍ አገባብ እንዲኖረው አይገደድም። የአገባቡን መንገድ ከቅኔው ትምህርት ጋር በሚገባ ያውቀዋል። ስለ አገባብ መንገድ ቢጠየቅ መጽሐፍ ልመልከት ሳይል ወዲያውኑ መልስ ይሰጣል። ባንድ ቅኔ ውስጥ መወድስም ይሁን ሌላ የጎንጅ ቅኔ ሲነገር በአገባብ ስለሚቀናበር ላላወቀው ስሚ በጣም ይከብዳል። ሁሉም የአገባብ አይነቶች ይኖራሉ። ስለዚህ የቅኔውን ምስጢር ከተረዳ በኋላ ቀጥሎ ይህ አቢይ አገባብ ነው፤ ይህ ንዑስ ነው፤ ይህ ደቂቅ ነው እያለ በአእምሮው ያስገባዋል። ቅኔንም ለመቅረጽ በሰፊው ይረዳዋል። በአጠቃላይ የግዕዝ ሰዋስው የሙያ ጥንቃቄ በጎንጅ የቅኔ መምሕራን ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ አለው። በነሱ ያለው ትንሽ ችግር የግዕዝን ቃላት እንደ ልብ ለመጠቀም አለመፍቀድ ነው። የግዕዝ ቋንቋ በቋንቋነቱ ብቻ በነሱ ዘንድ በስራ ላይ አይውልም። ብዙዎቹ የግዕዝ ቃላት የአማርኛ ፀያፍነት አላቸው እየተባለ በቅኔ እንዳይገቡ ይከለከላሉ። .. የጎንደር የቅኔ መምህራንም በጽሑፍ የሠፈረ አገባብ የላቸውም፤ እነሱ ይጠቀሙ የነበረው ከላይ በተጠቀሱት ክፍሎች አገባቦች ነው። ቅኔያቸውም ቢሆን የሰዋሰውን መንገድ የሚጠነቀቅ አይደለም። ዋናው ትኩረታቸው የመጻህፍትን ምስጢር በቅኔ መግለጽ ነበር። ከብሉያትና ከሐዲሳት ትርጓሜ ጋር ቅኔን ያያይዙታል። ይህም የሆነበት ምክንያት በጎንደር ለመጀመሪያ ጊዜ የመጻሕፍት ትርጉም በአማርኛ ሲዘጋጅ ቅኔም ከዚያው ጋር አብሮ በመስፋፋት ላይ ስለነበር ነው (ገ/ዮሀንስ 1993 29-32)

ገብረ ዮሀንስ እንደገለጹትና ብዙዎቹም እንደሚስማሙበት ቀዳሚዎቹ የቅኔ ጉባኤዎች የዋድላና የጎንጅ ጉባኤዎች መሆናቸው እርግጥ ነው። በመቀጠል ደግሞ የዋድላ ጉባኤ ወደ ጎንደር ሲስፋፋ የጎጃሙ ጉባኤ ደግሞ ወደ ሁለት በመከፋፈል የዋሸራ የቅኔ ጉባኤን አስከተለ። የተጠቀሱት 4ቱ የቅኔ ጉባኤዎች የየራሳቸውን የቅኔ መንገድና የአገባብ ስልት ተከትለው እያሌ ሊቃውንትን አፍርተዋል። የቅኔ



[stamp]

ጉባኤዎች እየተጠናከሩ ሲሄዱ ከአራት ወደ ሰባት ከፍ ማለታቸው የግእዝ ቅኔያት በተሰኘው መጽሀፍ መቅድም ውስጥ ተጠቅሱዋል።

> ... በዚህ አይነት ካደገና ከደረጃ በሁዋላ ቅኔ በሰባት ቤት ተከፍሏል።(እዚህ ላይ «ቤት» ማለት ወገን ወይም አይነት ማለት ነው)። ሰባቱ የቅኔ ቤቶች ማለትም ቅኔ የተስፋፋባቸው ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው። የታቦር (ሳይንት፣ ወሎ)፣ ጫረቃ (ዳውንት፣ጎንደር) የአብዲቆም (ዋድላ፣ ላስታ) የጎንደር (ቤጌምድር) የጎንጅ፣ የዋሸራ፣ የሚጫ (ጎጃም) ናቸው። ይሁን እንጅ ከነዚህ ቤቶች ውስጥ በጣም የጎሉት የዋድላ ፣ የጎንጅ፣የዋሸራና የጎንደር ቅኔ ቤቶች ናቸው (አለቃ አፈወርቅ 1980 22)።

ከተጠቀሱት ሰባት የቅኔ ቦታዎች (ጉባኤዎች) መካከል ሶስቱ የቆዩ የጎጃም የቅኔ ቦታዎች መሆናቸውን እንረዳለን። የቅኔው ትምህርት እየተስፋፋ፣ ትምህርቱም እየተወደደና እየተከበረ በመሄዱ ከጊዜ ምሁዋላ የመማሪያ ቦታዎችም ሆኑ ተማሪዎች እጅግ እየበዙ፣ በተለያየ የቅኔ መንገድ እየተራቀቁና ከሀይማኖታዊ ተግባር ባሻገር ቅኔን ለማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችም ጥቅም ላይ መዋል እየጀመረ መጥቱዋል።

የቅኔ ጉባኤዎችና ተከታይ ተማሪዎች እየበዙ በሄዱ መጠን የቅኔ መንገዶች (ቅኔ የሚገለጽባቸው ባህርያት) ከጊዜ ጊዜ፣ ከቦታ ቦታ እየበዙና የበለጠ እየረቀቁ ሄደዋል። የግእዝ ቅኔ መንገዶችን አስመልክቶ የተለያዩ የሙያው ሰዎች በጻፉዋቸው መጻህፍትና ባቀረቡዋቸው ጥናቶች የተለያየ ሀሳብ አቅርበዋል። አንዳንዶቹ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ከፍለው ቁጥራቸውን ከ300 ሲያበልጡዋቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በ3 ታላላቅ ርእሶች ይመድቡዋቸዋል። «መጽሀፈ ታሪክ ወግስ» በተሰኘው መጽሀፍ የሚከተለው ሰፍሩዋል።

> ... እነዚህም በ2 ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላሉ 1ኛው ሰምና ወርቅ ሲባል 2ኛው ጎዳና ይባላል። ይህም መቅለሉንና መክበዱን ለማሳየት እንጅ ሁሉም በሰምና ወርቅ የሚነገር ነው (መምህር አፈወርቅ፡ 1997፡ 41)።

መምህር አፈወርቅ፣ ዋና ዋና መንገዶችን በሁለት ይክፈላቸው እንጅ በተለያየ ጊዜ የተከሰቱት የቅኔ መንገዶች በሽህ የሚቆጠሩ መሆናቸውን ይጠቅስና በጉባኤ የሚነገሩ ከ300 በላይ እንዳሉ ይገልጻሉ። ለምሳሌ ያህልም፣ መንታ ሰረዝ መንገድ፣ አመጻኛ ዳኛ መንገድ፣ ነጠላ ሰረዝ መንገድ፣ ገስግስ መንገድ፣ እርከን መንገድ፣ ሰረገላ መንገድ፣ ሰንሰለት መንገድ፣ ህብር መንገድ፣ ... እያሉ የተለያዩ መንገዶችን ለማስረጃ ያህል በመጽሀፉ ውስጥ ጠቅሰዋል።

ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህም ከመምህር አፈወርቅ ተከሉ ጋር የተቀራረበ ሀሳብ አላቸው። የቅኔ መንገዶች ብዙና ልዩ ልዩ አይነት እንደሆኑ፣ ብዙዎቹ መንገዶች በሁሉም ዘንድ የሚታወቁ እንደሆነና በማስረጃነትም የየመምህራኑ ቅኔ እንደሚጠቀስ ያስረዳሉ። ሆኖም ታላላቆቹ የቅኔ መንገዶች ሁለት

መሆናቸውንና እነሱም በመምህር አፈወርቅ የተጠቀሱት ስምና ወርቅና ኅዳና መሆናቸውን አስፍረዋል፡፡

ከተጠቀሱት ሁለት ዋና ዋና የቅኔ መንገዶች መካከል ለጀማሪ አፍ መፍቻና መቀኛ የሚያደርጉት «ስምና ወርቅ» የተባለውንና እርሱን የመሳሰሉ ቀላል መንገዶችን መሆኑን፣ ቅኔ አዋቂ የተባለ ሰው ግን ኅዳና የተባለውን የቅኔ መንገድ እንደሚጠቀምና የበለጠ በቅኔ ለመራቀቅ ኅዳና የተባለውን መንገድ ማወቅ ተገቢ መሆኑን ይገልጹና በሁለቱ ዋና ዋና የቅኔ መንገዶች ስር ሌሎች የቅኔ መንገዶችን አስፍረዋል፡፡

> በዚህ መልክ የሔድን እንደሆነ የቅኔ መንገድ ዋናው ሁለት ክፍል ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም አንደኛው ስምና ወርቅ የተባለው መንገድ ነው፡፡ በእርሱም ውስጥ፣ ስምና ወርቅ፣ ሀብር ፣ወርቃ ወርቅ፣ ስም ረገፍ፣ ስም ገፊ፣ ጽድቅ፣ ግስ፣.. ይህንንም የመሳሰሉ ክፍሎች የሚገኙበት ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛ የተባለው መንገድ ደግሞ «ኅዳና» ነው፡፡ በእርሱም ውስጥ፣ ውስጠዘ፣ አታላይ፣ እግር ብረት፣ ውስጠ ወይራ፣ አሰናካይ፣ እግር በራስ፣ ሌሎችም ይህን የሚመሳሰሉ ናቸው (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ 1963፡ 208)፡፡

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንደሚሉት ቅኔን በግእዝ ቋንቋዋ ብቻ ሳይሆን በአማርኛ ቋንቋዋም መቀኘት እየተለመደ የመጣ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ሊቃውንት ለታላላቅ ሰዎች ቅኔን ሲሰጡ ከግእዙ ቋንቋዋ ይልቅ ወደ አማርኛው ቋንቋዋ አዘንብለዋል፡፡ እንዳንዶቹ ደግሞ እኩል በእኩል የግእዝና የአማርኛን ቋንቋዋ እየቀላቀሉ እንደሚቀኙት ይህም ራሱን የቻለ መንገድ እንደሆነና መንገዱም ጉራማይሌ ወይም «ፍሩንዱስ» መንገድ እንደሚባል ገልጸዋል፡፡ ይህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ የመጣ አንዱ የቅኔ መንገድ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

መምህር አፈወርቅ ተክሌና ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ስለቅኔ መንገዶች ካስፈሩት የተወሰነ ልዩነት ያለው ሀሳብ የጠቀሱት ዮሀንስ አድማሱ ናቸው፡፡ ዮሀንስ አድማሱ በ1959 ባቀረቡት የመመረቂያ ወረቀት የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> ቅኔ በሦስት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል እነዚህም ሀ/ ስምና ወርቅ ለ/ ብሂል ሐ/ ኅዳና ወይንም መንገድ፡፡ ብሂል በስምና ወርቅ ደንብ ስለማይዘልቅ ስለሚጠቀለል የስምና ወርቅ ዓዝ ነው ይላሉ፡፡ ይኸንንም አስተሳሰብ የሚቀበሉት የቅኔ ሊቃውንት ቅኔን በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፋፍሉታል፡፡ ሀ/ ስምና ወርቅ ለ/ ኅዳና፡፡ ምናልባት ትክክለኛው አከፋፈል ይህ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይሁን እንጅ ለትንታኔ የሚመቸው ብሔል ለብቻው ሲከፈልና ሲጠና ይመስለኛል (ዮሐንስ አድማሱ 1959 19)፡፡

የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎችንና መንገዶችን እስመልክቶ የቀረበው ሀሳብ ትክክለኛነት አረጋግጦ ለማለፍ ስለ ጉዳዩ የሚገልጹ ተጨማሪ ሳይንሳዊ መረጃዎችን ፈልጎ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛዎቹ ስለጉዳዩ እንስተው የጻፉት አባቶች እንድም



ILS LIBRARY

ከየመምህሮቻቸው በአፈ-ታሪክ መልክ በቃል እየተተረከ የተገለጸላቸውን ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ቀድመው ከተጻፉት መጻህፍት ያገኙትን በመገልበጥ የቀረበ በመሆኑ እንዳለ መቀበሉ የማያሳምን ነው።

ተዋነይ በግራኝ ጦርነት ምክንያት ጣና ሀይቅ ውስጥ ወደሚገኘው ደቀ እስጢፋ ገዳም ገብቶ ከቆየ በኋላ የራሱ ብቻ የሆነ አዲስ የቅኔ መንገድ ይዞ ስለመውጣቱና የጎጃም የቅኔ መንገድና ጉባኤ መስራች ስለመሆኑ በጉዳዩ ላይ የጻፉት ሁሉም ይስማሙብታል። ይህንም ሀሳብ ተአማኒ ሊያደርጉ የሚችሉ እራሱ የተቀኛቸውና ስለ እርሱ የቀረቡ ቅኔዎች ማሳያ ሊሆኑ ስለሚችሉ እውነታውን የበለጠ ያጎለዋል። ተዋነይ የጎጃም የቅኔ ጉባኤና መንገድ መስራች እንደሆነ ለማረጋገጥ አስቸጋሪነቱ የቀለለ ቢሆንም ከዋሸራ ጉባኤ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ግን የሚያመላክት በቂ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም።

አንዳንድ ጸሀፊዎች የዋሸራ የቅኔ ጉባኤና መንገድ ከጎንጅ የቅኔ ጉባኤና መንገድ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰዋል። ሁለቱ ጉባኤዎች ጎጃም ውስጥ ያሉ ከመሆናቸው ያለፈ ስለግንኙነታቸውና ልዩነታቸውን የሚያስረዳ በቂ መረጃ ማግኘት ግን አልተቻለም። አንዳንዶቹ የዋሸራን ጉባኤ ከጎንጅ ይልቅ ከዋድላ ጉባኤ ጋር የበለጠ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ከሚከተሉት የቅኔ መንገድና የማስተማር ስልት አኩዋያ እየጠቀሱ ሀሳባቸውን አቅርበዋል። እንደተባለው በሁለት የቅኔ ጉባኤዎች መካከል ከቅኔ ትምህርት አሰጣጥና ከአገባብ ትምህርት አቀራረብ አኳያ ልዩነት ያለ መሆኑን በተለያየ ጊዜ በሁለቱ ጉባኤዎች ይቀርቡ ከነበሩ ቅኔዎች እንረዳለን (የግእዝ ቅኔያት፤ 1980፤367-419 ተመልከት)።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ሊቃውንት የድድቆችን የቅኔ መንገድ ከጎንጅ የቅኔ መንገድና አቀራረብ ጋር ተቀራራቢና ተያያዥ እንደሆነ አድርገው የሚጽፉ አሉ። ብዙዎቹ ደግሞ የዋድላ ቅኔ ጉባኤ መስራች ድድቅ ወልደ ማርያም መሆኑን ጠቅሰዋል። ከዚህ እንጻር፣ የዋድላ ጉባኤን መስራች በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦች የሚነሱ በመሆናቸው መደምደሚያ ማስቀመጥ ያስቸግራል።

አንዳንድ ምሁራን የዋድላ የቅኔ ጉባኤ መሰረቱ ዮሀንስ ገብላዊ መሆኑን በድፍረት የሚገልጹ እንዳሉ ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ጉባኤ መስራች ድድቅ ወልደ ማርያም መሆኑንም ብዙዎቹ ይስማሙብታል።

ከዚህ አኳያ ሲመረመር ተዋነይን የጎጃም የቅኔ ጉባኤና መንገድ መስራች እንደሆነ ደፍሮ ለመናገር የሚያስችል መሰረት ቢኖርም የዋድላ ጉባኤና መንገድ መስራች እከሌ ነው ብሎ በእርግጠኝነት ለመጥቀስ ጉዳዩን የበለጠ ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎችን ፈልጎ ማግኘት ተገቢ እንደሆነ ያመለክታል። በአጠቃላይ የቅኔ ጉባኤዎችንና መንገዶችን አጀማመርና አመሰራረት እንዲሁም የመስራቾችን ማንነት በትክክል ለማረጋገጥ የግእዝ ቅኔን አጀማመርና አመጣጥ ታሪክ በጥልቀት አጥንቶ እውነታውን ማግኘት ትልቁ ስራ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

## 3.2 የቅኔ አይነቶች

ስለ ግእዝ ቅኔ አይነቶችና ትርጉማቸው የተለያዩ ሊቃውንት በዝርዝር ጽፈዋል። ርእስ ነገሩን አስመልክቶ የጻፉት አባቶች ሁሉ አቀራረባቸው በአመዛኙ ተቀራራቢ ነው። አልፎ አልፎ የሚስተዋለውም ልዩነት በስያሜ አሰጣጥና በአቀራረብ ቅደም ተከተል ላይ እንጂ በይዘት ረገድ አይደለም። ርእስ ነገሩን አስመልክቶ ብዙ ምሁራን የጻፉ ቢሆንም የተወሰኑትን መጥቀሱ ተገቢ ነው። ከብዙዎቹ በጥቂቱ መምህር ይኄይስ ወርቁ፣ አለማየሁ ሞገስ፣ ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፣ ዜና ማርቆስ እንዳለውና መምህር አፈወርቅ ተክሌ ተጠቃሽ ናቸው። የተጻፉትን መርምሮ የተሻለውን ለማግኘትና ለመረዳት ያግዝ ዘንድ የተወሰኑ ምሁራን ስለ ርእስ ጉዳዩ ያሰፈሩትን የቅኔ አይነቶች መመልከቱ ተገቢ ነው። የግእዝን ቅኔ አይነቶች በተለያየ መንገድ ከዘረዘሩት ምሁራን መካከል የሚከተሉት የተወሰኑት ናቸው።

... የግዕዝ ቅኔ በ17 ክፍል የተከፈለ ስም አለው።

1. ግዕዝ ጉባኤ ቃና ቅኔ
2. ዕዝል ጉባኤ ቃና ቅኔ
3. ዘ አምላኪየ ቅኔ
4. ሚ በዝኑ ቅኔ
5. ዋዜማ ቅኔ በ3 ክፍል የተመደበ
6. ስላሴ ቅኔ በ2 ክፍል የተመደበ
7. ዘ ይዕዜ ቅኔ በ3 ክፍል የተመደበ
8. መወድስ ቅኔ
9. ኩል ክሙ ቅኔ በ2 ክፍል የተመደበ
10. ግዕዝ ክብር ይእቲ ቅኔ
11. አራራይ ዕጣነ ሞገር ቅኔ
12. አራራይ ዐሠረ ነጋሢ ቅኔ
13. ዕዝል ክብር ይእቲ ቅኔ
14. ዕዝል ዕጣነ ሞገር ቅኔ
15. ዕዝል ዐሠረ ነጋሢ ቅኔ
16. አራራይ ክብር ይእቲ ሐዋርያቲሁ ክበበ
17. አራራይ እጣነ ሞገር ሕንጺሃ»

(መምህር ይኄይስ ወርቁ 1960:8)።

.... የቅኔ ዜማ ዐይነትና ክፍል፤

1. ግዕዝና እዝል ጉባኤ ቃና
2. ዘ አምላኪየ
3. ሚ በዝኑ
4. ዋዜማ
5. እጭር ዋዜማ

6. ሥላሴ
7. ዘ ይእዜ
8. ሣህልከ
9. መወድስ
10. ኵልክሙ
11. አጭር ኵልክሙ
12. ሕንጺሃ
13. ግዕዝ ክብር ይእቲ
14. እዝል ክብር ይእቲ
15. ግዕዝ ዕጣነ ሞገር
16. እዝል ዕጣነ ሞገር፤

(ዓለማየሁ ሞገስ 1950፡132-133)፡፡

...እንኳን ለቅኔው ለሌላው መዝሙር፣ ግጥም ወይም ዘፈን ይህንንም ለመሰለው ሁሉ ቤት አለው፣ ቤትም ይመታል፤ ቤት ይገጥማል ይባላል፡፡ ይኸንም ለማስረዳት የቅኔውን ሁሉ ቤት ለቅመው ደምረው 78 እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እርሱም እንደሚከተለው ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ጉባኤ ቃና | 2 |
| 2. | ዘአምላኪየ | 3 |
| 3. | ሚበዝኍ | 3 |
| 4. | ዋዜማ | 5 |
| 5. | አጭር ዋዜማ | 2 |
| 6. | ሥላሴ | 6 |
| 7. | ዘይእዜ | 5 |
| 8. | አጭር ዘይእዜ | 2 |
| 9. | ሣህልከ | 3 |
| 10. | ፍታሕ ሊታ | 8 |
| 11. | ኵልክሙ | 9 |
| 12. | ሕንጺሃ | 2 |
| 13. | ሐዋርያቲሁ ክበበ | 2 |
| 14. | ግዕዝ ክብር ይእቲ | 4 |
| 15. | ዕዝል ክብር ይእቲ | 4 |
| 16. | ግዕዝ እጣነ ሞገር | 7 |
| 17. | ዕዝል እጣነ ሞገር | 11 |

ድምር 78 ይሆና፤ የዚህንም ድምር እርግጠኛነት ለማስረዳት በቅኔ ተገልጿል (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ 1963፡180-181 ተመልከት)፡፡

... የቅኔ መስመር በሀረግ ይከፈላል፤ ሀረግ በስንኝ ይከፈላል (ይመደባል)፤ ቅኔው ደግሞ በሚዜምበት የዜማ አይነት መሰረት ግዕዝ፣ እዝልና አራራይ ቅኔ ተብሎ ይለያል፡፡ ዋናዎቹ የቅኔ አይነቶች ከሀረግና ከቤታቸው ቁጥር ጋር ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡ የዝርዝራቸውም ቅደም ተከተል በቅኔ ትምህርት ቤቶች ደረጃ በደረጃ በትምህርትነት በሚቀርብበት ተርታ ነው፡፡



...SITY ...IS LIBRARY

| የቅኔው ስም | የሀረጉና የቤቱ ልክ | |
|---|---|---|
| 1. ግዕዝ ጉባኤ ቃና | 4 | 2 |
| 2. ዕዝል ጉባኤ ቃና | 4 | 2 |
| 3. ዘአምላኪየ | 5 | 3 |
| 4. ሚበዝኁ | 8 | 3 |
| 5. ዋዜማ | 9 | 5 |
| 6. ሥላሴ | 11 | 6 |
| 7. ዘይእዜ | 11 | 5 |
| 8. አጭር ዘይእዜ | 4 | 2 |
| 9. ሣህለክ | 7 | 3 |
| 10. መወድስ | 18 | 8 |
| 11. ኩልኩሙ (መወድስ) | 20 | 9 |
| 12. ግዕዝ ክብር ይእቲ | 8 | 4 |
| 13. ዕዝል ክብር ይእቲ | 8 | 4 |
| 14. ግዕዝ እጣነ ሞገር | 18 | 7 |
| 15. ዕዝል እጣነ ሞገር | 18 | 11 |
| 16. ሐዋርያቲሁ ክበበ | 4 | 2 |
| 17. ሕንጼሃ | 3 | 2 |

ድምር 160 ሀረጎች፣ 78 ቤቶች፡፡ የቅኔ ቤቶች ጠቅላላ ድምር 78 ነው፡፡ እላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ባለ ሶስት ቤት አጭር ዋዜማ፣ ባለ ሁለትቤት አጭር ዋዜማ፣ እንዲሁም ባለ ሁለት ቤት አጭር ኩልክሙ አሉ፡፡ ቢኖሩም ከላይ ከተጠቀሱት መደበኛ የቅኔ አይነቶች ይጠቃለላሉ እንጅ በተለየ አይቆጠሩም (አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፣ 1980:23)

ከላይ የተጠቀሱት የሙያው ሊቃውንት የቅኔ አይነቶችን በዘረዘሩበት ጊዜ አብዛኛዎቹ የቅኔዎቹ ቤቶች ድምር 78 እንዲሆኑ አስበው የዘረዘሩዋቸው ይመስላል፡፡ አንድ የቀድሞ የቅኔ ሊቅ የግእዝ ቅኔ ቤቶች ጠቅላላ ድምር 78 መሆናቸውን ጠቅሰው የተቀኙ በመሆኑ (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ 1963፡180) ከጥንታዊው የቅኔ ምሁር ጥቅስ ላለመራቅ ጥረት ሲደረግ ይስተዋላል፡፡

አንዳንዶቹ የዘይእዜን ቅኔ አጭርና ረጅም በማለት በቅኔ አይነቶች ዝርዝር ውስጥ ሲያካትቱ የዋዜማን ቅኔ ግን አጭርና ረጅም ብለው በዝርዝሩ ውስጥ አያስገቡም፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የእጣነ ሞገርና የክብር ይእቲን ቅኔ እዝልና ግእዝ በማለት ከፋፍለው በቅኔ አይነቶች ዝርዝር ውስጥ ሲያካትቱ፣ የጉባኤ ቃናን ቅኔ ግን እዝልና ግእዝ በማለት በዝርዝሩ ውስጥ አላካተቱም፡፡ ከአቀራረባቸው መረዳት እንደተቻለው አብዛኛዎቹ ስለ ጉዳዩ የጻፉ ሊቃውንት ትኩረት ያደረጉት የቅኔዎቹ ቤቶች ድምር 78 እንዲሆን ተጠንቅቀ እንጂ ሁሉንም የቅኔ አይነቶች ወጥ በሆነ አቀራረብ ሲዘረዝሩ አይታዩም፡፡ ጥንቃቂያቸውም የቅኔ ቤቶቹ ድምር 78 ከመሆኑ ላይ ይመስላል፡፡

ለማስረጃ ያህል አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ «የግእዝ ቅንያት» በተሰኘው መጽሀፍ መቅድም ውስጥ የቅኔ አይነቶችን አስመልክቶ የዘረዘሩትን ብንመለከት፣ የዘይእዜን ቅኔ አጭርና ረጅም በማለት በቅኔ አይነቶች ውስጥ ሲዘረዝሩ፣ የዋዜማን ቅኔ ግን አንዱን ብቻ ጠቅሰው አልፈውታል። ሀብተ ማርያም ወርቅነህ በበኩላቸው የጉባኤ ቃናን ቅኔ እዝልና ግእዙን ለያይተው ሳያሳዩ፣ እጣነ ሞገርና ክብር ይእቲ ቅኔን እዝልና ግእዝ በማለት በሁለት በሁለት ከፋፍለው ዘርዝረዋቸዋል። በሌላም በኩል ሲታይ አለቃ አፈወርቅ ዘይእዜንም ዋዜማንም ረጅምና አጭር በማለት በሁለት በሁለት ከፋፍለው ሲመድቡዋቸው፣ ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ግን ዘይእዜን ብቻ በሁለት ከፍለው ዋዜማን ግን ሳይከፋፍሉ ትተውታል።

ከተገለጸው ልዩነታቸው ባሻገር ሁለቱን ጸሀፊዎች የሚያመሳስላቸው የሁሉም ቅኔ አይነቶች ቤት ድምር 78 እንዲሆን ማድረጋቸው ነው። ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የቅኔ አይነቶችን የዘረዘሩት የሙያው ሊቃውንት ሁሉንም የቅኔ አይነቶች በዝርዝር ከማሳየት ይልቅ የቅኔዎቹ ቤቶች ድምር 78 እንዲሆንና የቀድሞው የቅኔ ምሁር ስለቅኔ ቤቶች ቁጥር ጠቅሰው የተቀኙት ቅኔ እንዳይፋለስ ጥንቃቄ ያደረጉ መሆኑን ያስረዳል።

የተጠቀሱትን የቅኔ አይነቶች የበለጠ ለመረዳት የእያንዳንዱን የቅኔ አይነት፣ ትርጉዋሜ፣ ቅርጽና ይዘት እንዲሁም ታሪኩን፣ ንባቡን፣ ትርጉሙን፣ ፍችውን፣ ሙያውንና ርቀቱን በምሳሌ እያጣቀሱ ማየቱ ተገቢ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ለመነሻ ያህል በሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ በአለማየሁ ሞገስ፣ በአድማሱ ጀንበሬ፣ በመምህር ይሄይስ ወርቁና በዜና ማርቆስ እንዳለው መጻህፍት ውስጥ የተጠቀሱት ሀሳቦች መነሻ እንዲሆኑ ተደርጉዋል።

## 1. ጉባኤ ቃና

ከዋና ዋና የቅኔ አይነቶች አንዱ ጉባኤ ቃና ነው። ትርጉሙም የቅኔ ትምህርት ተሳካ፣ ተዋጣለት ጉባኤው ተቃና፣ ተጀመረ ማለት እንደሆነ የሚጠቅሱ አሉ። በሌላም በኩል የቅኔው ሁሉ መግቢያ መቃኛ ማለት እንደሆነም ይገልጻሉ። ጉባኤ ቃና ሁለት ቤት ሲሆን ዜማው ግን አጭርና ረጅም እየተባለ ወደ 5 አይነት ይደርሳል። በሌላም በኩል እዝል፣ ግእዝ፣ አጭርና ረጅም ጉባኤ ቃና የተሰኘ መጠሪያም አለው። ረጅም ጉባኤ ቃና የተባለው ሀረጉ ረጅም ሲሆን አጭር ጉባኤ ቃና ግን ሀረጉ ያጠረ ነው።

ይህም የቅኔ አይነት በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ የሚቀርበው፣ መወድስ በሚደረስበት ጊዜ «እምላኪየ እምላኪየ እገይስ ሀቤከ» ተብሎ ከሌሎች ቅኔዎች በፊት ነው። ስብሀተ ነግህ በተቆመ ጊዜ ረቡዕና አርብ ሲሆን እዝል ይሆናል። በአቢይ ጾም ጊዜ ግን ግእዝ ብቻ ይሆናል። በቅኔ ትምህርት ስርአት ውስጥም የአፍ መፍቻና የስልት መልመጃ ሆኖ ቀድሞ ለጀማሪዎች የሚቀርብ ነው። ቤቱ ሁለት በመሆኑ ለቅኔ

ትምህርት ጀማሪዎች በቀላሉ ቤቱን ገጥሞ፣ ሙያውን ቆጥሮና አሳክቶ ለመቀኘት ይረዳቸዋል።

ምሳሌ

ሀ. የቅኔ መነሻ ታሪክ

በድሮው ዘመን የግብጽ ንጉስ ፈርኦን እስራኤላውያንን ውሀ እያስቀዳና ጭቃ እያስቦካ ለብዙ ዘመናት ሲገዛቸው ኖሩዋል። ከዚህ ግፍ ለማምለጥ እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት ሸሽተው ሲሄዱ የኤርትራ ባህር ተከፍሎ በሰላም ተሻግረዋል። ፈርኦንም እነሱን እይዛለሁ ብሎ ሰራዊቱን አስከትሎ በፈረስ እያስገረ ሲደርስ ተከፍሎ የነበረው ባህር እንደገና ተገጥሞ ከነሰራዊቱና ከነፈረሱ አብሮ ሰጠመ፣ ቀጥሎ ለቀረበው ጉባኤ ቃና ቅኔ መነሻ ይህ ታሪክ ነው።

ለ. የቅኔው ንባብ

ኢይተርፍ ግፍእ ለዘእድሜሁ ኀንደየ፣

እስራኤል ለፈርኦን እስመ አጸርዎ ማየ።

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ ቃላት ትርጉም

ኢይተርፍ ⟶ አይቀርም

ግፍእ ⟶ ግፍ

ለ በቁሙ

ዘ ⟶ የ

እደሜሁ ⟶ እድሜው

ኀንደየ ⟶ ዘገየ

እስራኤል ⟶ የነገድ ስም

ለ ⟶ በቁሙ

ፈርኦን ⟶ የግብጽ ንጉስ

እስመ ⟶ እና፣ ስለ

አጸርዎ ⟶ አሸከሙት

ማየ ⟶ ውሀን

መ. የቅኔው ፍች

እድሜው ለዘገየ ሰው ግፍ አይቀርም፣

እስራኤሎች ፈርኦንን ውሀ አሸከመውታልና።

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

ኢይተርፍ ⟶ ማሰሪያ አንቀጽ

ግፍእ ⟶ የቅኔ (የአረፍተ ነገር ባለቤት)

ለ ⟶ አገባብ ፍችው በቁሙ ቀሪ፣ ሙያው አቀባይ

ዘ ⟶ አገባብ ፍችው ያ ሙያው በቂ ሆኖ የአቀባይ ባለቤት

እድሜ ⟶ የቅጽል ባለቤት

ጎንደየ ⟶ ያስር ነበር ዘ ወድቆ እስቀርቶታል

እስራኤል ⟶ የአስረጅ ባለቤት

ለ ⟶ አገባብ ፍችውን ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለአጸርም

ፈርኦን ⟶ የተጠቃሹ ባለቤት

እስመ ⟶ አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኢይተርፍ

አጸርም ⟶ ያስር ነበር እስመ ወድቆ እስቀርቶታል

ማየ ⟶ ተሳቢ፣ ታሳቢነቱ ለአጸርም

ረ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ፡ ግፍ አይቀርም፣ ውሀ ሲያስቀዱዋቸው የነበሩትን ሰዎች ሌሎቹ በተራቸው ውሀ አስቀድተዋቸዋልና

ወርቁ፡ እስራኤሎች ፈርኦንን ውሀ አሸከሙት ማለት ሸሽተው ሲሄዱ ፈርኦን ከነፈረሱ በነሱ ምክንያት ባህር ውስጥ መስጠሙን ለመናገር ነው፡፡ ከዚህ ላይ ባለቅኔው ለማሳሰብ የፈለገው ግፍ ሚዋልበት ሰው ሁሉ ብድሩን እንደማያጣ ግፍ የሚሰራ ሰው ደግሞ ተመልሶ በራሱ ላይ እንደሚውል ያሳስባል፡፡

## 2. ዘ አምላኪየ

ዘ አምላኪየ የተባለው ቅኔ ቤቱ 3 ነው፡፡ ይኸውም የስላሴ ምሳሌ ነው፡፡ መካከለኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል፡፡ ዜማው ግን ሁል ጊዜ እዝል ብቻ ሆኖ የሚዜመውም በዝማሜ ብቻ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያንም የሚቀርበው በአቢይ ጾም፣ መወድስ ሲቆምና በስብሀተ ነግህ አደራረስ ጊዜ በተለይም ሰኞ፣ ማክሰኞና ሀሙስ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ስሙም ዘ አምላኪየ የተባለበት ምክንያት የቅኔው መጀመሪያ «አምላኪየ አምላኪየ አገይስ ሀቤከ» የሚለው የዳዊት መዝሙር እየተዘመረ ስለሚቀርብ ነው፡፡

ምሳሌ

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

የቅኔው መነሻ ታሪክ የወርሀ ክረምት ወቅት ነው፡፡ በክረምት ወቅት የሚስተዋሉ ነገሮች ላይ ነው የሚያተኩረው

ለ. የቅኔው ንባብ

ምንተ ኮነ በአውደ ክረምት እግዚኡ፣
ገብር ደመና ዘጸሊም መልክኡ፣
እኮኑ ይስህቅ እስከ ይወርድ አንብኡ።

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ የግእዝ ቃላት ትርጉም

ምንት ⟶ ምን
ኮነ ሆነ
በ ⟶ በቁሙ
አውድ ⟶ አደባባይ
ክረምት ⟶ በቁሙ
እግዚኡ ⟶ ጌታው
ገብር ⟶ አገልጋይ
ዘ ⟶ የ
ጸሊም ⟶ ጠቁዋራ፣ የጠቆረ
መልክኡ ⟶ መልኩ
እኮኑ ⟶ እና፣ ስለ
ይስህቅ ⟶ ይስቃል
እስከ ⟶ ድረስ
ይወርድ ⟶ ይወርዳል (እስኪወርድ)
አንብኡ ⟶ እንባው

መ. የቅኔው ፍች

መልኩ የጠቆረ አገልጋይ ደመና በጌታው ክረምት አደባባይ ምን ሆነ? ምን ነካው? እንባው እስኪረግፍ ይስቃልና።

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

ምንተ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኮነ
ኮነ ⟶ ማሰሪያ አንቀጽ፣ ይስባል እንጂ አይሳብም
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
አውድ ⟶ የማድረጊያ ባለቤት
እግዚኡ ክረምት ⟶ ምሳሌ እግዚኡ ስም፣ ክረምት ወርቅ፣ ተመስሎ የቅኔ (አረፍተነገር) ባለቤት
ዘ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለገብር ደመና
ጸሊም ⟶ ውስጠ ዘ ሆኖ ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል
መልክኡ ⟶ የቅጽል ባለቤት
እኮኑ ⟶ አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኮነ
ይስህቅ ⟶ ያስር ነበር እኮኑ ወድቆ አስቀርቶታል

እስከ ⟶ አገባብ ፍችው ድረስ ሙያው መድረሻ
ይወርድ⟶ ያስር ነበር እስከ ወድቆ አስቀርቶታል
እንበኡ⟶ የመድረሻ ባለቤት

ረ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ፡ ዛሬ ይኽ ጠቋዋሪ አገልጋይ ምን ነካው? ምንስ ሆነ?

በጌታው ፊት እንባው እስኪረግፍ ይስቃልና፡፡

ወርቁ፡ ዝናብ በደመና አማካኝነት መዝነቡን ለመናገር ነው፡፡

ይስቃል ማለትም ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ሰማዩ ብልጭ ድርግም ማለቱን ለመናገር ነው፡፡

**3.** ሚ. በዝሁ

ሚ. በዝሁ ቅኔ ቤቱ 3 ነው፡፡ ሶስትነቱ እንደ ዘ አምላኪዬ ሁሉ የስላሴዎች ምሳሌ ነው፡፡ ከጉባኤ ቃና በስተቀር ሌላው ቅኔ ሁሉ መንደርደሪያ አለው፡፡ የሚ. በዝሁ ቅኔ ሁለተኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል፡፡ ዜማው ሁልጊዜ ግእዝ ነው፡፡ ሚ. በዝሁ የተባለበትም ምክንያት «እግዚኦ ሚ. በዝሁ እለ ይሳቀዩኒ» ከተባለው የዳዊት መዝሙር የሚነሳ ስለሆነ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያንም የሚቀርበው እሁድ ሁልጊዜ፣ በአቢይ ጾምና መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ነው፡፡ አደራረስ በሚደረስበት ጊዜ ከዘ አምላኪየ ጋር እየተፈራረቀ የሚቀርብ የቅኔ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

የቅኔው ታሪክ የሚያተኩረው ስለጌታ ስጋ መልበስና ሞቶ መነሳት ታሪክ ላይ ነው፡፡

ለ. የቅኔው ንባብ

ሀሜተ ክልኤቱ እህው ዘኢፈርሀ ወልድ በልአ በተከብቶ፣
ስጋ ጥኡመ እንዘ የአጹ ሆሁቶ፣
ወፍሉጠ ሞት ኮነ ባህቲቶ ዘበልአ እስመ ይመውት ባህቲቶ፡፡

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ የግእዝ ቃላት ትርጉም፡፡

ሀሜት ⟶ አሜት
ክልኤቱ ⟶ ሁለት
እህው ⟶ ወንድማማቾች
ዘ ⟶ የ

ኢፈርሀ ⟶ ያልፈራ
ወልድ ⟶ ልጅ
በልአ ⟶ በላ
በ ⟶ በቁሙ
ተከብቶ ⟶ መደበቅ፣ መሸሸግ
ስጋ ⟶ በቁሙ
ጥዑም ⟶ ጣፋጭ
የአጼ ⟶ ይዘጋል
ሆህቶ ⟶ በሩን
እንዘ ⟶ እየ (አፍዛዥ)
ፍሉጥ ⟶ የተለየ
ሞት ⟶ በቁም
ባህቲቶ ⟶ ብቻውን
እስመ ⟶ እና፣ ስለ
ይመውት ⟶ ይሞታል።

መ. የቅኔው ፍች

የሁለቱን ወንድማማቾች ሀሜት ያልፈራ ልጅ በሩን ዘግቶ ብቻውን ጣፋጭ ስጋ በላ። ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል እና በሞትም የተለየ ሆነ።

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

ሀሜት ⟶ ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለኢፈርሀ
ክልኤቱ ⟶ ቅጽል፣ ቀጽልነቱ ለአህው
አህው ⟶ የሀሜት ዘርፍ
ዘ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለወልድ
ኢ. ⟶ አገባብ ፍችው አል (ያል) ሙያው አፍራሽ
ኢፈርሀ ⟶ ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል
ወልድ ⟶ የቅኔ (የአረፍተ ነገር) ባለቤት
በልአ ⟶ ማሰሪያ አንቀጽ፣ ይስባል እንጅ አይሳብም
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
ተከብቶ ⟶ የማድረጊያ ባለቤት
ስጋ ⟶ ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለበልአ
ጥዑም ⟶ ቀጽል፣ ቀጽልነቱ ለስጋ

እንዘ ⟶ አገባብ ፍችው እየ (ችልታ) አፍዛኝ
ሙያው ማንጸሪያ

የአጹ ⟶ ያስር ነበር እንዘ ወድቆ አስቀርቶታል

ሆህት ⟶ ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለየአጹ

ወ ⟶ አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ

ፍሉጥ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኮነ

ሞት ⟶ የፍሉጥ ዘርፍ

ኮነ ⟶ በዋዊ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ

ባህቲቶ ⟶ ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለበልአ

ዘ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው በቂ ሆኖ
የአስረጅ ባለቤት

በልአ ⟶ ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል

እስመ ⟶ አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ
አስረጅነቱ ለኮነ

ይመውት ⟶ ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል

ባህቲቶ ⟶ ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለይመውት

ረ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ: ሀሜት የማይፈራ ሰው ቤቱን ዘግቶ ያረደውን ሥጋ ብቻውን በላ፡፡ በደህና ጊዜ ጎረቤትና ወገን የማይወድ ሰው የሚመጣውን መከራ ሁሉ ለብቻው ይቀበላል፡፡ ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል እንደተባለው፡፡

ወርቁ: ሁለት ወንድማማቾች የተባሉት አብና መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ስጋ ለብሷል፡፡ ማለትም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ስጋ ስለለበሰ በሞትም ጊዜ ብቻኛ ሆነ ብቻውንም ሞተ ማለት ነው፡፡ ባለቅኔው የሚያስተምረን ጌታ በለበሰው ስጋ ጸዋትወ መከራን መቀበሉን ነው፡፡

## 3. ዋዜማ

ዋዜማ ቅኔ ባለ 5 እና ባለ 2 ቤት ሲሆን ዜማውም አራራይ ነው፡፡ ምሳሌነቱ ረጅም ዋዜማ የ5ቱ አእማደ ምስጢራት ምሳሌ ሲሆን አጭር ዋዜማ ደግሞ የተስብእትና የመለኮት ምሳሌ ነው፡፡ ዋዜማ ማለት ብዙ ጊዜ በየበአላቱ ዋዜማ የሚደረስ ቅኔ ስለሆነ በዚያው ስም ዋዜማ ተብሎ ተጠርቱዋል፡፡ ረጅም ዋዜማ በበአላት ዋዜማ (ከበአሉ አንድ ቀን ቀድሞ) ሶስት የዋዜማ ቅኔዎች

ይቀርባሉ፡፡ አጭሩ ዋዜማ ግን በቅኔው መንገድ ቦታውን ስለያዘ ብቻ ዋዜማ አሉት እንጅ የሚቀርበው በመወድስ አደራረስ ጊዜ ነው፡፡ ከእርሱም በፊት የሚዘመረው የዳዊት መዝሙር «ለእግዚአብሔር ምድር በምልአ፣ እግዚአብሔር ነግሰ» የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት እንደ ሌሎቹ ቅኔዎች የዳዊትን መዝሙር ወይም መነሻ አልተከተለም ስሙንም አልያዘም ዋዜማ በእርያም አደራረስ ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ነግሰና በእግዚኦ ጸራህኩሙ ጊዜ ይቀርባል፡፡

ምሳሌ

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

በአንድ ቤተ ክርስቲያን አንድ የደብር አለቃ ተሹሞ ሳለ በላዩ ላይ አዲስ አለቃ ተሹሞ ይመጣበታል፡፡ አዲሱም ሹም መልአከ በሚል ስም ይታወቃል፡፡ በእድሜና በአካልም ገዝፎ ይታይ ነበር ይባላል፡፡ ብዙውን ጊዜ ነባር የቤተክርስቲያን አለቆች በላያቸው ላይ ሌላ አለቃ ሲሾምባቸው አይወዱም፡፡ ደስም አይላቸውም፡፡ ስለዚህ ቀደም ብሎ የነበረው የደብር አለቃ አዲሱን የደብር ሹም በሚከተለው ቅኔ ይተቸዋል፡፡ የቅኔውም መነሻ ይህ ነው፡፡

ለ. የቅኔው ንባብ

ለመልአከ ኢናከብሮ፣
ለእመ አስረጸ ክንፈ በመጠነ ነዊህ ቆሙ፣
ለኦፍ ወለትንንያ እስመ ክንፍ ቦሙ፣
ወበሲበቱ ለሰብእ ኢናከብሮ ቀዲሙ.
ጸአዳ ሲበት እስመ ሀለዎሙ፣
ለእጸው ወአእባን ኩሎሙ፡፡

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ ቃላት ትርጉም

ለ ⟶ ን
መልአከ ⟶ በቁም
ኢናከብሮ ⟶ አናከብረውም
እመ ⟶ ቢ
አስረጸ ⟶ አበቀለ
ክንፍ ⟶ በቁሙ ልክ
ነዊህ ⟶ ረጅም
ቆሙ ⟶ ቁመቱ
ለ ⟶ በቁሙ

ኦፍ → ወፍ
ወ → እና
ትንንያ → ትንኝ
በሙ → አላቸው
ሲበት → ሽበት
ሰብአ → ሰው
ቀዲሙ → አስቀድሞ
ጸአዳ → ነጭ
ሀለዎሙ → አላቸው
እጸው → እንጨቶች
አእባን → ድንጋዮች
ኵሎሙ → ሁሉም

### መ. የቅኔው ፍች

በቁመቱ ልክ ክንፍ ቢያበቅል መልአክን አናከብረውም፡፡ ክንፍስ ለወፍና ለትንኝም አላቸውና፡፡ ሰውንም በሽበቱ አስቀድመን አናከብረውም ነጭ ሽበትማ ለእጽዋትና ለድንጋዮች ሁሉ አላቸውና፡፡

### ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

ለ → አገባብ ፍችው ን ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለኢናክብሮ
መልአክ → የተጠቃሽ ባለቤት
ኢናክብሮ → ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጅ አይሳብም
ለ → አዳማቂ ትርጉም የለሽ
እመ → አገባብ ፍችው ቢ. ሙያው ማንጸሪያ
አስረጸ → ያስር ነበር እመ ወድቆ አስቀርቶታል
ክንፍ → ተሳቢ፣ ተሳቢነቱ ለአስረጸ፡፡
በ → ያለው አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
መጠን → የማድረጊያ ባለቤት
ነዊህ → ቅጽል ቅጽልነቱ ለቆሙ
ቆሙ → የመጠን ዘርፍ
ለ → አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ
ኦፍ ትንንያ → በወ ተጫፍረው የአቀባይ ባለቤት
ወ → አገባብ ፍችው እና ሙያው አጫፋሪ

| | | |
|---|---|---|
| እስመ | | አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኢናክብር |
| ክንፍ | ⟶ | የአስረጅ ባለቤት |
| ቦሙ | ⟶ | ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል |
| ወ | | አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ |
| በ | ⟶ | የአገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ |
| ሲበት | ⟶ | የማድረጊያ ባለቤት |
| ለ | ⟶ | አገባብ ፍችው ን ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለኢናክብር |
| ሰብእ | ⟶ | የተጠቃሽ ባለቤት |
| ኢናክብሮ | ⟶ | በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ |
| ቀዲሙ | | አንቀጽ አጎላማሽ |
| ጸአዳ | ⟶ | ቅጽል፣ ቅጽልነቱ ለሲበት |
| ሲበት | ⟶ | የአስረጅ ባለቤት |
| እስመ | ⟶ | አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኢናክብሮ |
| ሀለምሙ | ⟶ | ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል |
| ለ | ⟶ | አገባብ ፍችው በቁምቀሪ ሙያው አቀባይ |
| እጸው አእባን | | በ ወ ተጫፍረው የአቀባይ ባለቤት |
| ወ | ⟶ | አገባብ ፍችው እና ሙያው አጫፋሪ |
| ኩሎሙ | ⟶ | ቅጽል፣ ቅጽልነቱ ለእጸውና ለአእባን |

ሠ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ: መልአክን በቁመቱ ልክ ክንፍ አለው ብለን አናከብረውም። ክንፍማ ለወፍና ለትንኞችም አላቸውና። ሰውንም ቢሆን ሽበት አለው ብለን አስቀድመን አናከብረውም፣ ሽበትማ ለእንጨቶችና ለድንጋዮችም አላቸውና።

ወርቁ: ቀደም ብሎ በደብር አለቃነት ተሾሞ የቆየው ሰውዬ አዲስ የመጣው አለቃ በእንጀራው ላይ ስለመጣበት ማጥላላቱ ነው። ምንም እንኳ በኋላ የመጣው አለቃ አምሮና ጠምጥሞ ቢታይም በችሎታው ይህን ያህል አልነበረም በእውቀቱ ደካማ ነው ለማለት ነው።

## 5. ስላሴ

ስላሴ ቅኔ ቤቱ ስድስት ሲሆን ምላሴነቱም የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ነው። መንደርደሪያና መጽፊያ አለው። ዜማው ሁልጊዜ እዝል ነው። ቅኔውም የአበው

(ሽማግሌዎች) ቅኔ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ለአዋቂዎችና ለታላላቅ ሰዎች ነው፡፡ የስላሴ ቅኔ የሚቀርበው በዋዜማ ክስተትና አርያም አደራረስ፣ በጸሎተ ሰለስቱ ደቂቅና በይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ ጊዜ ሰብሀም በሚለው መዝሙር ነው፡፡ ስላሴ የተባለበትም ምክንያት «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ» በሚለው በጸሎተ ሰለስቱ ደቂቅ ድርሰት እየገባ የሚነገር ስለሆነ አምላከ አብርሀም፣ አምላከ ይስሀቅ፣ አምላከ ያእቆብ እያሉ ሶስትነትን የሚገልጸውን እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ስላሴ የሚለው ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

ምሳሌ

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

የቅኔው ታሪክ የሚያጠነጥነው ጌታችን መድሀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በ5 ችንካሮች የቸነከሩት መሆኑን የሚዘክር ነው፡፡ የታሪኩም መነሻ ይህ የጌታችን የስቀለት ታሪክ ነው፡፡

ለ. የቅኔው ንባብ

ወልድ ፈደለ አልፋ!
ላእሌሁ ለእጽ እመ ተሰፍሀ
ህማማተ ስጋ ደቂቅ ከመ ኪያሁ ያንብቡ፣
ሳእረ ቀኖተ ሀጺን ነሲእሙ ቀርቡ፣
ለመምህርሙ ትጉህ ይሁዳ እንተ ፈድፈደ ጥበቡ፣
ሰላሳ ብሩር አምጣነ አስቡ፣
ወጽህፈተ ዝንቱ ፊደል በማይ ህጸቡ፣
እስመ ሆረ ውስተ ደይን ምስካቡ፡፡

ሐ. በቅኔው ስር የተነገሩ ቃላት ትርጉም

ወልድ ⟶ ልጅ
ፈደል ⟶ በቁሙ
አልፋ ⟶ የመጀመሪያ
ላእሌሁ ⟶ በላዩ ላይ
ለ ⟶ የ
እጽ ⟶ እንጨት
እመ ⟶ ጊዜ
ተሰፍሀ ⟶ ተዘረጋ
ህማማት ⟶ መከራዎች
ስጋ ⟶ በቁሙ

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ደቂት ⟶ ልጆች
ከመ ⟶ አዳማቲ፣ ትርጉም አልባ
መምህሮሙ ⟶ መምህራቸው
ትጉህ ⟶ በቁሙ (ታታሪ)
እንተ ⟶ የ
ፈድፈደ ⟶ በዛ
ጥበቡ  በቁሙ
ሰላሳ ⟶ በቁሙ
ብሩር ⟶ ብር
አምጣነ ⟶ እና፣ ስለ
አስቡ ⟶ ደሞዙ
ጽህፈት ⟶ በቁሙ
ዝንቱ ⟶ ይህ
ማይ ⟶ ውሃ
ሀጸቡ ⟶ አጠቡ
ኪያሁ ⟶ እሱን
ያንብቡ ⟶ ያነቡ ዘንድ
ሳእር ⟶ ሳር
ቀኖት ⟶ ችንካር
ሀጺን ⟶ ብረት
ነሲኦሙ ⟶ ይዘው
ቀርቡ ⟶ ቀረቡ
እስመ ⟶ እና
ሆረ ⟶ ሄደ
ውስተ ⟶ ውስጥ
ደይን ⟶ መከራ
ምስካብ  ምኝታ
ይሁዳ ⟶ የሰው ስም

መ. የቅኔው ፍች

የመጀመሪያው ወልድ ፈደል በእንጨት ላይ በተዘረጋ ጊዜ የስጋ መከራዎች ልጆች እርስን ያነቡት ዘንድ የብረትን ችንካር ሳር ይዘው ቀረቡ። ጥበቡ የበዛ መምህራቸው ይሁዳ በ30 ብር ተቀጥሮላቸዋልና እርሱ ወደ መከራ መኝታ ቤቱም ስለሄደ የወልድ ፈደል ጽህፈትን በውሀ አጠቡት ደመሰሱት።

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያው

ፊደል ወልድ ⟶ ምሳሌ ፊደል ስም፤ ወልድ ወርቅ ተመስሎ የማነጻጸሪያ ባለቤት

አልፋ ⟶ የፊደል ዘርፍ

ላእሌሁ ⟶ የማድረጊያ ባለቤት

ለ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ዘርፍ አያያዥ ዘርፍ አያያዥነቱ ላእለ እጽ የሚያስኝ

እጽ ⟶ የላእለ ዘርፍ

እመ ⟶ አገባብ ፍችው ጊዜ ሙያው ማንጸሪያ

ተስፍሀ ⟶ ያስር ነበር እመ ወድቆ አስቀርቶታል

ደቂቀ ህማማት ⟶ ምሳሌ ደቂቅ ስም ህማማት ወርቅ ተመሥሎ የቅኔ (አረፍተ ነገር) ባለቤት

ስጋ ⟶ የህማማት ዘርፍ

ከመ ⟶ አዳማቂ

ኪያሁ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለያንብቡ

ያንብቡ ⟶ ዘንድ አንቀጽ

ሳእር ቀኖት ⟶ ምሳሌ ሳእር ስም ቀኖት ወርቅ ተመስሎ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለነሲኦሙ

ሀጺን ⟶ የቀኖት ዘርፍ

ነሲኦሙ ⟶ ቦዝ አንቀጽ

ቀርቡ ⟶ ማሰሪያ አንቀጽ

ለ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ዘርፍ አያያዥ፤ ዘርፍ አያያዥነቱ እስበ መምህር ይሁዳ የሚያስኝ

መምህር ይሁዳ ⟶ ምሳሌ መምህር ስም፤ ይሁዳ ወርቅ፤ ተመስሎ የእስበ ዘርፍ

እንተ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለመምህር ይሁዳ

ፈድፈደ ⟶ ያስር ነበር እንተ ወድቆ አስቀርቶታል

ጥበብ ⟶ የቅጽል ባለቤት

ሰላሳ ⟶ የብሩር ቅጽል

ብሩር ⟶ ኅብር ሆኖ የእስረጅ ባለቤት

እምጣነ ⟶ አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለቀርቡ

አስቡ ⟶ ያስር ነበር እምጣት ወድቆ አስቀርቶታል

ወ ⟶ አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ

ጽህፈት ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለህጸቡ

ፊደል ⟶ የጽህፈት ዘርፍ

በ → አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ማይ → የማድረጊያ ባለቤት

ሀጸቡ → በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ ይሰባል እንጅ አይሳብም

እስመ → የአገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለሀጸቡ

ሆረ → ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል

ውስተ → አገባብ ፍችው ውስጥ (ወደ) ሙያው ማድረጊያ

ምስካብ ደይን → ምሳሌ ምስካብ ሰም፣ ደይን ወርቅ፣ ተመስሎ የውስተ ዘርፍ

ሬ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ፡ ልጆች የፊደል ገበታ በተዘረጋ ጊዜ ሀ ሁ ን ለመማር መጠንቆያ ሳር ይዘው ቀረቡ:: መምህር በ30 ብር ተቀጥሮላቸዋልና:: መምህራቸውም ደክሞት ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ ተማሪዎቹ ህጻን መሆን አይቀርምና የፊደሉን ገበታ በውሀ አጠቡት ፊደሎችም ተደመሰሱ::

ወርቁ፡ ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ መከራ ተቀብሎዋል:: በብረት ችንካሮች ተቸንክሩዋል:: ይህ መከራ እንዲፈጸምበት ይሁዳ በሰላሳ ብር ሸጦታልና:: በጦር በተወጋ ጊዜም ከጎኑ ደምና ውሀ ፈስሰዋል:: ይሁዳም ወደ ደይን ሄድዋል ማለት ተፈርዶበት ተቀጥቱዋል ማለትን ያመለክታል::

## 6. ዘ ይእዜ

ቅኔው ዘ ይእዜ የተባለው «ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ» በማለት የሚጀምር ስለሆነ ነው:: አጭርም ረጅምም አይነት አለው:: ረጅሙ ባለ 5 ቤት ሲሆን የአምስቱ አእማደ ምስጢራት ምሳሌ ነው:: ዜማው እዝል ነው:: አጭሩ ደግሞ ሶስት ቤት ያለው ሲሆን ስሙም ሳህለክ ይባላል:: ዜማው አራራይ ነው:: ስሙ ሳህለክ ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት «ተሳህለነ እግዚኦ በከመ አቡየ» የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው:: የሳህለክ ቅኔ ብዙን ጊዜ የሚያተኩረው ከሀይማኖታዊ ቀኖና ውጭ ለሆነ ተግባር ማለትም ስለ ሀገርና ስለ መንግስት (ማህበራዊ ጉዳይ) ላይ ነው:: የሚቀኘውም ሰው በእውቀትም በእድሜውም ከፍ ያለ፣ ምስጢር ያደላደለ፣ ታሪክን በደንብ ያወቀ መሆን አለበት:: ረጅሙ ዘ ይእዜ የሚቀርበው (የሚደረሰው) በታላላቅ በአላት ዋዜማ በሚቆምበት ጊዜና በስብሀተ ነግህ አደራረስ ጊዜ ይቀኙታል:: ሳህለክ የሚባለው አጭሩ ዘ ይእዜ ግን መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ብቻ ነው የሚቀርበው::

ምሳሌ

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

የዚህ ቅኔ ታሪክ የሚያጠነጥነው ድንግል ማርያም ጌታን (ክርስቶስን) ስለመውለድ የነበረውን ታሪክ የሚያመለክት ነው፡፡

ለ. የቅኔው ንባብ

እምጥንት ኢመልኡ እስከ ይእዜ
አዳም ወሄዋን ዘአበዊሆሙ ቤተ፤
እመ ይወልዱ ክልኤተ ክልኤተ፤
ማርያምስ ዘነስአት ቅድስተ ቅዱሳን በረከተ
መልአት ምድረ ወሰማያተ
ወሊዳ ዋህደ ወተወሊደ አሀተ
መልአት ምድረ ወሰማያተ፡፡

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ ቃላት ትርጉም

| | | |
|---|---|---|
| እም | ⟶ | ከ፤ ጀምሮ |
| ጥንት | ⟶ | ድሮ |
| ኢ | ⟶ | አፍራሽ |
| መልኡ | ⟶ | ሞሉ |
| ይእዜ | ⟶ | ዛሬ |
| አዳም | ⟶ | የሰው ስም |
| ወ | ⟶ | እና |
| ሄዋን | ⟶ | የሰው ስም |
| ዘአበዊሆሙ | ⟶ | የአባቶቻቸው (ስላሴ) |
| ቤት | ⟶ | በቁሙ |
| እመ | ⟶ | ጊዜ |
| ይወልዱ | ⟶ | ይወልዳሉ |
| ክልኤተ ክልኤተ | ⟶ | ሁለት ሁለት |
| ማርያም | ⟶ | የጌታ እናት |
| ስ | ⟶ | ግን፤ ነገር ግን |
| ዘ | ⟶ | የ |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነስአት ⟶ ወሰደች

ቅድስት ⟶ ክብርት

ቅዱሳን ⟶ የተከበሩ

በረከት ⟶ በቁሙ

መልአት ⟶ ሞላች

ምድር ⟶ በቁሙ

ሰማያት ⟶ በቁሙ

ወሊዳ ⟶ ወልዳ

ዋህድ ⟶ አንድ

ተወሊዳ ⟶ ተወልዳ

እሀተ ⟶ አንድ ሁና

መልአት ሞላች

ምድር በቁሙ

ሰማያት በቁሙ

መ. የቅኔው ፍች

አዳምና ሄዋን ከጥንት ጀምሮ ሁለት ሁለት በወለዱ ጊዜ የአባቶቻቸውን የስላሴን ቤት አልሞሉም። ከቅዱሳን ይልቅ የተከበረች በረከትን የተቀበለች ማርያም ግን አንድ ወልዳና አንድ ሁና ተወልዳ ምድርና ሰማይን ሞላች የሚል ነው።

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

እም ⟶ አገበባ ፍችው ከ ሙያው መነሻ

ጥንት ⟶ የመነሻ ባለቤት

ኢመልኡ ⟶ ማሰሪያ እንቀጽ ይስባል እንጅ አይሳብም

እስከ ⟶ አገባብ ፍችው ድረስ ሙያው መነሻ

ይእቲ ⟶ የመድረሻ ባለቤት

አዳም ሄዋን ⟶ በ ወ ተጫፍረው የቅኔ ባለቤት

ዘ ⟶ አገባብ ፍችው የ ሙያው ዘርፍ ደፊ ዘርፍ ደፊነቱ ቤተ አበዊሆሙ የሚያስኘ

አበዊሆሙ ⟶ የቤት ዘርፍ

ቤት ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኢመልኡ

እመ ⟶ አገባብ ፍችው ጊዜ ሙያው ማንጸሪያ

ይወልዱ ⟶ እንቀጽ ያስር ነበር እመ ወድቆ አስቀርቶታል

ክልኤተ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለይወልዱ።

ማርያም ⟶ የአፍራሹ ቅኔ ባለቤት

ሰ ⟶ አገባብ ፍቺው ግን ሙያው አፍራሽ
በ ⟶ አገባብ ፍቺው የ ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለማርያም
ነስአት ⟶ ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል
ቅድስት ⟶ ቅጽል ቅጽልነቱ ለበረከት
ቅዱሳን የቅድስት ዘርፍ
በረከት ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለነስአት
መልአት ⟶ የአፍራሹ ቅኔ ማሰሪያ አንቀጽ
ምድር ሰማያት ⟶ በ ወ ተጫፍረው ተሳቢ ተሳቢነታቸው ለመልአት
ወ ⟶ አገባብ ፍችው እና ሙያው አጫፋሪ
ወሊዳ ⟶ ቦዝ አንቀጽ
ዋህድ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለወሊዳ
ወ ⟶ አገባብ ፍቾው ም ሙያው አጫፋሪ
ተወሊዳ ⟶ ቦዝ አንቀጽ
እሀተ ⟶ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለተወሊዳ

ረ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ:- አዳምና ሄዋን ሁለት ሁለት ቢወልዱም የአባታቸውን (ስላሴ) ቤት አልሞሉም። አንዲት ሴት ግን አንድ ወልዳና አንድ ሁና ተወልዳ ቤት ሙሉ ሆናለች ማለት ነው።

ወርቁ:-ባለቅኔው አዳምና ሄዋንን ከማርያም ጋር አዎዳድሩዋል። በውድድሩም መሰረት አዳምና ሄዋን መንታ መንታ ቢወልዱም ምድርን አለ መሙላታቸውን ማርያም ግን ሰማይና ምድርን የፈጠረውን ጌታን ስለ ወለደች ምድርን ሞልታለች የሚለውን ታሪክ ያስገነዝባል።

## 8. መወድስ

መወድስ የተባለው ቅኔ ሁለት አይነት ነው። አንደኛው ፍትሀ ሊተ የተባለው ሲሆን ቤቱም ስምንት ነው። የስምንቱ ብሂረ አሪት ምሳሌ ነው፤ ዜማውም አራራይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ኩልክሙ የተባለው ሲሆን ቤቱም ዘጠኝ ነው። የዘጠኙ ሀጹረ መስቀል ምሳሌ ነው። እንዲሁም ሌሎች አጭር መወድስ ወይም አጭር ኩልክሙ የሚባሉ አሉ ። ቤታቸውም ሁለት ነው።

የመወድስ ቅኔ የሚቀርበው በመወድስ አደራረስ ጊዜ «ፍትሀ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ» በሚለው መዝሙር ነው። መንደርደሪያው ሶስተኛው ቤት ሲሆን አምስተኛው ቤት ደግሞ ለእለም ይባላል።

የመወድስ ቅኔ ስምን መወድስ ሊሰኝ እንደቻለ የተገለጸ ነገር አልተገኘም፡፡ ሆኖም አንዳንድ ምሁራን ቅኔ ማለት ምስጋና ማለት ስለሆነና «ወደሰ አመስገነ» ከሚለው የግእዝ ግስ መወድስ የሚለው ቃል ስለሚገኝ መወድስ የሚለው ስያሜ ከምስጋና ጋር ተቆራኝቶ የተገኘ በመሆኑ የቅኔው መጠሪያ ሆኑዋል የሚሉ አሉ፡፡ «ፍትሀ ሊተ» የተባለው የዳዊት መዝሙር በሚጀመርበት ቃል ስለተጠራ እንደሆነ፤ «ኩልክሙ» የተባለው ደግሞ «ኩልክሙ አህዛብ ጥፍሁ እደዊክሙ» የተባለው መዝሙር እየተዘመረ ስለሚጀምር መሆኑ ተገልጽዋል፡፡ ኩልክሙ የተባለው ቅኔ አብዛኛውን ጊዜ ለታላላቅ ሰዎችና ለደብር አስተዳዳሪዎችና ለሊቃውንት የሚሰጥ (እንዲቀኙት የሚደረግ) የቅኔ አይነት እንደሆነ ተገልጽዋል፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

የቅኔው ታሪክ መነሻው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀልን የተመለከተ ነው፡፡

ለ. የቅኔው ንባብ

አ! አብረሃም መድህኔ አለም
ተእንገዱ ብከ እናግደ ህጺን ቅንዋት
ወአመ በገጽከ ቀርበ ተጸፍኦተ ገጽ ሀብስት
ነበረ በጥቃ ዚአከ እንግዳ ኩይናት
ወላእከ ትእዛዝ ገቦ ዚአከ ጽሩየ ማየ እቅርበ ለህጽበት
ለአለም
ይትሀነጽሂ ለአረጋዊ ህንጻ ቤትከ ስቅለት
በሀብል ተመጠነ ዘባንከ መሰረት
ወአመ ይጠፍእ ብከ ብርሀነ ጸሃይ ማሀቶት
እለተ ሞትከ አረጋዊ ነበረ በጽልመት

ሐ. በቅኔው ውስጥ የተነገሩ ቃላት ትርጉም

| | | |
|---|---|---|
| አ | ⟶ | ሆይ |
| አብረሃም | ⟶ | የሰው ስም |
| መድህኒ | ⟶ | አዳኝ |
| አለም | ⟶ | በቁሙ |
| ተእንገዱ | ⟶ | እንግዳ ሆኑ |
| ብከ | ⟶ | ባንተ |
| እናግድ | ⟶ | እንግዶች |
| ህጺን | ⟶ | ብረት |
| ቅንዋት | ⟶ | ችንካሮች |

ወ ⟶ ም
እመ ⟶ ጊዜ
በገጽከ ⟶ በፊትህ
ቀርበ ⟶ ቀረበ
ተጸፍኦት ⟶ በጥፊ መምታት
ገጽ ⟶ ፊት
ሀብስት ⟶ እንጀራ
ነበረ ⟶ ተቀመጠ
ጥቃ ⟶ አጠገብ
ዘእከ ⟶ የንተ
እንግዳ በቁሙ
ኩይናት ጦሮች
ላእከ ተላላኪ (መላክተኛ)
ትእዛዝ ⟶ ትዛዝ
ገቦ ⟶ ጎን
ጽሩይ ጥሩ
ማይ ⟶ ውሀ
አቅረበ ⟶ አቀረበ
ለ ⟶ በቁሙ
ሀጽበት ⟶ ማስታጠብ (እጥበት)
ይትህነጽ ⟶ ይሰራ ዘንድ
ሂ ⟶ ም (ከፋይ)
አረጋዊ ⟶ ሽማግሌ
ህንጻ ⟶ በቁሙ
ቤትከ ⟶ ቤትህ
ስቅለት ⟶ በቁሙ
በሀብል ⟶ በገመድ
ተመጠነ ⟶ ተለካ
ዘባንከ ⟶ ጀርባህ
መስረት ⟶ በቁሙ
እመ ⟶ ጊዜ
ይጠፍእ ⟶ ይጠፋል
ብከ ⟶ ባንተ
ብርሃን ⟶ በቁሙ
ጸሃይ ⟶ በቁሙ
ማህቶት ⟶ ብርሀን (ጧፍ)

እለተ ሞትከ ⟶ የሞትህ ቀን
ጽልመት ⟶ ጨለማ
ነበረ ⟶ ተቀመጠ

መ. የቅኔው ፍች

አብርሃም የአለም መድሀኒት ሆይ! የብረት ችንካሮች እንግዶች መጡብህ በጥፊ መመታት ገብታም በፊትህ በቀረበ ጊዜ እንግዳ ጦር ከአጠገብህ ተቀመጠ፡፡ ትእዛዝ ፈጻሚ ተላላኪ ጎንህም ለማስታጠብ ጥሩ ውሃ አቀረበ፡፡ ለአለም የቤትህ ህንጻ ስቅላት ለሽማግሌው ይሰራ ዘንድ መሰረቱ ጀርባህ በገመድ ተለካ፡፡ የጸሃይ ሻማ ብርሃንም በጠፋ ጊዜ ሽማግሌው የሞትህ ቀን በጨለማ ተቀመጠ፡፡

ሠ. የቅኔው ምሳሌና ሙያ

እ! ⟶ ቃለ አጋኖ
አብረሃም መድሀኒ ⟶ ምሳሌ አብረሀም ስም መድሀኒ ወርቅ ተመስሎ የስሚ ባለቤት
አለም ⟶ የመድሀኒ ዘርፍ
ተአንገዱ ⟶ ማሰሪያ አንቀጽ
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
ከ ⟶ ማድረጊያ ባለቤት
እናግድ ቅንዋት ምሳሌ እናግድ ስም ቅንዋት ወርቅ ተመስሎ የቅኔ (አረፍተ ነገሩ) ባለቤት
ሀጺን ⟶ የእናግድ ዘርፍ
ወ ⟶ አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ
አመ ⟶ አገባብ ፍችው ጊዜ ሙያው ማገጸሪያ
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
ገጽ ⟶ የማድረጊያ ባለቤት
ቀርበ ⟶ ያስር ነበር አመ ወድቶ አስቀርቶታል
ተጸፍኦት ህብስት ⟶ ምሳሌ ህብስት ስም ተጸፍኦት ወርቅ ተመስሎ የማገጸሪያ ባለቤት
ገጽ ⟶ የተጸፍኦት ዘርፍ
ነበረ ⟶ በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
ጥቃ ⟶ የማድረጊያ ባለቤት

ዚእከ → የጥቃ ዘርፍ

እንግዳ ኩይናት → ምሳሌ እንግዳ ስም ኩይናት ወርቅ ተመስሎ የዋዌ ባለቤት

ወ  አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ

ለእከ ገቦ → ምሳሌ ለእከ ስም ገቦ ወርቅ ተመስሎ የዋዌ ባለቤት

ትእዛዝ → የለእከ ዘርፍ

ዚአከ → የገቦ ዘርፍ

ጽሩይ → ቅጽል ቅጽልነቱ ለማይ

ማይ → ተሳቢ ተሳቢነቱ ለአቅረበ

አቅረበ → በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጅ አይሳብም

ለ → አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

ህጽበት  ህብር ሆኖ የአቀባይ ባለቤት

ይትህነጽ → ዘንድ አንቀጽ ሙያው ዋዌ

ሂ  አገባብ ፍችው ም ሙያው ከፋይ

ለ  አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

አረጋዊ  የአቀባይ ባለቤት

ህንጻ ስቅለት → ምሳሌ ህንጻ ስም ስቅለት ወርቅ ተመስሎ የዘንድ ባለቤት

ቤት → የህንጻ ዘርፍ

በ → አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ሀብል → የማድረጊያ ባለቤት

ተመጠነ → ማሰሪያ አንቀጽ

መሰረት ዘባን → ምሳሌ መሰረት ስም ዘባን ወርቅ ተመስሎ የቅኔ (የአረፍተ ነገር) ባለቤት

ወ → አገባብ ፍችው ም ሙያው ዋዌ

እመ → አገባብ ፍችው ጊዜ ሙያው ማንጸሪያ

ይጠፍእ → ያስር ነበር እመ ወድቆ እስቀርቶታል

በ → አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ማህቶት ብርሀን → ምሳሌ ማህቶት ስም ብርሀን ወርቅ ተመስሎ የማንጸሪያ ባለቤት

ጸሃይ → የብርሃን ዘርፍ

እለተ ሞትከ አረጋዊ → ምሳሌ አረጋዊ ስም እለተ ሞትከ ወርቅ ተመስሎ የዋዌ ባለቤት

ሞት ⟶ የእለት ዘርፍ
ነበረ ⟶ በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ
በ ⟶ አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ
ጽልመት ⟶ ሀብር ሆኖ የማድረጊያ ባለቤት

ረ. ቅኔውን ማራቀቅ

ሰሙ፡ በቤትህ ሊስተናገዱ እንግዶች ወደ አንተ መጡብህ፡፡ ማእድ በቀረበ ጊዜ እንግዶች በአጠገብህ ተቀመጡ፡፡ ራትም ሊቀርብ ሲል የቤትህ አሽከር እጅ ለማስታጠብ ውሀ አቀረበ፡፡

ወርቁ፡ የብረት ችንካሮች ወደ አንተ መጡ (ጌታ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ በብረት ችንካሮች መቸንከሩን ለመናገር)፣ ጌታ በአንድ በኩል በጥፊ መመታቱን በሌላ በኩል ደግሞ ጎኑን በጦር የተወጋ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በጦርም በተወጋ ጊዜ ከጎኑ ጥሩ ውሀ የፈሰሰው መሆኑን ያሳይል፡፡

ለአለም

ሰሙ፡ ቤት ሲሰራ ርዝመቱ (ቁመቱ) በሜትር (በገመድ) እንደሚለካ በቤትም ውስጥ ይበራ የነበረ መብራት በድንገት ቢጠፋ ቤተሰቡ ሁሉ በጨለማ እንደሚዋጥ ያሳያል፡፡

ወርቁ፡ ጀርባው በገመድ ተለካ ማለት ጌታ በመስቀል ላይ በዋለ ጊዜ በገመድ (በጅራፍ) ጀርባው መገረፋን እንዲሁም በመስቀል ላይ በዋለ ጊዜ ጸሀይ ብርሀንዋን የነፈገች መሆኑዋና ስቅለቱም በጨለማ ተጋርዶ የቆየ መሆኑን ለመናገር ነው፡፡

# ምእራፍ አራት

## የግእዝ ቅኔ እና ጎጃም

### 4.1 የቅኔ ትምህርት ቤት ህይወት በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ

የጎጃም የግእዝ ቅኔ መስራችና አባት ተዋነይ ስለመሆኑ በጽሁፍም ሆነ በቃል የተገኙ መረጃዎች አረጋግጠዋል። የተገኙትም የጽሁፍ መረጃዎች ስለ ጉዳዩ ተመሳሳይ ሀሳብ ያስፈሩ በመሆናቸው የጉዳዩን ተአማኒነት የበለጠ የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል።

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ተዋነይ እና ድድቅ ወልደ ማርያም በአንድ ጉባኤ ውስጥ የቅኔን መንገድ በመማር ላይ ሳሉ የግራኝ መሀመድ ጦርነት በመነሳቱ ምክንያት ድድቅ ወልደማርያም ወደ ጎንደር ሄዶ ዳውንት ውስጥ ጨረቃ ሚካኤል በተባለ ደብር ቅኔን እያስተማረ ሲቀመጥ፣ ተዋነይ በበኩሉ ወደ ጎጃም በመምጣት ቅኔን ያስፋፋ መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ታምኖበታል። /አፈወርቅ ዘውዱ 1980:19፣ አፈወርቅ ተክሌ 1997:24/

ተዋነይ ቅኔን ጎጃም ውስጥ ማስፋፋት ከመጀመሩ በፊት ጣና ሀይቅ ውስጥ ደቅ እስጢፋ በተባለ ቦታ ከሰው ተለይቶ በመቆየቱ የቅኔውን መንገድና አይነት አስማምቶ ለደቀ መዝሙራት ቶሎ በሚገባ ሁኔታ አገባቡን ወስኖ አዋጁን አሳጥሮ ለሁሉም መርህ በሚሆን ሁኔታ የግእዝ ቅኔን ስርአትና ህግ አበጅቶ ቀዳሚ የቅኔ ጉባኤውን በጎንጅ መሰረተ (አለማየሁ 1950:117)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተዋነይ የጎጃም የግእዝ ቅኔ መስራችና አባት መሆኑ በሙያው ያለፉና ስለ ተዋነይ የዓፉ ሊቃውንት ሁሉም ተስማምተውበታል።

የጎጃም (ጎንጅ) ቅኔ ከሌሎች ቅኔዎች የተለየ ባህሪ እንዳለው ቀደም ሲል በሰፈረው ጽሁፍ በሰፊው ተገልጹዋል። ከተጠቀሱት በተጨማሪ የጃቢ ጠህናን ወረዳ የቅኔ ጉባኤ መምህር የሆኑት መላከ ጥበብ ስሜነህ አበበ ልዩነቱን እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> ... የጎንጅዎች ግን፣ አገባባቸው፣ እርባ ቀመራቸውና አዋጃቸው ውሱን ነው። ግሳቸውም የተወሰነ ነው። የቅኔ ሙያቸው ግን እንደ መስዋእት ስንዱ የተበጠረ፣ የተለቀመ፣ የተወሰነ፣ በጣም ያልተንዛዛ፣ ምስጢሩ እጅግ የረቀቀና የሚማርክ በመሆኑ የጎንጅ ቅኔ ከሌሎች ይለያል (መላከ ጥበብ ስሜነህ፣ ኢ. ቁ. 1)።



መላከ ጥበብ ስሜነህ በፍኖተ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የግእዝ ቅኔን እስመልክቶ ለቀረቡላቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ በሰጡበት ወቅት፤

በጎጃም ቀዳሚ የሆነውን የጎንጅ የቅኔ ጉባኤ ተከትሎ በተመሰረተውና እሁንም ድረስ የሙያው ባለቤት የሆኑትን ሊቃውንት በማፍራት ላይ የሚገኘው የዋሸራ የቅኔ ጉባኤ ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ በሜጫ፣ በደብረ ኤልያስ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በደንበጫ፣ በመርጦለ ማርያም፣ በዲማ ጊዮርጊስና በሌሎችም የጎጃም አካባቢዎች ጉባኤው በሰፊው ተዘረጋ፡፡ ይህም በመሆኑ ጎጃምን ከሌሎች አካባቢዎች በተለየ ስለቅኔ ትምህርት ሲታሰብ ቀዳሚ ተጠቃሽ አደረገው፡፡ ለዜማ ጎንደር፣ ለቅዳሴ ትግራይ እንደ ሚታሰብ ሁሉ ስለቅኔ ሲወሳ ቀድሞ የሚታወሰው ጎጃም እየሆነ መጣ (ደብተራ ብርሀን 1999፤ ካ. ቁ. 5)፡፡ አሁንም ቢሆን እንደወትሮው መሆን ባይችል ሰፋፊ የቅኔ ጉባኤዎች ጎጃም ውስጥ ያሉ መሆናቸው በጥናቱ ወቅት ለመመልከት ተችልዋል፡፡

በሸለል ገብርኤል ነዋሪ የሆኑት ደብተራ ብርሀን እንደሚሉት የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎችና ጥንታዊ ስርአቱ በጎጃም ከጊዜ ወደጊዜ እየጠበበ፣ ተከታይ ተማሪዎችም እየቀነሱ፣ ቅኔ ለስጋዊ ህይወት ያለው ጠቀሜታም እየተሙዋጠጠ እንደሆን ይገልጻሉ፡፡

(ብርሀን፤ 1999 ኣ. ቁ. 5)። መሳከ ጥበብ ስሜነህ በዚህ ሀሳብ አይስማሙም፤ በጎጃም የቅኔ ጎተራው እንጠባጠበ እንጅ ገና አላፈሰሰም ይላሉ።

> የጎጃም የቅኔ ጉባኤ እንጠባጠበ እንጅ ገና አላፈሰሰም በ1941 ዓ/ም ጀምሮ በደብረ ምስራቅ ድንግራ ማርያም የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ላይ የሚገኙት መሪጌታ ለይኩን ብርሁ፣ በዋሸራ እነ አለቃ ደሴ፣ በጎንጅ ደብረ ምጥማቅ እነ አለቃ በቃና ማእበል ደሴ፣ በቢቸና እየንታ ውብሸት፤ በመንግስቶ መሪጌታ መስረት፣ በደብረ ኤልያስ መሪጌታ ገብረ ስላሴ፣ በቋሪት (አዳማ ተራራ) በጨጎዴ ደብረ መድሀኒት ሀና መሪጌታ ያሬድ ሽፈራው፤ በሙቶ የሚቆጠር የቅኔ ተማሪ በማስተማር ላይ ያሉ የሙያው ሊቃውንት ናቸው። ለመጭው ይታሰብበት እንጅ የጎጃም ቅኔ እንደ ወትሮውም ባይሆን አሁንም አልተሙዋጠጠም (መሳከ ጥበብ ስሜነህ 1999. ኣ.ቁ. 1)።

ስለ ጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች በተለያዩ መጻህፍትና ጥናቶች ሰፍሮ እንደሚገኘው፣ ጥናት አቅራቢውም በፍኖተሰላም፣ በድንግራ ማርያም፣ በሸለል ገብርኤልና በገዳመ አስቄጥስ አካባቢ ተገኝቶ እንደ ተመለከተውና ባለሙያዎችን ጠይቆ እንደተረዳው በአሁኑ ጊዜም ቢሆን የተወሰኑ የቅኔ መምህራን ከስፋፊ ጉባኤዎቻቸው ጋር ያሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሎዋል። ይሁን እንጅ በአካባቢው ጸንቶ የኖረው የቅኔ ቅርስ ድጋፍና እገዛ ካልተደረገለት የመቀነስ ብሎም የመመንመን አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል የሙያው ሰዎች ስጋታቸውን ደጋግመውና አጽንኦት ሰጥተው ገልጸውታል።

ጥናት አቅራቢው በቅርቡ የጥናት ስራውን ለማጠናቀር በተዘዋወረባቸው የቅኔ ጉባኤዎች የተመለከታቸውን ስርአቶች በሙያው ውስጥ እየኖሩ ያሉ የሙያው አባቶችን ጠይቆ ያገኛቸውን በማካተት በጎጃም የቅኔ ቤት ህይወት ምን መልክ እንዳለው ቀጥሎ ለማሳየት ሞክሩዋል።

### 4.1.1 እንግዳ /አዲስ/ የቅኔ ተማሪ አቀባበልና መስተንግዶ

ጎጃም ውስጥ ወደ ግእዝ የቅኔ ጉባኤዎች ለትምህርት ለሚሄድ የወሰነ ተማሪ የቅኔን ትምህርት ለመጀመር ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የዜማ ትምህርቶችን (ፊደልን ከነጉዋዙ፣ የንባብ ትምህርቶችን፣ የዜማና የሊሊት ትምህርቶችን፣ ...) በቅድሚያ ተምሮ ማጠናቀቅ ይጠበቅበታል። ምክንያቱም በቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ የግእዝ ቋንቋ ከነአገባቡ፣ የቅኔ ትምህርት ከነጉዋዙ የሚጠናበት በመሆኑ የበሰለ አእምሮን ይጠይቃል። በሌላም በኩል፣ የቅኔ ትምህርት የሚሰጥባቸው ጉባኤዎች ውሱን በመሆናቸው በየአድባራቱ የሚገኙ አይደሉም። ይህም በመሆኑ ቅኔን ለመማር ያሰበ ተማሪ ሁሉ በአካባቢው የቅኔ መማሪያ ጉባኤዎች ላያገኝ ይችላል። ትምህርቱን አማርጦ ለመማር ከፈለገ ከአካባቢው ርቆ መሄድን ይጠይቃል። የእለት ቀለቡንም በየመንደሩ ተንከራቶ ከውሻ ጋር ተጣልቶና ለምኖ ማግኘት ይጠበቅበታል። ከዚህ አንጻር የቅኔን ትምህርት ለመጀመር የወሰነ ተማሪ የተገለጹትን ችግሮች ለመጋፈጥ ይችል ዘንድ ለአካለ መጠን የደረሰ መሆኑ ደግሞ ተገቢ ነው።

አንድ ተማሪ ወደ አንድ የቅኔ ጉባኤ ሄዶ ለመማር ወስኖ ወደ ጉባኤው በእንግድነት በሚሄድበትና ወደ ጉባኤው በደረሰ ጊዜ ራሱን የቻለ የእንግዳ ተማሪ አቀባበልና የመስተንግዶ ስርአት አለው። ተማሪው ሊማር ወደ ፈለገበት የቅኔ ጉባኤ ተጉዞ ወደ ጉባኤው ከመቀላቀሉ በፊት የጉባኤው ተማሪዎች በቀላሉ ሊመለከቱት በሚችሉት ቦታ ላይ ራቅ ብሎ ይቀመጣል። ተማሪዎች ባለፉና ባገደሙ ቁጥር እንግዳው ተማሪ ከተቀመጠበት ብድግና ጎንበስ እያለ የአክብሮት ሰላምታ ይሰጣል። ቀድሞ እንግዳውን የተመለከተ ተማሪ ወደ እንግዳው በመሄድ ተገቢውን ሰላምታ ካቀረበ በሁዋላ ጉዋዙን (አኮፋዳ፣ ቅምጫና ....) ተቀብሎ ወደ ጉባኤው አዳራሽ ይዞት ይሄድና ማረፊያ አጎዛ ወይም ስሌን አንጥፎ ያስቀምጠዋል። የእለቱ እንግዳ ተቀባይ የሆኑ ተረኛ ተማሪዎች ውሀ አቅርበው እግሩን ያጥቡና ወደ ጎጇዋቸው ይዘውት ይገባሉ። በሌሎች ጎጆዎች ያሉ አንድ አንድ ተማሪዎች ደግሞ ያላቸውን የእለት ምግብ እየያዙ እንግዳው ተማሪ ወዳረፈበት ጎጆ ይሰበሰባሉ። የተገኘው ምግብም ከእንግዳው ተማሪ ጋር በጋራ ይበላል። እራት ከተበላ በኋላ የተሻለ የምኝታ ቦታ ያለው ተማሪ ምኝታውን ለእንግዳው ይለቅና እንግዳው እንዲስተናገድ ይደረጋል።



የቅኔ ተማሪዎች ለምነው ያሰባሰቡትን ቁራሽ እንጀራ በጋራ በመመገብ ላይ ሳሉ።

በማግስቱ እንግዳው ተማሪ ከቅኔ መምህሩ ጋር እንዲገናኝ ይደረጋል:: መምህሩ የሚመስላቸውን ጥያቄ ሁሉ ከጠየቁት በሁዋላ በጉባኤው እንዲማር ከፈቀዱለት ትምህርቱን እንዲቀጥል ይገለጽለታል:: የማይቀበሉት ከሆነ ደግሞ ምክንያቱን ገልጸው ያሰናብቱታል::

በመምህሩ ተቀባይነት አግኝቶ ትምህርቱን እንዲቀጥል የተፈቀደለት ተማሪ ለሁለትና ለሶስት ቀን ያህል በተረኛ እንግዳ ተቀባይ ተማሪዎች ሲስተናገድ ከሰነበተ በሁዋላ የእንግድነት ጊዜው ያበቃና እንደ ማነኛውም ተማሪ በራሱ መኖር እንዲጀምር ይገደዳል:: በቅድሚያ የሚያዳብለው ተማሪ ካገኘ ያጠያይቃል፤ ያፈላልጋል:: ያ ካልሆነ በጉባኤው የቆየ ተማሪ ለቆት የሄደ ባዶ ጎጆ ካገኘ ያፈላልጋል:: ጎጆ የማይገኝ ከሆነ ደግሞ አዲስ ጎጆ ለመስራት ይዘጋጃል:: በተማሪዎች እርዳታም አዲስ ጎጆ ይሰራለትና በአዲሱ ጎጆ ውስጥ ኑሮውን ይጀምራል::



የቅኔ ተማሪዎች መኖሪያ ጎጆወች፤

ምግቡንም ለማግኘት ወደ መንደር ወጥቶ መለመን ሲላለበት በመንደር ድልድል ውስጥ እንዲገባ ይደረግና በድልድሉ መሰረት እየለመነ እየበላ የመጣለትን ትምህርት መማር ይጀምራል (መምህር ለይኩን ካ. ቁ. 3፤ ደብተራ ብርሀን ካ.ቁ.5)።



የቅኔ ተማሪው ቁራሽ ልመና ወደ መንደር በሚሰማራበት ወቅት

### 4.1.2. የምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስርአት

በሰፋፊ የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚማር ተማሪ የእለት ምግቡን ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት ትልቁ ጉዳይ ነው። አንዳንድ አባቶች እንደሚገልጹት የቀድሞዎቹ የቅኔ ተማሪዎች ምግባቸውን የሚያገኙበት መንገድ ከአሁኖቹ የተለየ ነው። በቀድሞው ጊዜ በቅኔ ትምህርት ቤቶች አካባቢ በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የቅኔ ተማሪዎችን የመርዳት ባህል በሰፊው የተለመደ በመሆኑ የወትሮዎቹ የቅኔ ተማሪዎች ምግባቸውን ከአካባቢው ህብረተሰብ ያለልመና ማግኘት የሚችሉበት የተለመደ ስርአት የነበረ መሆኑን ይገልጻሉ። ስርአቱም «የቤት ምሪት» በመባል ይገለጽ እንደነበር ይናገራሉ።

ይህ የቤት ምሪት ስርአት በድሮው ጊዜ ህብረተሰቡ ለቅኔ ተማሪዎች የሚያደርገውን የምግብ ተራድኦ የሚያመለክት ነው። በቀድሞዎቹ የቅኔ ጉባኤዎች (ጎንጅና ዋሸራ) ይማሩ የነበሩ የቅኔ ተማሪዎች በመጀመሪያ ከሰኔ 12 ቀን እስከ ህዳር 12፣ ስርአቱ እየጠበበ ሲሔድ ከሰኔ 25 ቀን እስከ መስከረም 25፣ የበለጠ ተማሪው እየበዛ ስርአቱ የበለጠ እየጠበበ ሲሄድ ደግሞ ከሀምሌ 5 ቀን እስከ መስከረም 5 ቀን ድረስ በየመንደሩ ይመሩና ከተመሩበት ቤት ምግባቸውን እያገኙ ይከርሙ ነበር።

አባቶች እንደሚሉት በዋሸራ የቅኔ ጉባኤ ይከናወን የነበረው የምሪት ስነ ስርአት የራሱ የሆነ አፈጻጸም ስርአት ነበረው። የምሪት ስርአቱ የሚፈጸመው የተማሪውን የትምህርትና የጤና ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር። የምሪቱንም ስነ ስርአት የሚመሩት በወቅቱ «ጭቃ ሹም» እና «መጋቢ» እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው። ዘራፊዎች፣ አይነ ስውራንና አካል ጉዳተኞች በትምህርት ጉባኤው አካባቢ ባሉት መንደሮች እንዲመሩ ይደረጋል። ምሪቱም የሚከናወነው የባለጸጋን ከድሀ ቤት በመቀላቀልና የተማሪዎችን አቅም ባገናዘበ መልኩ ነበር። ቤቶች ብስል ከቀሊል (ሀብታም ከድሀ) እየተቀላቀሉ ምሪቱ እንዲፈጸም የሚደረገው የተመራው ተማሪ አንደኛው ቤት ጉዳት ቢደርስበት በሌላኛው ቤት እንዲካስ በማሰብ ነው። ተመሪ ተመሪውም የምሪት ጊዜው እስካበቃ ጊዜ ድረስ በየቀኑ ወደ ተመራበት ቤት በመሄድ ምግቡን ያለ ስጋት በነጻ እንዲመገብ ይደረጋል። ተማሪውም በራሱ ፈቃድ ለተመራበት ቤት ስራ በመስራት ሊያግዝ ይችላል። በመጨረሻም የምሪት ጊዜው ሲያበቃ ወደ ቀድሞው ኑሮ ይመለሳል (መላከ ጥበብ ስሜነህ ካ.ቁ.1፣ ምስጢረ ሰዋሰው 1974:27)

በአሁኑ ዘመን አንድ የቅኔ ተማሪ ምግቡን የሚያገኝበት መንገድ ከዚህ የተለየ ነው። እንደ ጉባኤው ስፋትና ጥበት በቡድን እየተከፋፈለና በየደጁ (መንደሩ) እየሄደ በመለመን ነው ኑሮውን የሚመራው።



የቅኔ ተማሪው ለምኖ የተሰጠውን ቁራሽ እንጀራ በሚቀበልበት ጊዜ፤

ተማሪው ወደ ልመና ከመሰማራቱ በፊት የሚለመኑ መንደሮች ለተማሪዎቹ ይደለደላሉ፡፡ የመንደሮቹ ድልድል የሚደረግበት ምክንያት አንደኛው ተማሪ ቀድሞ ቅርብ ወደሆኑ መንደሮች ሄዶ በመለመን ራሱን ጠቅሞ ሌሎችን ያለ አግባብ እንዳይጎዳ ለማድረግ ነው፡፡

ይህም እንዳይሆን በቅኔ ጉባኤው አካባቢ ያሉት መንደሮች ስርአት ባለው መንገድ በሰፈር በሰፈር ተለይተው ለተማሪዎች እንዲደለደሉ ይደረጋል፡፡ ይህንንም ተግባር እንዲያከናውኑ ከጉባኤው መካከል የተመረጡ ደልዳይ ተማሪዎች በአካባቢው የሚገኙትን መንደሮች ብዛት ይለያሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በቅርብ ያሉትን መንደሮች ለዘራፊዎች፣ ለአይነ ስውራንና ለአካል ጉዳተኞች ያለ እጣ ይደለደላሉ፡፡ የተጠቀሱትን ተማሪዎች ለምኖ የሚያበላ ፈቃደኛ ተማሪ ይመደብላቸዋል፡፡ ራቅ ራቅ ወዳሉ መንደሮች በመሄድ ተዘዋውረው መለመን የሚችሉ ጤነኛ ተማሪዎች በእጣ ይደለደላሉ፡፡ የድልድሉ ተግባር እንዳበቃ ውጤቱን ጉባኤው አውቆት እንዲፈጽመው ይደረጋል፡፡

የድልድሉ ተግባር ተጠናቆ ጉባኤው እንዲያውቀው የጉባኤው መምህርም እንዲያጸድቁት ከተደረገ በሁዋላ ሁሉም ወደ ተመደበበት መንደር እየሄዱ ለምኖ መኖርን ይጀምራሉ፡፡ የሚለመነው መንደር በየሳምንቱ ወይም ደልዳይ ተማሪዎች በወሰኑት ጊዜ ዝውውር እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡ በዚህ ሳምንት አንደኛው ቡድን

የለመነውን መንደር በሌላኛው ሳምንት ሌላኛው ቡድን ይለምነዋል ማለት ነው፡፡ የልመና ስርአቱ በዚህ መሰረት ይፈጸማል፡፡ ለልመና የወጣ ተማሪ በልመና ላይ እያለ ለየት ያለ ድግስ (ማህበር፣ ሰንበቴ፣....) አጋጥሞት ቁጭ ብሎ እንዲበላና እንዲጠጣ ካልተጋበ በስተቀር



የቅኔ ተማሪው ድግስ ከተዘጋጀበት ቤት በመድረሱ ለምኖ የቀረበለትን እንጀራና ጠላ በመመገብ ላይ እንዳለ፡

በልመና ላይ እያለ ከለመነው እንጀራም ይሁን ሌላ ምግብ ቆርሶ (ቆንጥሮ) መቅመስ የተከለከለ ነው፡፡ ለልመና የወጣ ተማሪ ከለመነው ምግብ የሚቀምሰው ልመናውን ጨርሶ ወደ ጉባኤው ከተመለሰና «የማርያም መሸኛ» የሚሆን ጸሎት ካደረሰ በሁዋላ ነው፡፡ ይህንን ስርአት የጣሰ ተማሪ የቅኔ ተማሪነትን ስነ ምግባር እንደጣሰ የሚቆጠር ከመሆኑ በተጨማሪ በመንፈሳዊ ህይወቱ ትልቅ ሀጢያትን እንደፈጸመ ሆኖ ይሰማዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ስነ ስርአት ያለ አስገዳጅ ህግ ሆኖ የሚኖር የጎጃም የቅኔ ትምህርት ቤቶች ደንብ ነው፡፡

ተማሪዎች የሚኖሩት በቡድን በቡድን ተከፋፍለው ነው። በጋራ የሚኖሩ የአንድ ቡድን አባላትም ኑሯቸውን የሚገፉት በጋራ ነው። ምግባቸውንም ቢሆን የሚያዘጋጁት በጋራና ስራውን በመከፋፈል ነው። ከቡድኑ አባላት መካከል የተወሰኑት ወደ ተመደበላቸው መንደር ለልመና ይወጣሉ።



ቅኔ ተማሪዎች ለእለት ጉርስ የሚሆን ቁራሽ በመለመን ላይ ሳሉ፤

ቀሪዎቹ የቡድኑ አባላት የምግብ ማብሰያ የሚሆን ውሀ ይቀዳሉ፣ እንጨት ይሰብራሉ። ልመና ያመሹ ተማሪዎች ለራት የሚሆን ምግብ ሳያገኙ ከተመለሱ ኮቸሮ ያኮችራሉ ወይም ቆሎ ቆልተው ተጨማሪ ምግብ ያዘጋጃሉ። ኮቸሮው የሚዘጋጀው ከደረቅ እንጀራ ነው። በቅድሚያ ቀድሞ በጽሀይ የደረቀ እንጀራ ሊኖር ይገባል። ኮቸሮ ለማኮቸር እንዲያመች የደረቀው እንጀራ ተከስክሶ እንዲደቅ ይደረጋል። በሌላ በኩል ጨውና ቃሪያ ከተገኘ ደግሞ በርበሬ ያለበት ውሀ በሸክላ ወይም በብረት ድስት እሳት ላይ ተጥዶ እንዲፈላ ይደረጋል። ተከስክሶ የተዘጋጀው ኮቸሮም በሌላ ሸክላ ወይም ሳህን ውስጥ እንዲዘጋጅ ይደረጋል። በመቀጠል የፈላው ውሀ (ወጥ) በኮቸሮው ላይ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እንዲፈስ ይደረግና ትኩሱ ውሀ የፈሰሰበት ኮቸሮ በደንብ እንዲርስ ከአስር እስከ አስራምስት ደቂቃ ሌላ እቃ ተከድኖ እንዲታፈን ይደረጋል። በመጨረሻም ለቡድኑ አባላት ለምግብነት ይውላል። ይህ የምግብ አይነት በጎጃም የቅኔ ተማሪዎች ዘንድ የተለመደና የዘወትር ምግብ ነው።

### 4.1.3 አለባበስና የቁሳቁስ አጠቃቀም

የቅኔ ተማሪዎች ከቅኔ ትምህርት ባሻገር ስለ እጅ ሙያና ስለ ተደበቀ ጥበብ ይማሩ ነበር። በተጨማሪም መጻህፍትን እየደጎሱ፣ ጭራ እየቆነኑ፣ ጃንጥላ፣ ስሌንና አኮፋዳ እየሰሩ፣ ደበሎ እየሰፉ፣ መስቀል እየቀረጹ ይሸጣሉ። ከልዩ ልዩ እጽዋት፣ ከስንዴና ከገብስ እራሪና እንዲሁም ከጥላሸት ጥቁር፣ አረንጓዴና ቀይ ቀለማትን አዋህደውና በጥብጠው፣ ቆዳ ፍቀው ግስ (መጽሄት)ና ሌሎች ቅዱሳት መጻህፍትን ይጽፋሉ። በተለይ ደበሎ የዘመኑ የቅኔ ተማሪዎች የዘወትር ልብስ ስለነበረ ደበሎ የመስፋት ችሎታ ያለው ተማሪ በዘመኑ ተፈላጊ ነበር።

ከወትሮ ጀምሮ የቅኔ ትምህርት ይሰጥባቸው ከነበሩት የጎጃም ጉባኤዎች አንዱ በደንበጫ ወረዳ ስር የሚገኘው የደብረ ምጥማቅ ገዳም የቅኔ ጉባኤ ነው። በወቅቱ በዚህ ጉባኤ ይማሩ የነበሩ የቅኔ ተማሪዎች ብዙዎች አዘውትረው ይለብሱት የነበረው፣ ከካኪ የተስፋ ቁምጣ፣ አንዳንዶቹ ሳንቲሙ ያለላቸው ከአቡገዳዲ የተስፋ ረጅም እጀ ጠባብ ከስር ይለብሱና በላዩ ላይ የአቡገዳዲ ነጠላ ይለብሳሉ። በዚያ ላይ ደግሞ የዚያ ዘመን የቆሎ ተማሪ መለያ የሆነው ደበሎ ይደርቡበታል።

ደበሎውን አዘጋጅቶ ልብስ ለማድረግ የአዘገጃጀትና የአሰፋፍ ስርአት ነበረው። በቅድሚያ ከአምስት እስከ አስር የሚሆን የበግ ቆዳ፣ ከተገኘ ጥቁዋቁሩ እንዲገዛ ይደረጋል። የተገዛው የበግ ቆዳ በቀላሉ ለመልፋት እንዲችል ተወቅጦ በደቀቀ ተልባ ወይም ጫቅማ ብጥብጥ በቆዳው የውስጥ ክፍል ይቀባል። የተቀባው ቆዳ ይተጣጠፍና ድንጋይ ወይም ሌላ ከባድ ነገር ተጭኖበት እንዲቆይ ይደረጋል። የተወሰነ ሰአት ከቆየ በሁዋላ እስኪለሰልስ (እስኪለፋ) ድረስ ቆዳው በእግር ይታሻል። መልፋቱ ተረጋግጦ መታሸቱ ሲያበቃ አንደኛው ለምድ (ነጠላ የበግ ቆዳ) ከላይ ተሸካሚ እንዲሆን ይደረግና ከተሸካሚው በስተግርጌ ሌሎች የለፉት የበግ ለምዶች አንዱ ከሌላው ጋር እየተገጣጠሙ በሲር ይሰፋሉ። ደበሎ የሚሰፋው አብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው በተማሪዎች ነው። በተለይ በአሰፋፍ ጊዜ የተለየ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው ማንኛውም ሰው ያለልምድ ሊሰፋው አይችልም።

የተስፋው ለምድ (ደበሎ) ውበት እንዲኖረው ለማድረግ ሲባል ከገበያ አረብ (በቀይ ቀለም የተነከረ ቆዳ) ይገዛና ከግርጌ ያለው የደበሎ ጠርዝ ሲቀር በተስፋው ለምድ ዙሪያ አልፎ አልፎ ዛጎል ወይም ማርዳ እየተደረገበት እንዲያምር ተደርጎ ይዘመዘማል። በዘመኑ የነበሩት የቅኔ ተማሪዎች የዘወትር ልብስ የሆነው ደበሎ (ለምድ) የሚዘጋጀው በዚህ አኩዋሁዋን ነበር። በዚህ መልክ የተዘጋጀው ደበሎም

የዘመኑ የቅኔ ተማሪ መለያ ሆኖ ይቆጠር ነበር። ምንም እንኳዋ ደበሎ ተዘውትሮ የሚለበሰው በቅኔ ቤት ቢሆንም በሌሎችም የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ገባኤዎች ደበሎን መልበስ የተለመደና የሚዘወተር ሆኖ ቆይቷዋል።

በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለው የቅኔ ተማሪዎች አለባበስ ከቀድሞዎቹ የተለየ ሆኑዋል። ከአቡገዳና ከካኪ ጨርቆች እየተሰራ ይለበስ የነበረው ቁምጣና እጀጠባብ በቴትሮንና በካሽሚር ጨርቆች ተቀይሩዋል። ከላይ ይደረቡ የነበሩት የአቡገዳ ነጠላና ደበሎ (ለምድ) ከሱፍ ክር በሚሰራ ጨርቅ (ጎጃም አዘነ) ተለውጡዋል።



የቅኔ ተማሪዎች ከጸሎት በኋላ ከጉባኤ አዳራሽ በመውጣት ላይ ሳሉ፡

የወትሮው የቅኔ ተማሪ የሚለየው በሚለብሰው ለምድ፣ በሚያንግተው አኮፋዳና በሚያንጠለጥለው ቅምጫና ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን የቅኔ ተማሪውን ከአርሶ አደሩ መለየት ያስቸግራል። ተማሪውም ሆነ አርሶ አደሩ የሚለብሱት ልብስ ተመሳሳይ ሆኑዋል ጎጃም አዘነ የተባለው ልብስ የአብዛኛው የጎጃም የገጠር ህብረተሰብ በተለይ ለወንዶች የዘወትር ልብስ ሆኑዋል። በዚህም ምክንያት የወትሮው የቅኔ ተማሪ መለያ የነበረው ደበሎ ሙሉ በሙሉ በጎጃም አዘነ በመለወጡ የጥንቱ የቆሎ ተማሪ ቅርስ ሆኖ የኖረው ደበሎ በየጉባኤዎቹ ለምልክት ማግኘት አልተቻለም የአርሶ አደሮችና



ILS LIBRARY ADD

የቅኔ ተማሪዎች አለባበስ ተመሳሳይ በመሆኑ አንዱን ከሌላው ለመለየት በቅኔ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ተማሪው በጉባኤው ውስጥ ስለቅኔ ትምህርት ሲቀጽል መመልከት የግድ ሆኑዋል፡፡

የቁሳቁስ አጠቃቀምንም በተመለከተ ልዩነቶች አሉ፡፡ የወትሮው የቅኔ ተማሪ ለምግብ መለመኛ ከሰሌን ወይም ከቁጠማ የተሰራ አኮፋዳ ይጠቀም የነበረ ሲሆን ለውሀ መጠጫ ደግሞ የቅል ዘር ሆኖ አንገት ያለው ቅምጫና ያንጠለጥል ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን አኮፋዳውም ሆነ ቅምጫናው ቀርቶ፤ ለምግብ መለመኛ ከእህል ማዳበሪያ መያዣ የተሰፋ ቀረጢት ወይም ፌስታል፣ ለውሀ መጠጫ ደግሞ ዘመኑ ያፈራውን የንጹህ ውሀ ማሸጊያ ላስቲክ ነው የሚጠቀሙት፡፡

የቀድሞዎችን የቅኔ ተማሪዎች ከአሁኖቹ የሚያመሳስላቸው ለልመና ወደ መንደር በሚሰማሩበት ጊዜ ለውሻ መከላከያና ለምግብ እቃቸው ማንጠልጠያ የሚሆን ሁለት ዱላ የሚይዙ መሆናቸውና እንደ አቁዋቁዋምና የቅዳሴ ተማሪዎች ሻሽ (ነጭ ጨርቅ) አዘውትረው የማይጠመጥሙ መሆናቸው ነው፡፡

የዘመኑ የቅኔ ተማሪዎች ደበሎ መልበሱን የተዉት ወደው አይደለም፡፡ አንድ የበግ ቆዳ ወትሮ በአንድና በሁለት ብር ይገዛ ነበር፡፡ አሁን ሰላሳና አርባ ብር ይሸጣል፡፡ በዚህም ምክንያት በሰላሳና አርባ ብር ሂሳብ አምስት ስድስት የበግ አጎዛ ገዝቶ መልበስ ስለማይቻል ጎጃም አዘነን በሀያና በሰላሳ ብር ብቻ ገዝቶ መልበስ ስለሚመረጥ ነው፡፡

የወትሮው የቅኔ ተማሪ መታወቂያ የሆነው ደበሎ እንዲጠፋ ያደረገው ዘመኑ ነው፡፡ ዘመኑ የበግ ቆዳን አስወደደ፡፡ በቀላሉ ሌትም ቀንም ቢለብሱት የሚመች ጎጃም አዘነ የተባለን ልብስ አመጣ፡፡ ዘመኑ ነው የደበሎ ቅርሳችንን ያጠፋው፡፡

ለአንድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ መነሻው የህብረተሰብ እድገት ነው፡፡ ህብረተሰብ በአስተሳሰብና በአኑዋኑዋር እየሰለጠነ ሲመጣ በነባሩ ባህሎችና ልማዶች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ይህም የየዘመናት ክስተት ሆኖ የቆየ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በቅኔ ተማሪ ማህበራዊ ህይወትና የባህል ቅርስ ላይ ለውጥ እንዲከሰት ስልጣኔ አስተዋጽኦ ማድረጉን እንመለከታለን፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የወትሮው የቅኔ ተማሪ ለውሀ መጠጫ ቅምጫናን ይጠቀም ነበር፡፡ የዘመኑ የቅኔ ተማሪ ደግሞ ቅምጫናውን ትቶ ዘመኑ ያመጣውን ለንጹህ ውሀ ማሸጊያ የተዘጋጀን ላስቲክ መጠቀም ጀመረ፣ ከገብያ ገዝቶ፣ ለማሙዋሸት በአተላ ዘፍዝፎ፣ ከብዙ ድካም በሁዋላ የተገኘን ያውም ከጅ አምልጦ ቢወድቅ ወዲያው የሚሰበር ቅል ለውሀ መያዣ ከመጠቀም የዘመኑ ፋብሪካ ያመረተውን የውሀ ላስቲክ መጠቀሙ ስለሚቀል ተማሪው የድሮ ቅርስ የሆነውን ቅምጫና ትቶ ላስቲክ መጠቀምን መምረጡ ጊዜው የወለደው፣ ስልጣኔ ያመጣው ለውጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በቅኔ ቤት ውስጥ የነበሩ ባህሎችና ቅርሶች አብዛኛዎቹ ተለውጠዋል፡፡ ሌሎችም በሂደት መለወጣቸው ግድ ነው፡፡ ይህ ለውጥ መከሰቱ የተፈጥሮ ግዴታ መሆኑ ታውቆ በየጊዜው ተከስተው የሚያልፉ የቅኔ ተማሪውንና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ፤ ባህልና ቅርስ የሚያመለክቱ ቁሳቁሶች ሙዚየም ተከፍቶላቸው በሚገባ ተጠብቀው እንዲገኙ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

### 4.1.4 የሆሳእና አዘገጃጀትና አጠቃቀም

«ሆሳእና» የሚለው ቃል ከዚህ ርእስ ጉዳይ አኳዋያ ሲተረጐም «ትምህርት እንዲቀና ወይም እንዲገልጽ የሚወሰድ መድኃኒት» የሚለውን ትርጉም የያዘ ሆኖ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚዘወተር ቃል ነው። ታደለ ገድሌ በ1997 «ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋታ ለትዝታ» በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ የቅኔ ተማሪዎች በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ስለሚያከናውኑዋቸው የጥበብ ተግባራት እንደሚከተለው ገልጸውታል፡

> ከጥበባቱ ውስጥ «እጸ ፋሪስና እጸ ሳቤቅ» በሚል በአፍልሆ መልክ ለትምህርት ተብሎ የሚሰጠው መድሀኒት አንዱ ነው። ልበ ብርሀን ያደርጋል በሚል የቅኔ ተማሪዎች እብነት (መድሀኒት) ይወስዳሉ። በተጨማሪም መድፍነ ጸር (ጠላት የሚደፍን የሚያጠፋ)፤ መግረሬ ጸር (ጠላት የሚያስገዛ)፤ በአርባ እግር ሰርዶ የሚደገም መስተፋቅር (የሚያፋቅርና የሚያዋድድ)፤ ጥላ ወጊ (የተጻራሪን ጥላ በዘንግ በመውጋት የሚያጠፋ)፤ ግርማ ሞገስ፤ አፍልሆ (መክስተ እውቀት)፤ ጋኔልን በድግምት ስቦ የማነጋገር ኩሸት፤ እጸ መሰውር (የሚሰውር ጥበብ)፤ አንደርብ (የድንጋይ በረዶ በጠላት ላይ በመጣል የሚያስጨንቅ ድግምት)፤ መኑ ስምኪ (ስምሽ ማነው? የናትና የራስን ስም በአስራ ሁለት እየተደገፈ የሚካሄድ ብልሀት)፤ ኮከብ ቆጠራ (የአኗኗር እድልን የሚናገር ጥበብ)፤... በቅኔ ቤት ጎልተው ይታወቃሉ (ታደለ ገድሌ፤ 1997፤ 69)

ታደለ ገድሌ እንዳሉት የቅኔ ተማሪዎች በቅኔ ትምህርት ጉባኤዎች ውስጥ እያሉ የተለያዩ የጥበብ ሙያዎችን ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉ መሆኑ ቢታወቅም የቅኔን ትምህርት ይገልጻል ተብሎ የሚታመነውን ሆሳእና ማዘጋጀትና መውሰድ (መጠቀም) በሁሉም የግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሰፊው የተለመደ ነው። በተለይ በጐጃም የቅኔ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለ ሆሳእና የቅኔ ሊቅ መሆን አስቸጋሪ እንደሆነ ነው አንዳንድ የሙያው ሊቃውንት የሚገልጹት። «ቅኔ ያለ አብሾ ጠላ ያለ ጌሾ» የተሰኘው ብሂልም ለማስረጃነት የቀረበ ነው።

በጐጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚወስዱት የሆሳእና አይነቶች ብዙ ናቸው። ሆሳእናውን ለመውሰድ የፈለገ አንድ የቅኔ ተማሪ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም ይችላል። በአካባቢው ከሚዘወተሩ የሆሳእና አይነቶች መካከል፡ አብሾ፣አፍልሆ፣ እጸ ፋርስና እጸ ሳቤቅ የተሰኙት በሰፊው የተለመዱት ናቸው። በጐጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ስለሚዘወተሩ የሆሳእና አይነቶች፣ አዘገጃጀትና አጠቃቀም መላከ ጥበብ ስሜነህ እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ሆሳእና ማለት ትርጉሙ መድሀኒት ማለት ነው። በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ሆሳእና እየተባሉ ከሚታወቁት ነገሮች መካከል አብሾ፣ አፍልሆ፣ እጸ ፋርስና እጸ ሳቤቅ የተሰኙት የተወሰኑት ናቸው። ሁሉም የየራሳቸው የሆነ የአዘገጃጀትና የአወሳሰድ ስርአት አላቸው። አብሾ፤ ከተወሰኑ የአብሾ ተክል ፍሬዎች የሚቀመምና በመጠጣት ወይም በመዋጥ የሚወሰድ ነው። አፍልሆ ደግሞ ከ41 ዓይነት የተለያዩ ተክሎችና አዝእርት የሚቀመም ሆኖ በሱባኤና በጸሎት የሚወሰድ ነው። እጸ ፋርስ ደግሞ በተለያየ መልክ ተዘጋጅቶ በመጠጣት የሚወሰድ ሲሆን እጸ ሳቤቅ ግን

በሰውነት ውስጥ ግንባር ወይም ክንድ ላይ በመቅበር የሚወሰድ የሆሳእና አይነት ነው (መላከ ጥበብ ስሜነህ 1999 ካ ቁ 1)

እንደ መላከ ጥበብ ስሜነህ አገላለጽ መድኃኒቱ በሚወሰድበት ጊዜ የራሱ የሆነ የአወሳሰድና የአፈጻጸም ስርዓት አለው፡፡ አንዳንዱ ዶሮ ሲጮህ እስከማይሰማበት ድረስ ወደጫካ በመሄድ ለሆሳእናው መውሰጃ ጉጆ ቀልሶ፣ ሰባኤ ተገብቶ፣ ጥሬ እየተበላና ጸሎት እየተደረሰ የሚወስድ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ለሆሳእናው መውሰጃ ተጨማሪ ገቢር ተዘጋጅቶለት መድኃኒቱን የወሰደው ተማሪ በወሰደው ሆሳእና መንፈሱ ተቃውሶ በሮ እንዳይጠፋ እየተጠበቀና የሆሳእናው ማስታገሻ ሌላ ገቢር ተዘጋጅቶለት በጥንቃቄ የሚወሰድ መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡

ሆሳእና በተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ እያሉ የሚወድ፣ አእምሮን የሚያሰላ፣ ልቦናን የሚያበራና ከአምላክ የተሰጠ ቅመም እንደሆነ የሚገልጹት ደግሞ ጉጃም ውስጥ ሽለል ገብርኤል በተባለ ደብር የሚኖሩት ደብተራ ብርሃን ናቸው፡፡



ሽለል ገብርኤልና በአካባቢው የሚኖሩ፤ ከግራ ወደቀኝ የመጀመሪያው መሪጌታ ማማሩ፤ ሁለተኛው መሪጌታ ታንት ይገኝ፤ ሶስተኛው ደብተራ ብርሀን፤

ሆሳእና አእምሮን የሚያሰላ ልቦናን የሚያበራ ከአምላክ የተሰጠን በረከት ነው። አወሳሰዱ እንደየባለሙያው የተለያየ ነው። ሆሳእናውም በተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ እያሉ ሊሰጥ ይችላል። በእናት ማህጸን ወስጥ ሳለ የሚወስድ አለ፤ ገና በህጻንነት እድሜ እያለ የሚወስድ አለ፤ የቅኔን ትምህርት ከመጀመር በፊትም የሚወስድ አለ፤ የቅኔ ጥበብ ከገባው በሁዋላም አይናፋርንትንና አይነጥላን ለመካላከል ሲባል የሚወስድ አለ (ብርሃን 1999 ኪ.ቁ.5)

በተለያየ መልክ የሚወስደው ሆሳእና በትክክል ሲሰምር የሚስተዋሉ የተለያዩ ምልክቶች እንዳሉ የሚገልጹት ደግሞ መሪጌታ ታንትይገኝ ናቸው። እንደ መሪጌታ ታንትይገኝ አገላለጽ የተወሰደው መድሀኒት የሰራ መሆኑ የሚታወቀው መድኃኒት የወሰደው ተማሪ በወቅቱ የሚያሳያቸውን ምልክቶች ነው በማስረጃነት የሚጠቀሱት።

መድኃኒቱን የወሰደው ተማሪ መንፈሱ ይለወጣል፤ ህሊናው ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ረቆ ሰማየ ሰማያት ይዘልቃል። እመቤታችን ምስለፍቁር ወልዳ፣ ስላሶች ኪሩቤል እንደተሸከሟቸው፤ ጻድቃን፣ ነበያትና ሰማዕታት በክብር እንደተቀመጡ በአይነ ህሊናው ይታዩታል። ለወደፊት የሚሆነው ነገር ሁሉ ይገለጽለታል። በአጠገቡ ያሉትንም ሆነ የሌሉትን ሰዎች በስም እየጠራ ለወደፊት ሊገጠማቸው የሚችለውን እድላቸውን በግልጽ ወይም በምልክት ይገልጽላቸዋል። በዚያን ወቅት መድኃኒቱን የወሰደው ተማሪ የሚናገረው ሁሉ እውነትና የሚፈጸም መሆኑ አያጠራጥርም (መሪጌታ ታንትይገኝ 1999 ኪ. ቁ. 4)

ሆሳእና በመድሀኒትነት ለቅኔ ተማሪዎች በሚሰጥበት ጊዜ የተለያየ የአፈጻጸም ስርአትና ባህል እንዳለው አባቶች ገልጸውታል። የዚህ ጥናት አቅራቢም በ1969 ዓ.ም በጉጃም፤ ደገሞ ውስጥ ጫልቀ ሚካኤል በተባለው የቅኔ ጉባኤ ውስጥ የቅኔ ተማሪ ሆኖ የጉባኤው አባል በነበረበት ጊዜ የተመለከተውን የሆሳእና አወሳሰድ ስርአት በምሳሌነት እንዲቀርብ አድርጓል።

በወቅቱ በቅኔ ጉባኤው ውስጥ ሆሳእና በመስጠት የሚታወቁት የኔታ ዲበኩሉ የተባሉ የጉባኤው ዘራፊ ነበሩ። ተማሪ አለም ቀረ የተባለ የጉባኤው አባል ዘራፊው የፈለጉትንና የጠየቁትን ሁሉ በማሟላቱ ሆሳእናውን የመውሰድ እድል አገኘ። እድሉ እንደ ተሰጠው ሆሳእናውን የሚወስድበት ከጉባኤው ራቅ ያለ አዲስ ጉጆ ስርቶ ማዘጋጀት ስለነበረበት፣ ጉጆውን በመስራትና በውሎ ጸሎት እንዲያግዙት ከመረጣቸው ተማሪዎች መካከል የዚህ ጥናት አቅራቢ አንዱ ነበር። ጉጆዋ ተሰርታ ካበቃች በሁዋላ ለእርዳታ የተመረጡት ተማሪዎች በጉጆዋ ዙሪያ ቆመው ቀኑን ሙሉ ጸሎት ሲያደርሱ ዋሉ። ሆሳእናውን የሚወስደው ተማሪ አለም ቀረም በእለቱ ምንም አይነት ምግብ እንዳይቀምስ ተከልክሎ ከጉዋደኞቹ ጋር አብሮ ጸሎት ሲያደርስ ዋለ። ስአቱ እየመሸ ሲሄድ የአዲሱዋ ጉጆ ወለል በለምለም ሳር ተሸፈነ። በላዩ ላይ ምንም ነገር ያልነካው አዲስ ሰሌን ተነጠፈበት። ጸሀይ ወደ ማደሪያዋ ለመግባት እግሮቿዋን መዘርጋት ስትጀምር ሆሳእናውን የሚሰጡት የኔታ ዲበኩሉ ወደ ጎጆዋ መጡና ዝቅ ብለው በተተከለ ድንጋይ ላይ ቆመው ከቀንድ በተሰራ ዋንጫ ውስጥ በያዙት ሆሳእና ላይ እፍ እፍ እያሉ ጸሎት ሲያደርሱ አመሹ።

በመጨረሻ፤ የኔታ ዲበኩሉ የጸሎት ስነስርዓቱ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል አዝዘው፤ አለም ቀረን አስከትለው ወደ ጉጆዋ ገቡ። ስነ ስርአቱ መልክአ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስ፣ መልክአ ሚካኤልና መልክአ ገብርኤል በመድገም ቀጠለ። ከተወሰነ ደቂቃ በሁዋላ የኔታ ዲበኩሉ የጸሎት ስነ ስርአቱ ሳይቋዋረጥ እስከንጋት መቀጠል እንዳለበት አዝዘው ከጉጆዋ ወጥተው ወደ ጉባኤው ተመለሱ። የጸሎት ስነስርአቱ ቀጠለ። በግምት ከሶስት ሰአት በሁዋላ የአለም ቀረ ድምጽ መሰማት ጀመረ አንዳንዴ ቃለ እግዚአብሄር ይጮሀል። ሌላ ጊዜ የመምህራንን ቅኔ ያስተጋባል። የጸሎት ስነስርአቱ ቀጥሎዋል።

በዚህ ሁኔታ የተወሰነ ሰአት ከቆየ በሁዋላ የኔታ ዲበክሉ በድንገት መጥተው መብራት እያበሩ ወደ ጉጆዋ ገቡ። ቃል እግዚአብሄር መጮሁ ቀጠለ። አልፎ አልፎ የቅኔ ዜማም ይሰማል። በዚህ ሁኔታ ለትንሽ ደቂቃ ከቆየ በሁዋላ አለም ቀረ፤ የጉዋደኞቹን ስም እየጠራ የእያንዳንዱን የወደፊት እጣ ፈንታ መተንበይ ቀጠለ። ግብርና ለሚከፍለው የግብርን ሙያ በምልክትና በድምጽ እያሰማ፤ ወታደርነት ለሚበጀው ዱላ እያነሳና እንደ ጠመንጃ እያነገተ፤ የመንግስት ቤት ለሚበጅው የቤተ መንግስትን ስራ በድምጽና በምልክት እያሳየ፤ ቤተ ክህነት ለሚከፍለው ቃል እግዚአብሄር እየጮኽ ሲቀባጥር ካመሸ በሁዋላ የኔታ ዲበክሉ በጠቆረ ብርሌ ከያዙት የሆሳእና ማርከሻ ቅመም እንዲቀምስ አደረጉት። ቀስ በቀስ አእምሮው መድከም፤ ልፍለፋውም መቀነስ ጀመረ። ከጉዋሮ የተጀመረው ጸሎት እንደቀጠለ ነው። አለምቀረ ብዙም ሳይቆይ ሰሌኑ ላይ ተጠቅልሎ ተኛ። የጸሎት አደራረስ ስነስርአቱ ግን አለምቀረ ከተኛበት እስኪነቃ ድረስ እንደቀጠለ አደረ።

ከላይ የተገለጸው ታሪክ ጥናት አቅራቢው በአካል ተገኝቶ ስለ ሆሳእና አወሳሰድ የተመለከተው ነው። በጥናት አቅራቢው እምነት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ የትምህርት ተቅዋማት የሚዘወተረውና የተለያየ የአፈጻጸም ስርአት ያለው ሆሳእና አይነቶቹ፣ አዘገጃጀቱ፣ የአወሳሰድ ስርአቱና የሚያስገኘው ውጤት በዝርዝር ራሱን ችሎ ሊጠናና ሊመረመር የሚገባው፣ በግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚዘወተረው ሌላው የሀገራችን ባህላዊና ጥበባዊ ቅርስ መሆኑን መጠቆም ተገቢ ነው።

#### 4.1.5 በደመና መነጠቅና በንፋስ ሰረገላ መክነፍ

ይህ ጽንሰ ሃሳብ በአንዳንድ የጐጃም የቅኔ ሊቃውንትና መምህራን ዘንድ እሁን ድረስ በነበረ እየተገለጸ ያለ አስተሳሰብ ነው። ለአስተሳሰቡ መኖር የተለያዩ መነሻዎች አሉት። በግእዝ ቅኔ አመጣጥ ታሪክ ውስጥ ስለ ደቀ እስጢፋ ወይም ተዋነይ የተገለጸውን ሃሳብ መነሻ የሚያደርግና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣ ይመስላል። በቤተ ክርስቲያን አፋዊ የጥበብ ታሪክ ውስጥ በደመና መጫን፣ በንፋስ ሰረገላ መክነፍ፣ መሰወር፣ መገለጥና የተለያየ ራእይ ማየት በሰፊው ሲነገር የኖረ አፋዊ የሆነ ሌላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በቅኔው ሙያ ለብዙ ዘመናት የቆዩ አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚናገሩትና እንደጻፉት፣ ደቀ እስጢፋ የተባለው ኢትዮጵያዊ ወደ ግሪክ (ጽርእ) ሄዶ ሰባት ዓይነት የሚያስደንቁ የፍልስፍና ጥበባትን ተምሮ እንደተመለሰ፣ ከሰባቱ መካከል ስድስቱ የጥንቆላ ጥበቦች በመሆናቸው በሀገሩ ህዝብ ዘንድ ተጠልተው ተቀባይነትን ያላገኙ በመሆናቸው በስውር (በህቡእ) እየተሰራባቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ እስካሁን ድረስ እንደሚኖሩ፣ ሰባተኛው የፍልስፍና ጥበብ የሆነው ቅኔ ግን በግጥሙ፣ በሚስጥሩ፣ በቃል አሰካከሩና በርቀቱ በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን ስላገኘ ሁሉም በግልጽ እንዲማረውና ለቤተ ክርስቲያንም አገልግሎት እንዲውል ስለመደረጉ ተገልጹዋል::

የግእዝ ቅኔንና በውስጡ እንዳሉ የሚገለጹትን የተለያዩ ጥበባት ሃይማኖታዊነት አጉልተው የሚገልጹት ደግሞ እነ አለቃ ኤልያስ ናቸው:: አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልኡልና ቀሲስ ክፍያለው መራሄ ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ በተለይ በደመና ስለመጫንና በነፋስ ሰረገላ ስለመክነፍ ሰፊ ሀተታ አቅርበዋል::

> የሀገራችን መምህራንና ሊቃውንት በአለም ታሪክ ከተጻፉት ስጋውያን ፈላስፎች በመንፈስ ቅዱስ ተለይተው ይታወቃሉ:: በጥበብ ስጋዊና በጥበብ መንፈሳዊ ታውቀው፣ መላእክትን መስለው፣ በምስጢረ ሰማያት ተራቀው፣ በሰማያዊ ማዕረግ መጥቀው፣ በምስጢር ሰረገላ እየበረሩ፣ አለማትን ዙረውና የተቻላቸውን መርምረው ተመልሰው በቀድሞው ቦታቸው በተገኙ ጊዜ ንጹህን መምህራን፣ ሊቃውንት፣ ክቡራን አእማደ ቤተ ክርስቲያን ተብለው በቅድስና ስም ለመጠራት እድል ያገኙት ይህን በመሰለው መንፈሳዊ ሀብት ነው:: ተዋነይ ከጐጃም ወደ ጐንደር፣ ከጐንደር ወደ ጐጃም በጣና ባህር ላይ ሲመላለስ ያለመርከብና ያለጀልባ ጥልቁንና ማዕበሉን እንደመስክ እየተረገጠው በተሰጠው ጸጋ፣ ፍልስፍና የቅኔ እውቀት እንደ ንስር ይበር ነበር:: በጣና ባህር ዙሪያ የነበሩ ታላላቆችም ሆኑ ህፃናት ይህንን ታምር እያዩ «ተዋነይ በጣና ይመስላል ደመና» እያሉ ይዘምሩለት ነበር ይባላል:: ክፍለ ዮሐንስም ፈጣሪውን በመአልትና በሌሊት አዲስ ምስጋና በቅኔ ያመሰግነው ስለነበር ንጽህናና ቅድስና ተሰጥቶት ፈጽሞ በቅቶ፣ በደመና ተጭኖ የጥር ስላሴም ሆነ የሀምሌ ስላሴ ሸዋ ባለው ደብረ ብርን ስላሴና ጐንደር ባለው ደብረ ብርን ስላሴ በአንድ ቀን ከሁለቱም ቦታ እየታየ የጐንደርንም ሆነ የሸዋውን ህዝብ ክፍለ ዮሐንስ ዛሬ የዋለው እኛ ዘንድ ነው እያሉ ይነጋገሩበትና ይደነቁበት ነበር:: እርሱም በቅኔው «እነሂ ወግበረ ቅኔ ዘበሆሳዕና፣ እምእደ ገፋኢ ወተገፋኢ ንትመሰጥ በደመና» ትርጉሙም፤ በሆሳዕና ያለን የቅኔ ጥበብና እኔ ከገፊውና ከተገፊው እጅ በደመና እንነጠቃለን፤ እያለ ርቀቱን ይገልጽ ነበር (እነ አለቃ ኤልያስ፡ 1992፡ 20-21)::

እነ አለቃ አልያስ በጻፉት በዚሁ መጽሀፍ ገጽ 325 ላይ ስለተዋነይ የፍልስፍና እና የጥበባት ሊቅነት ተጨማሪ ሃሳብ አስፍረዋል:: የጎጃሙ የግእዝ ቅኔ መስራች ተዋነይ፤ አገሩ ጎጃም፣ ይልማና ወረዳ ቆለላ ከተባለ አካባቢ፣ በጎንጅና በጃላሎ እጠገብ ከሚገኘው ልዩ ስሙ ወንደል ተክለ ሀይማኖት ከተባለ ቦታ የተወለደ መሆኑ ተገልጽዋል:: የኖረበትም ጊዜ በአጼ በካፋ ዘመነ መንግስት ሲሆን በዘመኑ እያሌ ተአምራትንና ጥበባትን ይፈጽም እንደነበር በተለያዩ ቅኔዎቹ ገልጾ ያለፈ መሆኑን ጠቅሰው ከቅኔዎቹ መካከል አንዳንዶቹን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ::

ከተጠቀሱት ቅኔዎች አንዱ በአጼ በካፋ ዘመነ መንግስት ወቅት በተዋነይ፣ በንጉሱና በንጉሱ ባለሙዋሎች መካከል የተፈጠረን ክስተት መነሻ ታሪክ በማድረግ ለንስሀ ሞት የተቀኘውን መወድስ ቅኔ አስፍረውታል።

ሀ. የቅኔው መነሻ ታሪክ

ንጉስ አጼ በካፋ ግብር አግብተው መኩዋንንቱን በሚያበሉብትና እርሳቸውም ምሳ በሚጋበዙበት ጊዜ ተዋነይ በእጸ መሰውር መጥቶ ማንም ሳያየው ከንጉስ ማእድ ቀርቦ ይመገብ ነበር። ታድያ ለንጉሱ የሚሰጠው የተወሰነ ምግብ ሲሆን እርሱ ቀርቦ የሚበላበት ጊዜ ንጉሱ ሳይጠግቡ እየቀሩ ፣ ስጡኝም እንዳይሉ እያፈሩ በረሀብ ሊሞቱ ሆኑ፤ በጣም ከሱ መነመኑ። ሊቃውንቱና መኩዋንንቱ ቀርበው በምን ምክንያት ነው ሰውነትዎ እያለቀ የሄደ? አይበሉም እንዳንልዎ ይበላሉ፤ ታመዋል እንዳንል አልታመሙም፤ ደህናነዎት። ምክንያቱ ምንድነው?» ብለው ጠየቁዋቸው። አጼ በካፋ ነገሩ እያስገረማቸው፤ ከጠየቁዋቸው ዘንድ «እኔ የምትሰጡኝ ምግብ ያው የተወሰነልኝ አላነሰኝም ነበር። ነገር ግን የሚወስደውን አላውቅም፤ ያልቃል። እኔም አልጠግብም» አሉዋቸው። ከዚህ በሁዋላ ብዙ ሊቃውንትና ጠቢባን ስለነበሩዋቸው ተመካክረው ጉዳዩን ይከታተሉ ጀመር። ከሊቃውንቱ አንዱ የሆነው አፈ ንጉስ ውሂብ በረቂቅ ፍልስፍና የታወቀ ሰው ስለነበር እጸ መክስት ይዞ በማእዱ ጊዜ ሲጠባበቀው እርሱስ ተዋነይ ኖሩዋል። ቀርቦ ከንጉስ ጋር ሲበላ ያዘው። ተዋነይም ደነገጠና እንደምንም ብሎ እጸ መሰውሩን ሰውሮ ከንጉሱም ከሊቃውንቱም ጋር ይነጋገር ጀመር። አጼ በካፋም ተዋነይ ተመልሶ ወደ ጐጃም እንዳይሄድ በአፈ ንጉስ ውሂብ ጠባቂነት እንዲቆይ ተደረገ። ለጥቂት ጊዜ እንደቆየ ወደ ጐንጅ ተመልሶ እጸ ህይወት የሚላትን እንጨት እንደገና ፈልጐ ካገኘ በሁዋላ ህያው ሆኖ ለመኖር እስቦ በአዲስ ሽክላ ዘፍዝፎና ከእልፍኝ ገብቶ አንዱን ህፃን አፍስስብኝ አለው። ህጻኑም የታየው ነገር አይታወቅም ደንግጦ እኩሌታውን አካሉ ላይ አፍሰሰበት። እኩሌታው አካሉ ላይ ሳይፈስበት ቀረና የፈሰሰበት ሰውነት ህያው ሆኖ ያልፈሰሰበት ግን ምውት ሆኖ ለሰባት አመታት ቆይቶ በሰባተኛ አመቱ የሚከተለውን ቅኔ በንስሀ መልክ ለእግዚአብሄር አቀረበ። እግዚአብሄር ቸር ነውና በሞት አሰናበተው (እነ አለቃ ኤልያስ፡ 1992፣ 325-326)።

ለ. መወድስ ቅኔ

ስህተኒ አእርፍ እምጻማ ተፈጥሮ
እንበለ እሁር ብርከ ሀበ ኢይገብእ ሞት፣
ወሰዱቅ ልብከ በኩሉ ትእግስት፣
እስመ አንተ ለሀኩሁ እምልህኩተ ስጋ ለስጋ ልህኩት

እግዚአብሄር ከመ ሞጣህት
ዘትዌልጦ ለሰብእ ወትሴስዮ ከመ ትካት

አለም
እመኒ ህጣውእየ አድባረ ህጺን ወብርት
መጠነ አህቲ ህጠተ ሆጻ በቅድመ አይንከ መህረት
ወከመ ኢይበልክ አንሰ ከቡደ ቀኖና መዝራእት
ፈተንኩከ በምናሴ ወአእመርኩከ በዳዊት

መ. ትርጉሜ

እኔ ባሪያህ ወደ ማልመለስበት ሞት ከመሄዴ አስቀድሞ ከተፈጥሮ ድካም አስፈታኝ። ልቦናህ በትእግስት እንኮይ የተኮላ የስጋን ስራ ከስጋ የምትፈጥረው አንተነህና ሰውን እንደመጋረጃ የምትለውጠው ሰውንም እንደቀደመ የምታደርገው ማለት እንዳልነበረ የምታደርገው እግዚአብሔር ሆይ ወደማልመለስበት ሞት ከመሄዴ አስቀድሞ ከተፈጥሮ ድካም አሳርፈኝ። ምንም ህጢያቶቼ የማይገፉ የብረትና የብርት ተራራዎች ቢሆኑ ቸርነት ገንዘቡዋ በሆነው አይንህ ፊት የአንዲት አሸዋ ቅንጣት መጠን አያህልም። እኔም ቀኖና ክንደህ የከበደ ነው እንዳልል በምናሴ ፈተንኩህ በዳዊትም አየሁህ እነሱን በይቅርታ ከህጢያት ነፃ አውጥተህቸዋልና (እነ አለቃ ኤልያስ፡ 1992፣ 325-326)።

በደመና ስለመጫን፣ በንፋስ ስለመክነፍ፣ ስለ እጸ መሰውርና ስለ እጸ መክሰት በግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥና በሙያው ሊቃውንት ዘንድ ለረጅም ጊዜ በአፈ ታሪክነት ሲነገር የኖረና ከአንዱ ወደ ሌላው በይባላል እየተላለፈ የኖረ አፈ ታሪክ መሆኑን ብዙ የሙያው ሰዎች ይገልጹታል። ስለዚህ ጉዳይ አስመልክቶ ጥያቄ የቀረበላቸው በድንግራ ማርያም ከ50 አመታት በላይ በቅኔ መምህርነት የኖሩት መሪጌታ ለይኩንም ሆነ መላከ ጥበብ ስሜነህ የየግላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል።

> በአፈ ታሪክ እየንታ እጹብና መምህር እንባቆም የተባሉ የጐንጅ የቅኔ ሊቃውንት በደመና ይጫኑ፣ በነፋስ ሰረገላ ይከንፉ እንደነበር የሚነገር አፈታሪክ አለ። «እየንታ እጹብ ጐንደር ከብር ይእቲ ጮኸው አክሱም እጣነ ሞገር ይቀኙ ነበር» እየተባለ ይነገራል። እኔ በደረስኩበት ዘመን ይህን ነገር አልተመለከትሁም። በሌላ በኩል ደግሞ «ተዋነይ ደቀ እስጢፋ በነበረ ጊዜ ወደ ምስራቅ የምትፈልቅ ምንጭ ነበረችው። ከዚያች ውሀ የጠጣ ሁሉ ቅኔን የመዝረፍ ክህሎት ይኖረዋል» የሚባል አፈታሪክ አለ። ይህንን ነገር እኔ በነበርኩበት ዘመን አልተመለከትኩም። ትክክልም ነበር ብዬ ለማመን እቸገራለሁ (መላከ ጥበብ ስሜነህ፡ 1999፡ ቃ.ቱ. 1)

ታዋቂው የጐጃም የቅኔ መምህር መሪጌታ ለይኩንም የሰጡት አስተያየት ከመላክ ጥበብ ስሜነህ አስተያየት የተለየ አይደለም። በደመና ስለመጫን፣ በንፋስ ስለመክነፍም ሆነ በእጽ ስለመሰወር በአፈ-ታሪክነት በሰፊው የሚነገር ስለመሆኑ ገልጸውታል። ይሁን እንጂ በማስረጃ የተረጋገጠ ትክክለኛ ታሪክ ነው ብለው ለማመን እንደሚቸገሩ ነው መምህር ለይኩንም የገለጹት (ለይኩን 1999 ካ.ቁ.3)።

በዚህ ርእስ ጉዳይ ስር የቀረበው የተለያየ ሃሳብ ሲመረመር የተነሱትን ውስን የጽሁፍና የቃል መረጃዎች ብቻ መነሻ አድርጐ አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው። ብዙዎቹ ታሪኮች ከአፈ ታሪክነት የዘለለ እውነታን የሚያመለክቱ አይደሉም። በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡትም ሆነ በጽሁፍ ያሰፈሩት አባቶች የሚሰጡት ሃሳብ ወጥነት የለውም። የአንደኛውን አስተሳሰብ ሌላኛው ሲቃወመው ይስተዋላል።

ይሁን እንጂ በሀገራችን እጅግ ተስፋፍቶ የኖረውና አሁንም ድረስ እየተስፋፋ የሚገኘው የተለያየ የጥንቆላ ስርአት፣ ራስን መሰወርና መግለጽ፣ በደመና መንሳፈፍም ይሁን በንፋስ ሰረገላ መክነፍ የተሰኙ ታሪኮች መነሻቸውን መመርመሩ ተገቢ ነው ለመነሻ ያህል በዚህ ጥናት ውስጥ ደቀ እስጢፋ ግሪክ (ጽርእ) ሄዶ ተምሮ አምጥቱዋቸዋል እየተባሉ የተገለጹት ሰባቱ የፍልስፍና ጥበባትም በዘፈቀደ ሊተው የሚገቡ ሀሳቦች አይደሉም። መነሻ ሀሳቡ በዚህ መስክ ጥናት ምርምር ለማድረግ የሚፈልግን ሰው ህሊና የሚኮረኩር በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆን አለበት።

ደቀ እስጢፋ በቅኔው ጥበብ ምክንያት ከንጉሱ ከእስክንድር ጋር ወዳጅነት መስርቶ ይኖር እንደነበር፣ በነበረውም ግንኙነትና ቅርርብ ምክንያት በንጉሱ ሚስት ተጠርጥሮ ሀሜት እንደደረሰበት፣ ሀሜታውም ለንጉሱ ጆሮ ይደርስና ደቀ እስጢፋን ይዞ ለማሰር በሞከረ ጊዜ ግሪክ (ጽርእ) ከተማረው በአንደኛው የመሰወር ጥበብ ተጠቅሞ የንጉሱን ሚስት በመያዝ ተሰውሮ የጠፋ ስለመሆኑ ተገልጿዋል። የታሪኩንም ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በንጉሱና በደቀ እስጢፋ መካከል ስለተፈጠረው ጉዳይ የሚያስረዳ ንጉሱና ደቀ እስጢፋ የተቀኙዋቸው ቅኔዎች በጽሁፍ ሰፍረዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የቅኔ ፍልስፍና መሰረቱ ሃይማኖታዊ ያልነበረና ራሱን የቻለ ጥበብ የነበረ መሆኑን፣ ሆኖም በዘመኑ እጅግ ገኖ ከነበረው የሃይማኖት ስርአት በስተቀር ሌላ መጠጊያ ስላልነበረው ወደ ሃይማኖታዊ ስርአቱ የተጠጋ ስለመሆኑ የሚገልጹ አባቶችም እንዳሉ ቀደም ሲል ተገልጿዋል።

«አውደ ነገስት» እየተባለ በሚጠራው መጽሀፍ መግቢያ ውስጥ፣ መጽሀፉ በደሴተ ጣና፣ ደቀ እስጢፋ ከተባለ ደብር የተገኘ ስለመሆኑ መገለጹ ደግሞ ስለ ደቀ እስጢፋ ጠቢብነት ለተነሳው ነጥብ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠውና ሰፊ ምርምር ሊደረግበት እንደሚገባ የሚገፋፋ ነው። ይህን አስመልክቶ በ1997 ዓ/ም በገብረ ስላሴ ብርሀኑ አሳታሚነት «ሓተታ መናፍስት ወአውደ ነገስት ከነጠልሰሙ» በሚል ርእስ በታተመው መጽሀፍ ገጽ- 151 ላይ «ንጽሀፍ እንከ ዘንተ መጽሀፈ ዓውደ ነገስት

ዘተረክበ በደሴተ ጣና እምደብረ ደቀ እስጢፋ፣ በደሴተ ጣና ደቀ እስጢፋ በተባለው ደብር ስለተገኘውና አውደ ነገስት ስለተባለው መጽሀፍ እንጽፋለን..!» የሚል ሀሳብ ሰፍሩዋል።

የተገለጹት አሳቦች ተደምረው ሲታዩ የሚያመለክቱት አንድ አቢይ ቁም ነገር ያለ ይመስላል። ስለ ግእዝ ቅኔ አመጣጥ ታሪክ በሚወሳበት ጊዜ፣ በጣና ደሴት «ደቅ» በተባለ ቦታ ለብዙ ጊዜ መኖሩና የቅኔን ምስጢር ማራቀቁ የተገለጸው ደቀ እስጢፋ ወይም ተዋነይ ቅኔንና ልዩ ልዩ የፍልስፍናና የጥንቆላ ትምህርቶችን ከግሪክ (ጽርእ) አምጥቷቸዋል መባሉ፣ እንዲሁም «አውደ ነገስት» የተሰኘው የፍልስፍናና የጥንቆላ መጽሀፍ መነሻው ደቀ እስጢፋ ከተባለው ደብር እንደሆነ መጠቀሱ፣ ቅኔና አብረውት መጥተዋል የሚባሉት የጥንቆላና የፍልስፍና ጥበባት እንደማንኛውም የቤተክርስቲያን አገልግሎት በማየት ብቻ የሚተው ሳይሆን ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሰፊ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው።

ደቀ እስጢፋ (ተዋነይ) እንደኖረ በሚጠቀሰው 15ኛው ክፍለ ዘመንም ይሁን ከዚያ በሁዋላና በፊት የኢትዮጵያን የእምነትና የጥበብ ስርአት ከግሪክ የፍልስፍናና የእምነት ጥበባት ጋር ሊያገናኛቸው የሚችል ሀረግ ስለመኖሩ፣ በጥንታዊዎቹ የግሪክ የፍልስፍናና የጥበባት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደቀ እስጢፋ ከግሪክ አምጥቷቸዋል የሚባሉት ቅኔ፣ የተለያዩ የጥንቆላ ፍልስፍናዎችና አውደ ነገስት በተባለው መጽሀፍ ውስጥ የሰፈሩት ጥበባት በግሪክ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ስለመሆናቸውና የወቅቱ የግሪክ የፍልስፍና ጥበባት በኢተዮጵያ ከነበሩት ጥበባት ጋር ቁርኝት ያላቸው ስለመሆናቸው መመርመሩ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በአፈ ታሪክነት እየተነገሩ ስላሉት በደመና ስለመጫን፣ በንፋስ ሰረገላ ስለ መክነፍ፣ ስለ መሰወር፣ ስለ መገለጥ፣ ስለ ጥንቆላና ስለ ሌሎች ጥበቦች መነሻ ፍንጭ የሚሰጥ ሃሳብ ለማግኘት የሚረዳ ይመስላል።

### 4.1.6 የግእዝ ቅኔ መነሻ ታሪክና የአተራረክ ስልት

ለግእዝ ቅኔ መኖር መሰረት ከሆኑት ነጥቦች አንዱ ታሪክ ነው። በስርአተ ቅኔ ውስጥ ታሪክ የሚባለው በየእለቱ እየተፈራረቁ የሚዘከሩ የስላሶች፣ የመላእክት፣ የነቢያት፣ የሰማእታት፣ የጻድቃን፣ የመነኮሳትና የሊቃውንት ታሪኮች፣ ወቅት እየጠበቁ የሚመጡ የተፈጥሮ ክስተቶች፣ ማለትም የእጸዋት መለምለም፣ መጠውለግና መድረቅ፣ የሰብሎች መብቀል፣ ማደግ፣ ማበብና ማፍራት፣ የመብረቅ፣ የማእበል፣ የደመና፣ የዝናም፣ የጐርፍና የጭቃ መከሰትና የሚያሳድሩት ተጽእኖ፣ በስርአተ ሃይማኖቱ ተደንግገው የሚጾሙ አጽዋማት (አቢይ ጾም፣ ጽጌ ጾም፣ ፍልሰታ . . ) በህብርና በውስጠ ወይራ የተመሰጠሩ ስነ ቃሎችና የአነጋገር ፈሊጦች ተካተው የሚቀርቡበት የሰምና የወርቅ መሰረት የሆነ የትምህርቱ አንዱ ክፍል ነው።



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ታሪክ በግእዝ ቅኔ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው የጥበብ ዘርፍ ነው። ቅኔን ቆጥሮ ለመምህሩ ለመንገርም ሆነ የጉባኤው ማስተማሪያ የሚሆን ቅኔ ለመዝረፍ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነት ስርአት በሚደነግገው ቀኖናዊ ህግ መሰረት በየክብረ በአላት ላይ የሚቅርቡ የተለያዩ የቅኔ አይነቶችንና እጣነ ሞገር ለመቀኘት እንደየቅኔው ባህሪ ለሰምና ለወርቁ መሰረት የሚሆን ታሪክ የግድ ያስፈልጋል።

ከዚህ አኩዋያ የተለያዩ ሊቃውንት ስለቅኔ ታሪክ መሰረቶች የየግላቸውን ሀሳብ ገልጸዋል። መላከ ጥበብ ስሜነህና ምስጢረ ሰዋሰው እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> ቅኔውን ማመስጠር የሚቻለው ከተለያዩ ታሪኮች በመነሳት ነው። ከብሉያት፣ ከሀዲሳት፣ ከመጽሐፈ መነኮሳት፣ ከመጽሐፈ ሊቃውንት፣ ከስነ ቃላትና ከአነጋገር ዘይቤ በመነሳት ነው የቅኔ ምሁራን ቅኔውን በስምና ወርቅ እያስተሳሰሩ የሚገነቡት (መላከ ጥበብ ስሜነህ፣ ከሌት ቁ.1)።

> መጻህፍት ለአገባብና ለቅኔ ትምህርት የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው። . . ትርጓሜ መጻህፍት ተምሮ የመጣ የቅኔ ተማሪ በታሪክና በሚስጢር ምርምር በኩል ትምህርቱ እንደሚገባው ይገመታል (ምስጢረ ሰዋሰው፣197፣24)።

ቀደም ብሎ ስለቅኔ ታሪክ ምንነትና መከሰቻዎች በተለገጸበት ወቅት የቅኔ ታሪክ መሰረት የሆኑ ጉዳዮች ተጠቅሰዋል። ከተጠቀሱት መካከል፣ በየእለቱ ለሚዘከሩ በአላት መታሰቢያ የሚተረከውን ታሪክ የተመለከተው ነው። በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስርአተ ሃይማኖት እንደተደነገገው፣ በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ባሉት ሰላሳ ቀናት ሁሉ የሚዘከሩ አንድና ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያየ ታሪክ ያላቸው በአላት አሉ። ለምሳሌ በየወሩ የመጀመሪያ ቀን የልደታና የዮሀንስ መታሰቢያ ይዘከራል። ይህም ታሪክ ቅኔን ለመቀኘ ት በመነሻ ታሪክነት ያገለግላል። በዚህ መልክ በሚታወቁ ከወሩ የመጀመሪያ ቀን እስከ ወሩ መጨረሻ በመታሰቢያነት የሚዘከሩ በአላት ስለሚኖሩ አመቱን በሙሉ ያሉት ቀናት የቅኔ መቁጠሪያ ታሪክ ይኖራቸዋል። አንድ ጉበዝ የቅኔ ተማሪም የቅኔውን ችሎታ ለማበልጸግ በየጊዜው የሚተረክለትን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል።

ለቅኔ ታሪክ መነሻ የሚሆኑት ሌሎች ጉዳዮች ደግሞ በወቅቶች መፈራረቅ ምክንያት የሚከሰቱ ተፈጥሩዋዊ ክስተቶች ናቸው። ለምሳሌ ያህል በክረምት ወቅት አብዛኛዎቹ እጸዋት፣ አዝርእትና ተክሎች የሚለመልሙበት፣ የተወሰኑት ደግሞ ጠውልገው ቅጠላቸውን የሚያረግፉበት፣ ወንዞች ሞልተው የሚጥለቀለቁበት፣ ባህሮች በማእበል የሚናወጡበት፣ ሰማይ በመብረቅ የሚታረሰበትና በደመና የሚሸፈንበት፣ መሬት በዝናብ የሚርሰበት፣ በጉርፍ የሚታጠብበትና በጭቃ የሚጨማለቅበት ወቅት በመሆኑ የክረምት ወቅት አንዱ የቅኔ ታሪክ ስለሚሆን የቅኔ ባለሙያዎች የሚፈጠሩ ክስተቶችን የቅኔያቸው የታሪክ መነሻ ያደርጉዋቸዋል። የቅኔ መምህራንም የየወቅቱን ክስተት ለተማሪዎቻቸው በታሪክነት ያስተምሩዋቸዋል። ቅኔዎቻቸውንም በተጠቀሱት ታሪኮች ተመስርተው እንዲቆጥሩ ይመክሩዋቸዋል። ይህን አስመልክቶ ታደለ ገድሌ «ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋታ ለትዝታ» በተሰኘው መጽሀፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና የአንድምታ ትርጓሜም (ከኦሪት እስከ ሐዲስ)፣ የመላእክትን፣ የጻድቃንንና የሰማዕታትን ተራዳኢነትና ተጋድሎ በተመለከተ በየዕለቱ ቅኔ መምህሩ ሲተርክና ሲተነትን በአንክሮ ያዳምጣል። የቅኔው ጎዳና ምስጢሩ ሲገባው ደግሞ ድርጊቱን በሰምና ወርቅ እያስጌጠ ቅኔ ቆጥሮ ይቀኛል። ጠልና ልምላሜ፣ ዝናምና ጊሜ፣ ክረምትና ሀጋይ፣ ጨረቃ፣ ኮከብና ፀሐይ፣ ብርሃንና ጽልመት፣ ሕይወትና ሞት፣ ቁርና ዐመዳይ፣ ባሕርና ቀላይ፣ ሰውና እንስሳቱ፣ አዝርእትና እጸዋቱ፣ በአጠቃላይም የተፈጥሮ ክስተቶች ከታሪክ ጋር እየተዛመዱና እየተመሳሰሉ የቅኔ መነሻ ምንጮች ሆነው ያገለግላሉ (ታደለ ገድሌ፣ 1997፣ ገጽ-6)።

ሃይማኖታዊ የሆኑ የመጻህፍት ታሪኮችና በየወቅቱ የሚመጡ የአጽዋማት መነሻ ምክንያቶችም የግእዝ ቅኔ መነሻ ታሪክ በመሆን ያገለግላሉ። ምንም እንኳዋን በአንዳንድ የሙያው ሊቃውንት አግባብነት የለውም (ገብረዮሀንስ 1992፣33) እየተባለ ተቃውሞ ያለበት ቢሆንም በነገስታት፣ በጳጳሳት፣ በመሳፍንትና በሊቃውንት የሹመት፣ የልደትና የሞት አከባበር ስርአት ምክንያት የሚፈጠሩ አጋጣሚዎችና ታሪኮቻቸውም የግእዝ ቅኔ መነሻ ታሪክ ሆነው የሚያገለግሉበት አጋጣሚ ይስተዋላል። ለማስረጃ ያህል «የግእዝ ቅኔያት» በተሰኘው መጽሀፍ ውስጥ በተራ ቁጥር 115 እና 267 እንዲሁም «ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ህይወት» በተሰኘው መጽሀፍ ውስጥ ደግሞ ከገጽ 359 ጀምሮ እስከ ገጽ 400 ድረስ የተዘረዘሩትን የመወድስ ቅኔዎች መመልከት ይቻላል።

ጥናት አቅራቢው በአካል ተገኝቶ እንደተመለከታቸውና በአካባቢው የሚኖሩ የቅኔው ባለሙያዎችን (መላከጥበብ ስሜነህ ካሴት ቁ .1) ጠይቆ እንደተረዳው በጐጃም የቅኔ ጉባዔዎች ውስጥ የቅኔ መነሻ ታሪክ ለተማሪዎች የሚተረከው ሌሊት ግስ ከወረደ (ከተገሰሰ) እና ቅኔ ከተዘረፈ ወይም ንጋት ላይ ከሚከናወነው የቅኔ ትምህርት በሁዋላ ነው። በተጠቀሰው ጊዜ መምህሩ የእለቱን በአልና የወቅቱን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ይተርኩላቸዋል። ይህ የሚደረገው ታሪኩ ለቅኔ ተማሪዎች በደንብ እንዲገባቸውና በጥዋቱ ለሚያካሂዱት የቅኔ ቆጠራ እንዲያመቻቸው ሲባል ነው። ለምሳሌ የእለቱ በአል ደብረ ታቦር ከሆነ የደብረ ታቦርን ታሪክ፣ ወቅቱ ደግሞ አቢይ ጾም ከሆነ የጾሙ ታሪክ ይተረካል። ተማሪዎቹም የሰሙትን ታሪክ መሰረት እያደረጉ እንደየደረጃቸው በሰምና በወርቅ እያመሳጠሩ ቅኔን ለመቁጠርና ለመንገር የሚያስችል እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል።

### 4.1.7 የቅኔ መምህራን ህይወት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስርአተ ትምህርት መሰረት በተለያየ የትምህርት ዘርፍ ተምረውና ለመምህርነታቸው የብቃት ማረጋገጫ እንደያካባቢው ይትበሀል እየተሰጣቸው በተለያየ የትምህርት ጉባኤ ተወስነው እያስተማሩ፣ የማያልፍ ታሪክ፣ ባህል፣ ጥበብና እውቀት ዘርተው የራሳቸውን ስጋዊ ህይወት ለማስተማር ሙያቸው መስዋእት ያቀረቡ አባቶች ብዙዎች ነበሩ። የዜማ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የአቋቋቁዋም፣ የትርጉዋሜና የመጽሀፍ መምህራን እየተባሉ

የኢትዮጵያን ሃይማኖታዊ የኪነ ጥበብና የባህል ቅርስ ሳይከለስና ሳይበረዝ ለትውልድ ያስተላለፉ፣ ለቤተ ክህነትና ለቤተ መንግስት አገልጋይ ምሁራንን በብቸኝነት ሲያፈሩ የኖሩ የዘመኑ ብቸኛ ምሁራን ነበሩ ::

ለሀገራቸው ኢትዮጵያ ታላላቅ ተግባራትን የፈጸሙ፣ እውቀትን በነጻ ያካፈሉ፣ የህዝባችን ጥንታዊ ስልጣኔ ተጠብቆ እንዲኖር ያበቁ፣ ማግኘትና ማጣት ሳያሸንፋቸው፣ ችግርና መከራ ሳይበግራቸው፣ የኢትዮጵያ ብቻ የሆነውን የትምህርት ጥበብና ባህል ለትውልድ ያስተላለፉ በመሆናቸው የሙያው መምህራን ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል:: ሙያውን በማስተማር ስላሳለፉት ድካም፣ ስላበረከቱት አስተዋጽኦና ስለነበራቸው ጽናት በማስታወስ ጥንታዊ መምህራን ሲዘከሩ የሚገባቸው የኢትዮጵያ ታላቅ ባለውለታ መሆናቸውን ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንደሚከተለው ገልፀውታል::

> ጥንታውያን የኢትዮጵያን መምህራን ክብር የሚገባቸውና ቋሚ ታሪክ ያላቸው ናቸው:: ስለዚህ ሳሉት ሽልማት ለሞቱትም የመታሰቢያ ሀውልት ሊቆምላቸው ይገባል:: ቀን ተለይቶ መታሰቢያቸው ሊከበርላቸው የሚገቡ ናቸው:: አርቆ በሚያሳይ መነጽር የተመለከትን እንደሆነ እነዚህ ሊቃውንት ሁሉ ለሀገራችን ታላላቅ ስራን የሰሩ፣ እውቀትን በነጻ ያካፈሉና ታላላቅ ዝናን ያተረፉ ናቸው :: ይህንን ሁሉ ሙያና የሀገር ባህል የጠበቁና ያስተላለፉ፣ ህዝባችን ጥንታዊ ስልጣኔ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረጉት፣ በቀላሉም ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የቻሉት እነርሱ ባስተማሩት ትምህርት አማካኝነት ነው:: ... መከራ የማያሸንፋቸው፣ ማግኘትና ማጣት ቢፈራረቁባቸው ግምት የማይሰጡ፣ በርሃብ የማይረቱ፣ ማዕረጋቸውን እንጅ ሆዳቸውን የማይወዱ አባቶች ነበሩ (ሀብተ ማርያም፣ 1963፣ 178)::

በዚያኛው ዘመን የነበሩ፣ አሁንም አልፎ አልፎ ሰፋፊ ጉባኤ ዘርግተው፣ ጥንታዊና ኢትዮጵያዊ የሆነውን የትምህርት ዘር ሲዘሩ የነበሩና ያሉ መምህራን ሙያቸውን ለልጅልጅ ለማስተላለፍ ታላላቅ ተጋድሎ ያደረጉ መሆኑ የነበረና አሁንም ድረስ የሚስተዋል እውነታ ነው:: ለሙያቸውና ለስራቸው ወሮታ ሳይፈልጉ፣ ለስጋዊ ህይወታቸው ቁም ነገር ሳያደርጉ፣ ብዙዎቹ ተማሪዎቻቸው ለምነው ከሚያመጡት ቁራሽና በቅምጫና ከሚቀዳ ውኃ እየተመገቡ፣ ትዳር መስርተው የሚኖሩትም ቢሆን ከትዳራቸው ይልቅ ለሚያስተምሩዋቸው ተማሪዎቻቸውና ለሙያቸው አድልተው ጥንታዊውን የሀገራችንን ትምህርት አሁን አለበት ደረጃ አድርሰዋል:: አብዛኛዎቹ መምህራን በተማሪነት ህይወታቸው ካሳለፉት ችግር በከፋ ሁኔታ እየኖሩ የዘረጉትን ጉባኤ በጽንአት በመምራት ሙያቸውን ለተተኪያቸው አስተላልፈዋል:: የቀድሞ መምህራን ለማስተማር ሙያቸው የነበራቸውን ፍላጐትና ያሳዩትን ጽናት አስመልክቶ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንደሚከተለው ገልጸውታል::

> ትምህርቱን ለማስተማር አሁን፣ በኋላና ነገ በማለት ጊዜ ሳይወሰን የቀን የሌሊት እያለ ያስተምር ነበር:: የቀረው ቀርቶ በትዳር ያለ አስተማሪ እንኳን ከቤቱ በሌሊት ወጥቶ ሲያስተምር ከቶ ቅር አይለውም ነበር:: ቀንም እንዲሁ ሲያስተምር ይውላል:: .. ለዚህም ሁሉ ድካሙ ዋጋ ሆኖ የሚከፈለው ነገር አልነበረውም:: ህዝብም ቢቀጥረው ቅሉ እርሻ ያርሱለት፣ አንድም ከአዝመራው ጥቂት ይሰጠው እንደሁ እንጂ ለኑሮው በቂ የሚሆን፣ ትዳሩን የሚያሸንፍበት ነገር አይሰጠውም ነበር:: መምህሩ ግን ሁሉንም ሲያስታውስ በማስተማሩ ብቻ

ተደስቶ፣ መንፈሱ ጸንቶና ችግሩን አሸንፎ ይኖራል። የቀረው ቀርቶ በቤቱ ውስጥ እንኳን ልዩ ልዩ ፈተና ቢደርስበት ከቁም ነገር አይቆጥረውም ነበር። አንድ ትዳር የያዘ የቅኔ መምህር ሁልጊዜ ለትዳሩ ሳያስብ ሲያስተምር በመዋሉና በማደሩ ሚስቱ ተበሳጭታ ማታ ለራት ሲቀርብ በሞሰብ ከድና ድንጋውን አቀረበችለት ይባላል። ይህ የሚያመለክተው ስራህ ማስተማር ከሆነ እራትህም እርሱው ይሁን ማለት ነው (ሀብተ ማርያም፡ 1963፡ 179)።

ለማስተማር ሙያቸው ህይወታቸውን ካስገዙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጉባኤ መምህራን መካከል የቅኔ መምህራን ተጠቃሽ ናቸው። የቅኔው ጥበብ የገባው ደቀ መዝሙር ቅኔ አዋቂ፣ ሊቀ ቅኔ፣ ዘራፊ፣ አስነጋሪ፣ የቅኔ መምህር እየተባለ ይጠራል። እንደየደረጀው ስሙም ከስመ ጥር የቅኔ ሊቃውንት ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ ዝናው ይናኛል።

የቅኔው ሊቃውንትም በፈለጉ ጊዜ ሁሉ ደስ የሚያሰኘውንና መንፈስ የሚያድሰውን ቅኔ ከጉባኤ ቃና ጀምረው እስከ መወድስ እንደ ማእበል ቃል በቃል ስለሚያወርዱት ከተግባራቸው የተነሳ በቅጽል ስማቸው ጭምር ገሞራው፣ ማእበል፣ ገስጥ፣ ነጎድጓድ፣ ግጨው.. እየተባሉ ሲጠሩና ሲሞገሱ የምንሰማቸው ብዙዎች ናቸው። ታደሰ ገድሌ «ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋታ ለትዝታ» በሚል ርእስ በ1997 ባሳተሙት መጽሃፍ የሚከተሉትን ዘርዝረዋል።

> ከያሬድ ቀጥሎ... በትውለድ ቦታው ዮሀንስ ገብላዊ.. ፣የተረከበው ወልደ ገብርኤል፣ ቅኔን ከነመሰረቱ ወስዶ ያነጸው ሰምረ አብ፣ ከሰምረ አብ እንደርጃት ቅኔን የተረከበው ልኡብ ኤልያብ፣ ተዋነይ፣ ድድቅ ወልደ ማርያም፣ ድድቅ ሶልያና፣ ማእበል ወልደ ህይወት፣ መምህር አካለ ወልድ፣ እነ አልቃ ገብረ መድህን፣ እነ ጥበቡ ገሜ፣ እነ አቃቤ ሰአት ከብቴ፣ እነ አራት አይና ጎሹ፣ እነ ተክሌ ዘዋሸራ፣ እነ አለቃ ወልደ ሰንበት፣ እነ ወይዘሮ ገላነሽ፣ እነ ወይዘሮ ለኪደሉ፣ እነ እቡይ ካሳ፣ ሲራክ ዘዋድላ(የቅኔ መስፍን) እነ ግጨው መንክርና መሪጌታ ያሬድ ይጠቀሳሉ። እንዲሁም እነ መሪጌታ እጹብ ዘጎንደር፣ እነ መሪጌታ ውብሸት፣ እነ መሪጌታ ገብረ ስላሴ ዘኤልያስ፣ መሪጌታ መንግስቱ ዘደብረ ማርቆስ፣ አስካለ ዘጋይንት፣ ዘመደ ብርሀን፣ አለቃ ይሄይስ፣ ማእበል ሰረገላ ብርሀን፣ አለቃ ምስራቅ፣ የንታ መአዛ፣ ሊቀ ብርሀናት አድማሱ ጀንበሬና ሌሎቹ ይወሳሉ (ታደሰ ገድሌ፡ 1997፡ 7)።

የቅኔ መምህራን በጐጃም ውስጥ ከሌላው አካባቢ በተሻለ በብዛት ይገኙ ነበር። ከእገሌ እገሌ ይበልጣል እየተባለም ይነገርላቸው የነበሩ ብዙ ናቸው። ትምህርቱም የእውቀት በር መክፈቻ ዋናው ቁልፍ፣ የእውቀት ደረጃ መለኪያ፣ የጥበባት ሁሉ መገለጫ ነው ተብሎ በቤተ ክህነቱም ሆነ በቤተ መንግስቱ ይሰጠው የነበረው ግምት የላቀ ስለነበር የቅኔ ተማሪው ወደ ቅኔ ጉባኤዎች በብዛት ይጐርፍ ነበር።

የቅኔ መምህራንን ህይወትና ባህሪ ለይተን ስንመረምር፣ ምንም እንኳ የሀገራችንን የቅኔ ባህልና የግእዝ ቋንቋዋ ተጠብቆ እንዲቆይ፣ የተለያዩ የኪነ ጥበባት ዘርፎች እንዲያድጉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ከሌሎች መምህራን የሚለያቸው የተለየ ጠባይ ይታይባቸዋል። መምህራኑ ስጋዊ ኑሯቸው ከሌሎች የሙያ መምህራን ያነሰ ህይወትን ይገፉ የነበረ ቢሆንም ትምህርት

በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪው የሚፈልገውን እንዳያገኝ የመሸንገልና የጠባይም ጉድለት ይታይባቸው የነበረ መሆኑ ከሌሎች መምህራን የሚለዩበት እንደሆነ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ይገልጹታል፡፡

> ሆኖም ተማሪው እንደፈለገ ትምህርት እንዳይሰጠው መምህራኑ እውቀታቸውን የመሸንገል ዘዴ ነበራቸው፡፡ በጠባይም ከዜማ መምህራን የተለየ ጉድለት ይታይባቸው ነበር፡፡ ከትህትና ይልቅ ኩራት ይታይባቸው የነበረው በቅኔ መምህራን ላይ ነው፡፡ እንኳንስ እነሱ ተማሪያቸው ሳይቀር ምስጢር ከለየና ቅኔ ከቆጠረ በኋላ ሰው ለማነጋገር ይቸግረው እንደነበረ የታወቀ ነው፡፡ መምህራኑ ምንም በእድሜ የሸመገሉ እንኳ ቢሆኑ የጠባይ ልጅነት ነበራቸው፡፡ ጠብን በመፈለግ ሌሎች የቅኔ መምህራን ወዳሉበት እየዞሩ፣ አንዳንድ ጊዜ ተማሪ መስለው በመቅረብ፣ አንዳንዴ ደግሞ ግልጥ በግልጥ ከመምህሩ ጋር ዘረፋ በመግጠም እንደበግ አውራ ሲዋጉ ይታዩ ነበር፡፡ የቅኔ መምህራን በዘረፋ ጊዜም ሆነ ወይም በቤተ ክርስቲያን በተቀኙ ጊዜ ከምስጋና ይልቅ የምጸቱንና የጉዳናውን መንገድ በመፈለግ እንዳይመረመርና እንዳይገኝ አድርጉ ሰድቦ መቀኘትን ይመርጡ ነበር (ሀብተ ማርያም 1963፣180)፡፡

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የጠቀሱት ነጥብ በተወሰኑ የቅኔ መምህራን ይንጸባረቅ የነበረ ባህሪ መሆኑን ሌሎች የሙያው ሰዎችም ይስማሙበታል፡፡ ይህ ማለት ግን በብህትውና ህይወት እድሜያቸውን ያሳለፉ፣ ስጋዊ ፍላጐታቸውን ለሃይማኖታቸው የሰጡ፣ የቅኔን ሙያ ለራሳቸው እውቅና ማግኛ ከማዋል ይልቅ ለመንፈሳዊ ጸጋ ያዋሉ አያሌ መምህራን የነበሩና ያሉ መሆኑ የማያጠራጥር ነው፡፡

የቅኔ ትምህርት ባህሪና መልኩ እንደ ቁዋንቁዋ ትምህርት ቢሆንም መምህራኑ ግን ቅዱሳን ከመሆናቸው የተነሳ መንፈሳዊ ትምህርት ነው ብለውና እንደ መንፈሳዊ ትምህርት ቆጥረው ከእግዚአብሄር ዘንድ ዋጋ እናገኝበታለን በነፍሳችንም እንጠቀምበታለን ብለው በማሰብ ስጋዊ ፍላጉታቸውን ረስተው ሙሉ ጊዜያቸውን ቅኔን በማስተማር ያሳለፉ አያሌ መንፈሳዊ መምህራን ነበሩ፡፡ በዘመኑ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መጻህፍት ሁሉ የሚነበቡትና የሚተረጐሙት፣ የምስጋና ጸሎትም የሚቀርበው በግእዝ ቁዋንቁዋ የነበረ በመሆኑ በዘመኑ ቅኔን መማር የቤተ ክርስቲያን የትምህርት መሰረት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ አንድ ተማሪ ዜማን ከነጓዙ ቢያውቅ፣ አቋቋምም ከነባህሉ ቢያጠናቅቅ ቅኔ ካላወቀና ካልተቀኘ በቤተ ክርስቲያን ህይወቱ እንደፈራና እንደቀለለ ይኖር ነበር እንጂ በቂ እውቀት አለኝ ብሎ በተማረው ትምህርት አይኮራም ነበር፡፡ ስለዚህ በዚያ ዘመንም ሆነ አሁን ቅኔን መማርና በአግባቡ ማወቅ እንደታላቅነትና አዋቂነት ይቆጠርና ያስከብር ነበር፡፡

በቅኔ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተምሮ፣ የቅኔ መምህር ሆኖ፣ የቅኔ ጉባኤ ለመዘርጋት እንደየቅኔ ትምህርት ጉባኤው የተለያየ ስርአት አለው፡፡ አንድ የቅኔ ተማሪ ተማሪነትን ተሻግሮ የቅኔ መምህር ለመሆን አስቀጻይ፣ አስነጋሪና ዘራፊ ሆኖ በጉባኤው ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል፡፡ በዘራፊነት ደረጃ የቆየ አንድ የቅኔ ተማሪ እጩ መምህር ሆኖ የቅኔ ጉባኤ ለመትከልና ሙሉ መምህር ለመሆን እንዲችል የሚፈጸሙ ተግባራትን መሪጌታ ለይኩን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡



ADDIS ... IES LIBRARY



መሪጌታ ለይኩን ብርሀኑ የግእዝ ቅኔን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ በሰጡበት ወቅት፤

በአንድ ጉባኤ በዘራፊነት ከአንድ ዓመት በላይ ያሳለፈ ተማሪ፤ የቅኔውን አገባብ፣ ለማስተማሪያነት የተመደቡ የቅኔ መንገዶችንና የየእለቱን ግስ ከነአመሉ መለየት ሲችል የጉባኤው የአስተማሪነት ስራ ለዘራፊው ይለቀቅለታል፡፡ የቅኔው ትምህርት ሲከናወን ማለትም ቅኔ ሲዘረፍ፣ የየእለቱ ታሪክ ሲነገርና ግስ ሲወርድ መምህሩ ክትትል እያደረገ ከስድስት ወር እስከ አንድ አመት ጊዜ ይቆያል፡፡ እጩ መምህሩ ግሱን ከነአመሉ አጣርቶ መያዙ በመምህሩ ሲታመንበት በግስ በኩል ያሉትን ፈተናዎች ያለፈ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡ ቅኔውን የሚያስመስክረው ግን በወትሮው ጊዜ ወደ ጉንጅ ወይም ዋሸራ ጉባኤዎች በመሄድ ነበር (መሪጌታ ለይኩን 1999 ካ.ቁ 3)፡፡

መሪጌታ ለይኩን ሃሳባቸውን በመቀጠል አንድ እጩ መምህር ቅኔውን የሚያስመሰክረው ጉንጅ ከሆነ የቃና ዘገሊላ፣ ዋሸራ ከሆነ ደግሞ የአስተርዮ ማርያም እጣነ ሞገር እንዲቀኝ ይደረግና በእለቱ በተቀኘው ቅኔ በሊቃውንቱ ዘንድ የፈጠረው ስሜት ታይቶ በአስተማሩት መምህር በኩል የፈተናው ውጤት ለተማሪው እንደሚገለጽለት ያስረዳሉ፡፡ እጩ መምህሩ ያስገኘው ውጤት (ይገባዋል!) ወይም እጅግ በጣም ጥሩ የሚያሰኘው ከሆነ ሊቃውንቱ በተሰበሰቡበት በአስተማሪው መምህርና በማህበሩ ፊት ከሽልማት ጋር የመምህርነት ማእረጉ ይሰጠዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህን የመሰለው ስርአት እየቀነስ መሆኑን አንዳንዱ ደግሞ በራሱ ስልጣን የቅኔ መምህር ነኝ በማለት ራሱን የሚሾመው የበዛ መሆኑን በጸጸት ይገልጹታል፡፡

የቅኔ መምህራን ህይወት በአሁኑ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ ያለ መሆኑን ከወትሮው ጋር እያነጻጸሩ የሚገልጹት ደግሞ መላከ ጥበብ ስሜነህ ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው አገላለጽ፤ በዚህ ዘመን የቅኔ መምህራን ህይወት ከወትሮው በበለጠ አደጋ ላይ የወደቀ በመሆኑ የቅኔው ሙያም እየቀለለ፣ ስነ ስርአቱም እየተጉዋደለ የመጣ መሆኑን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> የቅኔ መምህራን ወትሮ በአደባባይ አንድ መወድስ አበርክተው የአመት ቀለባቸውንና ልብሳቸውን ያገኙ ነበር፡፡ አንድ ስላሴ አቅርበው ይበል! ይበል! እየተባሉ በቤተ መንግስቱና በቤተ ክህነቱ ይከበሩና ይሾሙ ነበር፡፡ የወርቅ ካባ ሳይቀር ይሰጣቸው ነበር፡፡ በየአድባራቱ እየተሾሙ ደመወዝ ይከፈላቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ሳይቀር የግብረ ገብ መምህር እየተባሉ ደሞዝ ይከፈላቸው ነበር፡፡ አሁን ግን በቤተ መንግስቱም ሆነ በቤተ ክህነቱ ቀለብ መስፈሩ፣ ልብስ ማልበሱና ደመወዝ መቁረጡ ቀርቶ ክብሩና ተቀባይነቱም እየቀነሰ፣ የዘመኑ ትምህርት እየተጫነው ይገኛል፡፡ ተተኪ የቅኔ ተማሪዎችም በሙያው ተስፋ እየቆረጡና እየሸሹት በመሆናቸው ስጋዊ ፍላጎቱን ሰውቶ ለሙያው ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ተተኪ የቅኔ መምህር የማግኘቱ ተስፋ እየተሟጠጠ ያለ ይመስለኛል (መላከ ጥበብ ስሜነህ፡ 1999፡ ካ. ቁ 1)፡፡

የመላከ ጥበብ ስጋት የብዙዎቹ የሙያው ሰዎች ስጋት ሆኖ ተገኝቱዋል፡፡ ጥናት አቅራቢው የጥናቱን ዳታ ለማሰባሰብ በተዟዟወረባቸው የጎጃም አካባቢዎች ታዋቂ የነበሩ አንዳንድ የቅኔ ጉባኤዎች ተዘግተዋል፡፡ የቅኔ መምህራን ብዛትም ሆነ የማስተማር ፍላጎት ቀንሱዋል፡፡ አልፎ አልፎ በሚገኙ የቅኔ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችም ብዛት እጅግ ቀንሱዋል፡፡ ተማሪዎቹ በቅኔ ትምህርታቸው ገፍተው ሊቅ ሆነው ሲወጡ ለስጋዊ ህይወታቸው የሚጠቅም አንድም አይነት ተስፋ ከፊታቸው ስለማይታያቸው በቅኔ ትምህርቱ የመቀጠል ፍላጎታቸው የደከመ ነው፡፡ የብዙዎቹ ተማሪዎች አስተሳሰብ ከተገለጸው የተለየ አይደለም፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ብቻ የሆነው ጥንታዊው የቅኔ ትምህርት ጥበብ የመማር ማስተማር ሂደቱ ተሰናክሎ ስሩ እንዳይቀረጥና እንዳይደርቅ ትኩረት ሊሰጠውና በአዲስ መልክ ሊታይ የሚገባው አንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳይ ይመስላል፡፡

## 4.2 ቅኔ ቆጠራ ነገራና ዘረፋ

ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋና ግሰሳ በአንድ የቅኔ ጉባኤ ውስጥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ናቸው። አንድ የቅኔ ጉባኤ ቅኔ ለማስተማር ጉባኤ ከዘረጋ በጉባኤ ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት የስርአተ ትምህርቱ አካላት መኖራቸው የግድ ነው።

ተማሪዎች ወደ ቅኔ ቆጠራ ከመሰማራታቸው በፊት ለሚቆጥሩት የቅኔ አይነት ምሳሌ የሚሆናቸው በመምህሩ ወይም በዘራፊው ወይም በቀደምት ታዋቂ የቅኔ ሊቃውንት የተነገሩ ቅኔዎችን አጥንተው መያዝ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም ለሚቆጥሩት ቅኔ ወርቅ ሆኖ የሚጠቀስ የእለቱ ወይም የወቅቱ ታሪክ ሊተረክላቸው ይገባል። በጉባኤው መርሀ ትምህርት መሰረት የእለቱ ግስም ይገሰስላቸዋል።



የቅኔ ተማሪው በእለቱ በመምህሩ የሚወርደውን ግስ እየተቀበለ ለተማሪዎች በማስጋባት ላይ ሳለ፤

በበነጋታው ጥዋት ተማሪው ለቅኔ ቆጠራ ወደሚያመች ጸጥታ የሰፈነበት ቦታ ይሰማራና የሚቆጥረውን ቅኔ ባጠናው የመምህራን ቅኔ አኩዋያ እያወዳደረ፣ ቤቱን፣ ዜማውን፣ ሙያውንና ሰምና ወርቁን እየመረመረና እያመሳከረ ቆጠራውን ሲያከናውን ያረፍዳል:: ከስአት በሁዋላ ጀምሮ ተማሪው የቆጠረውን ቅኔ ለመምህሩ ወይም ለአስነጋሪ ተማሪ እየነገረና ስህተቱን እያሳረመ ይውላል:: ይህ ተግባር በየቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚስተዋል የአንድ ጉባኤ ታላቁ ተግባር ነው::

በተመረጡ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ስለሚከናወኑ ልዩ ልዩ የትምህርት አይነቶች የበለጠ ለመረዳት ያመች ዘንድ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር መመልከቱ ተገቢ ይሆናል::

### 4.2.1 የግስ ግሰሳና እርባታ ስርአት

በግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት አይነቶች አንዱ ግስ ነው:: የቅኔ መሰረቱ ደግሞ ግስን ከነሰራዊቱ፤ አገባቡና አረባቡ ስርአትና ህጉን ጠብቆ ማወቅ መቻል ነው:: የግእዝ ቅኔ እስካሁን ዋነኛ መነገሪያው የግእዝ ቋንቋ በመሆኑ የቋንቋዋውን ህጋጋት ተረድቶ ቅኔ ለመቀኘት በቋንቋዋው ህግ ውስጥ ስርአት ሆነው የሚጠኑ የሰዋስው ዘርፎችን ማለትም እርባ ቀመር፣ እርባ ግስ፣ ነጠላ ግስና አገባብን ማወቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል::

በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት ሰጥተን የምንመለከተው ነጠላ ግስንና ድርብ ግስን (እርባ ግስን) ይሆናል:: ነጠላ ግስ ማለት የቅኔ ተማሪው የግእዝን ቋንቋዋ ስልት በሚገባ ለማወቅና ቃላትን ለማጥናት፣ የነጠላና ህብር ቃላትን ደረጃ ለመረዳትና ለማወቅ መነሻ መሰረቱ ሲሆን አቀራረቡም የግእዙን የፊደል ተራ እየጠበቀና መድረሻውን ግእዝ (የመጀመሪያ ፊደል) እያደረገ፣ በሀላፊ ብቻ የሚነገር፣ ያለ እርባታ የሚሄድ የግስ አይነት ነው (ሀብተ ማርያም:1963: 145)::

ከዚህ አኩዋያ ስንመለከተው ነጠላ ግስ በራሱ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ነው:: አንደኛው ሊረባ የሚችለውን (ለምሳሌ ሎሀ፣ ለህሀ፣ ለቅሀ ...) እያለ የሚሄደውን ግስ የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሊረባ የማይችል፣ ዘርነት የሌለው፣ ከዘር አንቀጽ የማይገኝ፣ የቋንቋዋው ቤተሰብ የሆነ፣በውጥንቅጥነት የሚገኘውን ጥሬ ቃል ሁሉ (ለምሳሌ ለሲሁ፣ ምስሌሁ፣ ወልድ፣ ሀገር፣ ምስለ ...) የመሳሰለው ነባር ይባላል::

እርባ (ድርብ) ግስ የሚባለው ደግሞ በዝርዝር ሊረባ የሚችለው የግስ አይነት ነው:: ይህ የግስ አይነት፣ በ50 ሰራዊት ተዘርዝሮ፣ በ8 አርስት ተከፍሎ፣ በ5 አእማድ ተጠቅሎ፣ በአቢይ አንቀጽ፣ በንኡስ አንቀጽ፣ በደቂቅ፣ በባእድ ቅጽል፣ በመራህያንና በዝርዝር ቅጽል እየገባ በምልአት የሚገሰስ እርባታ አለው:: በዚህ መልክ የሚከናወነው ትምህርት እርባ ግስ እየተባለ ይጠራል:: እርባታ የተባለው በጠቅላላው በ4 ክፍል ይከፈላሉ:: እነሱም ስምንቱ አርስት ከሰራዊቶቻቸው ጋር አንድ ወገን፣ አእማድ የተባሉት በሌላ ወገን፣ የአእመረ ጓዝና የይቤ እርባታ በሌላ ወገን፣ እንዲሁም ተናባቢ ግስና ምሳሌ ግስ የተባሉት ደግሞ በሌላ ወገን ሆነው በአራት ክፍል ተከፍለው ይቆጠራሉ (ሀብተ ማርያም:1963:146)::

የግስ እርባታ ከላይ በተገለፀው መሰረት በአራት ተመድቦና በ13 ታላላቅ ክፍሎች በተከፈሉ መሪ ግሶች (ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ገብረ፣ አእመረ፣ ባረከ፣ሴመ፣ ብህለ፣ ቆመ፣ ይቤ፣ ...) ምሳሌነት እየተመራ የሚረባ ቢሆንም አልፎ አልፎ ህገወጥ የሆነ የአረባብ መንገድ የሚከተሉም ይኖራሉ:: ይሁን እንጅ በግእዝ ቋንቋዋ ውስጥ የሚ ገኙ ግሶች የሚረቡት ከላይ የተጠቀሱት ግሶችን የአረባብ ስርአት ተከትለው ነው:: ግሶች እንደየ ጉባኤዎቹ አይነት፣ የቅኔ አስተማሪው እንደሚከተለው የቅኔ መንገድና ችሎታ፣ የአንድ የግእዝ ቋንቋዋ ግስ የአረባብ ስርአት የተወሰነ ልዩነት ይታይበታል:: በአማካይ ሲታይ አንድ ግስ እስከ 400 ጊዜ ሊረባ ይችላል:: (ሀብተ ማርያም:1963:148) ከዚህ አኳዋያ የግሶችን የአረባብ ስርአትና የሚከተሉትን መንገድ በምሳሌ ማሳየቱ ለጥናቱ ጠቀሜታ ስለሚኖረው ሀብተማርያም ወርቅነህ፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት በሚል ርእስ በ1963 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ የሚገኘውን የአእመረን ግስ አወራረድና አለማየሁ ሞገስ፣ ሰዋስዎ ግእዝ፣ በሚል ርእስ በ1950 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሀፍ የሚገኘውን የይቤን ግስ አወራረድ በምሳሌነት ማሳየቱ ርእሰ ጉዳዩን ሙሉ ያደርገዋል::

## I. አእመረ

### ሀ. የአዕመረ አወራረድ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. አእመረ | አወቀ | 8. አእማርያን | ያወቁ |
| 2. የአምር | ያውቃል | 9. አእማሪት | ያወቀች |
| 3. ያእምር | ያውቅ ዘንድ | 10. አእማርያት | ያወቁ |
| 4. ያእምር | ይወቅ | 11. እሙር | የታወቀ |
| 5. አእምሮ | ማወቅ | 12. አእማሪ | የሚያውቅ አዋቂ |
| 6. አእምሮት | ማወቅ | 13. ማእምር | አዋቂ |
| 7. አእማሪ | ያወቀ | 14. አእምሮ | እውቀት |

### ለ. ዝርዝር እርባ ግስ

| 1. የራቀ ወንድ ሲያውቅ | | 2. የቅርብ ወንድ ሲያውቅ | |
|---|---|---|---|
| አእመረ | አወቀ | አእመርከ | አወቅህ |
| የአምር | ያውቃል | ተአምር | ታውቃለህ |
| ያእምር | ያውቅ ዘንድ | ታእምር | ታውቅ ዘንድ |
| ያእምር | ይወቅ | አእምር | እወቅ |

| 3. የሩቆቹ ወንዶች ሲያውቁ | | 4. የቅርቦቹ ወንዶች ሲያውቁ | |
|---|---|---|---|
| አእመሩ | አወቁ | አእመርክሙ | አወቃችሁ |
| የአምሩ | ያውቃሉ | ተአምሩ | ታውቃላችሁ |
| ያእምሩ | ያውቁ ዘንድ | ታእምሩ | ታውቁ ዘንድ |
| ያእምሩ | ይወቁ | አእምሩ | እወቁ |

5. የሩቅ ሴት ስታውቅ

| | |
|---|---|
| አእመረት | አወቀች |
| ተአምር | ታውቃለች |
| ታእምር | ታውቅ ዘንድ |
| ታእምር | ትወቅ |

6. የቅርቢቱ ሴት ስታውቅ

| | |
|---|---|
| አእመርኪ | አወቅሽ |
| ተአምሪ | ታውቂያለሽ |
| ታእምሪ | ታውቂ ዘንድ |
| አእምሪ | እወቂ |

7. የሩቆቹ ሴቶች ሲያውቁ

| | |
|---|---|
| አእመራ | አወቁ |
| የአምራ | ያውቃሉ |
| ያእምራ | ያውቁ ዘንድ |
| ያእምራ | ይወቁ |

8. የቅርቦች ሴቶች ሲያውቁ

| | |
|---|---|
| አእመርክን | አወቃችሁ |
| ተአምራ | ታውቃላችሁ |
| ታእምራ | ታውቁ ዘንድ |
| አእምራ | እወቁ |

9. እኔ ሳውቅ

| | |
|---|---|
| አእመርኩ | አወቅሁ |
| አአምር | አውቃለሁ |
| አእምር | አውቅ ዘንድ |
| አእምር | ልወቅ |

10. እኛ ስናውቅ

| | |
|---|---|
| አእመርነ | አወቅን |
| ነአምር | እናውቃለን |
| ናእምር | እናውቅ ዘንድ |
| ናእምር | እንወቅ |

### መ. የአንቀጽ ዝርዝር አረባብ

1. የሩቁ ወንድ

ሀ. የሩቁን ወንድ ሲያውቀው

| | |
|---|---|
| አእመሮ | አወቀው |
| የአምሮ | ያውቀዋል |
| ያእምሮ | ያውቀው ዘንድ |
| ያእምሮ | ይወቀው |

ለ. የቅርቡን ወንድ ሲያውቀው

| | |
|---|---|
| አእመረከ | አወቀህ |
| የአምረከ | ያውቅሀል |
| ያእምርከ | ያውቅህ ዘንድ |
| ያእምርከ | ይወቅህ |

መ. የሩቆቹን ወንዶች ሲውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመሮሙ | አወቃቸው |
| የአምሮሙ | ያውቃቸዋል |
| ያእምሮሙ | ያውቃቸው ዘንድ |
| ያእምሮሙ | ይወቃቸው |

ረ. የቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመረክሙ | አወቃችሁ |
| የአምረክሙ | ያውቃችሁዋል |
| ያእምርክሙ | ያውቃችሁ ዘንድ |
| ያእምርክሙ | ይወቃችሁ |

ሰ. የሩቂቱን ሴት ሲያውቃት

| | |
|---|---|
| አእመራ | አወቃት |
| የአምራ | ያውቃታል |
| ያእምራ | ያውቃት ዘንድ |
| ያእምራ | ይወቃት |

ሸ. የቅርቢቱን ሴት ሲያውቃት

| | |
|---|---|
| አእመረኪ | አወቀሽ |
| የአምረኪ | ያውቅሻል |
| ያእምርኪ | ያውቅሽ ዘንድ |
| ያእምርኪ | ይወቅሽ |



ILS LIBRARY ADDIS

| ቀ. የሩቆቹን ሴቶች ሲያውቃቸው | | በ. የቅርቦችን ሴቶች ሲያውቃቸው | |
|---|---|---|---|
| አእመሮን | አወቃቸው | አእመረክን | አወቃችሁ |
| የአምሮን | ያውቃቸዋል | የአምረክን | ያውቃችሁዋል |
| ያእምሮን | ያውቃቸው ዘንድ | ያእምርክን | ያውቃችሁ ዘንድ |
| ያእምሮን | ይወቃቸው | ያእምርክን | ይወቃችሁ |

| ተ. እኔን ሲያውቀኝ | | ቸ. እኛን ሲያውቀን | |
|---|---|---|---|
| አእመረኒ | አወቀኝ | አእመረነ | አወቀን |
| የአምረኒ | ያውቀኛል | የአምረነ | ያውቀናል |
| ያእምረኒ | ያውቀኝ ዘንድ | ያእምረነ | ያውቀን ዘንድ |
| ያእምረኒ | ይወቀኝ | ያእምረነ | ይወቀን |

## 2. የቅርቡ ወንድ

| ሀ. የሩቁን ወንድ ሲያውቀው | | ለ. የሩቆቹን ወንዶች ሲያውቃቸው | |
|---|---|---|---|
| አእመርኮ | አወቅኸው | አእመርኮሙ | አወቅሀቸው |
| ተአምሮ | ታውቀዋለህ | ተአምሮሙ | ታውቃቸዋለህ |
| ታእምሮ | ታውቀው ዘንድ | ታእምሮሙ | ታውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮ | እወቀው | አእምሮሙ | እወቃቸው |

| መ. የሩቂቱን ሴት ሲያውቃት | | ረ. የሩቆቹን ሴቶች ሲውቃቸው | |
|---|---|---|---|
| አእመርካ | አወቅሀት | አእምርኮን | አወቅሀቸው |
| ተአምራ | ታውቃታለህ | ተአምሮን | ታውቃቸዋለህ |
| ታእምራ | ታውቃት ዘነድ | ታእምaን | ታውቃቸው ዘንድ |
| አእምራ | እወቃት | አእምሮን | እወቃችው |

| ሰ. እኔን ሲያውቀኝ | | ሸ. እኛን ሲያውቀን | |
|---|---|---|---|
| አእመርከኒ | አወቅኸኝ | አእመርከነ | አወቅኸን |
| ተአምረኒ | ታውቀኛለሁ | ተአምረነ | ታውቀናለህ |
| ታእምረኒ | ታወቀኝ ዘንድ | ታእምረነ | ታውቀን ዘንድ |
| አእምረኒ | እወቀኝ | አእምረነ | እወቀን |

## 3. ሩቆች ወንዶች

| ሀ. ሩቁን ወንድ ሲያውቁት | | ለ. ቅርቡን ወንድ ሲያውቁት | |
|---|---|---|---|
| አእመርዎ | አወቁት | አእመሩከ | አወቁህ |
| የአምርዎ | ያውቁታል | የአምሩከ | ያውቁሀል |
| ያእምርዎ | ያውቁት ዘንድ | ያእምሩከ | ያውቁህ ዘንድ |
| ያእምርዎ | ይወቁት | ያእምሩከ | ይወቁህ |

መ. የሩቆችን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

አእመርዎሙ አወቁዋቸው
የአምርዎሙ ያውቁዋቸዋል
ያእምርዎሙ ያውቁዋቸው ዘንድ
ያእምርዎሙ ይወቁዋችው

ረ. የቀርቦቹን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

አእመሩክሙ አወቁዋችሁ
የአምሩክሙ ያውቁዋችሁዋል
ያእምሩክሙ ያውቁዋችሁ ዘንድ
ያእምሩክሙ ይወቁዋችሁ

ሰ. ሩቂቱን ሴት ሲያውቁዋት

አእመርዋ አወቁዋት
የአምርዋ ያውቁዋታል
ያእምርዋ ያውቁዋት ዘንድ
ያእምርዋ ይወቁዋት

ሸ. ቅርቢቱን ሴት ሲያውቁዋት

አእመሩኪ አወቁሽ
የአምሩኪ ያውቁሻል
ያእምሩኪ ያውቁሽ ዘንድ
ያእምሩኪ ይወቁሽ

ቀ. ሩቆቱን ሴቶች ሲያውቁዋችው

አእምርዎን አወቁዋቸው
የአምርዎን ያውቁዋቸዋል
ያእምርዎን ያውቁዋቸው ዘንድ
ያእምርዎን ይወቁዋቸው

በ. ቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቁዋቸው

አእመሩክን አወቁዋችሁ
የአምሩክን ያውቁዋችሁዋል
ያእምሩክን ያውቁዋችሁ ዘንድ
ያእምሩክን ይወቁዋችሁ

ተ. እኔን ሲያውቁኝ

አእመሩኒ አወቁኝ
የአምሩኒ ያውቁኛል
ያእምሩኒ ያውቁኝ ዘንድ
ያእምሩኒ ይወቁኝ

ቸ. እኛን ሲያውቁን

አእመሩነ አወቁን
የአምሩነ ያውቁናል
ያእምሩነ ያውቁን ዘንድ
ያእምሩነ ይወቁን

## 4. ቅርቦች ወንዶች

ሀ. ሩቁን ወንድ ሲያውቁት

አእመርክምዎ አወቃችሁት
ተአምርዎ ታውቁታላችሁ
ታእምርዎ ታውቁት ዘንድ
አእምርዎ እወቁት

ለ. ሩቆችን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

አእመርክምዎሙ አወቃችሁዋቸው
ተአምርዎሙ ታውቁዋችዋላችው
ታእምርዎሙ ታውቁዋቸው ዘንድ
አእምርዎሙ እወቁዋቸው

መ. ሩቂቱን ሴት ሲያውቁዋት

አእምርክምዋ አወቃችሁዋት
ተአምርዋ ታውቁዋታላችሁ
ታእምርዋ ታውቁዋት ዘንድ
አእምርዋ እወቁዋት

ረ. ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቁዋቸው

አእምርክምዎን አወቃችሁዋቸው
ተአምርዎን ታውቁዋቸዋላችሁ
ታእምርዎን ታውቁዋቸው ዘንድ
አእምርዎን እወቁዋቸው

ሰ. እኔን ሲያውቁኝ

| | |
|---|---|
| አእመርክሙኒ | አወቃችሁኝ |
| ተእምሩኒ | ታውቁኛላችሁ |
| ታእምሩኒ | ታውቁኝ ዘንድ |
| አእምሩኒ | እወቁኝ |

ሸ. እኛን ሲያውቁን

| | |
|---|---|
| አእመርክሙነ | አውቃችሁን |
| ተእምሩነ | ታውቁናላችሁ |
| ታእምሩነ | ታውቁን ዘንድ |
| አእምሩነ | እወቁን |

## 5. ሩቂቱ ሴት

ሀ. ሩቁን ወንድ ስታውቀው

| | |
|---|---|
| አእመረቶ | አወቀችው |
| ተአምሮ | ታውቀዋለች |
| ታእምሮ | ታውቀው ዘንድ |
| ታእምሮ | ትወቀው |

ለ. ቅርቡን ወንድ ስታውቀው

| | |
|---|---|
| አእመረተከ | አወቀችህ |
| ተአምረከ | ታውቅህ አለች |
| ታእምርከ | ታውቅህ ዘንድ |
| ታእምርከ | ትወቅህ |

መ. ሩቆቹን ወንዶች ስታውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእምረቶሙ | አወቀቻቸው |
| ተአምሮሙ | ታውቃቸዋለች |
| ታእምሮሙ | ታውቃቸው ዘንድ |
| ታእምሮሙ | ትወቃቸው |

ረ. ቅርቦችን ወንዶች ስታውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመረተክሙ | አወቀቻችሁ |
| ተአምረክሙ | ታውቃችሁዋለች |
| ታእምርክሙ | ታውቃችሁ ዘንድ |
| ታእምርክሙ | ትወቃችሁ |

ሰ. ሩቂቱን ሴት ስታውቃት

| | |
|---|---|
| አእመረታ | አወቀቻት |
| ተአምራ | ታውቃታለች |
| ታእምራ | ታውቃት ዘንድ |
| ታእምራ | ትወቃት |

ሸ. ቅርቢቱን ሴት ስታውቃት

| | |
|---|---|
| አእመረተኪ | አወቀችሽ |
| ተአምረኪ | ታውቅሻለች |
| ታእምርኪ | ታውቅሽ ዘንድ |
| ታእምርኪ | ትወቅሽ |

ቀ. ሩቆቹን ሴቶች ስታውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመረቶን | አወቀቻቸው |
| ተአምሮን | ታውቃቸዋለች |
| ታእምሮን | ታውቃቸው ዘንድ |
| ታእምሮን | ትወቃቸው |

በ. ቅርቦቹን ሴቶች ስታውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመረተክን | አወቀቻችሁ |
| ተአምረክን | ታውቃችሁዋለች |
| ታእምርክን | ታውቃችሁ ዘንድ |
| ታእምርክን | ትወቃችሁ |

ተ. እኔን ስታውቀኝ

| | |
|---|---|
| አእመረተኒ | አወቀችኝ |
| ተአምረኒ | ታውቀኛለች |
| ታእምረኒ | ታውቀኝ ዘንድ |
| ታእምረኒ | ትወቀኝ |

ቸ. እኛን ስታውቀን

| | |
|---|---|
| አእምረተነ | አወቀችን |
| ተአምረነ | ታውቀናለች |
| ታእምረነ | ታውቀን ዘንድ |
| ታእምረነ | ትወቀን |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## 6. የቅርቢቱ ሴት

### ሀ. የሩቁን ወንድ ስታውቀው

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮ | አወቅሽው |
| ተአምሪዮ | ታዊቂዋለሽ |
| ታእምሪዮ | ታውቂው ዘንድ |
| አእምሪዮ | እወቂው |

### ለ. የሩቆችን ወንዶች ስታውቃችሁ

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮሙ | አወቅሻቸው |
| ተአምሪዮሙ | ታውቂያቸዋለሽ |
| ታእምሪዮሙ | ታውቂያቸው ዘንድ |
| አእምሪዮሙ | እወቂያቸው |

### መ. የሩቂቱን ሴት ስታውቃት

| | |
|---|---|
| አእመርኪያ | አወቅሻት |
| ተአምሪያ | ታውቂያታለሽ |
| ታእምሪያ | ታውቂያት ዘንድ |
| አእምሪያ | እወቂያት |

### ረ. የሩቆቹን ሴቶች ስታውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮን | አወቅሻቸው |
| ተአምሪዮን | ታውቂያቸዋለሽ |
| ታእምሪዮን | ታውቂያአው ዘንድ |
| አእምሪዮን | እወቂያቸው |

### ሰ. እኔን ስታውቂኝ

| | |
|---|---|
| አእመርክኒ | አወቅሺኝ |
| ተአምርኒ | ተውቂኛለሽ |
| ታእምርኒ | ታውቂኝ ዘንድ |
| አእምርኒ | እወቂኝ |

### ሸ. እኛን ስታውቂን

| | |
|---|---|
| አእመርክነ | አወቅሽን |
| ተአምሪነ | ታውቂናለሺ |
| ታእምሪነ | ታውቂኝ ዘንድ |
| አእምርሪነ | እወቂን |

## 7. የሩቆች ሴቶች

### ሀ. ሩቁን ወንድ ሲያውቁት

| | |
|---|---|
| አእመራሁ | አወቁት |
| የአምራሁ | ያውቁታል |
| ያእምራሁ | ያውቁት ዘንድ |
| ያእምራሁ | ይወቁት |

### ለ. የቅርቡን ወንድ ሲያውቁት

| | |
|---|---|
| አእመራከ | አወቁህ |
| የአምራከ | ያውቁሀል |
| ያእምራከ | ያውቁህ ዘንድ |
| ያእምራከ | ይወቁህ |

### መ. ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

| | |
|---|---|
| አእመራሆሙ | አወቁዋቸው |
| የአምራሆሙ | ያውቁዋቸዋል |
| ያእምራሆሙ | ያውቁዋቸው ዘንድ |
| ያእምራሆሙ | ይወቁዋቸው |

### ረ. ቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

| | |
|---|---|
| አእመራክሙ | አወቁዋችሁ |
| የአምራክሙ | ያውቁዋችሁዋል |
| ያእምራክሙ | ያውቁዋችሁ ዘንድ |
| ያእምራክሙ | ይወቁዋችው |

### ሰ. የሩቂቱን ሴት ሲያውቁዋት

| | |
|---|---|
| አእመራሃ | አወቁዋት |
| የአምራሃ | ያውቁዋታል |
| ያእምራሃ | ያውቁዋት ዘንድ |
| ያእምራሃ | ይወቁዋት |

### ሸ. የቅርቢቱን ሴት ስያውቁዋት

| | |
|---|---|
| አእመራኪ | አወቁሽ |
| የአምራኪ | ያውቁሻል |
| ያእምራኪ | ያውቁሽ ዘንድ |
| ያእምራኪ | ይወቁሽ |

ቀ. ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቁዋቸው

| | |
|---|---|
| አእመራሆን | አወቁዋቸው |
| የአምራሆን | ያውቁዋቸዋል |
| ያእምራሆን | ያውቁዋቸው ዘንድ |
| ያእምራሆን | ይወቁዋቸው |

በ. የቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቁዋቸው

| | |
|---|---|
| አእመራክን | አወቁዋችሁ |
| የአምራክን | ያውቁዋችሁዋል |
| ያእምራክን | ያውቁዋችሁ ዘንድ |
| ያእምራክን | ይወቁዋችሁ |

ተ. እኔን ሲያውቁኝ

| | |
|---|---|
| አእመራኒ | አወቁኝ |
| የአምራኒ | ያውቁኛል |
| ያእምራኒ | ያውቁኝ ዘንድ |
| ያእምራኒ | ይወቁኝ |

ቸ. እኛን ሲያውቁን

| | |
|---|---|
| አእመራነ | አወቁን |
| የአምራነ | ያውቁናል |
| ያእምራነ | ያውቁን ዘንድ |
| ያእምራነ | ይወቁን |

## 8. የቅርቦቹ ሴቶች

ሀ. የሩቁን ወንድ ሲያውቁት

| | |
|---|---|
| አእመርካናሁ | አወቃችሁት |
| ተአምራሁ | ታውቁታላችሁ |
| ታእምራሁ | ታውቁት ዘንድ |
| አእምራሁ | እወቁት |

ለ. የሩቆቹን ወንዶች ሲያውቁዋቸው

| | |
|---|---|
| አእመርክናሆሙ | አወቃችሁዋቸው |
| ተአምራሆሙ | ታውቁዋችዋላችሁ |
| ታእምራሆሙ | ታውቁዋቸው ዘንድ |
| አእምራሆሙ | እወቁዋቸው |

መ. ሩቂቱን ሴት ሲያውቁዋት

| | |
|---|---|
| አእምርክናሃ | አወቃችሁዋት |
| ተአምራሃ | ታውቁዋታላችሁ |
| ታእምራሃ | ታውቁዋት ዘንድ |
| አእምራሃ | እወቁዋት |

ረ. ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቁወቸው

| | |
|---|---|
| አእመርክናሆን | አወቃችሁዋቸው |
| ተአምራሆን | ታውቁዋቸዋላችው |
| ታእምራሆን | ታውቁዋቸው ዘንድ |
| አእምራሆን | አወቁዋቸው |

ሰ. እኔን ስታውቁኝ

| | |
|---|---|
| አእመርክናኒ | አወቃችሁኝ |
| ተአምራኒ | ታውቁኛላችሁ |
| ታእምራኒ | ታውቁኝ ዘንድ |
| አእምራኒ | እወቀኝ |

ሸ. እኛን ስታውቁን

| | |
|---|---|
| አእምርከናነ | አወቃችሁን |
| ተአምራነ | ታውቁናላችሁ |
| ታእምራነ | ታውቁን ዘንድ |
| አእምራነ | እውቁን |

## 9. እኔ

ሀ. የሩቁን ወንድ ሳውቀው

| | |
|---|---|
| አእመርክዎ | አወቅሁት |
| አአምሮ | አውቀዋለሁ |
| አእምሮ | አውቀው ዘንድ |
| አእምሮ | ልወቀው |

ለ. የቅርቡን ወንድ ሳውቅ

| | |
|---|---|
| አእመርኩክ | አወቅሁህ |
| አአምረከ | አውቅሀለሁ |
| አእምርከ | አውቅህ ዘንድ |
| አእምርከ | ልወቅህ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **መ. የሩቆቹን ወንዶች ሳውቃቸው** | | **ረ. የቅርቦቱን ወንዶች ሳውቅ** | |
| አእመርክዎሙ | አወቅሁዋቸው | አእመርኩክሙ | አወቅሁዋችሁ |
| አአምሮሙ | አውቃቸዋለሁ | አአምረክሙ | አውቃችሁዋለው |
| አእምሮሙ | አውቃቸው ዘንድ | አእምርክሙ | አውቃችሁ ዘንድ |
| አእምሮሙ | ልወቃቸው | አእምርክሙ | ልወቃችሁ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሰ. የሩቂቱን ሴት ሳውቃት** | | **ሸ. የቅርቢቱን ሴት ሳውቅ** | |
| አእመርክዋ | አወቅሁዋት | አእመርኩኪ | አወቅሁሽ |
| አአምራ | አውቃታለሁ | አአምረኪ | አውቅሻለሁ |
| አእምራ | አውቃት ዘንድ | አእምርኪ | አውቅሽ ዘንድ |
| አእምራ | ልወቃት | አእምርኪ | ልወቅሽ |
| **ቀ. የሩቆቹን ሴቶች ሳውቃቸው** | | **በ. የቅርቦችን ሴቶች ሳውቅ** | |
| አእመርክዎን | አወቅሁዋቸው | አእመርኩክን | አወቅሁዋችሁ |
| አአምሮን | አውቃቸዋለሁ | አአምረክን | አውቃችሁዋለሁ |
| አእምሮን | አውቃቸው ዘንድ | አእምርክን | አውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮን | ልወቃቸው | አእምርክን | ልወቃችው |

## 10. እኛ

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሀ. የሩቁን ወንድ ስናውቀው** | | **ለ. የቅርቡን ወንድ ስናውቅ** | |
| አእመርናሁ | አወቅነው | አእመርናከ | አወቀንህ |
| ነአምሮ | እናውቀዋለን | ነአምረከ | እናውቅሀለን |
| ናእምሮ | እናውቀው ዘንድ | ናእምርከ | እናውቅህ ዘንድ |
| ናእምሮ | እንወቀው | ናእምርከ | እንወቅህ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **መ. የሩቆቹን ወንዶች ስናውቃቸው** | | **ረ. የቅርቦቹን ወንዶች ስናውቅ** | |
| አእመርናሆሙ | አወቅናቸው | አእመርናክሙ | አወቅናቸው |
| ነአምሮሙ | እናውቃቸዋለን | ነአምረክሙ | እናውቃችሁዋለን |
| ናእምሮሙ | እናውቃቸው ዘንድ | ናእምርክሙ | እናውቃችሁ ዘንድ |
| ናእምሮሙ | እንወቃቸው | ናእምርክሙ | እንወቃችሁ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሰ. ሩቂቱን ሴት ስናውቃት** | | **ሸ. ቅርቢቱን ሴት ስናውቅ** | |
| አእመርናሃ | አወቅናት | አእመርናኪ | አወቅንሽ |
| ነአምራ | እናውቃታለን | ነአምረኪ | እናውቅሻለን |
| ናእምራ | እናውቃት ዘንድ | ናእምርኪ | እናውቅሽ ዘንድ |
| ናእምራ | እንወቃት | ናእምርኪ | እንወቅሽ |

ቀ. የሩቆቱን ሴቶች ስናውቃቸዉ

| | |
|---|---|
| አእመርናሆን | አውቅናቸው |
| ነአምሮን | እናውቃቸዋለን |
| ናእምሮን | እናውቃቸው ዘንድ |
| ናእምሮን | እንወቃቸው |

በ. የቅርቦቹን ሴቶች ስናውቅ

| | |
|---|---|
| አእመርናክን | አወቅናችሁ |
| ነአምረክን | እናውቃችሁዋለን |
| ናእምርክን | እናውቃችሁ ዘንድ |
| ናእምርክን | እንወቃችሁ |

## ረ. ሌሎች አረባብ

| | |
|---|---|
| 1. አእምሮ አእምሮት | ማወቅ |
| 2. አእምሮቱ | ማወቁ |
| 3. አእምሮትከ | ማወቅህ |
| 4. አእምሮቶሙ | ማወቃቸው |
| 5. አእምሮትክሙ | ማወቃችሁ |
| 6. አእምሮታ | ማወቋዋ |
| 7. አእምሮትኪ | ማወቅሽ |
| 8. አእምሮቶን | ማወቃቸው |
| 9. አእምሮትክን | ማወቃችሁ |
| 10. አእምሮትየ | ማወቂ |
| 11. አእምሮትነ | ማወቃችን |

## ሰ. ቦዝ

| | |
|---|---|
| 1. አእሚሮ | አውቆ |
| 2. አኢሚረከ | አውቀህ |
| 3. አእሚሮሙ | አውቀው |
| 4. አእሚረክሙ | አውቃችሁ |
| 5. አእሚራ | አውቃ |
| 6. አእሚረኪ | አውቀሽ |
| 7. አእሚሮን | አውቀው |
| 8. አእሚረክን | አውቃችሁ |
| 9. አእሚርየ | አውቂ |
| 10. አእሚረነ | አውቀን |

## ሸ. ቅጽል

| | |
|---|---|
| 1. አእማሪ | ያወቀ ፣ የሚያውቅ፣ያወቀህ፣የምታውቅ፣ያወቅሁ፣ የማወቅ |
| 2. አእማርያን | ያወቁ፣ የሚያውቁ፣ያወቃችሁ፣የምታውቁ |
| 3. አእማሪት | ያወቀች፣የምታውቅ፣ ያወቅሽ፣ የምታውቂ |
| 4. አእማርያት | ያወቁ ፣የሚያውቁ፣ ያወቃችሁ፣ የምታውቁ |
| 5. እሙር | የታወቀ፣ የሚታወቅ፣የታወቅህ፣ የምትታወቅ፣ ያወቅህ፣የምታውቅ |
| 6. እሙራን | የታወቁ፣ የሚታወቁ፣ የታወቃችሁ፣ የምትታወቁ |
| 7. እምርት | የታወቅሽ፣ የምትታወቂ ፣ የታወቀች፣ የምትታወቅ |
| 8. እሙራት | የታወቁ ፣የሚታወቁ፣ የታወቃችሁ፣ የምትታወቁ፣ |
| 9. ምእማር | ማወቂያ ፣ ማሳወቂያ |
| 10. ምስትእማር | መተዋወቂያ |
| 11. እምረት | ማወቅ |

## II ይቤ

ይህ ግስ ክሌሎች የግእዝ መደበኛ ግሶች የተለየ በመሆኑ ነባር ግስ ይባላል። ነባር የተባለበትም ምክንያት በሶስተኛ ስነ ቀዳማይ በግእዝ የማይደርስ በመሆኑ ነው። በደቂቅ እርባታ ጊዜ የብህለን የአረባብ ስርአት ይከተላል ለማሳያ ይሆን ዘንድ የአረባብ ስርአቱ ቀጥሎ ቀርቡዋል።

| ነጠላ | | ብዙ | |
|---|---|---|---|
| **1. የይቤ አወራረድ** | | | |
| ይቤ | አለ | ይቤሉ | አሉ |
| ይብል | ይላል | ይብሉ | ይላሉ |
| ይበል | ይል ዘንድ | ይበሉ | ይሉ ዘንድ |
| ይበል | ይበል | ይበሉ | ይበሉ |
| ትቤ | አልህ | ትቤሉ | አላችሁ |
| ትብል | ትላለህ | ትብሉ | ትላላችሁ |
| ትበል | ትል ዘንድ | ትበሉ | ትሉ ዘንድ |
| በል | በል | በሉ | በሉ |
| ትቤ | አለች | ይቤላ | አሉ |
| ትብል | ትላለች | ይብላ | ይላሉ |
| ትበል | ትል ዘንድ | ይበላ | ይሉ ዘንድ |
| ትበል | ትበል | ይበላ | ይበሉ |
| ትቤሊ | አልሽ | ትቤላ | አላችሁ |
| ትብሊ | ትያለሽ | ትብላ | ትላላችሁ |
| ትበሊ | ትይ ዘንድ | ትበላ | ትሉ ዘንድ |
| በሊ | በይ | በላ | በሉ |
| እቤ | አልሁ | ንቤ | አልን |
| እብል | እላለሁ | ንብል | እንላለን |
| እበል | እል ዘንድ | ንበል | እንል ዘንድ |
| እበል | ልበል | ንበል | እንበል |

2. ባለቤቱ ሶስተኛ ሰው የሆነ ተባእታይ ነጠላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤሎ | አለው | ይቤሎሙ | አላቸው |
| ይብሎ | ይለዋል | ይብሎሙ | ይላቸዋል |
| ይበሎ | ይለው ዘንድ | ይበሎሙ | ይላቸው ዘንድ |
| ይበሎ | ይበለው | ይበሎሙ | ይበላቸው |
| ይቤለከ | አለህ | ይቤለክሙ | አላችሁ |
| ይብለከ | ይልሀል | ይብለክሙ | ይላችሁዋል |
| ይበልከ | ይልህ ዘንድ | ይበልክሙ | ይላችሁ ዘንድ |
| ይበልከ | ይበልህ | ይበልክሙ | ይበላችሁ |
| ይቤላ | አላት | ይቤሎን | አላቸው |
| ይብላ | ይላታል | ይብሎን | ይላቸዋል |
| ይበላ | ይላት ዘንድ | ይበሎን | ይላቸው ዘንድ |
| ይበላ | ይበላት | ይበሎን | ይበላቸው |
| ይቤለኪ | አለሽ | ይቤለክን | አላችሁ |
| ይብለኪ | ይልሻል | ይብለክን | ይላችሁዋል |
| ይበልኪ | ይልሽ ዘንድ | ይበልክን | ይላችሁ ዘንድ |
| ይበልኪ | ይበልሽ | ይበልክን | ይበላችሁ |
| ይቤለኒ | አለኝ | ይቤለነ | አለን |
| ይብለኒ | ይለኛል | ይብለነ | ይለናል |
| ይበለኒ | ይለኝ ዘንድ | ይበለነ | ይለን ዘንድ |
| ይበለኒ | ይበለኝ | ይበለነ | ይበለን |

3. ባለቤቱ ሁለተኛ ሰው የሆነ ተባእታይ ነጠላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤሎ | አልከው | ትቤሎሙ | አልሀቸው |
| ትብሎ | ትለዋለህ | ትብሎሙ | ትላችዋለህ |
| ትበሎ | ትለው ዘንድ | ትበሎሙ | ትላቸው ዘንድ |
| በሎ | በለው | በሎሙ | በላቸው |
| ትቤላ | አልሀት | ትቤሎን | አልሀቸው |
| ትብላ | ትላታለህ | ትብሎን | ትላቸዋለህ |
| ትበላ | ትላት ዘንድ | ትበሎን | ትላቸው ዘንድ |
| በላ | በላት | በሎን | በላቸው |
| ትቤለኒ | አልኸኝ | ትቤለነ | አልኸን |
| ትብለኒ | ትለኛለህ | ትብለነ | ትለናለህ |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትበለኒ | ትለኝ ዘንድ | ትበለነ | ትለን ዘንድ |
| በለኒ | በለኝ | በለነ | በለን |

### 4. ባለቤቶቹ ሶስተኛ ሰዎች የሆኑ ተባእታይ ብዙ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤልዎ | አሉት | ይቤልዎሙ | አሉዋቸው |
| ይብልዎ | ይሉታል | ይብልዎሙ | ይሉዋቸዋል |
| ይበልዎ | ይሉት ዘንድ | ይበልዎሙ | ይሉዋቸው ዘንድ |
| ይበልዎ | ይበሉት | ይበልዎሙ | ይበሉዋቸው |
| ይቤሉከ | አሉህ | ይቤሉክሙ | አሉዋችሁ |
| ይብሉከ | ይሉሀል | ይብሉክሙ | ይሉዋችሁዋል |
| ይበሉከ | ይሉህ ዘንድ | ይበሉክሙ | ይሉዋችሁ ዘንድ |
| ይበሉከ | ይበሉህ | ይበሊክሙ | ይበሉዋችሁ |
| ይቤልዋ | አሉዋት | ይብልዎን | አሉዋቸው |
| ይብልዋ | ይሉዋታል | ይብልዎን | ይሉዋቸዋል |
| ይበልዋ | ይሉዋት ዘንድ | ይበልዎን | ይሉዋቸው ዘንድ |
| ይበልዋ | ይበሉዋት | ይበልዎን | ይበሉዋቸው |
| ይቤሉኪ | አሉሽ | ይቤሉክን | አሉዋችሁ |
| ይብሉኪ | ይሉሻል | ይብሉክን | ይሉዋችሁዋል |
| ይበሉኪ | ይሉሽ ዘንድ | የበሉክን | ይሉዋችሁ ዘንድ |
| ይበሉኪ | ይበሉሽ | ይበሉክን | ይበሉዋችሁ |
| ይቤሉኒ | አሉኝ | ይቤሉነ | አሉን |
| ይብሉኒ | ይሉኛል | ይበሉነ | ይሉናል |
| ይበሉኒ | ይሉኝ ዘንድ | ይበሉነ | ይሉን ዘንድ |
| ይበሉኒ | ይበሉኝ | ይበሉነ | ይበሉን |

### 5. ባለቤቶቹ ሁለተኛ ሰዎች የሆኑ ተባእታይ ብዙ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤልዎ | አላችሁት | ትቤልዎሙ | አላችሁዋቸው |
| ትብልዎ | ትሉታላችሁ | ትብልዎሙ | ትሉዋቸዋላችሁ |
| ትበልዎ | ትሉት ዘንድ | ትበልዎሙ | ትሉዋቸው ዘንድ |
| በልዎ | በሉት | በልዎሙ | በሉዋቸው |
| ትቤልዋ | አላችሁዋት | ትቤልዎን | አላችሁዋቸው |
| ትብልዋ | ትሉዋታላችሁ | ትብልዎን | ትሉዋቸዋላችሁ |
| ትበልዋ | ትሉዋት ዘንድ | ትበልዎን | ትሉዋቸው ዘንድ |
| በልዋ | በሉዋት | በልዎን | በሉዋቸው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤሉኒ | አላችሁኝ | ትቤሉነ | አላችሁን |
| ትብሉኒ | ትሉኛላችሁ | ትብሉነ | ትሉኛላችሁ |
| ትብሉኒ | ትሉኝ ዘንድ | ትብሉነ | ትሉን ዘንድ |
| በሉኒ | በሉኝ | በሉነ | በሉን |

6. ባለቤትዋ ሶስተኛ ሰው የሆነች አንስተይ ነጠላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤሎ | አለችው | ትቤሎሙ | አለቻቸው |
| ትብሎ | ትለዋለች | ትብሎሙ | ትላቸዋለች |
| ትብሎ | ትለው ዘንድ | ተብሎሙ | ትላቸው ዘንድ |
| ትብሎ | ትበለው | ትብሎሙ | ትበላቸው |
| ትቤለከ | አለችህ | ትቤለክሙ | አለቻችሁ |
| ትብለከ | ትልሀለች | ትብለክሙ | ትላችሁዋለች |
| ትብልከ | ትልህ ዘንድ | ትብልክሙ | ትላችሁ ዘንድ |
| ትብልከ | ትበልህ | ትብልክሙ | ትበላችሁ |
| ትቤላ | አለቻት | ትቤሎን | አለቻቸው |
| ትብላ | ትላታለች | ትብሎን | ትላቸዋለች |
| ትብላ | ትላት ዘንድ | ትብሎን | ትላቸው ዘንድ |
| ትብላ | ትበላት | ትብሎን | ትበላቸው |
| ትቤለኪ | አለችሽ | ትቤለክን | አለቻችሁ |
| ትብለኪ | ትልሻለች | ትብለክን | ትላችሁዋለች |
| ትብልኪ | ትልሽ ዘንድ | ትብልክን | ትላችሁ ዘንድ |
| ትብልኪ | ትበልሽ | ትብልክን | ትበላችሁ |
| ትቤለኒ | አለችኝ | ትቤለነ | አለችን |
| ትብለኒ | ትለኛለች | ትብለነ | ትለናለች |
| ትብለኒ | ትለኝ ዘንድ | ትብለነ | ትለን ዘንድ |
| ትብለኒ | ትበለኝ | ትብለነ | ትበለን |

7. ባለቤትዋ ሁለተኛ ሰው የሆነች አንስታይ ነጠላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤልዮ | አልሽው | ትቤሊዮሙ | አልሻቸው |
| ትብሊዮ | ትይዋለሽ | ትብሊዮሙ | ትያቸዋለሽ |
| ትብሊዮ | ትይው ዘንድ | ትብሊዮሙ | ትያቸው ዘንድ |
| በሊዮ | በይው | በሊዮሙ | በያቸው |
| ትቤሊያ | አልሻት | ትቤልዮን | አልሻቸው |
| ትብሊያ | ትያታለሽ | ትብሊዮን | ትያቸዋለሽ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትበሊያ | ትያት ዘንድ | ትበሊዮን | ትያቸው ዘንድ |
| በሊያ | በያት | በሊዮን | በያቸው |
| ትቤልኒ | አልሽኝ | ትቤልነ | አልሽን |
| ትብልኒ | ትይኛለሽ | ትብልነ | ትይናለሽ |
| ትብልኒ | ትይኝ ዘንድ | ትብልነ | ትይን ዘንድ |
| በልኒ | በይኝ | በልነ | በይን |

8. ባለቤቶቹ ሶስተኛ ሰዎች የሆኑ አንስታይ ብዙ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤላሁ | አሉት | ይቤላሆሙ | አሉዋቸው |
| ይብላሁ | ይሉታል | ይብላሆሙ | ይሉዋቸዋል |
| ይበላሁ | ይሉት ዘንድ | ይበላሆሙ | ይሉዋቸው ዘንድ |
| ይበላሁ | ይበሉት | ይበላሆሙ | ይበሉዋቸው |
| ይቤላከ | አሉህ | ይቤላክሙ | አሉወችሁ |
| ይብላከ | ይሉሀል | ይብላክሙ | ይሉዋችሁዋል |
| ይበላከ | ይሉህ ዘንድ | ይበላክሙ | ይሉዋችሁ ዘንድ |
| ይበላከ | ይበሉህ | ይበላክሙ | ይበሉዋችሁ |
| ይቤላሃ | አሉት | ይቤላሆን | አሉዋቸው |
| ይብላሃ | ይሉዋታል | ይብላሆን | ይሉዋቸዋል |
| ይበላሃ | ይሉዋት ዘንድ | ይበላሆን | ይሉዋቸው ዘንድ |
| ይበላሃ | ይበሉዋት | ይበላሆን | ይበሉዋቸው |
| ይቤላኪ | አሉሽ | ይቤላክን | አሉዋችሁ |
| ይብላኪ | ይሉሻል | ይብላክን | ይሉዋችሁዋል |
| ይበላኪ | ይሉህ ዘንድ | ይበላክን | ይሉዋችሁ ዘንድ |
| ይበላኪ | ይበሉህ | ይበላክን | ይበሉዋችሁ |
| ይቤላኒ | አሉኝ | ይቤላነ | አሉን |
| ይብላኒ | ይሉኛል | ይብላነ | ይሉናል |
| ይበላኒ | ይሉኝ ዘንድ | ይበላነ | ይሉን ዘንድ |
| ይበላኒ | ይበሉኝ | ይበላነ | ይበሉን |

9. ባለቤቶቹ ሁለተኛ ሰዎች የሆኑ አንስታይ ብዙ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤላሁ | አላችሁት | ትቤላሆሙ | አላችሁዋቸው |
| ትብላሁ | ትሉታላችሁ | ትብላሆሙ | ትሉዋቸዋላችሁ |
| ትበላሁ | ትሉት ዘንድ | ትበላሆሙ | ትሉዋቸው ዘንድ |
| በላሁ | በሉት | በላሆሙ | በሉዋቸው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤላሃ | አላችሁዋት | ትቤላሆን | አላችሁዋቸው |
| ትብላሃ | ትሉዋታላችሁ | ትብላሆን | ትሉዋቸዋላችሁ |
| ትበላሃ | ትሉዋት ዘንድ | ትበላሆን | ትሉዋቸው ዘንድ |
| በላሃ | በሉዋት | በላሆን | በሉዋቸው |
| | | | |
| ትቤላኒ | አላችሁኝ | ትቤላነ | አላችሁን |
| ትብላኒ | ትሉኛላችሁ | ትብላነ | ትሉናላችሁ |
| ትበላኒ | ትሉኝ ዘንድ | ትበላነ | ትሉን ዘንድ |
| በላኒ | በሉኝ | በላነ | በሉን |

10. በለቤቱ አንደኛ ሰው የሆንኩ ተባእታይ አንስታይ ነጠላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| እቤሎ | አልሁት | እቤሎሙ | አልሁዋቸው |
| እብሎ | እለዋለው | እብሎሙ | እላቸዋለሁ |
| እበሎ | እለው ዘንድ | እበሎሙ | እላቸው ዘንድ |
| እበሎ | ልበለው | እበሎሙ | ልበላቸው |
| | | | |
| እቤለከ | አልሁህ | እቤለክሙ | አልሁዋችሁ |
| እብለከ | እልሀለሁ | እብለክሙ | እላችሁዋለሁ |
| እበልከ | እልህ ዘንድ | እበልክሙ | እላችሁ ዘንድ |
| እበልከ | ልበልህ | እበልክሙ | ልበላችሁ |
| | | | |
| እቤላ | አልሁዋት | እቤሎን | አልሁዋቸው |
| እብላ | እላታለሁ | እብሎን | እላችሁዋለሁ |
| እበላ | እላት ዘንድ | እበሎን | እላቸው ዘንድ |
| እበላ | ልበላት | እበሎን | ልበላቸው |
| | | | |
| እቤለኪ | አልሁሽ | እቤለክን | አልሁዋችሁ |
| እብለኪ | እልሻለሁ | እብለክን | እላችሁዋለሁ |
| እበልኪ | እልሽ ዘንድ | እበልክን | አላችሁ ዘንድ |
| እበልኪ | ልበልሽ | እበልክን | ልበላችሁ |

11. ባለቤቶቹ አንደኛ ሰዎች የሆኑ ተባእታይ/ እንስታይ ብዙ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንቤሎ | አልነው | ንቤሎሙ | አልናችሁ |
| ንብሎ | እንለዋለን | ንብሎሙ | እንላችሁዋለን |
| ንበሎ | እንለው ዘንድ | ንበሎሙ | እንላቸው ዘንድ |
| ንበሎ | እንበለው | ንበሎሙ | እንበላቸው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንቤለከ | አልንህ | ንቤለክሙ | አልናችሁ |
| ንብለከ | እንልሀለን | ንብለክሙ | እንላችሁዋለን |
| ንበልከ | እንልህ ዘንድ | ንበልክሙ | እንላችሁ ዘንድ |
| ንበልከ | እንበለው | ንበልክሙ | እንበላችሁ |
| | | | |
| ንቤላ | አልናት | ንቤሎን | አልናቸው |
| ንብላ | እንላታለን | ንብሎን | እንላቸዋለን |
| ንበላ | እንላት ዘንድ | ንበሎን | እንላቸው ዘንድ |
| ንበላ | እንበላት | ንበሎን | እንበላቸው |
| | | | |
| ንቤለኪ | አልንሽ | ንቤለክን | አልናችሁ |
| ንብለኪ | እንልሻለን | ንብለክን | እንላችሁዋለን |
| ንበልኪ | እንልሽ ዘንድ | ንበልክን | እንላችሁ ዘንድ |
| ንበልኪ | እንበልሽ | ንበልከን | አንበላችሁ |

### 4.2.2 የቅኔ ዘረፋ፣ ቅበላና ቅጸላ

በአንድ የቅኔ ጉባኤ ውስጥ ቅኔን መዝረፍ፣ መቀበልና መቀጸል በየእለቱ የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራት ናቸው። አተገባበራቸውም ሆነ አፈጻጸማቸው የተለያየ ነው። የቅኔ ዘረፋው ተግባር የሚከናወነው፣ በጉባኤው መምህር ወይም መምህሩ የዘረፋ ስልጣን በሰጣቸው ተማሪዎች አማካኝነት ሊሆን ይችላል። የቅኔ ቅበላው ስርአት የሚፈጸመው ደግሞ የቅኔ ሙያው ምስጢር በገባውና የሚዘረፈውን ቅኔ በተከታታይና በፍጥነት እየተቀበለ ሳይዘነጋ ለጉባኤው ማቀበል የሚችል፣ ከጉባኤው ተማሪዎች መካከል የሚመረጥ ተማሪ ነው።



ወጣቱ የቅኔ ተማሪ በተከታታይ የሚዘረፈውን ቅኔ እየተቀበለ
ለተማሪዎች በሚያስተጋባበት ወቅት፤

የቅኔ ቅጸላው የሚካሄደው ግን በሁሉም የጉባኤው ተማሪዎች አማካኝነት ነው። ከመምህሩ ጀምሮ ሁሉም ተማሪ እንደየእውቀት ደረጃው አንደኛው ለሌላው የማስቀጸል ባህሉ በቅኔ ጉባኤ ውስጥ የተለመደ ተግባር ነው። የሚቀጸለው ደግሞ በየእለቱ የሚወርደው ግስ፣ የሚተረከው ታሪክ ወይም የሚዘረፈው ቅኔ ከነንዝኑ ሊሆን ይችላል (ቪ. ካ. ቁ 2)።



የቅኔ ተማሪዎች በእለቱ የተዘረፈውን ቅኔ በጋራ ሆነው በሚቀጽሉበት ወቅት።

ስለ ቅኔ ዘራፊ፣ ተቀባይና አስቀጻይ ጽንሰ ሃሳብ የበለጠ ለመረዳት ርእስ ጉዳዩን አስመልክቶ የተለያዩ ባለሙያዎች የሰጡትን ሃሳብ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል። ዜና ማርቆስ እንዳለው ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር ሁለት በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሀፍ የሚከተለውን አስፍረዋል።

ቅኔ ዘራፊው የቅኔ ሲቅ እንደመሆኑ መጠን ባየው በሰማው ሁሉ ቅኔ እንደበረዶ የሚያወርድ፣ ቅኔ የሚፈጥር፣ የሚፈለስፍ፣ የሚመረምርና የሚያራቅቅ ምሁር ነው:: ቅኔ ተቀባይ ደግሞ ቅኔ ዘራፊው «ተነስ ተቀበል!» ሲል በፍጥነት ብድግ ብሎ ቅኔውን እንደማዕበል ሲያወርደው መምህሩ ወይም ዘራፊው እንደዘረፈው መጠን ቶሎ ቶሎ ቅኔውን እየተቀበለ ለአድማጮቹ የሚያኑብ በቅኔ የሰለጠነ ተማሪ ነው:: ቅኔ አስቀጻይ ግን የተዘረፈውንም ሆነ ተማሪው ለመምሩ ነገሮ ያሳረመውን ቅኔ ንባቡን፣ ፍችውን፣ ምሣሌውንና ሙያውን፣ ተሳሳቢውንም ሆነ ምስጢሩን ተንትኖ ለጀማሪው የሚያስጠና የለየ ተማሪ ነው (ዜና ማርቆስ 1997፣138-139)::

ዘረፋ ማለት በጉልበት ወይም በማታለል ንብረት መንጠቅ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: በቅኔ ሙያ እጅግ የሰለጠነ ደቀ መዝሙር ወይም የቅኔ ጉባኤው መምህር ጊዜ ወስዶና አስቦ መቁጠርና ማደራጀት ሳያስፈልገው ከብሉያት፣ ከሀዲሳት፣ ከነቢያት፣ ከሀዋርያት፣ ከሰማእታት፣ ከሊቃውንት፣ ከመነኮሳት፣ ከነገስታትና ከሰነቃላት ታሪክ እየተነሳ የቅኔን ህንጻ በቅጽበት እየገነባ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ቅኔን በቅጽበት መቀኘት ማለት ነው:: መምህር ለይኩን እንደሚከተለው ይገልጹታል::

የቅኔ ዘራፊ የመምህሩ ምክትል ሆኖ የሚያገለግል፣ በጉባኤ ውስጥ በመቆየት ቀሪ ጥቃቅን የቅኔ ሙያ ትምህርቶችን ከመምህሩ እየቀጸለ ጉባኤ ለመትከል ምርቃትን የሚጠባበቅ የመምህሩ ተተኪ የቅኔ ሙያ ባለቤት የሆነ ደቀ መዝሙር ነው (ለይኩን: 1999: ካ.ቁ 2፣ ቪ.ኮ.ቁ 2)::

መሪጌታ ለይኩን ሀሳባቸውን በማራዘም አንድ ደቀመዝሙር የቅኔው ምስጢር ገብቶት የቅኔ ዘራፊ ለመሆን በሚቃረብበት ጊዜ የሚያሳያቸው ባህሪያትና የሚፈጽማቸው የተለያዩ ተግባራት መኖራቸውን ይገልጻሉ:: ደቀመዝሙሩ፣ መምህሩ የሚዘርፋቸውን የቅኔ ቤቶች መገልበጥ፣ የሚዘረፉና የሚነገሩ ቅኔዎችን መንጠቅ ይሞክራል:: የቅኔው ምስጢር እና ሙያ የገባው ተማሪ የቅኔውን ቤት በሚገለብጥበት ጊዜ የሚከተላቸው ህግጋት አሉ:: መምህሩ በግእዝ ቤት የዘረፈውን በሳድስ፣ በካእብ የዘረፈውን በሳብእ፣ በሳልስ የዘረፈውን በሀምስ፣ በራብእ የዘረፈውን ደግሞ መልሶ በራብእ ይገለብጠዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ መምህሩ የዘረፈውን የቅኔ ምስጢር በአዎንታ አቅርቦት ከሆነ በአሉታ፣ በአሉታ አቀርቦት ከሆነ ደግሞ በአዎንታ እንደ አዲስ በማደራጀት የመምህሩን የቅኔ ምስጢር መገልበጥ ይጀምራል:: አንድ ደቀ መዝሙር የመምህሩን ቅኔ፣ ቤቱንና ምስጢሩን በዚህ ሁኔታ መገልበጥ ሲሞክርና ብቃቱንም እያጉለመሰ ሲሄድ የጀማሪ ዘራፊነት ማእረግ ለማግኘት የሚያስችል ብቃት ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ እንደሆነ መምህር ለይኩን ይገልጻሉ::



መሪጌታ ለይኩን ብርሀኑ በቅኔ ዘረፋ ላይ ሳሉ፤

በአብዛኛዎቹ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች፣ የቅኔ ዘረፋው ተግባር የሚከናወነው በጉባኤው መሪጌታና ሙሉ የዘራፊነት ስልጣን በተሰጣቸው ዘራፊ ተማሪዎች አማካኝነት ነው:: የየእለቱም የዘረፋ ተግባር የሚከናወነው የዘረፋውን ተግባር ለማከናወን በጉባኤው በሚወጣ ድልድል መሰረት ነው:: በዘረፋው ተግባር ድልድል ውስጥ ገብተው የዘረፋውን ተግባር በቋሚነት የሚያከናውኑት፣ ሙሉ የዘራፊነት ስልጣን በተሰጣቸው ተማሪዎችና በመሪጌታው አማካኝነት ነው:: የዘራፊነት ስልጣን የተሰጣቸው ተማሪዎች በሌሉበት ወቅት ግን በመሪጌታው ብቻ ይከናወናል:: የሙሉ ዘራፊነትን ደረጃ ለማግኘት የተለያዩ እርከኖችን ማለፍ ግድ መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ መሪጌታ ማማሩ ናቸው::

> የቅኔ ዘራፊዎች የተለያየ ደረጃ አላቸው:: በጉባኤው መምህርና በሌሎች ዘራፊዎች ሙሉ በሙሉ ታምኖበት «ዘራፊነት ይገባዋል!» ተብሎ የዘራፊነት ማእረግ የተሰጠው ደቀ መዝሙር ዘራፊ ይባላል:: ይህ ማእረግ የተሰጠው ደቀ መዝሙር በመደበኛው የቅኔ ዘረፋ ድልድል ውስጥ ገብቶ እስከ ሙሉ ቤት ድረስ ቅኔን የመዝረፍ ስልጣን ያለው ነው:: እጩ ዘራፊ የሚባለው ግን የመምህሩን ወይም የዘራፊዎችን ቅኔዎች ቤትና ምስጢር መገልበጥ በመቻሉና በቅኔው ሙያ እጅግ እየበሰለ በመገኘቱ የጀማሪ ዘራፊነት ማእረግ የተሰጠው ጀማሪ ዘራፊ ነው:: የዘረፋ ተግባርም የሚያከናውነው መምህሩና ሌሎች ዘራፊዎች በሌሉበት ጊዜ ሆኖ ዘረፋም የሚፈቅድለት ከጉባኤ ቃና እስከ ዋዜማ ብቻ ነው (ማማሩ: 1999: ካ .ቁ.4)::

የቅኔ ዘረፋ ራሱን የቻለ የአጀማመር፣ የአተገባበርና የአፈፃፀም ስርአት አለው። ማታ ተማሪው ከየዋለበት ቦታ ተሰብስቦ በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ የጸሎቱ (ማስታኩቱ) ስነ ስርአት እንዳበቃ መምህሩ የእለቱን ትምህርት ለማስተማር በተዘጋጀው ቦታ ይቀመጣሉ። ጀማሪ ተማሪዎች ቅኔ የለዩ ተማሪዎችን  በቡድን በቡድን ከበው ሲቀመጡ፣ ራሳቸውን ችለው ትምህርቱን ለመከታተል የሚችሉት ደግሞ ለየብቻቸው ይቀመጣሉ። በመምህሩ አማካኝነት ግስ ወርዶ እንዳበቃ የቅኔ ዘረፋው እንዲቀጥል መምህሩ በጭብጨባ ያሳውቃሉ። የእለቱ ቅኔ ተቀባይ ተማሪ የሚዘረፈውን  ቅኔ ለመቀበል ተነስቶ ይቆማል። የእለቱ ተረኛ ዘራፊ ወይም መምህሩ በለሆሳስ ተጀምሮ በፉከራ መልክ እየጐላ በሚሄድ  ድምጽ የዘርፋ ተግባሩን ማከናወን ይጀምራሉ። የቅኔ ዘርፋው ከጉባኤ ቃና ይጀምርና ለቅጸላ ፋታ እየተሰጠ በቅደም ተከተል እስከ መወድስ  ድረስ ይዘርፋል። እንደ እለቱ ተረኛ ዘራፊ አቅምና ችሎታ ዘርፋው ከአንድ ሙሉ ቤት በላይ ማለትም ሁለትም ሶስትም ሙሉ ቤት ሊዘርፍ  ይችላል (ቪ.ክ.ቁ.2)።



የቅኔ ዘራፊው በስሜት ውስጥ ሆኖ በቅኔ ዘረፋ ላይ ሳለ፤

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ቅጸላውና ዘረፋው እንዳበቃ፣ በእለቱ የተዘረፈው ቅኔ በዘረፋ ተቀባይ ተማሪው አማካኝነት በቅድም ተከተል እየተነበበ የእያንዳንዱ ቅኔ ትርጉም ይፈታል። ታሪኩም ይገለጻል። ሙያው፣ አግባቡና ሰምና ወርቁ ይተነተናል፤ ይራቀቃል። የእያንዳንዱ ቅኔ ዘር፣ ትርጉም፣ ታሪክ፣ ሰዋስው፣ ምሳሌና ሙያ፣ ርቀትና ምስጢሩ በዝርዝር ተማሪዎች እንዲያጠኑት ይደረጋል። ባጠኑት ቅኔ መሰረት በነጋታው እንደየደረጃቸው ቅኔ ለመቁጠር በማወዳደሪያነትና በምሳሌነት ይጠቀሙበታል።

### 4.2.3 ቅኔ ቆጠራና ነገራ

ቅኔ ቆጠራና ነገራ፣ በአንድ የቅኔ ትምህርት ቤት (ጉባኤ) ውስጥ በቅደም ተከተል ከሚከናወኑ የግእዝ ቅኔ ትምህርቶች መካከል የተወሰኑት ናቸው። በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ 'ቆጠራ' ማለት ቅኔን ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ ማደራጀትና ማራቀቅ ማለት ሲሆን 'ነገራ' ማለት ደግሞ የተቆጠረን ቅኔ ለጉባኤው መምህር ወይም አስነጋሪው መንገር የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የያዘ ነው። ቅኔ ቆጣሪ፣ አስቆጣሪ፣ ነጋሪና አስነጋሪ ለሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች ዜና ማርቆስ እንዳለው የሚከተለውን አስፍረዋል።

> ቅኔ ቆጣሪ ማለት በየቁጥቋጦው፣ በየዛፉና በየአውደ ቤተ ክርስቲያኑ ስር ቁጭ ብሎ ቅኔ የሚቆጥር፣ የሚደርስ፣ የሚያሳካ ተማሪ ነው። ቅኔ አስቆጣሪ ደግሞ የራሱን ቅኔ ሲቆጥር ጀማሪውን ተማሪ ከአጠገቡ አስቀምጦ የግእዙን ቋንቋ ቃላት ወደ አማርኛ እየተረጐመ የሚነግር፣ የቅኔው ሀረግና ዜማ ልክ መሆኑን የሚያስረዳ ቅኔ የለየ ተማሪ ነው። ቅኔ ነጋሪ ማለት ቅኔ ቆጥሮ እያገጣጠመና እየደረሰ ለመምህሩ የሚነግር እና የሚያሳርም ተማሪ ሲሆን ቅኔ አስነጋሪ ማለት ደግሞ ወደ ጫካ ወይም ዘዋራ ቦታ ሄዶ ቅኔን ቆጥሮ፣ አገጣጥሞና ደርሶ የሚያመጣውን ተማሪ እያስነገረ የቅኔውን ሀረግ፣ ዜማና ተሳሳቢውን እያስተካከለ የሚያርም እጩ መምህር ወይም የጉባኤዉ መምህር ነው (ዜና ማርቆስ 1997፣ 139)።

በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ትምህርታቸውን የሚያጠኑ ተማሪዎች የተለመደ የቅኔ አቆጣጠርና አነጋገር ስርአት አላቸው። ተማሪዎቹ ንጋት ላይ የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቀው በጥዋቱ ከጉባኤው አዳራሽ ወጥተው ይበተናሉ። ብዙም ሳይቆዩ ከሁለት እስከ ሁለት ተኩል ባለው ጊዜ የእለቱን የቅኔ ቆጠራ ተግባር ለማከናወን ወደየቦታው ይሰማራሉ። አብዛኛዎቹ በአካባቢው ባለው ጫካ ውስጥ ገብተው ይሰገሰጋሉ። ጥቂቶቹ ደግሞ በአካባቢው ወዳለ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ በካቡና በአጸዱ ዙሪያ ይደበቃሉ። የቅኔው ጀማሪ የሆኑ ተማሪዎች ቅኔ የለዩትን ከኋላ ከኋላ እየተከታተሉ አብረው ይሰማራሉ። ጀማሪ የቅኔ ተማሪዎች ለምን ቅኔ የለዩትን ተከትለው ለቆጠራ እንደሚሰማሩና ለቅኔ ቆጠራ ለምን ዘዋራ የሆነ ቦታ እንደሚመርጡ ደብተራ ብርሃን የሚከተለውን ሃሳብ ስንዝረዋል።

ጀማሪዎቹ የለዩ ተማሪዎችን በቆጠራ ጊዜ የሚከተሉት ቅኔ በሚቆጥሩበት ሰአት፣ የትርጉም፣ የዜማና የሙያ እንቅፋት ሲያውካቸው እርዳታ ለማግኘት ነው። ሁሉም ተማሪዎች ወደ ቆጠራ ሲወጡ የሚመርጡት ዘዋራ ቦታ ነው። የዚህ ምክንያቱ በሚቆጥሩበት ጊዜ በአካባቢው የሚያዩት ነገር ገጥሙዋቸው ቆጠራቸው እንዳይሰናከል፣ ሃሳባቸው እንዳይበታተንና የቆጠራው ተግባር እንዳይደናቀፍ ለመጠንቀቅ ነው» /ደብተራ ብርሃን 1999 ካ.ቁ.5/

ለቅኔ ቆጠራው ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚሰማሩት ተማሪዎች የቆጠራ ተግባራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ሃሳባቸው ተሰባስቦ ቅኔን በቀላሉ ለመቁጠር ያስችላቸው ዘንድ፣ አንዳንዶቹ ከማደሪያ ጎጇዎቸው ይዘውት የወጡትን አጉዋዛ ወይም ሰኔል ከመሬት ላይ አንጥፈውና በላዩ ላይ ጋደም ብለው ማሰብና ማሰላሰል ይጀምራሉ። ገሚሶቹ በለበሱት ደበሎ /ለምድ/ በአሁኑ ጊዜ «ጎጃም አዘነ» ተጠቅልለው ይተኙና ምስጢር ይፈልጋሉ። ገሚሶቹ ደግሞ ፊታቸውን በጉልበታቸው ሸፍነው፣ የቆጠራ ተግባራቸውን ለመጀመር ሃሳባቸውን ያወጡ ያወርዳሉ። ከተወሰነ ሰአት በሁዋላ አንዳንዱ መጋደሙና መቀመጡ ሲሰለቸው ከወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሰ የቆጠረውን ቅኔ ማሳካትና ማደራጀት ይሞክራል።

የቅኔ ቆጠራው ያልተሳካለት ከቆየበት ቦታ ተነስቶ ሌላ ቦታ ይቀይራል። ምስጢር አልገለጽልህ ሲለው በሃሳብ ሲባዝን ይስተዋላል። አንድን ቅኔ ቆጥሮ ለመምህሩ ለመንገር ቅድሚያ የቅኔው ምስጢር የሚሆን አሳማኝ ታሪክ ማግኘትን ይጠይቃል። ቅኔውን የተሙዋላ አድርጎ ለመንገር ደግሞ ምስጢር ማግኘት ብቻ በቂ አይደለም። የተገኘውን ምስጢር በሰምና በወርቅ ለይቶ፣ ግጥሙን አሳክቶ፣ ዜማው እንዳይሰብር ተጨንቆ፣ አገባቡ እንዳይፋለስ፣ ሙያው እንዳይጣረስና ጸያፍ ቃላት እንዳይኖሩ ተጠንቅቆ ማሰብን ይጠይቃል። ይህ በመሆኑ ቅኔን አስተካክሎ ቆጥሮ ለመምህር ለማቅረብ ያለው ፈተና በተለይ ለጀማሪ ተማሪ እጅግ ከባድ ነው።

በጠዋቱ ለቅኔ ቆጠራ የተበተኑት ተማሪዎች እንደየደረጃቸው ቅኔን ሲቆጥሩ ውለው ከቀኑ አምስት ሰአት ጀምሮ የቆጠሩትን ቅኔ ለመንገር ወደ ትምህርት ጉባኤው ይመለሳሉ። እንደ ቆጠራው ጊዜ ሁሉ በነገራውም ጊዜ የቅኔውን መንገድ በለዩና በጀማሪ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል ልዩነት አለ። ጀማሪ ተማሪዎች በቆጠራው ጊዜ ከሚገጥማቸው ችግር ያልተናነሰ በነገራውም ጊዜ ግራ ሲጋቡ መታየታቸው የተለመደ ነው። ቆጥሮ ያመጣውን ቅኔ በጉባኤው መካከል ቆሞ ለመንገር አፍሮ ሲሳቀቅና ሲሸማቀቅ፣ ጭንቀቱና ሰቀቀኑ በግንባሩ ላይ በጉልህ ይታያል። እንዲያውም አንዳንዱቹ ለግእዙ ቁዋንቁዋ እንግዳ በመሆናቸው በአስነጋሪው የታረመላቸውን ቅኔ ንባቡን እንኩዋ መያዝ ተስኑዋቸው አሳርመው ከሄዱ በሁዋላ እንደገና ተመልሰው አስነጋሪውን ደጋግመው ሲጠይቁና ሲያስቸግሩ ይስተዋላሉ። በዚህም ምክንያት፣ ጀማሪ ተማሪዎች የታረመላቸውን ቅኔ አንድ የለየ ተማሪ ዘሩን ይዞ እንዲያስቀጽላቸው የሚደረግበት ጊዜ የበዛ ነው።



ጀማሪው የቅኔ ተማሪ የቆጠረውን ቅኔ ለመምህሩ በመንገር ላይ ሳለ፤

በቅኔው ሙያ የበሰሉትና የሰለጠኑት ግን በቆጠራም ሆነ በነገራ ጊዜ የሚያስጨንቃቸውም ሆነ የሚያደናግራቸው ነገር የለም። ምስጢር የማግኘት፣ ሃሳብ የማመንጨትም ሆነ የቋንቋዋ ችግር አያሳስባቸውም። የፈለጉትን የቅኔ አይነት በፈለጉት ስልትና ዘዴ አዋቅረውና አደራጅተው ያቀርቡታል። የበለጠ ተሰሚነትና ተደናቂነትን ለማግኘት በማሰብ ህብር በሆነ ውብ ቃላትና ሀረጋት ቤቱንና ስንኙን ያዋቅራሉ። የቆጠሩትንም ቅኔ በሚነግሩበት ጊዜ መፍራት፣ ማፈርም ሆነ መሳቀቅ አይታይባቸውም። እንዲያውም የቅኔያቸውን ውበትና ብስለት አድማጮቻቸው ሰምተው እንዲያደንቁላቸው በመፈለግ ድምጻቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ የፋከራን ስሜት በሚያንጸባርቅ ሁኔታ የቆጠሩትን ቅኔ መንገር የተለመደ ባህሪያቸው ነው (ቪ.ካ.ቁ .2)።



*የቅኔው መንገድ የገባው ተማሪ የቆጠረውን ቅኔ በስሜት ለመምህሩ በሚነግርበት ወቅት*

የቅኔ ነጋሪው እውቀት የጠለቀ ሆኖ ለአስነጋሪነት ደረጃ የተቃረበ ከሆነና የነገራው ስነ ስርዓት የሚካሄደው በጉባኤው የበላይ መምህር ከሆነ፣ የነገራው አቀራረብም ሆነ ስልቱ ከሌሎች የተለየ ነው። ስነ ስርአቱ የሚካሄደው የጉባኤው አስቀጻዩች፣ አስነጋሪዎችና ዘራፊዎች በተገኙበት ስለሚሆን የቅኔ ነገራውን ባህሪ የተለየ ያደርገዋል። በነገራው ቦታ የተገኘት ሁሉ ስነ ስርአቱን በጥልቀት ነው የሚከታተሉት 'እጩ መምህርነት ይገባኛል!' የሚል አስተሳሰብ በውስጡ የያዘው ስልጡን ተማሪ የሚቆጥረው ቅኔ ከአንድ ሙሉ ቤት (ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ) በላይ ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሁለትም ሶስትም ሙሉ ቤት ቆጥሮ ሊነግር ይችላል። ነጋሪው የቆጠረውን ቅኔ ለመንገር ከመምህሩ ፊት በቀረበ ጊዜ ሀሳቡን አደላድሎ፣ በኩራት የቆጠረውን ቅኔ እንደሚነግር ሚስጢረ ሰዋስው፤ ከመሪጌታ ይሄይስ አገኘሁት ያሉትን ሃሳብ እንደሚከተለው አስፍረውታል።

> መምህሩ፣ ዘራፊዎችና ደቀመዛሙርቱ በተሰበሰቡበት ሃሳባቸው በኩራት ተሞልቶ፣ ልባቸውን ነፍተውና ደረታቸውን ገልብጠው ለነገራ ይቆማሉ። በተለይም በአነባበባቸው አድማጭ እስኪደነቅ ድረስ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግና ንባቡን በማውረድና በማውጣት ያሰቡትን ቅኔ ደረጃ በደረጃ እያከታተሉ እንደ መትረየስ ይተገትጉታል። በዚህም ጊዜ ሃሳባቸው ከመጋሉ የተነሳ ከፍ ያለ የመንፈስ ሙቀትና የፉከራ ስሜት በመላ ሰውነታቸው ላይ ይነበባል (ምስጢረ ሰዋስው፣ 1974፣ 40)።



የቅኔው መንገድ የገባው ተማሪ የቆጠረውን ቅኔ በስሜት ለመምህሩ በሚነግርበት ወቅት
ሌሎች ተማሪዎች በአንክሮ ሲከታተሉ

በጎጃም የግእዝ ቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ የሚስተዋለው ሌላው ጉዳይ ቅኔ በሚነገርበት ጊዜ የሚከናወነው ስነ ስርአት ነው። አንድ የቅኔ ተማሪ የቆጠረውን ቅኔ የሚነግረው ከአስነጋሪው ፊት ለፊት ከአስር ሜትር በማይበልጥ ርቀት ላይ በመቆም ሲሆን አስነጋሪው ግን ከፍ ባለ ቦታ ላይ ተቀምጦ ነው የማስነገሩን ስራ የሚመራው። ለአስነጋሪነት የተቃረቡት ተማሪዎችና አስቀጻዮች ብዙውን ጊዜ መንገር የሚፈልጉት ለጉባኤው መምህር ነው። በዚህም ምክንያት የቆጠሩትን ቅኔ ሳይነግሩ መምህሩን ለማግኘት ሲሞክሩ ይስተዋላሉ። መምህሩን ለማግኘት ሳይችሉ ብቻ ነው ወደ አስነጋሪዎች ሄደው የሚነግሩት።



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

አንድ ተማሪ እየቆጠረ ያለውን ቅኔ ደጋግሞ ከነገረና እውቀቱ በቂ ሆኖ ሲገኝ አንድ ቀን የቆጠረውን ቅኔ ነግሮ እንደጨረሰ አስነጋሪው ወይም መምህሩ የሚቀጥለውን ቅኔ ጨምሮ እንዲቆጥር ይገልጹለታል። በዚህ ጊዜ ተማሪው እጅ ይነሳና በማግስቱ ጉባኤ ቃና ሲነግር ከነበረ ዘ አምላኪየን ጨምሮ፣ ዘ አምላኪየ ሲነግር ከነበረ ሚ በዝሁን ጨምሮ፣ ሚ በዝሁ ሲነግር ከነበረ ዋዜማን ጨምሮ፣ ዋዜማ ሲነግር ከነበረ ስላሴን ጨምሮ፣ ስላሴ ሲነግር ከነበረ ዘ ይእዜን ጨምሮ፣ ዘ ይእዜን ሲነግር ከነበረ ደግሞ መወድስን ጨምሮ ቆጥሮ እንዲመጣ ይባላል። ተማሪው መወድስ ቅኔን መንገር ሲጀምር በጉባኤው ውስጥ 'ቤት ሞላ' ይበላል። ቤት ሞላ ማለት አንድ የቅኔ ተማሪ በአንድ የቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ ሁሉንም የቅኔ ዓይነቶች ለመቁጠርና ለመንገር በቃ (ቻለ) እንደማለት ነው። በሌላም በኩል ቅኔን በማህሌት ውስጥ ለመቀኘት ተቃረበ እንደማለትም ይቆጠራል።

አንድ ተማሪ በሚማርበት የቅኔ ጉባኤ ውስጥ ቤት መሙላቱ እንደተረጋገጠ መምህሩ ቅኔ እንዲቀኝ ይፈቅድለታል። የቅኔ ጉባኤው ያለበት ደብር ማህሌቱ ሰፊና ሊቃውንቱ የበዙ ከሆነ ወደ ገጠር ወጥቶ እንዲቀኝ ይደረጋል። ያ ካልሆነ ግን ጉባኤው ባለበት ደብር እንዲቀኝ ሊደረግ ይችላል።

### 4.2.4 ቅኔ ነጠቃና ግልበጣ

ቅኔ ነጠቃና ግልበጣ፣ በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በሰፊው የሚተገበር ሲሆን በተለይም ነጠቃ በማህሌት ቁመትና በክብረ በአላት አገልግሎት ሳይቀር የሚከሰት የግእዝ ቅኔ ሌላው ነጸብራቅ ነው። ነጠቃና ግልበጣ የሚባሉትን ጽንሰ ሃሳቦች በቀላሉ ለመገንዘብ ያህል፤ ነጠቃ ማለት፣«ቅኔ በመንገር ወይም በመዝረፍ ወይም በመቀኘት ላይ ያለው ባለቅኔ የሚያቀርበውን የቅኔ ምስጢር አስቀድሞ በመረዳት ትክክለኛውን ምስጢር የያዘውን ሃሳብ መንጠቅ ወይም ቀድሞ መናገር» የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የሚይዝ ሲሆን፣ መገልበጥ ማለት ደግሞ፣ «በቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህሩ ወይም ዘራፊው የዘረፈውን ቅኔ ቤቱን ወይም ምስጢሩን በመለወጥ በተቃራኒው ማቅረብ» የሚለውን ሃሳብ የሚይዝ ነው። ይህንን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ መላከ ጥበብ ስሜነህ የሚከተለውን ተናግረዋል።

> መንጠቅ ማለት፣ አንድ የቅኔ አዋቂ ቅኔን በሚዘርፍበት ወይም በሚቀኝበት ወይም በሚነግርበት ጊዜ የቅኔው ምስጢር የገባው ሌላው የቅኔ ሊቅ በይበልጥ የቅኔውን መንደርደሪያ መቀማት ወይም ቀድሞ መናገር ማለት ነው። መገልበጥ ማለት ደግሞ አንድ መምህር ወይም ዘራፊ ቅኔን በሚዘርፍበት ጊዜ የቅኔው ጥበብ የገባው እና ለዘራፊነት የቀረበ አንድ ደቀ መዝሙር፤ በዘራፊው የተዘረፈው ቅኔ ቤቱ በግዕዝ ተዘርፎ ከሆነ በሳድስ፣ በካዕብ ተዘርፎ ከሆነ በሳብዕ፣ በሳልስ ተዘርፎ ከሆነ በሀምስ፣ እንዲሁም በራብዕ ተዘርፎ ከሆነ በተፈቃቃሪው ገልብጦ መቀኘት ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መምህሩ የዘረፈው ቅኔ ሚስጢሩ በአምንታ ከሆነ በአሉታ፣ በአሉታ ከሆነ ደግሞ በአምንታ ገልብጦ ማቅረብ ማለትም ሊሆን ይችላል (መላከ ጥበብ ስሜነህ፣1999 ካ.ቁ.1)።

እንደተገለጸው የቅኔ ነጠቃ ተግባር በቅኔ ትምህርት ጉባኤዎች ውስጥ ቅኔ በሚዘረፍበትና በሚነገርበት ወቅት እንዲሁም በማህሌትና በክብረ በአላት ላይ ቅኔ በሚቀርብበት ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ተግባር ነው:: ግልበጣ ግን በቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ በቅኔ ዘረፋ ወቅት ብቻ የሚተገበር ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚቀርብ ቅኔ ላይ ግን ተፈጻሚ አይሆንም::

ብዙውን ጊዜ የግልበጣና የነጠቃ ተግባር የሚከናወነው በቅኔው ትምህርት በበሰሉና በተሰጥዖ በተደገፉ ተማሪዎችና የቅኔ ባለሙያዎች ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በችሎታቸው ከመተማመን በመነሳት በጀብደኝነትና በአዋቂነኝ ባይነት መንፈስ እርስ በርስ በፉክክር መልክ የሚፈጽሙት ተግባር ነው:: ሌላው ደግሞ፤ በቅኔው ሙያ የበሰሉ ደቀ መዛሙርት 'የቅኔው ምስጢር ገብቶናል፤ ለአስነጋሪነትም ሆነ ለዘራፊነት የበቃ ችሎታ አለንና እድሉ ይሰጠን' የሚል አስተሳሰባቸውን ለመምህሩ ለማሳወቅ ካለ ፍላጐት የሚመነጭ አስተሳሰብ ምልክት እንደሆነም ተገልጽዋል::



የቅኔ ጉባኤው ዘራፊ በመምህሩ የተዘረፈውን ቅኔ በመገልበጥ ላይ ሳለ፤

በቅኔ ነጠቃ ወቅት የቅኔው ምስጢርና ሃሳብ የገባው ነጣቂ በተከታታይ ሶስትና አራት ቤት ሊነጥቅ ይችላል:: የነጠቃ ችሎታው የሚገመገው ግን የነጠቀውን የቅኔ ንባብ ከነግጥሙ በማግኘቱ ወይም ባለማግኘቱ ብቻ አይደለም:: በዘራፊው ወይም ቅኔውን በተቀኘው ምሁር የተጣለውን የአስተሳሰብ መሰረት ሳይለቅ አስተካክሎ ሃሳቡን አግኝቶ በመናገሩ ላይ ነው

የነጣቂው ችሎታ የሚመዘነው:: በነጠቃ ጊዜ የባለቅኔውን ቅኔ ሃሳቡን ከነግጥሙ ቢያገኘውም ባያገኘውም ምስጢሩን እስካገኘ ድረስ የነጣቂውን የችሎታ ሚዛን አይቀንሰውም:: የባለቅኔውን ቀና ምስጢርና አቅጣጫ ስቶ በማይሆን መንገድ ለመንጠቅ ከሞከረ ለፍላፊና አላዋቂ ሊያሰኘው ይችላል (መምህር ለይኩን፡ 1999፡ካ.ቁ.3፤ ቪ. ካ .ቁ 1 እና 2)::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቅኔው ምስጢር የገባው ደቀ መዝሙር ብዙውን ጊዜ የነጠቃና የግልበጣ ተግባር ውስጥ የሚገባው 'ዘራፊነት ቢሰጠኝ ችሎታ አለኝ የሚለውን መልእክት ለጉባኤው መምህር ለማስተላለፍ ነው:: መምህሩም ድርጊቱ ለምን እየተፈጸመ እንደሆነ በቀላሉ ስለሚገባው ነጠቃና ግልበጣ የሚያዘወትረው ተማሪ የሚነጥቀውንም ሆነ የሚገለብጠውን ቅኔ በጥንቃቄ መመርመርና መገምገም ይጀምራል:: በግምገማው ሂደት ተግባሩ መልካም ሆኖ ተቀባይነት ካገኘ አስቀጻይ የነበረው ለእጨ ዘራፊነት፣ እጨ ዘራፊ የነበረው ደግሞ ለዘራፊነት ይታጫል:: በሂደትም ለዘራፊነት የታጨው ተማሪ በቅድሚያ ቅኔ እንዲያስነግር ከተደረገ በኋላ በሂደት ሙሉ የዘራፊነት ስልጣን ይሰጠዋል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዘራፊነት ደረጃ ቅኔን የማስነገርና የመዝረፍ ተራ ገብቶ የተማሪ አስተማሪነቱን ስራ ይወጣል::



የቅኔ መምህሩ የዘርፉትን ቅኔ ዘራፊው በገለበጠበት ወቅት ታዳሚ ተማሪዎች አድናቆታቸውን በፈገግታ ሲገልጹ፤

## 4.3 የቅኔ አቀራረብ ስርአት በማህሌትና በክብረ በአላት

### 4.3.1 የቅኔ አቀራረብ ጅማሬ በቤተ ክርስቲያን

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስርአተ አምልኮ ውስጥ ቅኔ የተወሰነ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት ከመንፈሳዊ አገልግሎቶች አንዱ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የአቀራረብ ደረጃዎች እንደነበሩት ይነገራል:: ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አድባራትና ገዳማት ይታወቁባቸው ከነበሩት አገልግሎቶች መካከል አንዱ የቅኔ አገልግሎት ስርአት እየሆነ መጣ:: የእያንዳንዱ ደብር ወይም ገዳም ክብረ በአል በተከበረ ቁጥር በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የገዳማትና አድባራት ቀሳውስት የክብረ በአሉ ተካፋይ እንደሚሆኑና በክብረ በአሉ ላይም የተለየ የአገልግሎት ድርሻ ይሰጣቸው እንደነበር ይገለጻል:: የቅኔውን አገልግሎት የተረከበው ደብር ወይም ገዳም ይከተለው የነበረ የቅኔ አቀራረብ ስርአት እንደነበር ገብረ ዮሀንስ ይገልጻሉ::

> ቅኔን በተመለከተ ልዩ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር:: ሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በየዓመቱ አይለዋወጡም፤ ቋሚ ናቸው:: ቅኔ ግን ሁልጊዜ አዲስ እየሆነ ነው የሚቀርበው:: በመሆኑም ልዩ ዝግጅት ይደረግበት ነበር:: .በየደብሩ፣ በየገዳሙ የሚገኙ መምህራን ተወያይተው ቅኔውን ያቀናብሩታል:: ያ በጉባዔ የተዘጋጀው ቅኔ ለተወካዮች ይሰጣል:: ተወካዮችም በተላኩበት ቦታ ስም የተሰጣቸውን ቅኔ ያበረክታሉ:: በዚህም ምክንያት ስም ተጠቅሶ 'እገሌ ይህንን ቅኔ ተቀኘ' አይባልም ነበር:: የገሌ ደብር ወይም ገዳም ካህናት የተቀኙት ቅኔ ተብሎ ይጠቀስ ነበር እንጅ (ገብረ ዮሀንስ 1993፣36)::

ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም እንደሚገልጹት ከሆነ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት፣ በተለይ የክብረ በአላት ቅኔዎች፣ በደብሩ ወይም በገዳሙ ካህናት በጋራ ይዘጋጁ የነበረ መሆኑን ነው የሚገልጹት:: ይህን መሰል የቅኔ አቀራረብም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየቀረ የመጣ መሆኑን ይገልጻሉ::ከጊዜ በኋላ በሊቃውንት ጉባኤ የተዘጋጀን ቅኔ ማቅረብ እየቀረ፤ በአንጻሩ በግለሰብ የተዘጋጀን ቅኔ ማቅረብ እየተጀመረ የመጣ መሆኑን ይጠቅሳሉ::

> ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የሊቃውንት ጉባዔ ያዘጋጀው ቅኔ በተወካይ ተልኮ በክብረ በዓላት በላኪው ስም መነገሩ የቀረው:: ቀስ በቀስ ሊቃውንት በአድባራትና በገዳማት ሥም ለአገልግሎት ወደ ሌላ ደብር ሲላኩ የራሳቸውን ደብር ወይም ገዳም ወክለው የግላቸውን ቅኔ መቀኘት ጀመሩ:: ቀስ በቀስም ቅኔን በጉባዔ አዘጋጅቶና አቀናብሮ መቀኘት እንደነውር መቆጠር ጀመረ (ገብረዮሐንስ 1997፣37)::

ከነተዋነይና ዮሀንስ ገብላዊ በኋላ ቅኔ በጉባኤ በጋራ እየተዘጋጀ ይቀርብ የነበረ መሆኑን፤ አቀራረቡም መንፈሳዊ ባህሪን ተላብሶ፣ በለሆሳስ እንደነበረ ገብረ ዮሀንስ ገብረ ማርያም ገልጸውታል:: በተለይ ለአገልግሎት ይቀርቡ የነበሩ ቅኔዎች በጋራ ይደረሱና ይዘጋጁ የነበሩ መሆኑን አምኖ ለመቀበል ተጨማሪ ጥናት የሚጠይቅ ይመስላል:: ሃሳቡ ተቀባይነት ያለው ቢመስልም ጥናት አቅራቢው የጥናት ስራውን ለማቀናበር ከተመለከታቸው መጸህፍትም ሆነ በቃል ከጠየቃቸው ምሁራን ይህን ሀሳብ የገለጸለት አላገኘም:: ይሁን እንጂ በተለይ የእምነት

ስርአት እጅግ ገኖ በነበረበት በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ከመን ለእግዚአብሄር ክብር ሲባል የተሻለ ነገር ማቅረብ እንደ ትልቅ ጸጋ ይቆጠር ስለነበር የተሻለ ቅኔ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ ሲባል በጋራ ቅኔን ማዘጋጀትና ማቀናበር የሚጠበቅ ተግባር ይመስላል።

### 4.3.2 የቅኔ አቀራረብ ህግና ስርአት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስርአት መሰረት እያንዳንዱ ቅኔ የሚቀርብበትና የሚዜምበት የየራሱ ህግና ስርአት አለው። በጎጃም ገዳማትና አድባራት ውስጥ ለአገልግሎት ተግባር ሲባል በቤተ ክርስቲያን የሚቀርብ ቅኔ ሁለጊዜ አዳዲስ ድርሰት ሆኖ፣ በአዳዲስ ምስጢር ላይ የሚቀናበር ነው። በተዋነይ ዘመን የተጀመረውን ቅኔ ከቅዱስ ያሬድ ቅኔዎች የሚለየው አንዱና ዋነኛው ነጥብ፤ የያሬድ ቅኔዎች እንደ ልጆች 'ቡሒ በሉ' በያመቱ የመጀመሪያው ራሱ እየተደገመ የሚቀርብ መሆኑና በተዋነይ ዘመን የተጀመረው ቅኔ ግን በየጊዜው አዳዲስ ምስጢርና ሃሳብ የያዘ፣ ጆሮ ያልነካው እንግዳ ድርስት የሚቀርብ መሆኑ ነው።

በኢትዮጵያ የቅኔ ጉባኤዎች ተወስነው የሚታወቁት ቅኔዎች ሁሉ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ጊዜ የሚቀርቡበት፣ በሊቃውንቱ የተደነገገ የየራሳቸው ህግና ስርአት አላቸው። የትኛው ቅኔ በየትኛው አገልግሎት ጊዜ ሊቀርብ እንደሚገባ በዚህ ጥናት ምእራፍ 3 «የቅኔ አይነቶች» በሚለው ርእስ ስር በዝርዝር ተመልክቷል።

### 4.3.3 የሚቀርብበት ጊዜና ወቅት

ቅኔ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወቅት የተወሰነ የአቀራረብ ስርአት እንዳለው ሁሉ የሚቀርብበት ጊዜና ወቅትም አለው። ቅኔን በማህሌት ወይም በክብረ በአላት ላይ እንዲቀኝ የተፈለገው ሰው ቅኔ መቀኘት እንዲችል የቅኔው አይነት ተለይቶ በደብሩ ወይም በገዳሙ መምህር ይሰጠዋል። ቅኔው የሚሰጠው ቅኔው ከሚቀርብበት እለት በፊት ወይም ቅኔው በሚቀርብበት እለት ከተወሰነ ሰአት በፊት ሊሆን ይችላል። አልፎ አልፎም ቅኔ እንዲቀኝ እድሉ ከተሰጠው ሰው ውጭ ያለ ባለቅኔ በራሱ ፍላጎት ተንደርድሮ ወደ ማህሌቱ በመግባት ቅኔውን የሚቀኝበት አጋጣሚም እንዳለ መሪጌታ ታንት ይገኝ ይገልጻሉ።

> ቅኔ ለባለቅኔ የሚታደልበትን ጊዜ አስመልክቶ የተደነገገ ህግና ስርአት የለም። የደብሩ መሪጌታ እንዲቀኝለት ለፈለገው የቅኔ ባለሙያ ከእለቱ አስቀድሞ ወይም በእለቱ /በተለይ ቅኔው ከጉባኤ ቃና እስከ ዘይእዜ ከሆነ/ ሊሰጥ ይችላል። የሚከለክለው ህግ የለም። በተለይ አንዳንዴ በክብረ በአላት ዋዜማ የሚቀርቡ ቅኔዎች አዳይም አያስፈልጋቸው። በዋዜማው የቁመት ስነስርአት የተገኘ፣ የቅኔው ምስጢር የነፋው የቅኔ ደቀ መዝሙር ያለተራው እየዘለለና እየፎከረ በመግባት ከተገቢው ቁጥር በላይ የቅኔውን ማዕበል ያወርደዋል (መሪጌታ ታንቲገኝ፡ 1999፡ ካ. ቁ. 5)

መሪጌታ ታንቲገኝ ሀሳባቸውን በማስረዘም፣ በተለይ በክብረ በአላት ዋዜማ ቁመት ጊዜ ቅኔ እንዲቀኝ እድሉ ያልተሰጠው፣ የቅኔው ምስጢር የነፋው፣ እታይ ባይ የቅኔ ተማሪ ካለ፣ ቅኔው የሚቀርብበት ጊዜ ሲደርስ የመጀመሪያውን ስንኝ እየተናገረ በፉከራ ወደ ጉባኤው

መካከል ይገባና ከሚፈቀደው በላይ የቅኔውን ዝናብ እንደሚያወርደው ይገልጻሉ፡፡ በማህሌቱ የተሰበሰበው ሊቃውንትም ያለተመሪ ጮህ ባለድምጽ እያከታተለ የሚያቀርበውን የቅኔ ምስጢርና ርቀት እየመረመረ አድናቆት ለሚገባው ይበል! ይበል! እያለ አድናቆቱን እንደሚገልጽለት፣ አልፎ አልፎም ሳይፈቀድለት ለመቀኘት እየዘለለ ወደጉባኤው የሚገባው የቅኔ ተማሪ ስለሚበዛ ስርአት ለማስያዝ እንደሚያስቸግርም መሪጌታ ታንቲገኝ ጨምረው ገልጸውታል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ቅኔን ያለተመሪና ያለተራ እየዘለሉ በመግባት መቀኘት ብዙ ግዜ የተለመደ አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ በተለይ ታላላቅ የቅኔ ጉባኤዎች ባሉበት አካባቢ በሚከበር ክብረ በአል ላይ የበለጠ የሚደጋገም ነው፡፡ ከዚህ በላይ ግን በደብሩ ወይም በገዳሙ መምህር እንዲቀኝ እድሉ የተሰጠው ባለቅኔ የቅኔው ማቅረቢያ ጊዜ ሲደርስ ወደ ጉባኤው መካከል ገብቶ ይቆማል፡፡ ብዙም ሳይቆይ በፍላጎት ወይም በግብዣ ባለቅኔው የሚናገረውን ቅኔ እየተቀበለ በዜማ የሚያዜመው የቅኔ ተመሪ ከባለቅኔው ፊት ይቆማል፡፡ በመቀጠልም እንደ ቅኔው አይነት፣ እንደዜማው መጠንና ልክ ባለቅኔው የሚናገረውን ቅኔ እየተቀበለ ተመሪው በተከታታይ ያዜመውና የቅኔው ነጋራ ሲያበቃ ሁለቱም /መሪና ተመሪ/ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ይመለሳሉ፡፡ የተለመደውና ተገቢው የቤተ ክርስቲያን የቅኔ አቀራረብ ስርአትም ይህ ነው (ቪ..ካ.ቁ.2)፡፡



እጣነ ሞገር ቅኔ በቅኔ ማህሌት በሚቀርብበት ጊዜ፡

እጣነ ሞገር ቅኔ ከሌሎች ቅኔዎች የተለየ የአቀራረብ ስርአት አለው:: ቅኔውን እንዲቀኝ የተፈለገው ሰው ተዘጋጅቶ እንዲመጣ እድሉ የሚሰጠው ቅኔው ከሚቀርብበት እለት ቀደም ብሎ ነው:: ብዙውን ጊዜ ቅኔውን እንዲቀኝ እዱሉ የሚሰጠው ቅኔን ተምሮ በቅርቡ ወደ ደብሩ የመጣ የቅኔ ተማሪ ካለ ወይም ለደብሩ እንግዳ ባለ ቅኔ ወደ ደብሩ ከመጣ ቅድሚያ እንደሚሰጥና አቀራረቡ ከሌሎች የቅኔ አቀራረቦች የተለየ እደሆነ የሚገልጹት ደግሞ ደብተራ ብረሃን ናቸው::

> እጣነ ሞገር ቅኔ የሚቀርበው እሁድ እሁድ ብቻ ነው:: ቅኔውን እንዲቀኝ የተነገረው ባለ ቅኔ ክብር ይእቲን ጨምሮ አዘጋጅቶና ቆጥሮ መቅረብ የተለመደ ነው:: ክብር ይእቲ ቅኔ የሚዜመው በቅኔ አቅራቢው በራሱ ነው:: ተመሪ አያስፈልገውም:: የሚቀርበውም እርገት ከመውረዱ አስቀድሞ በተመስጦና በለሆሳስ ነው:: እንደ ሌሎች ቅኔዎች ጨኸትና ፉከራ አያስፈልገውም:: ... እጣነሞገር የሚቀርበው ደግሞ ከቅዳሴ በኋላ ነው:: አቀራረቡም ባለቅኔው ከማህሌት መካከል ገብቶ በመቆም ከፊትለፊቱ ለቆመው ተመሪ ቅኔውን በዜማ እንዲጮኸው እያከታተለ ይነገረዋል:: ተመሪውም የቅኔውን ዜማ ባማረ ድምጽ ያስረቀርቀዋል (ደብተራ ብርሃን 1999 ካ. ቁ 5)::

እጣነ ሞገር ቅኔ ቀርቦ የእለቱ የአገልግሎት ስርአት ከተጠናቀቀ በኃላ የሚስተዋል ሌላ የቅኔ ባህል አለ:: በተለይ እጣነ ሞገር ቅኔው የቀረበው የቅኔ ተማሪዎች በተገኙበትና አቅራቢያውም የቅኔ ተማሪ ከሆነ በቅኔ አቅራቢውና በቅኔ ተማሪዎች መካከል የሚፈጠረውን ግብግብ አስመልክቶ፤ ምስጢረ ሰዋስው ከመምህር ኢዮስያስ ያገኘውን ሀሳብ እንደሚከተለው አስፍሮታል::

> ቅኔ የተቀኘው ተማሪ እጣነ ሞገር ተቁሞና አልቆ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ በቅኔ ቤት ደንብ መሰረት የተቀኘውን ቅኔ ለተማሪዎች ለመፍታት ይገደዳል:: ስለዚህም ተቀኝው ተማሪ ተማሪዎች ከበውት ከመካከል ይቀመጣል:: ከተማሪዎች መካከል አንዱ ተማሪ ተነስቶ ቅኔውን ያነባል፤ ተቀኝው ይፈታል:: ክርክሩ በዚህ ጊዜ ይቀጥላል:: ተማሪዎቹ ተቀኝውን ተማሪ በጥያቄ አፋጠው ይይዙታል:: በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ ተማሪዎች ቅኔውን ከተቀኙ በሁዋላ ጥያቄውን ፈርተው ተደብቀው ከማህሌት ሾልከውና ወደ ቤተልሔም የሔዱ መስለው በካቡ ላይ ዘለው ይጠፋሉ (ሚስጢረ ሰዋሰው 1974:43)::

ከላይ እንደተገለጸው ቅኔውን ያቀረበው ተማሪ ለጊዜው ጠፍቶ ቢያመልጥም ተማሪዎቹ ማታውኑ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ካለበት ቦታ ድረስ በመሄድ አስጨንቀው የተቀኘውን ቅኔ እንዲፈታው ማድረጋቸው የተለመደ ነው::

# ማጠቃለያ

ምንም እንኩዋን የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የተመረጡ የጎጃም ቅኔ ጉባኤዎችን መነሻ በማድረግ በክፍለ ሀገሩ ስለሚከናወኑ የግእዝ ቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋ፣ ነጠቃ፣ ግልበጣና የአፈጻጸም ስርአታቸውን መዳሰስ ቢሆንም ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ ስለ ግእዝ ቅኔ ምንነት፣ መነሻ መሰረቱና አጀማመሩ፣ የተገዋዘበት መንገድና አይነቶቹ እንዲሁም ከሙያው ጋር ቁርኝት ያላቸው ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቱዋቸው እንዲታዩ ተደርጉዋል።

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸው ውጤቶች መነሻ መሰረቶች ስለጉዳዩ የተጻፉ የጽሁፍ ውጤቶችና ከሙያው ምሁራን የተገኙ ሀሳቦች ናቸው። ጥናት አቅራቢው በመስኩ የነበረው ሰፊ ልምድም ለግኝቱ ትልቅ ቦታ ነበረው። በዚህ ጥናት ማጠቃለያ ትኩረት ተሰጥቱዋቸው እንዲታዩ የተደረጉት ነጥቦች የጥናት አቅራቢውን ትኩረት የበለጠ ሊስቡ የቻሉት ብቻ ናቸው።

ትኩረት ከሳቡት ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው የግእዝ ቅኔ ጀማሪ /ደራሲ/ ማንነትንና የተጀመረበትን ጊዜ በተመለከተ የተነሱት ነጥቦች ናቸው። ይህን ነጥብ አስመልክቶ አራት የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዳሉ በጥናቱ ተመልክቱዋል። የቅኔ መነሻ የኦሪት ዘመን ሰዎች ፈጣሪያቸውን ለማመስገን ሲሉ ይገጥሙዋቸው የነበሩ የመዝሙር ግጥሞችን ከዳዊት የምስጋና መዝሙሮች ጋር እያጣቀሱ የቅኔ መነሻ የዳዊት መዝሙር ስለ መሆኑ የሚገለጸው የመጀመሪያው አስተሳሰብ ነው። ሁለተኛው አስተሳሰብ በዘመነ ኦሪት ማብቂያ በአዲስ ኪዳን መግቢያ አካባቢ አገው እየተባለ በሚጠራው የኢትዮጵያ ክፍል «ዘሲቱኤል» በተባለ ሰው የተደረሰ ስለመሆኑ የሚገለጸው ሀሳብ ነው። ድጉዋ በተባለው መጽሀፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ግጥም መሰል አረፍተ ነገሮችና የግጥም ስንኞች እየተጠቀሱ የግእዝ ቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ የሚነሳው አስተሳሰብ ደግሞ ሶስተኛው አስተሳሰብ ነው። ትክክለኛው የግእዝ ቅኔ የተጀመረው ከቅዱስ ያሬድ በኋላ ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን በተነሱ የሙያው ሊቃውንት ስለመሆኑ የሚነሳው አስተሳሰብ ደግሞ የመጨረሻው አስተሳሰብ ነው።

ይህ አስተሳሰብ በራሱ በሁለት የተለያዩ አመለካከቶች የተከፋፈለ ነው። አንደኛው በዋድላ የቅኔ ጉባኤ ተከታዮች ዘንድ የሚጠቀሰውና የግእዝ ቅኔ ደራሲ ዮሀንስ ገብላዊ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ድድቅ ወልደማርያም ስለመሆኑ የሚቀነቀነው አስተሳሰብ ነው። ሁለተኛ አስተሳሰብ ደግሞ በጎንጅ የቅኔ ጉባኤ ተከታዮች ዘንድ የሚነገረው አስተሳሰብ ነው። ጎንጅዎች ትክክለኛው የግእዝ ቅኔ ደራሲ የጎንጅ የቅኔ ጉባኤ መስራች ተዋነይ የተሰኘው ሊቅ እንደሆነ በድፍረት ይገልጻሉ። ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ተዋነይ የተባለውን የቅኔ ሊቅ ደቀ እስጢፋ የሚል ስያሜ በመስጠት ቅኔን ደቀ እስጢፋ የደረሰው ስለመሆኑ ገልጸዋል።

በጥናት አቅራቢው እምነት የግእዝ ቅኔን ጀማሪ ማንነትና ጊዜውን ለይቶና ወስኖ ለመግለጽ በቅድሚያ ሊያግባባ የሚችል የግእዝ ቅኔን ትርጉም ወስኖ ማስቀመጡ ተገቢ

እንደሆነ ያምናል። አንድን የግእዝ ቅኔ ቅኔ ሊያስኙት የሚችሉት ባህርያትና ገጽታዎች ተለይተውና ተወስነው ካልተቀመጡ ትክክለኛው የግእዝ ቅኔ መቸና በማን እንደተጀመረ ለይቶ ለመግለጽ ያስቸግራል። የዚህ ጥናት አቅራቢ፣ የግእዝ ቅኔ ትርጉም ሊሆን ይገባል ብሎ ያመነበትን ትርጉም በማስቀመጥና በትርጉሙ ውስጥ የተካተቱ ባህርያትን የሚያሙዋሉ ቅኔዎችንና በዚያ ወቅት የነበሩ የሙያው ሊቃውንትን ማንነት በመመርመር የራሱን የመቁዋጫ ሀሳብ አስቀምጡዋል።

የግእዝ ቅኔ ማለት አቀራረቡ በግጥም የሆነ፣ የተለያዩ ቅርጽ እና መጠን ባላቸው ቃላትና ሀረጋት በተገነቡ ቤቶች የተከፋፈለ፣ በሰምና በወርቅ የተመሰጠረ፣ የራሱ የሆነ የዜማ ስርአትና ልክ ያለው፣ ወቅት ወይም እለትን መሰረት ባደረገ ታሪክ የሚቀናበር፣ ቃላትና ሀረጋትን የሚያስተሳስር ምሳሌና ሙያ ያለው፣ መንፈሳዊውንም ሆነ አለማዊ ህይወትን መነሻ እያደረገ ለስርአተ አምልኮ፣ ለምስጋና፣ ለውደሳና ለነቀፌታ ተግባር የሚውል፣ ራሱን የቻለ የአደረጃጀት፣ የአዘገጃጀትና ያቀራረብ ደንብ፣ ስርአትና ህግ ያለው ጥንታዊ የሀገራችን የፍልስፍናና የስነ ጽሁፍ ትምህርት ዘርፍ ነው።

ከላይ በተጠቀሰው ትርጉም ውስጥ የሚስተዋሉ ባህርያት፣ ተግባራትና ገጽታዎችን የሚያሙዋላ ቅኔ በሰፊው እየተለመደ የመጣው ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ መሆኑን ከዚያ ዘመን በፊትና በኋላ የተደረሱ ቅኔዎችን ከተቀመጠው ትርጉም አኩዋያ በመመርመር ማረጋገጥ እንደሚቻል የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ነው።

በዚህ የጥናት ስራ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ሌላው ነጥብ፣ ቅኔ ከሌሎች ስድስት የተለያዩ ጥበባት ጋር ደቀ እስጢፋ በተባለ ጥበበኛ ከጽርእ /ግሪክ/ ስለመምጣቱ፣ ደቀ እስጢፋ እየተባለ የሚጠራው ሰው የተዋነይ ሌለኛው መጠሪያ ስም ስለመሆኑና ተደጋግሞ ስለሚጠቀሰው የጥንቆላና የምትሀት ጥበብ አስመልክቶ የሚነሳው አስተሳሰብ ነው።

ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የሙያ ሊቃውንት በጻፉዋቸው መጻህፍትና በአንደበታቸው አያሌ አስተያየቶችን አስፍረዋል። ደቀ እስጢፋ የተባለ ጠቢብ ወደ ጽርእ ወርዶ ሰባት አይነት ጥበባትን ተምሮ የተመለሰ ስለመሆኑ፣ ከሰባቱ ጥበባት መካከል አንደኛው ቅኔ ስለመሆኑና ቅኔ ደገኛ ትምህርት ሆኖ በመገኘቱ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ እንዲሆን ሲደረግ ሌሎች ግን የጥንቆላና የምትሀት ተግባራት በመሆናቸውና ተቀባይነት ባለማግኘታቸው በድብቅ ሲሰራባቸው የኖረ ስለመሆኑ ተጠቅሱዋል። በሌላም በኩል ደግሞ ይኸው ደቀ እስጢፋ የተባለው የጥበብ ሰው እስክንድር ከተባለ ንጉስ ጋር ቤተኛ ሆኖ በመኖር ላይ ሳለ የንጉሱን ሚስት በተማረው ጥበብ በምትሀት ሰውሮ ጣና ውስጥ ደቀ እስጢፋ በተባለ ቦታ ተሰውሮ የቆየ ስለመሆኑም ተገልጹዋል።

ተዋነይ የተባለው የቅኔ ሊቅ በበኩሉ በአጼ በካፋ ዘመነ መንግስት በምትሀት እየተሰወረ ወደ ንጉሱ ማእድ በመቅረብ አብሮ እየተመገበ ለብዙ ጊዜ ካሳለፈ በኋላ የንጉሱ ባለሙዋል የሆኑ ሊቃውንት የተዋነይን ተግባር በምትሀት ስለደረሱበት እጸ መክስት ተጠቅመው ንጉሱ ማእድ ቀርቦ በመመገብ ላይ ሳለ የያዙት ስለመሆኑ፣ ተዋነይም አምልጦ ጣና ደሴት ደቀ

እስጢፋ በተባለ ቦታ በመኖር ላይ ሳለ በጥበቡ ምክንያት ግማሽ አካሉ በድን ሆኖ በመቆየቱ በንስሀ መልክ ለፈጣሪው ያቀረበው ቅኔ በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሱዋል፡፡

በሌላ በኩል አወደ ነገስት የተባለው የጥንቆላ መጽሀፍ መገኛ መሰረቱ /ቦታው/ ከላይ የተጠቀሰው ደቀ እስጢፋ የተባለው ደብር እንደሆነ በዚሁ መጽሀፍ መግቢያ ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኝ መሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ተመልክቱዋል፡

ደቀ እስጢፋ የተባለው የጥበብና የፍልስፍና ባለሙያ ጽርእ /ግሪክ/ ሄዶ ቅኔንና ሌሎች የጥንቆላና የምትሀት ትምህርቶችን ተምሮ የተመለሰና በደሴት ጣና ደቀ እስጢፋ በተባለ ቦታ የኖረ መሆኑ ከተገለጸ፣ ይኸው የጥበብ ሰው በምትሀት በመሰወር የንጉሱን ሚስት አስኮብልሎ ጣና ውስጥ ደቀ እስጢፋ የገባ መሆኑ ከተጠቀሰ፣ ተዋነይ የተባለው የቅኔ ሊቅ ደግሞ በግራኝ ሙሀመድ ወረራ ምክንያት ከሚማርበት ትምህርት ቤት ወደ ጣና ደሴት ደቀ እስጢፋ በመሰደድ በዚያው ቅኔን እያራቀቀ የቆየ መሆኑ ከተገለጸ፤ ተዋነይም እንደደቀ እስጢፋ ሁሉ የመሰወር ጥበብ ባለቤት መሆኑ ከታወቀ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደቀ እስጢፋ የተባለው የጥበብ ሰው የተዋነይ ሌላው ስያሜ መሆኑን የሚጠቅሱ ምሁራን ካሉ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሙያው ሊቃውንት ዘንድ የጥንቆላና የምትሀት መጽሀፍ እንደሆነ የሚጠቀሰው አውደ ነገስት መገኛው ጣና ደሴት ደቀ እስጢፋ መሆኑ ከታወቀ፣ ከግእዝ ቅኔ ባሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ በአፈ ታሪክነትና በተረትነት ሲዘከር የኖረውና አሁንም ያለው የጥንቆላ፣ የምትሀት፤ የመሰወር፣ በደመና የመጫን፣ በነፋስ ሰረገላ የመክነፍና የሌሎች ምስጢራዊ ጥበባት መነሻ ምንጩ /ቦታው/ በጣና ደሴት ውስጥ የሚገኘው ደቀ እስጢፋና አካባቢው፤ የሙያው ባለቤት ደግሞ ደቀ እስጢፋ ወይም ተዋነይ የተሰኘው ሊቅ ይሆኑ ይሆን? የሚለው አስተሳሰብ የዚህ ጥናት አቅራቢን ህሊና የሳበ አቢይ ጉዳይ ሆኖ ከማለፉ ባሻገር ጉዳዩ ትልቅ የምርምርና የጥናት መስክ ሊሆን እንደሚችልም አመላክቱዋል፡፡

ቀድሞ እንደተጠቀሰው ይህ ጥናት ማእከል የሚያደርገው በተለያዩ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎችና ማህሌቶች የሚቀርበውን የግእዝ ቅኔ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ውስጥ በክፍለ ሀገሩ ቀድሞ ስለነበረው፣ አሁን ስላለውና ወደፊት ሊያጋጥም ስለሚችለው ክስተት የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን በማንሳት ጥናትና ምርምር ተድርጎዋል፡፡ በተደረገውም ጥናት የሚከተሉት ነጥቦች ተስተውለዋል፡፡

1. ከወትሮ ጀምሮ በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች፣ በክብረ በአላትና በቅኔ ማህሌት የሚስተዋሉ የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋ፣ ነጠቃና ግልበጣ በአሁኑም ዘመን በተለያየ ደረጃ የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በ1966 ዓ.ም ከተካሄደው የስርአት ለውጥ በኋላ ተግባሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና እየደበዘዘ መጥቱዋል፡፡ በተለይ የቅኔ ነጠቃና ግልበጣ ስርአት፤ እንዲሁም ቅኔን በእልህና በፉከራ መልክ የመቀኘቱ ባህል ቸል እየተባለ የመጣ መሆኑ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡
2. የቅኔ ተማሪዎችን አለባበስና ቁሳቁስ አጠቃቀም በተመለከተ የነበረው ባህል ግን ሙሉ በሙሉ ተለውጡዋል፡፡ ወትሮ የጎጃም የቅኔ ተማሪ መለያ ልብስ የነበረውና ከበግ ቆዳ



IES LIBRARY

የሚዘጋጀው ደበሎ /ለምድ/ በአሁኑ ጊዜ ከሱፍ ክር በሚሰራ ነጠላ /ጎጃም እዘን/ ተለውጠዋል። ለምግብ መያዣ ይውል የነበረው ከሰሌን ወይም ከቄጠማ የሚሰራው አኮፋዳ ዘመኑ ባመጣው የማዳበሪያ ቀረጢትና ከፕላስቲክ በሚሰራ ፌስታል ተለውጠዋል። ለውሀ መቅጃ ይውል የነበረው ቅምጫና /እንገታም ቅል/ ወቅቱ ባፈራው የውሀ መያዣ ፕላስቲክ ተተክቷል። በአጠቃላይ የወትሮው የቅኔ ተማሪ አለባበስና ቁሳቁስ አጠቃቀም ሙሉ በሙሉ የተለወጠ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

3. ምግብ አሰባሰብና የአመጋገብ ስርአቱን አስመልክቶ የተስተዋለው ልዩነት ውስን ነው። የቅኔ ተማሪው ለምግብ ፍለጋ በሚሰማራበት ጊዜ በማህበረሰቡ ዘንድ የነበረው ክብርና ሞገስም ቀንሷል። ወትሮ በተለይ እንደ ዋሸራና ጎንጅ ባሉት የቅኔ ጉባኤዎች አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ተማሪዎችን በየመንደሩ በመከፋፈል ክረምቱን ሙሉ ይመግባቸው የነበረ መሆኑ በተለያዩ መጻህፍት የተጠቀሰ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እንዲህ አይነቱ ባህልና ልምድ አይስተዋልም። ከዚህ ባሻገር የምግብ ልመና ስርአቱ፣ የአመጋገብ ባህሉም ሆነ የእንግዳ ተማሪ አቀባበልና የመስተንግዶ ስርአቱ ከወትሮው የጎላ ልዩነት ያልተስተዋለበት መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል።

4. የሆሳእና አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምም ሆነ የአወሳሰድ ስርአቱ ከወትሮው የጎላ ልዩነት ባይኖረውም ሆሳእናን ወስዶ የቅኔ ሊቅ የመሆን ፍላጐት የወትሮቹን የቅኔ ተማሪዎች ያህል በአሁኑ ጊዜ የጎላ አይደለም። ሆሳእናን ወስዶ ሊቅ በመሆን ከሚገኘው ጥቅም ይልቅ በሆሳእናው ምክንያት ሊፈጠር ይችላል ተብሎ የሚታሰበው የመንቀዥቀዥና የማበድ ሁኔታ በጉባኤዎች ውስጥ ጎላ ብሎ የሚወራ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በተማሪዎች ዘንድ ሆሳእናን ወስዶ ሊቅ የመሆን ፍላጐት እየደበዘዘና እየተረሳ በመሄድ ላይ መሆኑ በጥናቱ ተስተውሏል።

5. በወትሮዎቹና በአሁኖቹ የጎጃም የቅኔ ተማሪዎች መካከል ጉልቶ የሚስተዋለው ሌላው ልዩነት፣ ከቁም ጽሁፍ ጋር በተያያዘ የሚስተዋለው ልዩነት ነው። የወትሮው የቅኔ ተማሪ ብራና ፍቆ፣ ቀለም ቀምሞና ብእር ቀርጾ የሚማርበትን ግስ በቁም ጹሁፍ ማጻፍ የተለመደ ተግባሩ ነበር። በአሁኑ ጊዜ የቅኔ ማስተማሪያ መጻህፍትም ሆኑ ሌሎች መንፈሳዊ መጻህፍት በዘመናዊ ማተሚያ ማሽን ተዘጋጅተው በቀላሉ የሚገኙ በመሆናቸው የሀገራችን ታላቅ ባህልና ቅርስ የነበረው መጻህፍትን በእጅ የቁም ጽሁፍ የመጻፍና የመደጐስ /መጠረዝ/ ጥበብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመረሳት ላይ መሆኑ በጥናቱ ተስተውሏል።

6. በወትሮው የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎችና መምህራን ዘንድ ዘመናዊ /አስኩዋላ/ ትምህርትን መማር እንደ ሀጢያት ስራ ይቆጠር ነበር። በአሁኑ ዘመን ይህ አስተሳሰብ ተለውጦ በከተማ አካባቢ ባሉ የቅኔ ጉባኤዎች የሚማሩ የቅኔ

ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ደብተር ይዘው ወደ መንግስት ትምህርት ቤቶች በመሄድ የሚማሩ ብዙዎች እንደሆኑ በዚህ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል።

7. በዘመኑ የጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ጉልቶ የሚስተዋለው ሌላው ጉዳይ፣ የቅኔ ጉባኤዎቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ፣ የተተኪና የተከታይ ደቀመዛሙርት ቁጥር እየቀነሰና ታዋቂ የነበሩ ጉባኤዎችም እየተዘጉ የመሆናቸው ጉዳይ ነው። በክፍለ ሀገሩ ከጥንት ጀምሮ በታላቅ የቅኔ ጉባኤነቱ የሚታወቀው የደንበጫ ሚካኤል የቅኔ ጉባኤ በአሁኑ ጊዜ ተዘግቷዋል። አልፎ አልፎ ያሉት ጉባኤዎችም ቢሆን ወትሮ በመቶ በሚቆጠሩ ጎጆዎች አያሌ ተማሪዎችን ሲያስተናግዱ እንዳልነበር ዛሬ የደቀ መዛሙርቱ ቁጥር እጅግ ቀንሷዋል፣ የጉባኤዎችም ሙቀትና ድምቀት ተቀዛቅዟዋል። በቤተ ክህነትም ይሁን በቤተ መንግስት በኩል ትኩረት የተሰጣቸው አይመስልም። በዚህም ምክንያት መምህራኑም ሆኑ ተከታዮቻቸው ከመንፈሳዊ ህይወት ባሻገር የእለትን ጉርስ እንኳዋን ለማግኘት የሚያስችል ስጋዊ ተስፋ በማጣታቸው በሙያቸው ተስፋ የመቁረጥ ባህሪ እየተስተዋለባቸው መሆኑ በጥናት ስራው ወቅት የተስተዋለው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

ምን ቢደረግ ይሻላል? ጥናት አቅራቢው ለጥናቱ መደምደሚያ ያነሳው ጥያቄ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በጥናት ስራው የተደረሰባቸው መደምደሚያች ናቸው። የተጠቀሱትን ነጥቦች ለመቋዋጨት ከጥናቱ ግኝቶች የሚነሱ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆሙ ተገቢ ነው። ከዚህ አኩዋያ የሚመለከታቸውን መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን፣ የቋዋንቋዋና የታሪክ እንዲሁም የተለያዩ ተቆርቋዋሪ ባለሀብቶችንና ምሁራንን ሀሊና መኮርኮር ከተቻለ በሚል የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

1. በክፍለ ሀገር ከሚገኙ ታዋቂና ጥንታዊ የቅኔ ጉባኤዎች መካከል የተወሰኑትን በመምረጥ፣ የተለየ ድጋፍና የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን ስርአት በመፍጠር፣ ይዘውት የኖሩትን የመማር ማስተማር ስርአት ጠብቀው እንዲቆዩ ጥበባዊ ቅርሱና ባህሉም ሳይከለስና ሳይበረዝ ለትውልድ የሚተላለፍበት እድል እንዲኖር ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ሌሎች በጐ አድራጊ ድርጅቶችና ግለሰቦች ትኩረት ሰጥተውት እየተዳከመ ያለው ጥንታዊው የሀገራችን ባህል ተጠብቆ የሚኖርበት እድል ቢመቻች።

2. ከጥንታዊውና አሁን ካለው የግእዝ ቅኔ ባህልና ልማድ ጋር የተቆራኙ ቅርሶችን /አልባሳት፣ ቁሳቁስና የአተገባበር ስርአቱን/ አሰባስቦ በቅርስነት ጠብቆና ተንከባክቦ በማቆየት ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፍ የግእዝ ቅኔ ባህልና ቅርስ ጥበቃ ማእከል ቢቋዋቋዋም። የሚመለከታቸው ወገኖችም ለዚህ ተግባር ተገቢ ድጋፍ ቢያደርጉ፣

3. ቅርሱና ቁዋንቁዋው እንዳይጠፋ የሚቆረቆሩና ሀብቱና እውቀቱ ያላቸው ወገኖች ስርአተ ትምህርት አስቀርጸው የማስተማሪያ መጻህፍት አዘጋጅተው ፤ የትምህርት ሚኒስቴርን የማስተማር ፈቃድ ወስደውና መምህራንን ቀጥረው የግእዝን ቅኔና መቀኛ ቁዋንቁዋውን፣ የድጉስና የቁም ጽሁፍ ጥበቡን መማር ለሚፈልጉ ሁሉ በዘመናዊ መልክ ማስተማር የሚቻልበት ሁኔታ ቢመቻች፤

4. ከሚመለከታቸው አካላትና ግለሰቦች ጋር በመተባበር ተከታታይ የግእዝ ቅኔ ማቅረቢያ ምሽቶችንና መድረኮችን በማዘጋጀት የሙያው ባለቤቶች ሙያቸውንና ችሎታቸውን ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ ዜጎች የሚያሳዩበትን እድል በማመቻቸት ጥበባዊ ቅርሱ የበለጠ እንዲታወቅ፣ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍና ከታዳሚው የሚገኘው ገቢም ለታዋቂ የቅኔ ጉባኤዎች ማደራጃና ማጠናከሪያ የሚሆንበት እድል ቢፈጠር

5. የግእዝ ቅኔ በመማርና በማስተማር እድሜያቸውን ለገፉ፣ ጥበባዊ ቅርሱ ከነባሉ እስካሁን ድረስ ተጠብቆ እንዲቆይ የላቀ ተጋድሎ ላደረጉና በሙያው ክብርና እውቅና ላገኙ የሙያው ሊቃውንት መታሰቢያና መወደሻ የሚሆን መድረክና ቀጣይነት ያለው የመታሰቢያ ስርአት የሚፈጠርበት እድል ቢኖር፤ እየተዳከመና እየሞተ ያለውን የሀገራችንን ብቸኛ የግእዝ ቅኔ፣ ቁዋንቁዋና ባህሉን ጠብቆ ለማቆየት የመፍትሄው መነሻ ሀሳብ እንደሆን የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ነው።

# አስረጂዎች /References/


ሁብተማርያም ወርቅነህ፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፣ አ.አ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት (ብ.ሰ.ማ.ቤት)፣ 1963

ሀይለ ገብርኤል ዳኘ፣ የኢትዮጵያ የትምህርት ፍልስፍና፣ አ.አ፣ 1961

ሀሩይ ወልደ ስላሴ፡- መጽሀፈ ቅኔ፣ አ.አ፣ ብ.ሰ.ማ. ቤት፣ 1918፡፡

ምስጢረ ሰዋስው፣ "ጥንታዊ የግእዝ ቋዋንቋዋ ትምህርት አሰጣጥ" አ.አ.ዩ፣ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1974፡፡

በላይነህ ደሴ ፣ "የቅዱስ ያሬድ ስራዎችና ድራማዊ ባህሪያቸው" አ.አ.ዩ የትያትርና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1987 ፡፡

ታደለ ጉድሴ ፣ ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋታ ለትዝታ፣ አ.አ፣ ጉተንበርግ ማተሚያ ቤት፣ 1997፡፡

አለሙ ሀይሌ ፣ "የግእዝ ቋዋንቋዋ ትምህርት አሰጣጥ በቅኔ ቤትና በኮሌጅ ደረጃ"፣ አ.አ.ዩ፣ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1975

አለማየሁ ሞገስ፣ ሰዋስዎ ግእዝ ተሰነአወ፣ አ.አ.፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት፣ 1950፡፡

____________ ፣ የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማርያ፣ አ.አ፣ ብ.ሰ.ማ. ቤት፣ 1954

____________ ፣ የግእዝ ቅኔ ዜማ፣ አ.አ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት፣1967፡፡

አምሳሉ አክሊሉ "አጭር የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ታሪክ" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ በእስቴንሲል የተባዛ 1976፡፡

አሸናፊ ደምሴ "የቅኔና የስነ ግጥም አንድነትና ልዩነት" አ.አ.ዩ፣ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1982፡፡

አበበ ከበደ፣ "የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሸራ ውስጠዘ የግእዝ ቅኔና ቅኔው ከሌሎች ቅኔዎች የሚለይባቸው ባህርያት"፣ አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1993፡፡

አበባው ይግዛው፣ "ቅኔን ቅኔ የሚያሰኘው ይበልታው ነው"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሚያዝያ 25 ቀን 1977፣ ገጽ 3 እባ 8፡፡

አባጉር፣ "የቅኔ ሚዛኑ ምስጢሩ"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ መጋቢት 20 ቀን 1977፣ ገጽ 3 እና 7፡፡

አድማሱ ጀንበሬ፣ መጽሀፈ ቅኔ፣ አ.አ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1963፡፡

አፈሊቅ አክሊሉ፣ "ቅኔ ግጥም ነውን?"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ግንቦት 23 ቀን 1977፣ ገጽ 3 እና 7 ፡፡

አፈወርቅ ተክሌ ፣ መጽሀፍ ታሪክ ወግስ፣ አ.አ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1997 ፡፡

አፈወርቅ ዘውዴ፣ ሀገረ መጻህፍት ሰዋስው ግእዝ ወአማርኛ፣ አ.አ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ፡፡

ኢሳያስ አለሜ እንግዳ፣ "ቅኔን ቅኔ ያሰኘው ሚዛኑ ጭምር ነው"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ መጋቢት 13 ቀን 1977፣ ገጽ 3

ኤልያስ ነብየልኡልና ከፍያለው መራሄ፣ ትርጉዋሜ ቅኔ ፈለገ ህይወት፣ አ.አ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ::

ከፍያለው መራሄ፣ የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ፣ አ.አ፣ ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻ ድርጅት፣ 1986 ::

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሀፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሀዲስ፣ አ.አ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948::

ዜና ማርቆስ እንዳለው፣ ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር አንድ፣ አ.አ፣ ሆራይዘን ማተሚያ ቤት፣ 1994 ::

___________ ፣ ግእዝ ቁዋንቁዋ ለአራተኛ ክፍል፣ አ.አ፣ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማእከል የታተመ፣ 1995 ::

___________ ፣ ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር ሁለት፣ አ.አ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1997 ::

የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎች አካዳሚእና የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የግእዝ ቅኔያት የኪነጥበብ ቅርስ፣ አ.አ፣ ብ.ሰ.ማ ቤት፣ 1980

___________ ፣ የግእዝ ቅኔያት የኪነጥበብ ቅርስ ሁለተኛ ክፍል፣ አ.አ፣ ብ.ሳ.ማ. ቤት 1984 ::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ሰዋሰው ግእዝ፣ አ.አ፣ ንግድ ማተማያ ጅት፣ 1992

ያሬድ ፋንታ፣ ፍኖተ ግእዝ ዘመናዊ፣አ.አ፣ መስከረም 1986 ::

ይሄይስ ሀይለሚካኤል፣ "የግእዝ መወድስ ቅኔ" ፣ አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1975::

ይሄይስ ወርቁ፣ ንባብ ወትርጓሜ ዘቅንያት አእማደ ምስጢራት፣ አ.አ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1960::

ዮናስ አድማሱና ሌሎቹ፣ "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ በስቲንስል የተባዛ፣ 1966::

ዮሀንስ አድማሱ፣ "ሰምና ወርቅ"፣ አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዋዎችና ስነ ጽሁፍ ዲማጽ 1959

ደስታ ተክለ ወልድ፣ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አ.አ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962::

ጀማል ከፍያለው፣ "ስለ ግእዝ ቅኔ በመጠኑ"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሚያዝያ 7 ቀን 1980፣ ገጽ 3 እና 6::

---------------------፣ "የቅኔ ጠቢባን የት ደረሱ"፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ የካቲት 11 ቀን 1980፣ ገጽ 3::

ገብረ ስላሴ ብርሀኑ(አሳታሚ)፤ ሀተታ መናፍስት ወአውደ ነገስት ከነጠልሰሙ፤ አ. አ፤ አክሱም ማተሚያቤት፤ 1997::

ገብረ የሀንስ ገብረ ማሪያም፣ ተቋመ ጽዩን እና ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ ክርስትያን፣ አ. አ፤ ጥር 1992::

---------------------፣ ግስ መዝገበ ቃላት ግእዝና አማርኛ ቋዋንቋዋ መማሪያ፣ አ.አ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1994::

ጥኡመ ልሳን ካሳ፣ ያሬድና ዜማው፣ አ.አ.፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1981::

ጽጌ አባተ፣ "ቅኔያዊ ውርስ"፣ አ.አ.ዩ"፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲማጽ፣ 1972::

ፊቃደ አዘዘ፣ የስነ ቃል መምሪያ፣ አ.አ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991::

Alemayehu Moges, "Geez and Amharic study without qune is incomplete". A.A,

__________,"Teaching and Curricula in Traditional Education of Ethiopian Orthodox Church", Addis Ababa University, 1972.

Bendor,M.L, Language in Ethiopia, London, and Oxford University Press, 1976.

Danielson, Lary, Religious Folklore, in Elliot Ring, 1986.

Dorson, Richard M. Folklore and Folktale, an Introduction, Chicago and London, The University of Chicago Press, 1972.

Ephraim Isaac, "Religious of Ethiopia", a note to the reader, tezeta org. 2001

Inbakom Kalewold, Translated by Mengistu Lema, "Traditional Ethiopian Education", Columbia University, 1970.

Kefyalew Merahie The meaning of Quine is the river of life, A.A commercial printing enterprise, 2006

Mike Ballantyne, "what is folklore?" the British Columbia Folklore Society, Mik@ Folklore b.c.ca. 2001

Oring Elliot, Folk groups and Folklore Genres, an introduction, Loson, Utah University press, Utah, 1986.

Phankerust Slivin, Cultural History of Ethiopia 1959.

Ruth Finnegan, Oral Literature in Africa, Oxford Clarinda press, 1970.

Tades Beyene, "Mengistu Lema Geez Quine" Proceedings the Ethiopian (8th) International Conference of Ethiopian Studies, A.A 1984.

Zainab Haruna, "Lecture notes for Folklore 2500", Zainab, WWW, Ultimate. Counter. Com. 2003.

## ማህደረ ቃላት (Vocabularies)

ሀምስ .... የግእዝ ፊደል አምስተኛው ሆሄ፤

ሀረግ .... ከግእዝ ቅኔ አንድ ስንኝ ከፊሉ ወይም ሩቡ፤

ሀዲስ ኪዳን .... ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ የተጻፈ፤ ስለ ክርስትና እምነት የሚያወሳና ልዩ ልዩ ክፍሎች ያሉት የሀይማኖት መጽሀፍ፤

ሁብር .... ልዩ ሆኖ ሳለ ምስጢሩም ንባቡም አንድ መስሎ የቀረበ፤

ሆሳእና .... ትምህርት እንዲቀና በሚል የሚወሰድ የባህል (ሀበሳ) መድሀኒት፤

ሆኛ .... አንድ ስንኝ ቤት ከመምታቱ በፊት ያለው ሀረግ ከቤቱ ጋር ሲገጣጠም፤

ለምድ .... ከበግ ቆዳ የሚዘጋጅ፤ የወትሮው የቅኔ ተማሪ መለያ ልብስ፣

ለአለም .... የመወድስ ቅኔ በዋዜው ቤት ሲመታ ከስድስተኛው ቤት፤ ቤት ሳይመታ ደግሞ ከአምስተኛው ቤት በሁዋላ ያለው የመወደስ ቅኔ ክፍል መጠሪያ፣

መልከ ማርያም ... ስለ ማርያም ክብር በግጥም የተዘጋጀ የምስጋና ጸሎት

መልከ ኢየሱስ ... ስለ ክርስቶስ ክብር በግጥም የተዘጋጀ የምስጋና ጸሎት፣

መልካም! (ይበል! ይበል!) ... ጥሩ ቅኔ ለተቀኘ ባለ ቅኔ «ጥሩ ቅኔ ነው! ግሩም ድንቅ ቅኔ ነው!» በሚል ከአድማጭ የሚሰጥ የአድናቆት መልእክት፤

መመርገድ .... ልዩ ልዩ የያሬድ የዜማ ድርሰቶችን በከበሮና በጸናጽል አማካኝነት መዘመር፣

መመራት .... ከቅኔ አቅራቢው (ቅኔ ከሚቀኘው) ፊት ቆሞ ባለ ቅኔው የሚነግረውን ቅኔ በዜም ማቅረብ፣

መሪ .... ቅኔን በማህሌት የሚያቀርበው ባለቅኔ፤

መሪ ጌታ .... የቅኔ፣ የአቋቋቁዋም፣ የቅዳሴ ፣ የዜማ፣ የመዋሲት፣ የመጽሀፍ፣ ወ.ዘ.ተ አስተማሪዎች መጠሪያ፤

መራህያን .... በሰው ስም ፋንታ ተተክተው የሚነገሩ የእርባታ መደቦች፤ (አነ ፣ ንህነ፣...)

መስተጋብእ .... ዜማው የቅዱስ ያሬድ የሆነ ከዳዊት መዝሙር የተውጣጣና በትምህርት መልክ የሚሰጥ፤

መንደርደሪያ .... በዛምላኪያ፣ በሚበዝሁ፣ በዋዜማ፣ በስላሴና በዘይእዜ ቅኔዎች በሁለተኛው ቤት፤ በመወደስ በሶስተኛው ቤት፣ በግእዝ እጣነ ምገር በአራተኛው ቤት፣ በእዝል እጣነ ሞገር ደግሞ በስድስተኛው ቤት የሚገኝ ስንኝ፤

መንፈሳዊ ትምህርት ቤት .. የፊደል መቁጠሪያ ፣ የንባብ መማሪያ፣ የቃል ትምህርትና የያሬድ ዜማዎች መጮህያ የትምህርት ገባኤ፣

መወድስ .... በግእዝ ቅኔ የትምህርት ገባኤዎች ከሚሰጡት የትምህርት አይነቶች ውስጥ የመጨረሻው የቅኔ ትምህርት መጠሪያ፤

» .... ምስጋና የሚለውን ቃል የሚወክል ሆኖ ብዙውን ጊዜ ከክስተት ቀጥሎ የሚቀርብ ራሱን የቻለ ትምህርት ።

መዋስእት .... ለሙታንና በአመት አንድ ጊዜ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ሞት የሚፈጸም የፍትሀት ጸሎት፣

መደልደል .... የቅኔ ተማሪዎች ምግባቸውን ለማግኘት ለልመና የሚሰማሩ ባቸውን ቤቶች ማደላደል፣ መመደብ፣ ተራ ማውጣት፣

መጽፈያ .... የዋዜማ፣ የስላሴና የዘይቤ አራተኛው ቤት፣ የመወድስ ዘጠነኛው ቤት፣ የግእዝ እጣነ ሞገር ሰባተኛው ቤት፣ የእዝል እጣነ ምገር ደግሞ ዘጠነኛው ቤት መጠሪያ፣

መጸንጸል .... ከያሬድ ድርሰቶች ውስጥ አንዱን ንኡስ ክፍል ወይም ቅኔን በጸናጽልና በከበሮ መዘመር፣

መጽሀፈ መነኮሳት.... ስለ መነኩሳት የቀኖና ስርአት የሚያትት መጽሀፍ፣

መጽሀፍ ቤት .... መጽሀፍትን አስተካክሎ መረዳት፣ መተርጎም፣ ስለ መሰረት ሀይማኖትና የክርስትና ታሪክ ምስጢራትን ጠንቅቆ ለማወቅ የሚያስችል፣ እንዲሁም ብሉያት፣ ሀዲሳት፣ መጽሀፈ ሊቃውንትና መጽሀፈ መነኮሰት በትርጉዋሜና በአንድምታ የሚመረመሩበት ጉባኤ፣

ሙሉ ቤት .... አንድ የቅኔ ተማሪ በአንድ የቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊማራቸው የሚገቡ የቅኔ አይነቶች በጠቅላላ (ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ)

ሙያ .... በግእዝ ቅኔዎች ውስጥ ቃላትና ሀረጋት እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ አገባባቸው የሚታወቅበት ስልት፣

ማህበር .... ሰዎች ለነፍሳቸው ጽድቅን ለማግኘት በየወሩ በተመረጡ ባእላት ስም የሚጠጡት (የሚዘክሩት) የጽዋ ስርአት፣

ማህሌተ ገንቦ.... ካህናት ጥሪ ተደርጎላቸው በድግስ ቤት ውስጥ በተገኙ ጊዜ ስለድግሱ ብዛት፣ ስለ ባለቤቶቹ ደግነትና ስለተፈጠረው የደስታ መንፈስ በማዜማ፣ በማሸብሸብና በመወረብ የሚያቀርቡት ዝማሬ፣

ማህሌተ ጽጌ .... ከመስከረም ሀያ አምስት ቀን ጀምሮ እስከ ህዳር ሀያ ስድስት ቀን ስለ ድንግል ማርያም የሚዘመር መዝሙር።

ማህሌት .... መዘምራን ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸናጽል፣ በከበሮና በመቋሚያ የያሬድ ርስቶችንና ሌሎች ሀይማኖታዊ መዝሙሮችን በዜማ ማውረድ፣ መመርገድ፣ መጽፋት፣ መዝሙር...፣

ማህሌት መቆም .... የተለያዩ መዝሙራትን እንደያገባባቸው እየዘምሩ ማንጋት፣ መዋል፣ ማምሸት ወይም ማደር፣

ማርዳ ..... መካከሉ ክፍት የሆነ፣ በክር ወይንም በሲር እየተሰካ በአንገት በማጥለቅ ወይም በልብስና በጸጉር ላይ በመስካት ለጌጥ አገልግሎት የሚውል፣

ማስረገጥ .... በማህሌት ቁመት ጊዜ የተወረበውን ወረብ እየለዋወጡ ማሸብሸብና የሸብሸባውን ሂደት መምራት፣

ማስታኮት .... ለፈጣሪ ምስጋናን በቃል ማቅረብ፣

ማንሻ .... «መጽፊያ» የሚለውን ቃል ተመልከት፣

ማእበል .... በቅኔ ሙያ ልቅና ላገኘ የቅኔ ሊቅ የሚሰጥ የማእረግ ስም፤

ምስጢራዊ ትርጓሜ ....ንባቡን ሳይሻና አገባቡን ሳይጠብቅ ምስጢሩን ብቻ በመጠበቅ የሚቀርብ የአተረጓጐም ስልት፤

ምቅናይ .... ከያሬድ የድርሰት ስራዎች መካከል ከግእዝ ቅኔ ባህሪ ጋር ቅርበት ያለው የድርሰት ስራው፤

ምእራፍ .... ማረፊያ ማለት ሆኖ «ሰላም ለኪ» ብሎ ጀምሮ የጾም ምእራፍ እስኪፈጸም ድረስ ያለው ትምህርት፣ በበአላትና በእለተ ሰንበት የሚቀርብ የጸሎት፣ የምስጋና የዜማ ድርሰት፤

ምናባዊ አለም .... እውነታነቱ ገና ያልተረጋገጠ አእምሮ ውስጥ የሚፈጠር ከተለመደው ወጣ ያለ አስተሳሰብ፣

ሩቅና ቅርብ .... በግእዝ ቅኔ ትምህርት ህግጋት ውስጥ ከሚፈጠሩት ስህተቶች አንዱ (እሱ መጣህ)

ሰለስት .... ትርጉሙ ሶስተኛ ማለት ሆኖ፤ በዳዊት መዝሙር በሶስተኛው መስመር እየገባ የሚዘመር፤

ሰም ለበስ .... በአንድ የግእዝ ቅኔ ውስጥ ወርቁ የሚገኘው በምስጢር ሲሆንና በግልጽ ሳይታይ ሲቀር፤

ሰምና ወርቅ .... በአንድ የግእዝ ቅኔ ውስጥ ሁለት ሀሳቦች ተጣምረው ተነግረው አንደኛው ሀሳብ ለሁለተኛው ምሳሌ ሲሆነው፤

ሰም ገፊ .... ከአንድ የግእዝ ቅኔ ሁለት ስንኞች መካከል አንዱ ስለሰም ሁለተኛው ደግሞ ስለወርቅ ጉዋዝ ብቻ ሲያወራ፣

ሰንበቴ .... እሁድ እሁድ በቤተ ክርስቲያን ግቢ የሚሰበሰብና ክርስቲያንነትን ለመግለጽ የሚሰጥ መዋጮ፣ ስለሰንበት የሚቀርብ እንጀራና ጠላ ወይም ገንዘብ፤

ሱባኤ .... ምኞተንና ፍላጎትን ለፈጣሪ ለማድረስ ሲባል ራስን ከአለማዊ ህይወት አገልሎ ቀኖና መግባት (ጾምና ጸሎት ማድረግ)

ሳህለከ .... አጭሩና ባለ ሶስት ቤት የሆነው የዘይዜ ቅኔ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ለነገስታት፣ ለመኩዋንንትና ለሊቃውንት የሚቀርብና አቀራረቡም በዝማሜ የሆነ የቅኔ አይነት፤

ሰአታት .... በሰአትና በጊዜ ተወስኖ ማለትም የሌሊትና የቀን በሚል የሚቀርብ የጸሎት አይነት ሲሆን በሀገራችን አብዛኛውን ጊዜ የሚቀርበውና የሚጸለየው በሌሊት ነው፤

ሳልስ .... የግእዝ ፊደላት ሶስተኛው ሆሄ፤

ሳንቃ .... ለቤተክርስቲያን መውጫና መግቢያ በሮች መዝጊያ እንዲሆን ተጠርቦ የተዘጋጀ ትልቅ ጣውላ (ጠርብ)፤

ሳድስ .... የግእዝ ፊደላት ስድስተኛው ሆሄ፤

ሴትና ወንድ .... በግእዝ ቅኔ ህግጋት ውስጥ የሚፈጠር የስህተት አይነት (እሱ መጣች)

ስብሀተ ነግህ .... በዘመነ አጽዋማት በነግህ (ንጋት ላይ) በካህናት የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት፣



...ES LIBRARY

ሻሽ .... በቤተ ክርስቲያን ካህናትና በዜማ ቤት ዘማርያን ዘንድ ተዘውትሮ በራስ ላይ የሚጠመጠም ነጭ ጨርቅ

ቀመር .... ቅኔን ቆጥሮ ለመንገር ወይም ለመቀኘት፤ እንዲሁም ቅኔውን ከሙያው፤ ከዜማው፤ ከታሪኩና ከምስጢሩ ጋር ለማዋሀድ የሚከናወነው ተግባር፤

ቅምጫና .... የአንገትና የሆድ ቅርጽ ያለው በወትሮው ዘመን የቅኔ ተማሪዎች ለውሀ መጠጫ የሚይዙት የቅል አይነት፤

ቅባት .... በኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነት ዶክትሪን (ስነሰርአት) ውስጥ በአንድ ወቅት የክርስቶስ ባህሪን አስመልክቶ ተከስቶ የነበረ የእምነት ፍልስፍና፤

ቅኔ .... እንደ እለት ዜና ሁሉ ወቅታዊነት፣ ትኩስነትና የወዲያውነት ባህሪ ያለው፤ በአእምሮ ታስቦና ተፈጥሮ ወዲያው የሚዘረፍና የሚነገር፤ እንጼ ከቀረበ ለማህሌት አገልግሎትም ሆነ ለማስተማር በድጋሚ የማይዘረፍ፤ የተለያየ ሙያና የአገባብ ስርአት ያለው የእለት ድርሰት፤

ቅኔ ቆጣሪ .... በየቆጥቋጠው፣ በየዛፉና በየአውደ ቤተክርስቲያኑ ስር ቁጭ ብሎ ወይም ተጋድሞ ቅኔን ከነሙያው የሚያሳካ፣ ወይም የሚያስላስል የቅኔ ተማሪ፤

ቅኔ ቆጠራ .... ቅኔን ማሰብ፣ ማስላሰል፣ ማደራጀት ማራቀቅ፣

ቅኔ ቤት .... የቅኔ ትምህርት ከነጓዙ የሚሰጥበት የቅኔ ጉባኤ፤

ቅኔ ተቀባይ .... መምህሩ ወይም ዘራፊው ቅኔውን እንደ ማእበል ሲያወርደው እንደተዘረፈ መጠን ቶሎ ቶሎ እየተቀበለ ለአድማጮች የሚያሰማ ወይም የሚያስተላልፍ ቅኔን የለየ ተማሪ፤

ቅኔ ነገራ .... ተማሪው የቆጠረውን ቅኔ ጉድለት አውቆ ለማሳረም እንዲችል ለጉባኤው መምህር ወይም አስነጋሪ መንገር ወይም ማሳወቅ፣

ቅኔ ነጋሪ .... ቆጥሮ ወይም ደርሶ ያዘጋጀውን ቅኔ ለመምህሩ ወይም ለአስነጋሪው የሚነግርና የሚያሳርም የቅኔ ተማሪ፤

ቅኔ አስቀጻይ .... የተዘረፈውንም ሆነ ጀማሪ ተማሪው ለአስነጋው ነግሮ ያሳረመውን ቅኔ ንባቡን፣ ፍችውን፣ ምሳሌውንና ሙያውን ተንትኖ ለጀማሪው የሚያስረዳ ቅኔው ህግ የገባው ተማሪ፣

ቅኔ አስቆጣሪ .... የራሱን ቅኔ በመቁጠር ላይ እያለ ጀማሪውን ተማሪ አጠገቡ አስቀምጦ የቅኔውን ዜማ፣ ሙያና የቁዋንቁዋ ትርጉም የማያስረዳ ቅኔ የለየ ተማሪ፤

ቅኔ አስነጋሪ .... ቅኔ ቆጥሮ የመጣን ተማሪ እያስነገረ የቅኔውን ዜማ ልክ፣ ሙያና አገባብ እያስተካከለ የሚያርም እጩ መምህር፤

ቅኔ ከነጓዙ .... የቅኔው ትምህርትና ቅኔን ለመማር የሚረዱ ሌሎች የትምህርቱ አካሎች በጠቅላላው፣

ቅኔ ዘራፊ .... የግእዙ ቅኔ ሙያ የገባው፣ በሰማው ነገር ሁሉ እያመሰጠረ ቅኔን ሳይቆጥር እንደ ዝናብ የሚያወርድ፤ የሚፈለስፍ፤ የሚመረምርና የሚያራቅቅ የቅኔው መምህር ምክትል፤

ቅጸላ .... በየእለቱ የሚሰጠውን ትምህርት ማጥናት መከለስ፤

ቅጽል .... ከስም ጋር ሳይነበብና ሳይያያዝ የባለቤትነትን ጠባይና ግብር፣ መልክና አይነት እንዲሁም መጠን የሚገልጽ፤



ILS LIBRARY

| | |
|---|---|
| ባህረ ሀሳብ .... | የቁጥር መጽሀፍ የሆነ፣ የእመቱን በአላትና አጽዋማት የሚያስረደ የዘመን አቆጣጠር ማሳያ መጽሀፍ፤ |
| ባእድ ቅጽል .... | በእርባታ ጊዜ በደቂቅ እርባታ ውስጥ በመነሻና በመድረሻ በዋናው ግስ ያልነበረን ባእድ ቀለም በመጨመር ማርባት፤ |
| ቤተ ክርስቲያን .... | የጸሎት ማድረሻ፣ የክርስትና ማንሻ፣ የቁርባን መቀረቢያ፣ የፍትሀት መፍቻ፣ የኪዳን ማድረሻ፤ የማህሌት መቆሚያ፣ የቅዳሴ መቀደሻ፤ የቅኔ መቀኛ የሆነ የእግዚአብሄር ቤት፣ |
| ቤት .... | በቅኔ ትምህርት ቤት አነጋገር የቅኔው አንድ ስንኝ እንዲሁም የስንኙ የመጨረሻው ተመሳሳይ ሆሄ፡፡ |
| ቤት መምቻ .... | የመወድስ ቅኔ የመጀመሪያው ስንኝ |
| ቤት ምሪት .... | በወትሮው ዘመን የቅኔ ተማሪዎችን በምግብ አቅርቦት ለመርዳት ሲባል ምግባቸውን ከአካባቢው ማህበረሰብ ማግኘት የሚያ ስችላቸው የአፈጻጸም ስርአት፣ |
| ቤት ሞላ .... | የቅኔ ተማሪ በቅኔ ጉባኤ ውስጥ ሁሉንም የቅኔ አይነቶች ለመቁጠርና በደንብ ለመንገር ቻለ፤ በማህሌትም ውስጥ እጣነ ሞገር ለመቃኘት ቻለ፤ |
| ቤት ገጠመ .... | በአንድ የግእዝ ቅኔ ውስጥ በመጀመሪያው ወይም ከስንኞቹ ባንደኛው መጨረሻ ላይ የተነገረው (የተባለው) ቃል በሌላው እንዳለ ሳይለወጥ ተደግሞ ሲቀርብ፤ |
| ቤት ፈረሰ .... | በግእዝ ቅኔ ውስጥ በስንኞቹ መጨረሻ ያለው ሆሄ አንዱ ከሌላው የተለየ ሲሆን፤ ወይም ቤት የተመታበት የመጀመሪያው ሆሄ ሲቀየር፤ |
| ብራና .... | የጥጃ፣ የፍየል ወይም የበግ ቆዳ (አንጋፋ) በውሀ ተዘፍዝፎና በእርጥቡ ተወጥሮ፣ ተላጭቶ፣ ተረሞ (ተፍቆ) የተዘጋጀ ወረቀት መሰል የጽህፈት ስሌዳ፣ |
| ብህትውና .... | ከአለማዊ ህይወት እርቆ በገዳማትና በጫካ ውስጥ በጾምና በጸሎት ተወስኖ የመኖር ህይወት፣ |
| ነባር .... | የነጠላ ግስ አይነት የሆነ፣ ሊረባ የማይችል፣ ዘርነት የሌለው፣ ከዘር አንቀጽ የማይገኝ ጥሬ ቃል፤ |
| ነጠላ ትርጓሜ .... | ዘይቤን ብቻ በመከተል የሚቀርብ የአተረጓጎም አይነት፤ |
| ነጠላ ግስ .... | የግእዝን ቁዋንቁዋ ስልት ለማወቅ መነሻ የሆነ በግእዝ ፊደላት ቅደም ተከተል የሚገኝ፣ መዳረሻውን ግእዝ (የመጀመሪያ ፊደል) እያደረገ በሀላፊ ብቻ የሚነገርና ያለ እርባታ የሚሄድ የግስ አይነት፤ |
| ነጠቃ .... | በባለ ቅኔው እየቀረበ ያለን የቅኔ ምስጢር አስቀድሞ በመረዳት ትክክለኛውን ምስጢር የያዘውን ዋና ሀሳብ መንጠቅ ወይም አስቀድሞ መናገር፣ |
| ንባብ ቤት .... | የቤተ ክህነት ትምህርትን የሚማር ተማሪ ከፊደለ ሀዋርያ እስከ ዳዊት ድረስ ያለውን ትምህርት የሚማርበት የትምህርት ጉባኤ፣ |
| ንኡስ መርገድ .... | በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማህሌት ሲቆም በጸናጽልና በከበሮ የሚዘምሩት የአዘማመር ስልት፤ |
| ንኡስ አንቀጽ .... | ከአቢይ አንቀጽ ቀጥሎ የሚገሰሱትን ግሶች የሚያመላክት፤ |

ንኡስ አገባብ ... በነባር፣ በዝማች አንቀጽ፣ በሀላፊና በትንቢት እየገባ ማስሪያ አንቀጽነትን የማያስለቅቅ፣

አምምና ጠምጥሞ የካህንነት ችሎታና ብቃቱ ሳይኖረው የተማረና አዋቂ መስሎ።

አረብ .... በቀይ ቀለም የተነከረና ለፍቶና ለስልሶ የተዘጋጀ የከብት ቆዳ፣

አራራይ .... በቅዱስ ያሬድ ከተደረሱት የዜማ አይነቶች አንዱ።

አርባእት .... በዳዊት መዝሙር በአራተኛው መስመር እየገባ የሚዘመርና በቅዱስ ያሬድ የተደረሰ፣

አርያም .... የቅዱስ ያሬድ ድርሰት አካል የሆነና መላእክት አምላካቸውን ሲያመሰግኑ ተገልጾለት የደረሰው።

አቋቋም .... የማህሌት ቁዋቁዋም ስርአትን የሚያስተምር ሆኖ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ የአገልግሎቱን ስርአትና የዜማውን ልክ የሚገልጽ፣ የሚያስተምር።

አስረ ንጉስ .... ከጣነ ሞገር ቅኔ መንደርደሪያ አስቀድሞ የሚገኝ፣ ብዙውን ጊዜ፣ ለነገስታትና ለሊቃውን ክብር የሚቀርብ የጣነ ሞገር ቅኔ አንዱ ክፍል።

አስራት .... ለስርአተ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወይም ለምጽዋት ከተገኘ ገቢ ላይ ከአስሩ አንዱ የሚከፈል ክፍያ፣

አሸበሸበ .... አስረጋጭ ካህናት፣ በለዘብ፣ በማህሌት ወይም በማህሌት ገንቦ፣ አሸበሸበ፣ አረገረገ፣ ወዲያና ወዲህ ተወዛወዘ፣ ተንቀሳቀሰ፣ ተነቃነቀ፣

አቡሻክር .... የምእተ አለም መስፈሪያና መቁጠሪያ የሆነ አለም ከተፈጠረ 7499 ዘመን ሆኖታል ከሚል ሀሳብ የሚነሳ፣ የጊዜ ስሌዳ መቁጠሪያ ስርአትን የያዘ መጻህፍ።

አቡን .... በድጉዋና በጾመ ድጉዋ ውስጥ ከሚገኙት ንኡሳን ክፍሎት አንዱ።

.... የቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ የማእረግ ስም።

አቡገርዴ .... የቅኔ ተማሪዎች ከደበሉዋቸው በስር የሚለብሱት አንሶላ መስል ነጭ ጨርቅ፣

አቡጊዳ .... ከግእዝ ፊደላት አቀማመጥ (አደራደር) ስርአት ውስጥ አንደኛው ዘዴ።

አቢይ መርገድ .... «ንኡስ መርገድ» የተሰኘውን ቃል ተመልከት።

አቢይ አንቀጽ .... በግስ ስርአት ውስጥ፣ ሀላፊ፣ ትንቢት፣ ዘንድ እና ትእዛዝን የያዘና አጠቃቀማቸውን የሚያስረዳ የግስ አረባብ ስርአት፣

አቢይ አገባብ .... «ንኡስ አገባብ» የሚለውን ቃል ተመልከት።

አብነት .... በቅኔ የትምህርት ጉባኤዎች አጠራር ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል መድሀኒት (የሀበሻ መድሀኒት)

አብሾ .... ከተለያዩ የተክል ፍሬዎች የሚቀመምና ትምህርት እንዲገልጽ በመጠጣት ወይም በመዋጥ ከተጨማሪ ገቢር ጋር ተዘጋጅቶ የሚወሰድ መድሀኒት።

እንድምታ .... አንድ ቃል አንድ ጊዜ ከተተረጎመ በሁዋላ እንደገና አንድም እየተባለ እስከ ሶስትና ከዚህ በላይ የተለያየ ትርጉም የመስጠት ስርአት፤

እንድና ብዙ .... «ሩቅና ቅርብ» የተሰኘውን ቃል ተመልከት (እሱ ናቸው)

እኩፋዳ .... የወትሮው የቅኔ ተማሪ ለምኖ የሚያገኘውን ምግብ የሚይዝበት ከሰሌን ወይ ከቆጠማ የተሰራና የተሰፋ፣

አዋጅ .... የሰዋስው መመሪያ

አገባብ .... የነገርን ቅጽል፣ ከግእዝ እስከ ሳብእ የሚያናግረውን በአንድና በብዙ፣ በቅርብና በሩቅ፣ በወንድና በሴት፣ በስምና በግብር፣ በገቢርና በተገብሮ፣ ነገረ ፊደላት እንዴት እንደገቡ፣ እንዴትስ እንደተተረጎሙ የሚያሳይ፤ የመጻህፍትን አካሄድ የቅኔን መንገድ፣ የቁዋቁዋን ጠባይና ልማድ የሚያሳውቅ የቅኔ ትምህርት አንደኛው ክፍል፤

አደራረስ .... ትልቅ መንፈሳዊ በአል ሲከበር ወይም ታዋቂ ሰው ሲሞት የሚፈጸም መንፈሳዊ ስርአት ዝማሬ ወይም የማህሌት ቁመት፤

አጸድ .... የቤተ ክርስቲያን አጥር ግቢ፤

አፍልሆ .... ከአርባ አንድ አይነት የተለያዩ ተክሎችና እጽዋት የሚቀመምና ትምህርት እንዲገልጽ በሚል የሚወሰድ የሆሳእና (መድሀኒት) አይነት፤

እርባ ቀመር .... ከዘር የሚወጡትን የግስ አርስት የሚሆኑት ፊደላት (ቀለማት) ከሰራዊታቸው ጋር አመላቸውን የሚያሳይ፣ ገቢርና ተገብሮ የመሰለውንም ስርአት በስርአት የሚሄደውን ግስ ሁሉ በየፈርጁ ከፍሎ አካሄዱንና ጠባዩን የሚያስተዋውቅ የሰዋስው ትምህርት ቀዳሚው ክፍል።

እርባታ .... የግስ አረባብ ስርአት ሂደት፤

እርባ ግስ .... በሀምሳ ሰራዊት ተዘርዝሮ፣ በስምንት አርስት ተከፍሎ በአምስት አእማድ ተጠቃሎ፣ በአቢይ አንቀጽ፣ በንኡስ አንቀጽ፣ በቢቂት አገባብ፣ በባእድ ቅጽል፣ በመራህያንና በዝርዝር ቅጽል እየገባ በምልአት የሚገሰስ የግስ አረባብ ስርአት፣

እዝል .. .. «አራራይ» የተሰኘውን ተመልከት፤

እጀ ጠባብ .... የእጅ ማስገቢያው ጠበብ ያለ ከፊቱ ያልተከፈተና ሸሚዝ የሚመስል በቅኔ ተማሪዎች የሚዘወተር የልብስ አይነት፤

እጸ ህይወት .... ህይወትን ወደነበረበት የሚመልስ እጽ (የተክል አይነት)

እጸ መሰውር .... ከእይታ መሰወር የሚያስችል እጽ (የተክል አይነት)

እጸ መከስት ... የተደበቀን (የተሰወረን) ነገር ገልጾ የሚያሳይ ወይም የሚከስት እጽ (የተክል አይነት)

እጸ ሳቤቅ .... ትምህርት እንዲገባ (እንዲገለጽ) ሲባል ከተጨማሪ ገቢር ጋር በሰውነት ክፍል ውስጥ የሚቀበር፤

እጸ ፋርስ .... ከተለያየ ገቢር ጋር በመቀላቀል ትምህርት እንዲቀና (እንዲገለጽ) በሚል የሚወሰድ የመድሀኒት (ሆሳእና) አይነት፤

ወረብ .... የተመረገደውን በመከተል፤ ሌላም አረፍተ ነገር በመጨመር ወይም በመለወጥ በተለያየ የዜማ ቃና የሚቀርብ፤ በሁዋላም የዜማውን ፍጥነት እያለዋወጡና እያመላለሱ ካህናት የሚወርሱት ወረብ፣ ሽበሽባ፤

| | |
|---|---|
| ወርቃ ወርቅ .... | በቅኔ አቀራረብ ስርአት በአንድ ቅኔ ውስጥ ሁለት ወርቅ ሲገኝ፣ ማለት በአንድ እለት ሁለት በአላት ውለው የሁለቱ በአላት ታሪክ እንዱ ስም ሌላው ወርቅ ሆኖ ሲቀርብ። |
| ዋዌ .... | በግእዝ ቅኔ ውስጥ አንድ ስንኝ (አረፍተ ነገር) ከተሰራ በኋላ ሌላ አረፍተ ነገር ለመስራት ሁለተኛውን አረፍተ ነገር በዋዌ መክፈል፣ በዋዌ ካልተከፈለ በአንድ ቅኔ ውስጥ ሁለት ማሰሪያ አንቀጽ እንዲኖር ያደርጋል። ለምሳሌ፣ አበበ አተወ ውስተ ቤቱ፣ ወረከባ ለእሙ። (አበበ ወደ ቤቱ ገባ፣ እና ቱንም አገኛት) በግእዙ ወ በአማርኛ ም የሚያመለክቱት ዋዌን ነው። |
| ውስጠ ወይራ.... | አንዱ የቅኔ መንገድ(ስልት) ሲሆን የሰምባለቤት ወይም ተሳቢ በወርቅ ዘርፍላይ ወድቆ የወርቅን ጉዋዝ ሲያመጣ፣ |
| ውስጠ ዘ ... | ከቅኔ መንገዶች አንዱ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ በሳልስ፣ በሳድስና በስም ወስጠዘ የሚነገር፣ በቃላት አቀራረቡና አደራደሩ ለየት ያለና በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግር የቅኔ አይነት፣ |
| ኩልክሙ .... | ዘጠኝ ቤት (ስንኝ) ያለው የመወድስ ቅኔ አይነት ሲሆን ብዙውን ጊዜ ኩበክሙ ከተባለው የዳዊት መዝሙር ቀጥሎ ስለሚቀርብ ኩልክሙ የሚለውን መጠሪያ ወርሱዋል። |
| ኪዳን ቢያደርስ .... | ጥዋት ጥዋት የሚቀርብን ጸሎት ቢጸልይ፣ |
| ካራ .... | «ቅባት» የተሰኘውን ተመልከት፣ |
| ካእብ .... | የግእዝ ፊደል ሁለተኛው ሆሄ፣ |
| ክስተት .... | በጾምና በጸሎት ጊዜ የሚዘመር፣ አርያምና ስለስትን እየተካ የሚቀርብ መዝሙር፣ |
| ክብረ በአላት .... | በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ የሚከበሩ የመታሰቢያ በአላት አከባበር ስርአት፣ |
| ክብር ይእቲ .... | እጣነ ሞገር ቅኔ ከመቅረቡ አስቀድሞና እርገት ከመውረዱ በፊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚቀርብ፣ በክርስቶስ ጸዋታወ መከራ ታሪክ ላይ የሚመሰረት ባለ አራት ቤት የቅኔ አይነት፣ |
| ኮቸሮ ማኮቸር .... | ደርቆና ተከስክሶ የተዘጋጀን እንጀራ ለምግብ በሚያመች ሁኔታ ማዘጋጀት፣ |
| ዛጎል፣ .... | «ማርዳ» የሚለውን ተመልከት፣ |
| ዜማ ስበረ .... | በግእዝ ቅኔ አቀራረብ ጊዜ አንድ ቤት (ስንኝ) ወይም ሀረግ ከተወሰነለት ምጣኔ (ልክ) ሲያጥር ወይም ሲረዝም። |
| ዜማ ቤት .... | ጽዋትዎ ዜማ ማለትም ቅዳሴ፣ ጾመ ድጓ፣ ምእራፍ፣ ድጓ፣ ዝማሬና መዋሴት የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ሁሉ የሚጠኑበት የትምህርት ጉባኤ፣ |
| ዝማሜ .... | በመቋሚያ (ዘንግ) አማካኝነት እየተወዛወዙ በዜማ የሚቀርብ የዝማሬ አይነት፣ |
| ዝማሬ .... | የስጋ ወደሙ ስነስርአት እንደተከናወነ ስለምስጢረ ቁርባን ክብር የሚዘመር ድርሰት፣ |
| የሆሳእና ማርከሻ .... | ትምህርት እንዲገለጽ የተሰጠ (የተወሰደ) አብነት (መድሀኒት) የተወሰነለት ጊዜ ሲያበቃ መድሀኒቱ አደጋ እንዳያደርስ የሚሰጥ የማስታገሻ መድሀኒት፣ |

የማርያም መሸኛ.... የቅኔ ተማሪው በማርያም ስም ቁራሽ እንጀራ ሲለምን አምሽቶ ወደ ጉባኤው ከተመለሰ በሁዋላ ምግብ ሳይቀምስ የሚያደርሰው የጸሎት ስነ ስርአት፤

የቁጫን መውጫ .... በውስጥ የሚፈጠርን የጋለ ስሜት ማስታገሻ፤

የቅኔ መንፈስ .... ባለ ቅኔ፤ ቅኔ መዝረፍ ሲጀምር በውስጡ የሚፈጠር ሀያል መንፈስ (ስሜት)

የትምህርት ጉባኤ ... የቅኔ ትምህርት ቤት፤

የውሎ ጸሎት .... ያለ ማቋዋረጥ ቀኑን ሙሉ የሚከናወን የጸሎት ስነ ስርአት፤

ይትበሀል .... አባባል፣ አደራረስ፤

ይገባዋል .... እጩ የቅኔ መምህር የመሪጌትነት ክብር ለማግኘት በቅኔ ሊቃውንት ፊት ቅኔ እንዲቀኝ ይደረግና ያገኘው ውጤት እጅግ በጣም ጥሩ ከሆነ «ይገባዋል» በሚል ማእረግ ይመረቃል።

ደቀ መዝሙር.... የቅኔ ተማሪ፤

ደቂቀ ግእዝ .... በቅኔ የትምህርት ጉባኤ ውስጥ በትምህርት ላይ ያሉ የቅኔና የግእዝ ቁዋንቁዋ ተማሪዎች፤

ደቂቅ .... ከንኡስ አንቀጽ ቀጥለው እስከ ፍጻሜው ያሉ አርባ ግሶች፤

ደበሎ .... «ለምድ» የተሰኘውን ቃል ተመልከት፤

ደብረዘይት .... የአቢይ (የሁዳዴ) ጾም አምስተኛው እሁድ፤

ደጎስ (መደጎስ) .... የተጠረዘን የመጽሀፍ ገበታ አረብ አልብስና በሙቅ አጣብቆ በልዩ ልዩ ቅርጽ ማስጌጥ፣ ማሳመር መቅረጽ፣

ድጓ .... የብዙ የዜማ መጻህፍትና ድርሰቶች ምንጭ የሆነ፣ በታላላቅ በአላትና እሁድ እሁድ የሚዘመር በቅዱስ ያሬድ የተደረሰ የቤተ ክርስቲያን የዜማ መጽሀፍ፤

ድድቅ .... የቅኔን ብርታት የሚገልጽ ሆኖ የእውቀትና የምስጢር ጀግና የሚለውን ሀሳብ ያመለክታል፤

ገሞራው .... «ማእበል» የተሰኘውን ቃል ተመልከት፤

ገበዝ .... የቤተ ክርስቲያንን ውስጣዊ አገልግሎትና የቅዳሴን ስርአት እንዲሁም ንዋየ ቤተክርስቲያንን የሚጠብቅ፤ የሚቆጣጠር፤

ገቢርና ተገብሮ .... በቅኔ ህግጋት ውስጥ ከሚታዩ ስህተቶች አንዱ (የሚስብ ግስና የማይሳብ ቃል አብረው ሲገኙ)፤

ጉራማይሌ .... «ፍሩንዱስ» የተሰኘውን ቃል ተመልከት፤

ጉባኤ .... የቅኔ ተማሪዎች የተሰበሰቡበት ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ስርአቱ የሚፈጸምበት አዳራሽ፤

ጉባኤ መትከል .... በቅኔ መምህርነት የተመረቀ አዲስ መምህር ወይም ቦታውን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ የተዛወረ የቅኔ መሪጌታ፤ አዲስ የቅኔ ጉባኤ መክፈት (መጀመር)

ጉት .... ከተራው አረፍተ ነገር የተለየ ሆኖ በውስጡ ህብርነት ያለው አስተያየት የያዘ ወይም ስውር ምስጢርን የሚያስተላልፍ ግጥም መሰል አረፍተ ነገር፤

ግልበጣ .... በቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህሩ ወይም ዘራፊው የዘረፋትን ቅኔ ቤቱን ወይም ምስጢሩን በመገልበጥ የተዘረፈውን ቅኔ በተቃራኒው ማቅረብ፤

ግሰሳ .... የቅኔ መምህሩ ወይም ዘራፊው የግእዝ ቋንቋዋ መሰረት የሆነውን ግስ የሚያስተምሩበት ስርአት ወይም አቀራረብ፤

ግስ ማውረድ.... የግስን ዘር ማርባት (ሆረ ሄደ፣ የሀውር ይሄዳል፤....)

ግስ ከነ ቀመሩ.... ግስና በስሩ የሚጠኑ ሙያዎች፤

ግስ ወረደ .... በእለቱ ለጉባኤው ተማሪዎች የሚቀርበው የግስ ክፍል ቀረበ፤

ግብረ ሀዋርያ .... የቤተ ክህነት ተማሪዎች የተለያዩ መጻህፍትን ማንበብና መዝሙረ ዳዊትን መድገም የሚጀምሩበት የትምህርት አይነት (ድርስህን)

ግእዝ .... ከያሬድ የዜማ ድርሰቶች አንዱ፤

.... በግእዝ ፊደል ውስጥ የመጀመሪያው ሆሄ፤

ግጨው .... «ማእበል» የተሰኘውን ተመልከት፤

ጎጃም አዘነ .... በጎጃም ውስጥ የቅኔ ተማሪዎችን ጨምሮ ተዘውትሮ የሚለበስ የተለያየ ቀለም ያለው ነጠላ መሰል ጨርቅ፤

ጎዳና .... አንዱ የቅኔ መንገድ (ክፍል)

ጭራ እየቆነነ.... የፈረስን ጭራ በተዋበ የእጅ ስራ እያዘጋጁ፤

ጸናጽል .... በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማህሌት ቁመት አገልግሎት ከሚውሉ መሳሪያዎች አንዱ፤

ጸዋትው .... ጾታን፣ ሰገንን፣ ግስን ሁሉ በየወገኑ ለይተን እንድናወርድ የሚያስተምረን የግስ ግሰላ ስርአት፤

ጸያፍ .... በግእዝ ቅኔ አቀራረብ ጊዜ የማይባል፣ የተከለከለ፤ ነውር የሆነ፤

ጸጋ .... «ቅባት» የተሰኘውን ተመልከት፤

ጾመ ድጓ .... በቅዱስ ያሬድ የተደረሰ፤ በጾም ጊዜ በተለይ በጾመ አርባ (ሁዳዴ) የሚዘመር ድርሰት፤

ፊደለ ሀዋርያ.... ጀማሪ ተማሪዎች ማጋዝ፣ ወርድና ቁም ንባብ ማንበብ የሚጀምሩበት የትምህርት ክፍል፤

ፍርንዱስ .... አንድ ቅኔ ከአንድ በላይ በሆነ ቋንቋዋ ተቀላቅሎ ሲቀርብ (ሲነገር)፤

ፍትሀ ሊተ .... ቤቱ ስምንት ዜማው አራራይ የሆነ የመወድስ ቅኔ አንደኛው መጠሪያ፤

ፍትሀት .... «መዋሰት» የተሰኘውን ቃል ተመልከት፤

ፍች .... የቅኔን መያና ትርጉም ተንትኖ የሚያሳይ የቅኔ ትምህርት አንዱ አካል «ሙያ» የሚሉትም አሉ።

ፍካሬ .... ከዳዊት መዝሙር የመጀመሪያው ክፍል፤

## የግእዝ ቅኔን አስመልክቶ ለአባቶች ከቀረቡ ጥያቄዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ

1. የግእዝ ቅኔ በምን ጊዜ፣ እንዴትና በማን ተመሰረተ?

2. በዋድላች በጎንጅዎችና በዋሸሮች ጥንታዊ ጉባኤዎች መካከል ያለው ልዩነትና ተመሳሳይነት ምንድን ነው? የመለያየታቸው ምክንያትስ ምን ይሆን?

3. የቅኔን አጀማመር በተመለከተ የተለያዩ ሊቃውንት የተለያየ አመለካከት አላቸው። ለማያቀርቡትም ሀሳብ ምክንያት ይሰጣሉ። አንዳንዱ ከያሬድ በፊት፣ ሌላው በያሬድ ዘመን፣ ሌላው በዮሀንስ ገብላዊ፣ ሌላው በተዋናይ ይላል ለሀሳባቸው መለያየት ምክንያቱ ምን ይሆን? እርስዎስ ምን ይላሉ?

4. የያሬድ ቅኔዎች ከጥንታዊዎቹ /ሆሚየር፣ ከበደ ሚካኤል/ ግጥሞች ሀይማኖታዊ ከመሆናቸው በስተቀር/ በምን ይለያሉ? የ17ኛውን የግእዝ ቅኔ መስፈርቶች የሚያሙዋሉ ነበሩ? ካላሙዋሉ የግእዝ ቅኔ ሊባሉ ይችላሉ?

5. የጎጃም የቅኔ ትምህርት መቼና በማን ተመሰረተ፣ አመሰራረቱስ እንዴት ነው? ከሌሎቹ አካባቢዎችስ በምን ይለያል? ለምን?

6. የግእዝ ቅኔ አስቀጻይ፣ አስነጋሪና ዘራፊ በምን ይለያያሉ? ይህ ማእረግስ እንዴት ነው የሚሰጠው? ማእረጉስ የሚሰጠው በመን መስፈርት ነው? በማንስ ነው የሚሰጠው?

7. ቅኔ መቁጠር፣ መዝረፍ፣ መንጠቅ፣ መገልበጥና መቀኘት ማለት ምን ማለት ነው? አንዱስ ከሌላው በምን ይለያል?

8. ቅኔ ነጠቃና ግልበጣ የሚካሄደው መቼ? የት እና በማን ነው? አንዱ ከሌላው በምን ይለያል? ለምንስ ተግባሩ ይፈጸማል?

9. የቅኔ ጉባኤዎች የሚሰፉት በምን ወቅትና ጊዜ ነው? ለምን?

10. የቅኔ ተማሪዎች ምግባቸውን እንዴት ነው የሚያገኙት? የቀለብ አሰባሰብ ስልታቸው እንዴት ነው?

11. አዲስ /ጀማሪ/ የቅኔ ተማሪ አቀባበልና ወደ ጉባዔ አገባብ የተለየ ስርአት አለውን? መመዘኛ መስፈርትስ ይኖረዋል?

12. የቅኔ ሊቃውንት በግእዝ ቅኔ ጥበብ እየበሰሉና እየረቀቁ በሄዱ ቁጥር በደመና እስከመጫንና በንፋስ እስከ መክነፍ ይደርሳሉ ይባላል፡፡ ይህ አፈ ታሪክ መነሻው ምንድን ነው? ታማኝነቱስ ምን ያህል ነው?

13. የጥንቱ የቅኔ ተማሪ አለባበስና የአመጋገብ ስርአት ከአሁኖቹ ተማሪዎች በምን ይለያል? ከተለየ ምክንያቱ ምንድን ነው?

14. የቅኔ መምህራን ህይወታቸውን የሚመሩት እንዴት ነው? ምግባቸውን እና የሚያስፈልጋቸውን ሌሎች ነገሮችስ እንዴትና ከማን ያገኛሉ?

15. የቅኔ ትምህርት እንዲገለጽልን በማለት ሆሳእና/የአበሻ መድሐኒት/ መውሰድ በቅኔ ቤት የተለመደ ነው፡፡ አወሳሰዱ እንዴት ነው? የሚወስደው መዳህኒትስ ምንድን ነው? መድሃኒቱ በሚወስድበት ጊዜ የሚፈጸም የተለየ ስርአት አለ? ለምን ይህ የተለየ ስርአት አስፈለገ ?

16. ስለግእዝ ቅኔ ሊገለጽ የሚፈለግ ሌላ ተጨማሪ ሀሳብ ካለ ቢገለጽ?

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

## ተጠያቂዎች (ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች)

### ምንጭ (ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ)

| ተ.ቁ | የተጠያቂው ስም | እድሜ | የሚሰሩበት ቦታ | ስሙ-ያው ያላቸው ቀረቤታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪጌታ ለይኩን ብርሃኑ | 87 | ድንግራና አባጠር ማርያም | • አብዛኛውን የቅኔ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በዋሸራ ማርያም ደብረ ምእራፍ ገዳም ከቅኔው ሊቅ ከመምህር ማእበል ፈንቴ ሲሆን በቅኔ መምህርነትም የተመረቁት ከማእበል ፈንቴ ጉባኤ ነው<br>• የቅኔ ትምህርታቸውን አጠናቀው የቅኔ ጉባኤ የተከሉት በ1942 አ/ም ድንግራ ማርያም ደብር ነው።<br>• በቅኔ መምህርነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት በድንግራ ማርያም ደብር ውስጥ ሲሆን አሁንም ፍኖተሰላም አካባቢ በማህደረ ሰላም ቅድስት ኪዳነ ምህረት ደብር ውስጥ ቅኔን በማስተማር ላይ የገኛሉ። |
| 2 | መላከ ጥበብ ስሜነህ አበበ | 52 | በፍኖተ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ የቅኔ ጉባኤ መምህርና ሰባኬ ወንጌል | • የቅኔ ትምህርታችውን የተከታተሉት ጃም ውስጥ ድንግራ ማርያም ከመሪጌታ ለይኩን ብርሃኑ፤ ጫልቆ ከመሪጌታ አምደ ሚካኤል፤ ደንበጫ ከመሪጌታ ብዙ አየሁ፤ ጨጎዴ ከመሪጌታያሬድ ሽፈራው፤ ዘንገባል ከመምህር ዲበ ኩሉ፤ ደብረ ምጥማቅ ከመምህር ይትባረክና ሜጫ ከመምህር ጠበቡ ተምረዋል።<br>• አሁን በፍኖተ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ የቅኔ ጉባኤ መምህርና ሰባኬ ወንጌል ናቸው። |
| 3 | ደብተራ ብርሃን ይታየው | | ሽለል ገብርኤል ደብር አገልጋይ | • ሙያውን ሽለል ከመሪጌታ ታደለ እውነቴ፡ ጫልቆ ከመምህር አምደሚካኤል፡ የተማሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሽለል ገብርኤል ደብር በድብትርና በማገልገል ላይ ናቸው። |
| 4 | መሪጌታ ታንቶ ይገኝ | 55 | የበህራ ማርያም የጉባኤ መምህር | • ሙያቸውን ሽለል ከመሪጌታ ታደለ እውነቴ፡ ጫልቆ ከመምህር አምደ ሚካኤል፤ ደብረ ኤልያስ ከመምህር ምናሴ፡ ድንግራ ከመምህር ለይኩን ተምረዋል። በአሁኑ ጊዜ በየበህራ ማርያም የጉባኤ መምህር ናቸው። |
| 5 | መሪጌታ ማማሩ ነጋዱ | | የወበሽ ሚካኤል የጉባኤ መምህር | • የቅኔ ትምህርታችውን የተከታተሉት ጎጃም ውስጥ ጫልቆ ከመሪጌታ አምደ ሚካኤል፡ ደንበጫ ከመሪጌታ ብዙአየሁ፡ ጨጎዴ ከመሪጌታ ያሬድ ሽፈራው፡ ገዳመ እስቴፕስ ከመሪጌታ መዝሙር ሽለል ከመሪጌታ ታደለ እውነቴ፡ ተምረዋል። በአሁኑ ጊዜ በየወበሽ ሚካኤል የጉባኤ መምህር ናቸው። |